

የ አ ካ ባ ቢ ህ ግ

ለቅድመ ሰራ ሰልጣኝ
የተዘጋጀ ማኑዋል

ማውጫ

ገፅ

ምዕራፍ አንድ፡- የአካባቢ ሕግ በጠቅላላው.....1

መግቢያ.....1

1. የአካባቢ ህግ ትርጓሜ.....3
2. የአካባቢ ህግ ምንጮች.....4
3. አለም አቀፍ የአካባቢ ስምምነቶች(መልቲላተራል ስምምነቶች) ምንነት.....5
4. መልቲላተራል የአካባቢ ስምምነቶች የአዘገጃጀት ሂደት.....8
   - 4.1. ቅድመ ድርድር.....8
   - 4.2. ድርድር.....9
   - 4.3. መቀበል እና ፊርማ.....9
   - 4.4. ማጽደቅ እና አክሴሽን.....10
   - 4.5. በስራ ላይ ማዋል.....11
5. መልቲላተራል የአካባበቢ ስምምነቶች ተቋማዊ አደረጃጀቶች፣ አሰራሮች እና አተገባበር.....12
   - 5.1. ተቋማዊ አደረጃጀቶች እና አሰራሮች.....12
     - 5.1.1. የአባል ሀገራት ስብሰባ.....12
     - 5.1.2. የኮንቬንሽን ፅህፈት ቤቶች.....12
     - 5.1.3. አማካሪ አካላት.....12
   - 5.2. መልቲላተራል የአካባቢ ስምምነቶች የአተገባበር ስልቶች.....13
     - 5.2.1. የስምምነቶች አተገባበርን ለመከታተል በአባል ሀገራት የሚዘጋጁ ሪፖርቶች.....13
     - 5.2.2. የማረጋገጫ ስልቶች.....13
     - 5.2.3. ግዴታን ማክበር..... 14
6. አለም አቀፍ የአካባቢ ህግ መርሆች.....14
   - 6.1. ዘላቂ ልማት እና ዘላቂ ልማትን ማቀናጀት.....15
   - 6.2. የቅድም ጥንቃቄ መርህ.....16
   - 6.3. የመከላከል መርህ.....17
   - 6.4. የበከለ ይክፈል መርህ.....18
   - 6.5. በአካባቢ ጉዳዮች ላይ ያሉ መረጃዎች፣ የብዙሀን ተሳትፎ እና የፍትህ ተደራሽነት.....19
   - 6.6. የጋራ ግን የየቅል የሆነ ሀላፊነት መርህ 22
7. ብሔራዊ የአካባቢ ፖሊሲዎች እና ሕጎች.....23
   - 7.1. የኢትዮጵያ የአካባቢ ፖሊሲ.....23
   - 7.2. የአካባቢ ጉዳዮች በሕገ መንግስት ውስጥ.....25
   - 7.3. የአካባቢ ፖሊሲውን ለማስፈፀም የወጡ ዝርዝር ሕጎች የመወያያ ጥያቄዎች.....25

ምዕራፍ ሁለት፡- ቁልፍ የአካባቢ ጉዳዮችን የሚመሩ አለም አቀፍ እና ብሔራዊ ህጎች...

1. አለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ.....27
   1.1. የግሪን ሀውስ ኢፌክት.....27
   1.2. የመቀት ሳቢ ጋዞች.....27
2. አለም አቀፍ አየር ንብረት ለውጥ ስምምነቶች.....29
   2.1. የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ መዋቅራዊ ኮንቬንሽን.....31
   2.2. የኪዮቶ ፕሮቶኮል.....32
3. የአየር ንብረት ለውጥ ተፅእኖና የኢትዮጵያ ምላሽ.....33
   3.1. ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ያላቸው..... 36
   ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና መርሀ ግብሮች
      3.1.1. የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲውና የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዮች..... 38
      3.1.2. ብሄራዊ የማጣጣሚያ የድርጊት መርሐ-ግብር..... 38
      3.1.3. ብሄራዊ የአየር ንብረት ለውጥ ስርየት ተግባሮች..... 39
      3.1.4. የኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ መርሐ-ግብር.....39
      3.1.5. የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱና የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዮች.....40
4. የከባቢ አየር ሽፋን መሳሳት አለም አቀፍ ስምምነት እና ሀገራዊ ህጎች.....42
   4.1. የቬና ኮንቬንሽን.....44
   4.2. የሞንትሪያል ፕሮቶኮል.....45

5. የአደገኛ ቆሻሻዎች እና ኬሚካሎች አለም አቀፍ ስምምነት እና ሀገራዊ ህጎች.....46
   5.1. የአደገኛ ቆሻሻዎችን ለመቆጣጠር የተደነገጉ አለም አቀፍ ስምምነቶች.....48
      5.1.1. የባዝል ኮንቬንሽን.....48
   5.2. አደገኛ ቆሻሻዎችን በሚመለከት የተደነገጉ አህጉራዊ ስምምነቶች..... 52
      5.2.1. የባማኮ ኮንቬንሽን..... 52
   5.3. ኬሚካሎች..... 52
      5.3.1. ኬሚካሎችን በሚመለከት የተደነገጉ አለም አቀፍ ስምምነቶች.....54
         5.3.1.1. የሮተርዳም ኮንቬንሽን.....55
            5.3.1.1.1. የቅድመ እሺታ ሥርዐት..... 56
         5.3.1.2. የስቶክሆልም ኮንቬንሽን..... 58
   5.4. የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ እና የደህንነተ ሕይወት አለም አቀፍ ስምምነቶች እና ሀገራዊ ህጎች.....59
      5.4.1. የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ.....62
         5.4.1.1. የብዝሀ ሕይወትን የተመለከቱ አለም አቀፍ መዋቅሮች.....63
         5.4.1.2. የብዝሀ ህይወት ኮንቬንሽን.....64
            5.4.1.2.1. የብዝሀ ህይወት ኮንቬንሽንን የተመለከቱ ተቋማዊ አደረጃጀቶች.....65
            5.4.1.2.2. የኮንቬንሽኑ ተከባሪነት፣ተጠያቂነት እና የግጭት አፈታት.....66

      5.5.1. ደህንነተ ህይወት.....66

         5.5.1.1. የደህንነተ ህይወት ፕሮቶኮል አስፈላጊነት.....67

5.5.1.2. የካርታ፦ኔና ፕሮቶኮል አባል ለመሆን መሚላት የሚገባቸው ጉዳዮች.....68
5.5.1.3. የካርታ፦ኔና ፕሮቶኮሉ አላማ.....68
5.5.1.4. ከፕሮቶኮሉ የሚመነጩ ብሄራዊ ግዴታዎች.....69
5.5.1.5. ከፕሮቶኮሉ የሚገኝ ብሔራዊ ጠቀሜታ.....69
5.5.1.6. ከቀዳሚ ግንዛቤ የመነጨ የእሽታ ሥነ ሥርዓትን ስለመተግበር.....69
5.5.1.7. መረጃ ስለማግኘት.....70
5.5.1.8. የቀዳሚ ጥንቃቄ መርህን ስለ መተግበር.....71
5.5.1.9. የሰውን ጤና ስለመጠበቅ.....72
5.5.1.10. የሰብልና የሌሎች ህያውያን ብዝሀ ህይወትን ስለመጠበቅ.....72
5.5.1.11. ጉዳትን ስለመካስ.....73
5.6. በርሀማነት፣የተራራዎች፣የጫካዎች እና የዋልታዎች ስነ-ምህዳር አያያዝ እና ተያያዥ ህጎች
5.6.1. በርሀማነት.....74
5.6.2. በረሀማነትን የተመለከቱ አለም አቀፍ ህጎች.....75
5.6.3. የተራራዎች ስነ ምህዳር.....77
5.6.4. የደኖች ስነ ምህዳር.....79
5.6.5. የዋልታዎች ስነ ምህዳር.....80
የመወያያ ጥያቄዎች
ምዕራፍ ሶስት፡- ከአካባቢ ጥበቃ ጋር ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮች እና የፍትህ አካላት ሚና.....83

1. የንፁህ ውሀ አቅርቦት 83
1.1. ከንፁህ ውሀ አጠቃቀም ጋር ተያያዥ የሆኑ አለም አቀፍ ህጎች..... 84
2. የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ..... 85
2.1. የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማን በሚመለከት የተደነገጉ አለም አቀፍ እና ሀገራዊ ስምምነቶች.....87
2.1.1. የኤስፖ ኮንቬንሽን.....87
3. የሰብአዊ መብት እና አካባቢ.....87
4. በአካባቢ ጉዳዮች የኮርፖሬሽኖች ተጠያቂነት.....88
5. የታዳሽ ሀይሎች አጠቃቀም.....88
6. በአካባቢ ላይ በሚደርስ ጉዳት ላይ የሚተገበሩ የተጠያቂነት እና የጉዳት ካሳ ህጎች.....90
6.1. የሀገራት ሀላፊነት እና የፍትህ ብሄር የግለሰቦች ተጠያቂነት ልዩነት.....91
6.2. ሀገራት በአካባቢ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች ያለባቸው ተጠያቂነት.....92
6.3. በአካባቢ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች የግለሰቦች የፍትህ ብሔር ተጠያቂነት..... 93
6.4. በአካባቢ ላይ የሚደርስ ጉዳትን በተመለከተ የሚኖር የወንጀል ተጠያቂነት.....94
6.5. በአካባቢ ላይ ለሚደረሱ ጉዳቶች የካሳ አከፋፈል.....100
6.6. በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን በሚመለከት የሚኖር የመክሰስ መብት..... 102
(Right to standing)
የመወያያ ጥያቄዎች
የአገር ውስጥ እና አለምአቀፍ የፍርድ ቤት ውሳኔዎች.....104
ዋቢ መፅሀፍት.....115

ምዕራፍ አንድ

የአካባቢ ሕግ በጠቅላላው

ሠልጣኞች በዚህ ምዕራፍ ማብቂያ ላይ

- የአካባቢ ህግ ትርጓሜን ይረዳሉ
- የአካባቢ ህግ ምንጮችን ይለያሉ
- አለም አቀፍ የአካባቢ ስምምነቶች (መልቲላተራል ስምምነቶች) ምንነትን ይገነዘባሉ
- መልቲላተራል የአካባቢ ስምምነቶች የአዘገጃጀት ሂደቶችን ያውቃሉ
- መልቲላተራል የአካባበቢ ስምምነቶች ተቋማዊ አደረጃጀቶች፣ አሰራሮች እና አተገባበርን ይገነዘባሉ
- አለም አቀፍ የአካባቢ ህግ መርሆችን ያብራራሉ
- ብሔራዊ የአካባቢ ፖሊሲዎች እና ሕጎችን ይረዳሉ

መግቢያ

በአለም አቀፍ ደረጃ አካባቢን ለመንከባከብ የተወሰዱ እርምጃዎች በአብዛኛው የቅርብ ግዜ ክንውኖች ናቸው።በአጠቃላይ በሀገራት መካከል በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን በተቀናጀ ሁኔታ ለመፍታት የሚያስፈልገው ግንዛቤ ከ አስርት አመታት በፊት አልነበረም።ከ 19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ በሀገራት መካከል ከ ውቅያኖሶች፣ ዝርያቸው በመናመን ላይ የሚገኙ እንስሳት እና እጽዋት እና ከተለያዩ የተፈጥሮ ሀብቶች ጋር በተያያዙ የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል።ሆኖም እነዚህ ቀደምት አለም አቀፍ ጥረቶች በአንጻሩ የተቀናጁ አልነበሩም።

ባለፉት አስርት አመታት በአካባቢ ላይ እየደረሰ ያለው ጉዳት ያስከተለው ተጽእኖ እና በአጠቃላይ በአለም ህዝብ ዘንድ ስለአካባቢ ያለው ግንዛቤ በከፍተኛ ደረጃ በማደጉ ሀገራት እ.ኤ.አ በ 1960 ዎቹ ስለ አካባቢ ሁኔታ ትኩረት ማድረግ ጀምረዋል።በመሆኑም መንግስታት የዜጎቻቸውን የኑሮ ደህንነት በበቂ ሁኔታ ሊያስጠብቁ የሚችሉ ልዩ አስተዳደራዊ እርከኖችን፣የሚንስቴር መስሪያ ቤቶችን እና የአካባቢ ጥበቃ ኤጀንሲዎችን አቋቁመዋል። የአካባቢ ህግ ከፍተኛውን ትኩረት ያገኘው እ.ኤ.አ በ 1972 በ ስዊድን ሀገር በተካሄደው የተባበሩት መንግስታት የሰዎች አካባቢ(United Nations Conference on the Human Environment) ስብሰባ ወቅት ሲሆን ይህም በአለም ታሪክ ለመጀመሪያ ግዜ በአካባቢ ላይ ጉዳት

የሚያስከትሉ የሰዎች እንቅስቃሴዎችን ለመገደብ የሚያስችሉ የአካባቢ አያያዝ እና አጠባበቅን የሚመለከቱ የህግ ማዕቀፎች እንዲዘጋጁ ትልቁን አሻራ አሳርፎ አልፏል፡፡በአሁኑ ወቅት በመሬት ላይ የሚኖሩ ህይወት ያላቸው እና ህይወት የሌላቸው ፍጥረቶችን እንዲሁም ስነ መህድራዊ ሂደቱን ለመንከባከብ የሚረዱ በይዘታቸው ሰፋ ያሉ ብሔራዊ እና አለም አቀፍ የአካባቢ የህግ ሥርዐቶች ተደንግገው ይገኛሉ፡፡

አካባቢያዊ ችግሮች በዋናነት የሚመነጩት ከሁለት ዋና ዋና የሰዎች እንቅስቃሴዎች ነው::እነዚህም

1) የተፈጥሮ ሀብቶችን ዘላቂነታቸውን በማያረጋግጥ ሁኔታ መጠቀም እና
2) አካባቢያችን በተፈጥሮ በካይ የሆኑ ንጥረ ነገሮችን ስቦ ጎጂ ወደ አልሆኑ ቁሶች ከሚለውጥበት አቅሙ በላይ በካይ ንጥረ ነገሮች ወደ ከባቢ አየር መለቀቁ ነው፡፡

በእነዚህም ጎጂ የሰዎች እንቅስቃሴዎች ምክንያት የተለያዩ ስነ መህድራዊ ጉዳቶች በአለማችን ላይ ተከስተዋል፡፡ለምሳሌ ያህል

- የብዝሀ ሕይወት መመናመን
- የውሀ አካላት መበከል እና ተያያዥ የሆኑ የሰዎች የጤና ችግር
- የአየር መበከል እና የሚያስከትለው የሰዎች የአተነፋፈስ ስርአት መዛባት
- የአፈር ለምነት መቀነስ፣በረሀማነት እና ረሀብ
- የአሳ ሀብት መመናመን
- በኦዞን ሽፋን ንጣፍ መሳሳት ምክንያት በአንዳንድ አካባቢዎች የቆዳ ካንሰር እና የአይን በሽታ ተጠቂዎች ቁጥር መጨመር
- ከዚህ በፊት ተከስተው የማያውቁ በሽታዎች መታየት እና የተስቦ በሽታዎች መስፋፋት

ናቸው፡፡

የተፈጥሮ ህጎችን (the laws of nature) ማምለጥ የማይቻል በመሆኑ ተገቢው እውቅና ሊሰጣቸው ይገባል[1]፡፡አንዱ የተፈጥሮ ሕግ የሰዎች እንቅስቃሴ በአካባቢ ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ የሚያሳድር መሆኑ ነው::እያንዳንዱ በምድራችን ላይ የሚኖር ግለሰብ የራሱ የሆነ ስነ መህድራዊ አሻራ ይኖረዋል፡፡ ስነ መህድራዊ አሻራ ማለት የእያንዳንዱ ግለሰብ የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም እና ለአካባቢ ብክለት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ነው[2]፡፡የሰዎች ስነ መህድራዊ አሻራም በተለያዩ የአለም ክፍሎች በሚኖሩ

[1] በአካባቢ ህግ ላይ ለፍትህ አካላት የተዘጋጀ ሀንድ ቡክ (የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም፣እ.ኤ.አ 2006) ገፅ 3
[2] ዝኒ ከማሁ

ህዝቦች መካከል ከፍተኛ ልዩነት ይኖረዋል።ለምሳሌ በበለፀጉ ሀገራት የሚኖሩ ሰዎች በማደግ ላይ በሚገኙ ሀገራት ውስጥ ከሚኖሩ ሰዎች የተፈጥሮ ሀብቶችን በአንፃራዊ በከፍተኛ ሁኔታ የሚጠቀሙ ሲሆን በዛው መጠን ለአካባቢ ብክለት የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው።

ሁለተኛው የተፈጥሮ ህግ ማናቸውም በአካባቢያችን የሚገኙ እንደ አየር፣ውሀ፣ አፈር እና የተለያዩ የእንስሳት እና የእጽዋት ዝርያዎች እርስ በእርስ በእጅጉ የተሳሰሩ ሲሆኑ በአንዱ ላይ የሚደርስ ጉዳት በሌሎቹ ላይ ሰፊ እና በቀላሉ ሊተነበይ የማይችል ጉዳት ያደርሳል።ለምሳሌ በአንድ የማዕድን ማውጫ አካባቢ የኬሚካል ማስተላለፊያ ቱቦ ቢፈነዳ ጉዳቱ በዙሪያው የሚገኝ አፈርን በመበከል የሚያበቃ ሳይሆን ወንዞች እና ምንጮችን በመበከል ወደ ባህር ሊጓጓዝ የሚችል ሲሆን በእንስሳት እና በእጽዋት አማካይነት ወደ ምግብ ሰንሰለት ውስጥ ሊገባ ይችላል።ከዚህም ጋር ተያያዥ የሆነው የተፈጥሮ ህግ ማንኛውም በአካባቢ ላይ የሚደርስ ጉዳት ተጽእኖው ድንበር የማይወስነው መሆኑ ነው፤በአንድ ግዛት ላይ የሚደርስ አካባቢዊ ጉዳት በአንድም ይሁን በሌላ መንገድ በሌሎች አካባቢዎች ላይ ተጽእኖውን ማሳረፉ የማይቀር ነው።ይህም የአካባቢ ጥበቃ አለማቀፋዊ ትብብርን በእጅጉ የሚፈልግ መሆኑን በግልጽ ያሳያል።

1) የአካባቢ ህግ ትርጓሜ

የአካባቢን ህጋዊ ትርጓሜ ማወቅ የአካባቢ ህጎችን አተገባበር ስፋት እንዲሁም አካባቢያዊ ጉዳቶች በሚደርሱበት ወቅት የተጠያቂነትን ወሰን ለመለየት ይረዳል።አካባቢ (environment) የሚለው ቃል የተገኘው “environner” ከሚለው ጥንታዊ የፈረንሳይ ቃል ሲሆን ትርጓሜውም “መክበብ” ማለት ነው[3]።አካባቢ በአጠቃላይ በግለሰብም ሆነ በህብረተሰብ ህይወት ውስጥ ቀጥተኛ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ተፈጥሮአዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ሁኔታዎች ድምር ውጤት ነው።ከዘመናዊው የዘላቂ ልማት ትርጓሜ አንጻር አካባቢ የሚለው ቃል በሰዎች ኑሮ ዙሪያ የሚገኙ ቁሳዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮችን የያዘ ሲሆን እነዚህም መሬት፣ ውሃ፣ ከባቢ አየር፣ የአየር ንብረት፣ ድምጽ፣ ሽታ፣ ጣዕም፣ ሀይል፣ የቆሻሻ አያያዝ፣ የባህር ብክለት፣ታሪካዊ ቦታዎችን ያካትታል[4]።ከ ስነ መልክዐ ምድር አንጻር አካባቢ የሚለው ቃል አንድን ውስን ቦታ ወይም መላውን የመሬት አካል የከባቢ አየርን ጨምሮ የሚሸፍን ይሆናል።

[3] ዝኒ ከማሁ ገፅ 4

[4] በአለም አቀፍ የአካባቢ ህግ ላይ የሥልጠና ማኑዋል (የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም፣2006) ገፅ 15

በኢትዮጵያ ህግ በአካባቢ ጥበቃ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 295/1994 አንቀጽ 2 (3) ላይ አካባቢ የሚለው ቃል ሁሉንም የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ ሀብቶች የሚሸፍን ሰፋ ባለ ሁኔታ እንደሚከተለው ተተርጎሞ ይገኛል፡

> “ አካባቢ ማለት በመሬት በከባቢ አየር በአየር ሁኔታ እና በአየር ንብረት በውሀ በህያዋን በድምፅ በሽታ በጣዕም በማህበራዊ ጉዳዮች እና በሥነ ውበት ሳይወሰን በተፈጥሮአዊ ሁኔታቸው ወይም በሰው አማካኝነት ተሻሽለው ወይም ተለውጠው የሚገኙ ነገሮች በሙሉ ያሉበት ቦታ እንዲሁም መጠናቸውን ወይም ሁኔታቸውን ወይም ደግሞ የሰው ወይም የሌሎች ሕያዋን በጎ ሁኔታን የሚነኩ ተሰጋብሮቶቻቸው ድምር ነው፡፡”

የአካባቢ ህግ ሰፊ የሆነ የህግ ክፍል ሲሆን ዋና ትኩረቱን አካባቢያዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አድርጎ በተጨማሪም በአካባቢ ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ የሚያሳድሩ ሌሎች ጉዳዮችንም አካትቶ የያዘ ነው፡፡ የአካባቢ ህግ በሁለት ዋና ዋና ንዑስ ክፍሎች የተከፈለ ነው፡፡እነዚህም አለም አቀፍ የአካባቢ ህግ እና ብሄራዊ የአካባቢ ህግ ተብለው ይከፈላሉ፡፡ የሁለቱ ህጎች ዝምድና በዋናነት ጎልቶ የሚታየው ህጎቹ በተደነገጉበት አላማ እና በህጎቹ የተፈጻሚነት ወሰን ነው፡፡

አለም አቀፍ የአካባቢ ህግ ሉአላዊ በሆኑ ሀገራት መሀከል አካባቢያዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በአለም አቀፍ ደረጃ የሀገራትን ግዴታ የሚወስን የህግ አይነት ነው፡፡በሌላ በኩል የብሄራዊ ህግ ተፈጻሚ የሚሆነው በአንድ ሀገር ውስጥ ሲሆን ዜጎች እርስ በእርስ እና ከአስፈጻሚ አካላት ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚቆጣጠር የህግ አይነት ነው፡፡ ሀገራትም አለም አቀፍ ግዴታቸውን ለመተግበር የሚያስችላቸውንም ብሄራዊ ህጎችን አዘጋጅተው ይተገብራሉ፡፡

2) የአካባቢ ህግ ምንጮች

መንግስታት ህገ መንግስታቸውን እና ሌሎች ዝርዝር ህጎችን መሰረት በማድረግ የአብዛኛውን ህዝብ ደህንነት፣መሬት፣ ውሀ እና አየር ይንከባከባሉ፡፡ በተጨማሪም መንግስታት በአንድ በተወሰነ የአካባቢ ጉዳይ ላይ የተለየ ግዴታን የሚጥሉ ሁለትዮሻዊ ወይም መጠነ ብዙ ስምምነቶችን በመፈራረም አካባቢያቸውን ለመንከባከብ ጥረት ያደርጋሉ፡፡

በሀገር ደረጃ አብዛኛዎቹ ህገ መንግስቶች ስለ አካባቢያዊ መብቶች ወይም መንግስት የተፈጥሮ ሀብቶችን እና አካባቢን ለመንከባከብ ያለበትን ግዴታ የያዙ ናቸው፡፡በአለም ላይ ከ100 በላይ የሚሆኑ ህገ

መንግስቶች ዜጎች ንጹህ እና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት እንዳላቸው እና መንግስት በአካባቢ ላይ የሚደርስ ጉዳትን ለመከላከል ያለበትን ግዴታ ይዘዋል።

3. አለም አቀፍ የአካባቢ ስምምነቶች(መልቲላተራል ስምምነቶች) ምንነት

መልቲላተራል የአካባቢ ስምምነቶች የአለም አቀፍ ስምምነቶች አንድ አካል ናቸው። ከሌሎች አለም አቀፍ ስምምነቶች የሚለያቸውም በአካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ማተኮራቸው፣ ጽኑ የሆኑ አለማቀፋዊ ግዴታዎችን ማስከተላቸው እና በርካታ ሀገራትን በአባልነት መያዛቸው ነው።አንዳንዶቹ ስምምነቶች ጥቂት ሀገሮችን በአባልነት የያዙ ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ አብዛኛውን የአለም ሀገራትን ያሳተፉ ናቸው። መልቲላተራል የአካባቢ ስምምነቶች በተለያየ መልክ ሊሰየሙ ይችላሉ (ምሳሌ agreement,convention,covenant,protocol,treaty)። በ1969 ዓ.ም አለም አቀፍ ውሎችን በተመለከተ የተደነገገው የቪየና ኮንቬንሽን አለም አቀፍ ውልን በሚከተለው ሁኔታ ትርጓሜ ሰጥቶታል፡

> "An international agreement concluded between states in written form and governed by international law,whether embodied in a single instrument or in two or in two or more related instruments and whatever its particular designation"[5]

ከትርጓሜውም ለመረዳት እንደሚቻለው አለም አቀፍ ውል በሀገራት መካከል በፅሁፍ የሚደረግ ስምምነት ሲሆን ይህም በሀገራቱ ላይ ፅኑ ግዴታን የሚያስከትል እና በአለም አቀፍ ህግ መሰረት ተፈፃሚ የሚሆን ነው።አለም አቀፍ ውሎችን በተመለከት የተደነገገው የቪየና ኮንቬንሽን በስራ ላይ የዋለው እ.አ.አ በ1980 ዓ.ም ሲሆን እ.አ.አ ከመስከረም 2005 ዓ.ም ጀምሮ 105 አባል ሀገራት አሉት። እንደ አጠቃላይ መርህ በአለም አቀፍ ውሎች ውስጥ የሚገኙ መመሪያዎች ተፈፃሚ የሚሆኑት በአባል ሀገራት ላይ ብቻ ሲሆን አለም አቀፍ ውሎችን በተመለከተ የተደነገገው የቪየና ኮንቬንሽን ውስጥ የተጠቀሱ መመሪያዎች ግን ኮንቬንሽኑን በፈረሙም ሆነ ባልፈረሙ ሀገራት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል። በአብዛኛው እንደሚታየውም አለም አቀፍ ውሎች (treaties) እና ኮንቬንሽኖች ተመሳሳይ ትርጓሜ ያላቸው ሲሆን በተለዋዋጭነትም መጠቀም ይቻላል። ፕሮቶኮል ማለት አንድ ኮንቬንሽን በስራ ላይ ከዋለ ቦሀላ በቀጣይ ኮንቬንሽኑን ለማሻሻል ወይም ተጨማሪ መብቶችና ግዴታዎችን ለማካተት የሚዘጋጅ እና በአባል ሀገራት ላይ ፅኑ ግዴታን የሚያስከትል አለም አቀፍ ሰነድ ነው።

[5] እ.ኤ.አ በ 1969 ዓ.ም አለም አቀፍ ውሎችን በተመለከተ የተደነገገው የቬና ኮንቬንሽን አንቀፅ 2

አካባቢያዊ ስምምነቶች በአጠቃላይ በሁለት አርስ በእርስ በተገናኙ ትውልዶች የተከፈሉ ሲሆን እነዚህም የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ትውልድ ስምምነቶች በመባል ይታወቃሉ።[6] የመጀመሪያ ትውልድ የአካባቢ ስምምነቶች የሚያተኩሩት በተወሰኑ የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም እና አያያዝ ላይ (በዱር አራዊት፣በአየር፣በባህር እና በመሳሰሉት) የሚያተኩሩ ሲሆኑ በአብዛኛው የዘርፍ ስምምነቶች ናቸው (Sectoral agreements):: እ.ኤ.አ በ1971 ዓ.ም የውሃ-አዘል መሬቶችን አስመልክቶ የተፈረመው የራምሳር ኮንቬንሽን ፣እ.ኤ.አ በ1972 ዓ.ም ቆሻሻዎችን በባህር ላይ በማረገፍ በባህር ላይ የሚደርስ ብክለትን ለመከላከል የተፈረመው London dumping Convention እና እ.ኤ.አ በ1973 ዓ.ም በመርከቦች አማካኝነት የሚደርስ ብክለትን ለመከላከል የተፈረመው ስምምነት (International convention for the prevention of pollution from ships) በምሳሌነት የሚጠቀሱ የመጀመሪያ ትውልድ ስምምነቶች ናቸው።[7]

የሁለተኛው ትውልድ መልቲላተራል ስምምነቶች በአንድ የአካባቢ ጉዳይ ላይ ያልተወሰኑ ሲሆኑ ትኩረታቸውም በዘላቂ ልማት ላይ እና በዘላቂ የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም ላይ ነው[8]።አብዛኛዎቹ እነዚህ ስምምነቶች የተፈረሙት እ.ኤ.አ በ1992 ዓ.ም የተካሄደውን የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ እና የልማት ስብሰባን (United Nations Conference on Environment and Development UNCED) ተከትለው ነው። ይህ ስብሰባ በብራዚል ሪዮ ዲጀኔሮ ከተማ የተካሄደ ሲሆን ስብሰባውም የመሬት ስብሰባ በመባል ይፈታወቃል። በስብሰባው ከ 180 ሀገራት የመጡ የመንግስት ተወካዮች ተካፍለው ነበር። በዚህ ስብሰባ ወቅት ሁለት ኮንቬንሽኖች ለፊርማ ቀርበው የነበሩ ሲሆን እነዚህም የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፍ ኮንቬንሽን (United Nations Framework Convention on Climate Change (UNFCC)) እና የብዝሀ ህይወት ኮንቬንሽን ናቸው።የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፍ ኮንቬንሽን በይዘቱ የአየር ንብረት እና ከባቢ አየር ላይ የሚያተኩር ቢሆንም የአየር ንብረት ለውጥ በስነ መህዳር ላይ እያሳደረ ያለውን ተጽእኖ፣የእርሻ ምርት እና የዘላቂ ልማት ጉዳዮችንም ጨምሮ የያዘ ነው።በሌላ በኩል የብዝሀ ህይወት ኮንቬንሽን የእርሻ፣ የደን፣ የአሳ፣ የመሬት አጠቃቀም እና የተፈጥሮ አጠባበቅ ጉዳዮችን አስተሳስሮ የያዘ ኮንቬንሽን ነው።ሌላው ከመሬት ስብሰባው በኃላ የጸደቀው የተባበሩት መንግስታት በረሀማነትን የመከላከል አለም አቀፍ ኮንቬንሽን ሲሆን አላማውም በረሀማነትን መከላከል እና ድርቅ የሚያስከትለውን ተጽእኖ መቀነስ ነው።በቅርብ ግዜ ከጸደቁ እና በስፋት ከሚታወቁ መልቲላተራል የአካባቢ ስምምነቶች መካከል፡ የተወሰኑ አደገኛ ኬሚካሎችና ፀረተባዮች አለም አቀፍ ንግድን በቀዳሚ ግንዛቤ ላይ በተመሰረተ የእሽታ ሥርዐት

[6] በመልቲላተራል የአካባቢ ስምምነቶች ላይ የተደራዳሪዎች መመሪያ(የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም) ገፅ 7
[7] ዝኒ ከማሁ
[8] ዝኒ ከማሁ

እንዲተገበር እ.ኤ.አ በ 1998 ዓ.ም የተደነገገው የሮተርዳም ኮንቬንሽን፣ ለረጅም ግዜ ሳይረክሱ ወይም ይዘታቸውን ሳይለቁ ከሚቆዩ ከካርበን የተሰሩ ኬሚካሎችን ለመቆጣጠር እ.ኤ.አ በ 2001ዓ.ም የተደነገገው የስቶክሆልም ስምምነት እንዲሁም በአካባቢ ጉዳዮች ላይ ያሉ መረጃዎች፣ የብዙሀን ተሳትፎ እና የፍትህ ተደራሽነት ላይ እ.ኤ.አ በ 1998 ዓ.ም የተደነገገው የአርሀስ ኮንቬንሽን ናቸው።

መልቲላተራል የአካባቢ ስምምነቶች በተለያየ መልክ ሊቀርቡ ይችላሉ።እነዚህም

- **አለም አቀፍ ወይም አህጉራዊ**፡- መልቲላተራል የአካባቢ ስምምነቶች ስምምነቶቹን ተቀብለው ተግባራዊ እንደሚያደርጉት ሀገራት ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ መሰረት ተፈፃሚነታቸው የተለያየ ይሆናል። በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ስር የሚዘጋጁ መልቲላተራል የአካባቢ ስምምነቶች በአለም ላይ ለሚገኙ ሀገራት በሙሉ አባል እንዲሆኑ ክፍት ይደረጋል። በሌላ በኩል የተወሰኑ መልቲላተራል የአካባቢ ስምምነቶች አህጉራዊ ወይም ክፍለ አህጉራዊ የተፈፃሚነት ወሰን ይኖራቸዋል። ለምሳሌ የአደገኛ ቆሻሻዎችን ድንበር ዘለል ዝውውር አወጋገድ ላይ የተደነገገው የባዝል ስምምነት ተግባራዊ የሚሆነው በአለም ላይ በሚገኙ ሀገሮች በሙሉ ሲሆን አደገኛ ቆሻሻዎች ወደ አፍሪካ እንዳይገቡ ለማገድ እና በአፍሪካ አገሮች መካከል የአደገኛ ቆሻሻዎችን ድንበር ዘለል ዝውውር እንዲሁም አወጋገድ ለመቆጣጠር የወጣው የባማኮ ኮንቬንሽን ግን ተፈጻሚ የሚሆነው በአፍሪካ አህጉር ብቻ ነው።
- **Appendix-driven or Annex-driven conventions**:- Appendix-driven ስምምነቶች ከዋናው የስምምነቶቹን አነቀጾች ከያዘው ክፍል በተጨማሪ ሌሎች መግለጫዎችን አካትተው የያዙ ናቸው። ዘራቸው በመመናመን ላይ የሚገኙ የዱር እንስሳት እና የእጽዋት ንግድን በሚመለከት እ.ኤ.አ በ1973 ዓ.ም የወጣው ኮንቬንሽን (The Convention on International Trade in Endangered Species of Wild Fauna and Flora) የ Appendix-driven ስምምነት ጥሩ ምሳሌ ነው።በኮንቬንሽኑ ውስጥ ዝርያቸው በመመናመን ላይ የሚገኙ የእንስሳት እና የእጽዋቶችን ስም ዝርዝር የያዙ ሶስት ተጨማሪ መግለጫዎች ይገኛሉ።በመርከቦች አማካኝነት የሚከሰትን ብክለት ለመከላከል እ.ኤ.አ በ1973 ዓ.ም የወጣው ኮንቬንሽን የተለያዩ የብክለት አይነቶችን የሚያብራሩ ዕዝሎችን የያዘ ነው።ለምሳሌ ዕዝል 1 ነዳጅ ዘይት፣ ዕዝል 2 መርዛማ ፈሳሽ፣ ዕዝል 3 ጎጂ ቁስ ነገሮች፣ዕዝል 4 ከመኖሪያ ቤቶች ውስጥ የሚወጡ ፈሳሽ ቆሻሻዎች፣ዕዝል 5 ቆሻሻዎች፣ዕዝል 6 በመርከቦች አማካኝነት የሚከሰት የአየር መበከልን ይዞ ይገኛል።

- **ማዕቀፋዊ ስምምነቶች**፡-የተወሰኑ ስምምነቶች ራሳቸውን ችለው የቆሙ እና ሁሉንም ጉዳዮች አካትተው የያዙ ናቸው፡፡ማእቀፋዊ ስምምነቶች የሚደነገጉት ሌሎች ቀጣይ እና ተደጋጋፊነት ያላቸው ስምምነቶች እንዲዘጋጁ መዋቅራዊ አደረጃጀቶችን ለማመቻቸት ነው፡፡ ለምሳሌ የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ማእቀፋዊ ኮንቬንሽን የተደነገገበትን ዋና አላማ ለማሳካት ሌሎች ተጨማሪ ፕሮቶኮሎች እንዲደነገጉ ምክንያት ሆኗል፡፡እንደ አጠቃላይ ደንብ በአንድ ማዕቀፋዊ ኮንቬንሽን ላይ አባል የሆኑ ሀገራት ብቻ በቀጣይ በሚደነገጉ ፕሮቶኮሎች ላይ አባል መሆን ይችላሉ፡፡

4. መልቲላተራል የአካባቢ ስምምነቶች የአዘገጃጀት ሂደት

መልቲላተራል የአካባቢ ስምምነቶች በስፋት እና በሚያተኩሩበት ጉዳይ የተለያዩ ቢሆኑም ለዝግጅት የሚያልፉባቸው ደረጃዎች ተመሳሳይ ናቸው፡፡ዋና ዋና የሚባሉት የዝግጅት ሂደቶች ቅድመ ድርድር፣ ድርድር፣መቀበል (adoption) እና መፈረም ፣እንዲሁም ማጽደቅ እና አክሴሽን በመባል ይታወቃሉ፡፡እያንዳንዱም የዝግጅት ሂደት የራሱ የሆነ የተለየ ባህርይ እና የተለየ ውጤት ይኖረዋል፡፡

4.1. ቅድመ ድርድር

በቅድመ ድርድር ሂደት መንግስታት ወይም Intergovernmental Organizations ከአንድ ሀገር ግዛት በላይ ወይም አለማቀፍ አካባቢያዊ አንድምታ ያላቸው ጉዳዮች ላይ ቅድመ ዝግጅት ያደርጋሉ፡፡ Intergovernmental Organizations የሚባሉት የአለም ሚትዮሮሎጂ ድርጅት፣የአለም የጤና ድርጅት፣የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም፣የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም እና አለም አቀፉ የአየር ንብረት ፓነል ናቸው፡፡ በዚህ ደረጃ ወቅት በአጀንዳ በተያዘው ጉዳዩ ላይ እርምጃ መወሰድ አለበት የለበትም እንዲሁም የሚወሰደው እርምጃ ተግባራዊ ይሆናል አይሆንም የሚሉ ነጥቦች ላይ ውሳኔ ይሰጣሉ፡፡ለቅድመ ድርድር ተብለው የሚዘጋጁ መደበኛ ወይም መደበኛ ያልሆኑ ውይይቶች በብሔራዊ፣አህጉራዊ ወይም በአለም አቀፍ ደረጃ ሊካሄዱ ይችላሉ፡፡

በቅድመ ድርድር ሂደት ወቅት ሳይንሳዊ ትንተናዎች በአብዛኛው ግዜ ቁልፍ የድርድሩ አካል ናቸው፡፡ለምሳሌ እ.ኤ.አ በ1988 ዓ.ም የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም እና የአለም ሚቲዮሮሎጂ ድርጅት አለም አቀፉ የአየር ንብረት ለውጥ ፓነል (Intergovernmental Panel On Climate Change (IPCC)) እንዲቋቋም ያደሩጉ ሲሆን የተቋቋመውም በአየር ንብረት ለውጥ ላይ ገለልተኛ የሆነ ሳይንሳዊ ትንተናዎችን እንዲያዘጋጅ ነው፡፡ፓነሉ እ.ኤ.አ በ1990 ዓ.ም ያቀረበው የመጀመሪያ የግምገማ

ጥናት ሪፖርት ለተባበሩት መንግስታት ማዕቀፋዊ ኮንቬንሽን ድርድር ሳይንሳዊ መሰረት ሊጥል ችሏል፡፡በተመሳሳይ እ.ኤ.አ በ 1995 ዓ.ም የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም ለረጅም ጊዜ ሳይረክሱ በሚቆዩ ከካርበን የተሰሩ ኬሚካሎች ላይ በሚዘጋጅ ህግ ላይ የህጉን አስፈላጊነት እና አተገባበር ላይ ግምገማ እንዲደረግ ለአለም አቀፉ የኬሚካል ፎረም ጥሪ አቅርቦ የነበረ ሲሆን የተገኘው ውጤትም ለስቶክሆልም ኮንቬንሽን ድርድር መሰረት ሊሆን ችሏል፡፡

4.2. ድርድር

የድርድር ሂደት የሚጀምረው የተደራዳሪዎች መዋቅር ከተዘጋጀ በኋላ ነው፡፡ድርድሮች ከመጀመራቸው በፊት የስነ ስርአት ጉዳዮችን የሚመለከት የቅድመ ዝግጅት ኮሚቴ (Preparatory Comitee) ይቋቋማል፡፡ይህም እንደተጠናቀቀ የድርድር ሂደቱን የሚያስተባብሩ ቅርንጫፍ አካላት (bodies) እና በተወሰኑ የድረድር ጉዳዮች ላይ ትኩረት የሚያደርጉ Working groups ይቋቋማሉ፡፡ መደበኛው ድርድር ሁሉም አባል ሀገራት በተገኙበት የሚካሄድ ሲሆን መደበኛ ያልሆኑ ድርድሮችም በቡድን በመሆን ጎን ለጎን ይካሄዳሉ፡፡

4.3. መቀበል እና ፊርማ (Adoption and Signiture)

የቅድመ ድርድር እና የድርድር ደረጃዎች ከታለፉ በኃላ ቀጣዩ ስምምነቱን የመቀበል እና የመፈረም ሂደት ይሆናል፡፡ስምምነቱን የመቀበል እና የመፈረም ሂደት የሚካሄደው በዲፕሎማቲክ ስብሰባ ወይም በፕሌኒፖቴንሻሪዎች ስብሰባ ነው፡፡ፕሌኒፖቴንሻሪ ማለት አንድ የመጣበትን መንግስት ወይም ድርጅት በሙሉ ስልጣን እንዲወክል የተደረገ ግለሰብ ነው(ምሳሌ አምባሳደር)፡፡ ሀገራት አንድን መልቲላተራል ስምምነት ከተቀበሉ (adoption) በኃላ ቀጣዩ የፊርማ ሂደት ይሆናል፡፡በአብዛኛው ሀገራት የተቀበሉትን ስምምነት ለመፈረም የሚኖራቸው ግዜ የተገደበ ሲሆን የግዜ ገደቡም በስምምነቶቹ ውስጥ ተካትቶ ይገኛል፡፡ለምሳሌ በበረሀማነት ላይ የተደነገገው ኮንቬንሽን ሀገራት ስምምነቱን ከተቀበሉት ቦሀላ ለፊርማ ክፍት ሆኖ የተቀመጠው ለአንድ አመት ብቻ ነበር፡፡በተለየ ሁኔታ ሌሎች ስምምነቶች ደግሞ ለምሳሌ በውሀ አዘል መሬቶች ላይ የተደነገገው የራምሳር ኮንቬንሽን አይነቶቹ ለፊርማ ያለ ግዜ ገደብ የተቀመጡ ናቸው፡፡

በተመሳሳይ ለድርድር ሂደት እንደሚያስፈልገው ሁሉ የመቀበል እና የፊርማ ስብሰባ ሂደትም በሥነ ሥርዐት ደንቦች የሚመራ ይሆናል፡፡ነገር ግን ብዙውን ግዜ በተግባር የሚደረገው ተሰብሳቢዎች በድርድር ሂደት ወቅት የተጠቀሙበትን የሥነ ሥርዐት ደንብ በመቀበል እና ፊርማ ስብሰባ ወቅትም መልሰው ለመጠቀም ስምምነት ላይ ይደርሳሉ፡፡

በንድፈ ሀሳብ ደረጃ ለመቀበል እና ለፊርማ የሚካሄድው ስብሰባ የድርድር ሂደቱ ከተጠናቀቀ ከሰአታት በኃላ ሊካሄድ ይችላል።ነገር ግን በተግባር እንደሚታየው እነዚህ ስብሰባዎች ብዙውን ግዜ የሚካሄዱት ድርድሩ ከተካሄደ ከተወሰነ ግዜ ቦሀላ ሲሆን ይህም ለ Intergovernmental Negotiating Committee Secretariat ተጨማሪ ሰነዶችን እንዲያዘጋጁ ሲረዳ ተደራዳሪዎችም የድርድሩን ሪፖርት ለየሀገሮቻቸው የመንግስት ባለስልጣናት ለማሳወቅ በቂ ግዜ ይኖራቸዋል።

4.4. ማጽደቅ እና አክሴሽን

አብዛኛውን ግዜ መልቲላተራል የአካባቢ ስምምነቶች ሀገራት እንዲፈርሙ የሚደረገው ስምምነቱን በየሀገሮቻቸው ብሄራዊ ህጎች መሰረት እንደሚያጸድቁት ቅድመ ሁኔታን በማስቀመጥ ነው።የማጽደቅ ሂደት መንግስታት በስምምነቱ ላይ ያላቸውን አቋም መልሰው እንዲያስተውሉ በቂ ግዜ ይሰጣቸዋል።በተጨማሪም ስምምነቶችን የማጽደቅ ሂደት በድርድሩ ሂደት የሀገራት ተወካዮች የተወከሉበትን ስልጣን እንዳልተላለፉ ለማረጋገጥም ይረዳል። ስምምነቱም በአንድ ሀገር ሲጸድቅ አጽዳቂው ሀገር ስምምነቱ በሚያስከትላቸው ህጋዊ ግዴታዎች ተገዢ እንደሚሆን በይፋ ይታወቃል።

የማፅደቅ እና የአክሰሼን ዋና አላማ ፈራሚ አባል ሀገራት ህጋዊ ግዴታን የሚያስከትሉ አለም አቀፍ ስምምነቶችን የሚቀበሉበት ስልት ነው። አንዳንድ ሀገራት አስገዳጅ ህጋዊ ግዴታን የሚያስከትሉ አለም አቀፍ ስምምነቶችን በመፈረም ብቻ ስምምነቶቹን ማፅደቅ የሚያስችል የህግ ችሎታ አላቸው። ሆኖም አብዛኛዎቹ ሀገራት አለም አቀፍ ስምምነቶቹን ለማፀደቅም ሆነ አክሲድ ለማድረግ የሚያስችል ተጨማሪ ህጎችን እንደየሀገራቱ የህግ ሥርዐት ያዘጋጃሉ[9]።አለም አቀፍ ህጎች በብሄራዊ ህጎች ውስጥ እንዴት እንደሚካተቱ በተመለከተ ሞኒስት እና ዱዋሊስት የተባሉ ቲዎሪዎች ይገኛሉ። የሞኒስት ቲዎሪን የሚከተሉ ሀገራት አንድ አለም አቀፍ ስምምነትን መፈረማቸው ብቻ አለም አቀፍ ውሉከብሄራዊ ህጎች ጋር እኩል ተፈፃሚነት እንዲኖረው ያስችላቸዋል። በሌላ በኩል የዱዋሊስት ቲዎሪን የሚከተሉ ሀገራት አንድ አለም አቀፍ ውልን መፈረማቸው ብቻ ውሉ በብሄራዊ ደረጃ እንዲተገበር የማያስቸለው ሲሆን ተግባራዊ ለመሆንም በቅድሚያ አለም አቀፍ ውሉ ወደ ብሄራዊ ህግ መተረጎም ይኖርበታል። ኢትዮጵያም የዱዋሊስት ቲዎሪን የምትከተል ሲሆን በኢፌዴሪ ሕገ መንግሰት አንቀፅ 9 እንደተጠቀሰው ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ ህግ አካል እንደደሆኑ ተገልጿል። ሌላው ከማጽደቅ ጋር ተመሳሳይ የሆነው ሂደት አክሴሽን ይባላል። አንድ በመልቲላተራል ስምምነት የቅድመ ድርድር ወይም የድርድር ሂደት ያልተሳተፈ ወይም ስምምነቱ

[9] መልቲላተራል የአካባቢ ስምምነቶችን በተመለከተ ለተደራዳሪዎች የተዘጋጀ መመሪያ(የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም) ገፅ 5

እንዲጸድቅ ከተቀመጠለት የግዜ ገደብ በኃላ በስምምነቱ ላይ አባል ለመሆን ዝግጁነቱን ሲጠይቅ ሂደቱ አክሴሽን ይባላል፡፡

አንድ ሀገር በአንድ አለም አቀፍ ስምምነት ላይ አባል ከሆነ በኃላ በስምምነቱ ውስጥ የተጠቀሱ የተወሰኑ አንቀፆች እንዲሻሻሉ ወይም እንዲወጡ በመጠይቅ ስምምነቱን በሪዘርቬሽን ማፅደቅ ይቻላል[10]፡፡ሆኖም እንዲህ አይነቱ ሁኔታ ተፈፃሚ የሚሆነው መልቲላተራል የአካባቢ ስምምነቱ በሪዘርቬሽን ማፅደቅን የማይከለክል ሲሆን ነው፡፡ በተጨማሪም አንዳንድ መልቲላተራል የአካባቢ ስምምነቶች በተወሰኑ አንቀፆች ላይ ሪዘርቬሽን ማድረግን የሚፈቅዱ ሲሆን ሪዘርቬሽንን የተመለከቱ ድንጋጌዎች በሌሉበት ሁኔታ አባል ሀገራት የስምምነቱን አላማ በማይፃረር መልኩ በድንጋጌዎቹ ላይ ሪዘርቬሽን ማድረግ ይችላሉ፡፡

4.5. በስራ ላይ ማዋል (Entry in to force)

በቅድመ ድርድር እና በድርድር ሂደት ወቅት ተደራዳሪዎች ስምምነቱ እንዴት ወደ ተግባር እንደሚገባ ለመወሰን የሚያስችል የተለየ ደንብ ያዘጋጃሉ፡፡ከእነዚህም ደንቦች አንዱ አካባቢያዊ ስምምነቱን ወደ መተግባር ከመገባቱ በፊት በቅድሚያ ስምምነቶቹን ስንት ሀገራት ማጽደቅ እንዳለባቸው እንደ አንድ ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ ነው፡፡ለምሳሌ የራምሳር ኮንቬንሽን በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት በሰባት ሀገሮች መፅደቅ የነበረበት ሲሆን በተመሳሳይ የብዝሀ ህይወት ኮንቬንሽንም በቅድሚያ በ30 ሀገሮች መፅደቅ ነበረበት፡፡ ሌላኛው አካሄድ አካባቢያዊ ስምምነቶች በስራ ላይ ከመዋላቸው በፊት የተወሰኑ ሀገራት በስምምነቱ መሳተፍ እንዳለባቸው እንደ ግዴታ በማስቀመጥ ነው፡፡ ለዚህም ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው እ.ኤ.አ በ1997 ዓ.ም የጸደቀው የኪዮቶ ፕሮቶኮል ነው፡፡የኪዮቶ ፕሮቶኮል በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ሁለት ቅድመ ሁኔታዎች ተቀምጠው የነበር ሲሆን እነዚህም

1. በተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ መዋቅራዊ ኮንቬንሽን (UNFCC) አባል የሆኑ 55 ሀገራት በቅድሚያ ሲያጸድቁት እና
2. በኪዮቶ ፕሮቶኮል Annex 1 ላይ የተዘረዘሩት በኢንዱስትሪ የበለጸጉ ሀገራት ሲጸድቅ ነው፡፡

ቅድመ ሁኔታዎቹ የተቀመጡበት ዋና ምክንያት በኪዮቶ ፕሮቶኮል የተቀመጠውን የልቀት መጠን ቅነሳን ግብ ለማሳካት በኢንዱስትሪ የበለጸጉ ሀገራትን ተሳትፎ ማረጋገጥ አስፈላጊ ስለነበረ ነው፡፡

[10] ዝኒ ከማሁ ገፅ 8

5. መልቲላተራል የአካባበቢ ስምምነቶች አተገባበር፣ ተቋማዊ አደረጃጀቶች እና አሰራሮች

አንድ መልቲላተራል አካባቢያዊ ስምምነት በስራ ላይ ከዋለ በኃላ የአባል ሀገራት ዋና ትኩረት የሚሆነው ስምምነቱን መተግበር ላይ ይሆናል፡፡አብዛኛው የአተገባበር ስራ በአባል ሀገራት የሚከናወነው በብሄራዊ ደረጃ ስምምነቶቹን ለመተግበር የሚያስችሉ ህጎችን እና አስተዳደራዊ አደረጃጀቶን በማዘጋጀት ነው፡፡በሀገራት ደረጃ ስምምነቶች በበቂ ሁኔታ እየተተገበሩ መሆናቸውን ለመቆጣጠር የሚረዱ ረፖርት የማድረጊያ፣ የማረጋገጫ (verification) እና ግዴታን የማክበር (compliance) ሥርዐቶች በአለም አቀፍ ደረጃ ተዘርግተው ይገኛሉ፡፡

5.1 ተቋማዊ አደረጃጀቶች እና አሰራሮች

5.1.1 የአባል ሀገራት ስብሰባ (Conference/meeting of the parties)

የአባል ሀገራት ስብሰባ (Conference of the parties (COP)) የሚባለው አንድ ኮንቬንሽንን ካጸደቁ ሀገራት የመጡ ተደራዳሪዎች የሚገናኙበት ስብሰባ ነው፡፡ስብሰባው በተወሰነ ግዜ የሚደረግ ሲሆን በአብዛኛው በአመት አንድ ግዜ ይካሄዳል፡፡ስብሰባው በመደበኛነት የመልቲላተራል የአካባቢ ስምምነቶች አተገባበርን የሚገመግም ሲሆን በዋናነትም በአተገባበር ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችን መርምሮ የማሻሻያ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

5.1.2. የኮንቬንሽን ፅህፈት ቤቶች (Convention Secretariats)

ይህ ፅህፈት ቤት የመልቲላተራል የአካባቢ ስምምነቶችን አተገባበር እና የአባል ሀገራት ስብሰባ እንዲካሄድ የማስተባብር ስራ ይሰራል፡፡በተጨማሪም ፅህፈት ቤቱ ለአባል ሀገሮች የተለያዩ መረጃዎችን የማድረስ፣ በኮንቬንሽኖች እና በፕሮቶኮሎች ላይ የሚነሱ ጥያቄዎች ላይ የማማከር እና በአባል ሀገራቱ እውቅና ከተሰጣቸው ሌሎች አህጉራዊ እና አለም አቀፍ አካላት ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶችን ያስተባብራል፡፡አባል ሀገራቱም ከፅህፈት ቤቱ ጋር የሚደረግ ግንኙነትን የሚያስተባብር ግለሰብ (focal point) ወይም አግባብነት ያለው ብሄራዊ ባለስልጣን እንዲሾሙ ይጠበቃል፡፡

5.1.3. አማካሪ አካላት (Advisory bodies)

መልቲላተራል የአካባቢ ስምምነቶችን በሚመለከት የተለያዩ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ የሳይንስ ፓነሎች፣ የቴክኒክ ቡድኖች እና የተለያዩ ኮሚቴዎች ተቋቁመዋል።የሳይንስ ፓነሎች በዋናነት የተቋቋሙት በኮንቬንሽኖች ውስጥ የሚገኙ ቴክኒካዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አባል ሀገራቱንለማማከር ነው።የአባል ሀገራት ስብሰባ (COP) የቴክኒክ ቡድኖችን በአንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ መፍትሄ እንዲያፈላልጉ እና ውጤቱንም ለአባል ሀገራት ሪፖርት እንዲያደርጉ በአብዛኛዎቹ የመልቲላተራል አካባቢያዊ ስምምነቶች ስልጣን ተሰጥቷቸዋል።ለምሳሌ ብዙዎቹ ኮንቬንሽኖች የፋይናንስ ጉዳዮች ላይ ትኩረት የሚያደርጉ መልቲላተራል የገንዘብ ተቋማት ወይም በስፋት የሚታወቀውን የአለም አቀፉን የአካባቢ ተቋም (Global Environmental Facility) አቋቁመዋል።

5.2. መልቲላተራል የአካባቢ ስምምነቶች አተገባበር ስልቶች

5.2.1. የስምምነቶች አተገባበርን ለመከታተል በአባል ሀገራት የሚዘጋጁ ሪፖርቶች (Reporting Mechanisms)

ብዙዎቹ ለአካባቢያዊ ስምምነቶች አባል የሆኑ ሀገራት ያፀደቋቸውን ኮንቬንሽኖች ለመተግበር የተወሰዱ እርምጃዎችን የያዙ መረጃዎችን በመደበኛነት ለሴክሬታሪያቱ ሪፖርት ያደርጋሉ።የሪፖርቱ ዋና አላማም የስምምነቶቹን አተገባበር ለመቆጣጠር እና ስምምነቶቹ በእርግጥ እየተተገበሩ እንዳሉ ለማረጋገጥ ነው።ሪፖርት የማድረግ ግዴታዎች በስምምነቶቹ ውስጥ ወይም በአባል ሀገራት በሚደረጉ ተጨማሪ ውሳኔዎች ውስጥ ተካትተው ይገኛሉ።ከግዜ ወደ ግዜ የመልቲላተራል አካባቢያዊ ስምምነቶች ቁጥር እየተበራከቱ መምጣታቸው እና የተለያዩ ስምምነቶች የተለያየ የሪፖርት አቀራረብ ሥርዐትን ማስቀመጣቸው በአተገባበራቸው ላይ ክፍተት እንዲታይ ምክንያት ሆኗል።

5.2.2. የማረጋገጫ ስልቶች (Verification)

የመልቲላተራል የአካባቢ ስምምነቶች አተገባበርን በሚመለከት በአባል ሀገራት በመደበኛነት ለሴክሬታሪያቱ የሚቀርቡ ሪፖርቶችን ተአማኒነት እንዲረጋገጡ የሚያስችሉ አንቀጾች በስምምነቶች ውስጥ ተካትተው ሊገኙ ይችላሉ።ሪፖርቶቹ ሊረጋገጡበት ከሚቻልባቸው ዘዴዎች አንዱ አንድ አባል ሀገር በሌላ አባል ሀገር ለሴክሬታሪያቱ በቀረበ የአተገባበር ሪፖርቱ ላይ ያለውን ስጋት በፅሁፍ

ለሴክሬታሪያቱ ሲያቀርብ ነው።ሌላኛው የማረጋገጫ መንገድ ገለልተኛ ገምጋሚ ቡድኖችን በማቋቋም ነው። የኪዮቶ ፕሮቶኮል በአባል ሀገራት የሚቀርቡ የአተገባበር ሪፖርቶችን ለማረጋገጥ ያስቀመጠው ዘዴ ገለልተኛ የሆነ የኤክስፐርቶች ገምጋሚ ቡድን በማቋቋም ነው።ቡድኑም በአባል ሀገራት የተከናወኑ የስምምነት አተገባበሮች ላይ የቴክኒክ ግምገማዎችን በማካሄድ በግምገማው የተገኙ ውጤቶችን ለሴክሬታሪያቱ ሪፖርት እንዲያደርግ ስልጣን እና ሀላፊነት ተሰጥቶታል። ውጤቶቹም በመቀጠል መልቲላተራል ስምምነቶች ውስጥ የተቀመጡ ግዴታዎች በአባል ሀገራት መከበራቸውን ለሚገመግመው ግዴታን የማክበር (Compliance) ኮሚቴ ቀርበው ይገመገማሉ። ከዚህም ለመረዳት የሚቻለው ሪፖርት የማድረግ እና የማረጋገጥ ስራዎች ዋና አላማ በአባል ሀገራቱ በበቂ ሁኔታ ያልተተገበሩ እና ያልተከበሩ ግዴታዎችን ግልጽ እንዲወጡ ማድረግ ነው።

5.2.3. ግዴታን ማክበር (compliance)

በአሁኑ ወቅት አለም አቀፍ ስምምነቶችን በተመለከተ በዋናነት ትኩረት የሚደረግበት ቁልፍ ጉዳይ በስምምነቶች ውስጥ የተቀመጡ ግዴታዎችን የማክበር ጉዳይ ነው።እስከ አሁን በአለም አቀፍ ደረጃ ከ አንድ ሺህ በላይ የሚሆኑ መልቲላተራል አካባቢያዊ ስምምነቶች የተፈረሙ ሲሆን የአለም አቀፉ ህብረተሰብ ትኩረት እነዚህ ስምምነቶች በበቂ ሁኔታ መተግበራቸውንና መከበራቸውን ማረጋገጥ ነው ።በርካታ አካባቢያዊ ስምምነቶች ግዴታን ማክበር ላይ ትኩረት አድርገው የሚሰሩ አካላት እንዲቋቋሙ የሚደነግጉ አንቀጾችን አካትተው ይገኛሉ።እነዚህ አካላት ግዴታ አለመከበራቸውን የሚያመላክቱ ድርጊቶችን ለይተው የሚያስቀምጡ ሲሆን መነሻቸውም ከቸልተኝነት ወይም ከአቅም ማነስ መሆናቸውን ያጣራሉ።ስምምነቶቹንም በአቅም ማነስ መክንያት መተግበር ላልቻሉ አባል ሀገራት በቀጣይ ግዴታዎቻቸውን ለመወጣት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ድጋፍ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻሉ።

6. አለም አቀፍ የአካባቢ ህግ መርሆች

የአካባቢ መርሆች ከግዜ ወደ ግዜ እያደገ የሚገኘውና የህዝብ አለም አቀፍ ህግ (Public International Law) አንድ አካል በሆነው በአለም አቀፉ የአካባቢ ህግ ውስጥ ትልቁን ሚና ይጫወታሉ።እነዚህ መርሆች የአለም አቀፉን የአካባቢ ህግ ባህሪያት የሚያመላክቱ ሲሆኑ የህግ ሥርዐቶቹን ለመተርጎም እና ክፍተቶችን ለማሟላት ያገለግላሉ።በአሁኑ ወቅት አብዛኛዎቹ ጽኑ የሆኑ (binding) እና ጽኑ ያልሆኑ (non-binding) አለም አቀፍ የአካባቢ ስምምነቶች እነዚህን መርሆች በመመርኮዝ የተደነገጉ ናቸው ።

በባለፉት ሶስት አስርት አመታት የአካባቢ ህግ ያሳየው እድገት ለተለያዩ ጽንሰ ሀሳቦች መፈጠር ምክንያት ሆኗል፡፡የእነዚህ መርሆች እና ጽንሰ ሀሳቦች አስፈላጊነት እና ሚና ከፍተኛ መሆን ከአለም አቀፍ የአካባቢ ህግ አፈጣጠር እና እድገት ጋር የተገናኘ ነው፡፡ በአለም አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጁ የአካባቢ ህጎች በውስጣቸው በርካታ ጉዳዮችን መያዛቸው በቀላሉ ለመረዳት አስቸጋሪ ቢያደርጋቸውም የእነዚህ መርሆች መኖር ችግሩን ለማቃለል በእጅጉ አግዘዋል፡፡

ዋና ዋና የተባሉት የአካባቢ መርሆች የጸደቁት እ.ኤ.አ በ1972 ዓ.ም በተካሄደው በስቶክሆልም ኮንፈረንስ እና እ.ኤ.አ በ1992 ዓ.ም በ ሪዮ ዲጀነሮ በተካሄደው የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ እና ልማት ስብሰባ ወቅት ነው፡፡ ከእነዚህም ስብሰባዎችም የስቶክሆልም እና የሪዮ ዲክላሬሽኖች የተገኙ ሲሆን ውሳኔዎቹም በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ፀድቀዋል፡፡በተባበሩት መንግስታት የአካባቢ እና ልማት ስብሰባ ወቅት ከአካባቢ እና ልማት ዲክላሬሽን በተጨማሪ አጀንዳ 21 የተባለ የድርጊት መርሀ ግብር ፀድቀዋል፡፡የሪዮ ዲክላሬሽን በዋናነት የሚያተኩረው አካባቢን እና ልማትን አቀናጅቶ በያዘው የዘላቂ ልማት ዕንሰ ሀሳብ ላይ ሲሆን በዲክላሬሽኑ መርህ አራት መሰረት ዘላቂ የልማትን ግብን ለማሳካት የአካባቢ ጥበቃ የልማት ሂደቱ ዋና አካል መሆን እንዳለበት እና ለብቻው ተነጥሎ መታየት እንደሌለበት ይደነግጋል፡፡

እነዚህም መርሆች በአካባቢ እንክብካቤን በሚመለከት ለወጡ ከመቶ በላይ ለሚሆኑ ስምምነቶች እንዲተበሩ ለማስቻል ትልቁን ድርሻ ተጫውተዋል፡፡የሪዮ ዲክላሬሽን የአለም አቀፉን ህብረተሰብ የዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ ለሚያደርግው ጥረት ሀያ ሰባት አለም አቀፍ የአካባቢ መርሆችን የያዘ ነው፡፡

6.1. ዘላቂ ልማት እና ዘላቂ ልማትን ማቀናጀት

ምንም እንኳን የዘላቂ ልማት ጽንሰ ሀሳብ ለተለያዩ ትርጓሜዎች የተጋለጠ ቢሆንም በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነትና እውቅናን ያገኘው የብሩትላንድ ኮሚሽን እ.ኤ.አ በ1987 ዓ.ም የሰጠው ትርጓሜ ነው፡፡ ኮሚሽኑ በቀድሞው የኖርዌይ ጠቅላይ ሚንስትር በነበሩት ብሩትላንድ በሊቀመንበርነት ይመራ የነበረ ሲሆን በኮሚሽኑ ሪፖርት መሰረት ዘላቂ ልማት ማለት የወደፊት ትውልዶች ፍላጎቶቻቸውን በማያስተጓጉል ሁኔታ የአሁኑን ትውልድ ፍላጎቶች ያሟላ የልማት እንቅስቃሴ ማለት ነው፡፡የዘላቂ ልማት መለኪያዎች በአጀንዳ 21 ፣ በሪዮ ዲክላሬሽን እና በቀጣይ በተደነገጉ አለማቀፋዊ እና አህጉራዊ ስምምነቶች ውስጥ ይገኛሉ፡፡

በሪዮ ዲክላሬሽን መርህ አራት መሰረት ዘላቂ ልማትን ለማሳካት የአካባቢ ጥበቃ የልማት ሂደቱ ዋና አካል ሲሆን ተነጥሎም ሊታይ አይችልም፡፡በተጨማሪም በሪዮ ዲክላሬሽን መርህ ሀያ አምስት መሰረት ሰለም፣ልማት እና የአካባቢ ጥበቃ እርስ በእርስ የተሳሰሩ እና የማይነጣጠሉ ናቸው፡፡

እ.ኤ.አ በ2002 ዓ.ም በደቡብ አፍሪካ ጆሃንስበርግ ከተማ ዋና ትኩረቱን ድህነትን ማጥፋት ላይ ያተኮረ የአለም የዘላቂ ልማት ስብሰባ ተካሂዶ የነበር ሲሆን ዘላቂ ልማትን የማቀናጀት ጉዳይም ዋናው የስብሰባው አጀንዳ ነበር፡፡ በምእተ አመቱ የልማት ግብ ቁጥር 7 ላይ የአካባቢን ቀጣይነት የማረጋገጥ ግብ የተቀመጠ ሲሆን የግቡ ዋና አላማም የዘላቂ ልማት መርህን በሀገራት ፖሊሲዎች እና የልማት መርሀ ግብሮች ውስጥ ማቀናጀት ነው፡፡ በኢትዮጵያ የህግ ሥርዐትም ዘላቂ ልማትን የማቀናጀት መርህ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ተጠቅሶ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 43 (1) የኢትዮጵያ ህዝቦች በአጠቃላይም ሆነ በኢትዮጵያ ያሉ ብሔሮች፣ብሔረሰቦች ሕዝቦች በተናጠል የኑሮ ሁኔታቸውን የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ መሆኑ በግልፅ አስፍሯል፡፡ በሌላ በኩል የኢትዮጵያ የአካባቢ ፖሊሲ ቁጥር 4.1 (ሀ) ላይ የአኗኗር ሁኔታ ዘላቂነት እንዲኖረው ለማድረግ የሥነ ሕዝብ ዕቅድን፣የተፈጥሮ ሀብት አያያዝን፣አካባቢን መልሶ እንዲያገግም ማድረግንና መንከባከብን ማቀናጀት እንደሚያስፈልግ ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995 መግቢያ ላይ በግልፅ እንደተጠቀሰው መንግስታዊ ሰነድ በአካባቢ ላይ ሊያስከትለው የሚችለውን ተፅእኖ ለመለየት ገና ከመፀድቁ በፊት አካባቢያዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ባህላዊና፣ማህበራዊ ታሳቢዎችንና ግቦችን ዘላቂ ልማትን ለማምጣት በሚያመች ሁኔታ እንዲዋሀዱና እንዲቀናጁ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

6.2. የቅድም ጥንቃቄ መርህ (Precautionary Principle)

ከአካባቢ ህግ መርሆች ውስጥ በስፋት እና በዋናነት የሚጠቀሰው የቅድመ ጥንቃቄ መርህ ነው፡፡በአብዛኛው የአካባቢ ህጎች የሚተገበሩት በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን ተጽዕኖ የሚያስረዳ በሳይንስ የተረጋገጠ የተሟላ መረጃ በሌሉባቸው በእጅጉ የተወሳሰቡ ጉዳዮች ላይ ነው፡፡ለምሳሌ አንድ የልማት እንቅስቃሴ በአካባቢ እና በሰዎች ጤንነት ላይ የሚስከትለውን ተጽእኖ ሙሉ በሙሉ በእርግጠኛነት ለመወሰን አይቻልም፡፡ በቅድመ ጥንቃቄ መርህ መሰረት አንድ የልማት አንቅስቃሴ በአካባቢ ላይ ጉዳት ያስከትላል ወይም ቀድሞ ወደነበረበት ይዞታው ለመመለስ የማያስችል አደጋ ሊያስከትል ይችላል የሚል ስጋት ሲኖር እና የአደጋውን መጠን በሳይንስ በበቂ ሁኔታ ማረጋገጥ አለመቻል በአካባቢ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመከላከል የሚያስችል እርምጃ የሚወሰድበትን ግዜ ወደፊት ለማስተላለፍ እንደ ምክንያት ሊወሰድ አይችልም፡፡ ከዚህም ለመረዳት የሚቻለው አንድ

የልማት እንቅስቃሴ የሚያደርሰውን አካባቢያዊ ጉዳት ለመገመት የሚያስችል ሳይንሳዊ መረጃ እስኪገኝ ከመጠበቅ ይልቅ ድርጊቱ የሚያስከትለውን ጉዳት በውቅቱ መቆጣጠር እንደሚያስፈልግ ነው።በቅድመ ጥንቃቄ መርህ መሰረት በአካባቢ ላይ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል የልማት እንቅስቃሴ የሚያካሂድ ግለሰብ ወይም ድርጅት እንቅስቃሴው በአካባቢ ላይ ጉዳት የማያስከትል ስለመሆኑ የማስረዳት ሸክም ይኖርበታል።

በሪዮ ዲክላሬሽን መርህ 15 መሰረት አካባቢን ለመጠበቅ ይቻል ዘንድ እያንዳንዱ ሀገር እንደ የሀገሩ የኢኮኖሚ አቅም ሁኔታ የቅድመ ጥንቃቄ መርህን መተግበር እንዳለበት ያስረዳል።የቅድመ ጥንቃቄ መርህ በአብዛኛዎቹ አለም አቀፍ የአካባቢ ስምምነቶች ውስጥ ተካትቶ የሚገኝ ሲሆን ለምሳሌ ያህል ኢትዮጵያ ካፀደቀቻቸው ኮንቬንሽኖች እና ፕሮቶኮሎች መካከል፡

- እ.ኤ.አ በ1992 ዓ.ም የተደነገገው የብዝሀ ህይወት ኮንቬንሽን መግቢያ
- እ.ኤ.አ በ2000 ዓ.ም የተደነገገው የስቶክሆልም ኮንቬንሽን መግቢያ
- እ.ኤ.አ በ1992 ዓ.ም የተደነገገው የአየር ንብረት ለውጥ ኮንቬንሽን አንቀጽ 3(3)
- እ.ኤ.አ በ1991 ዓ.ም የተደነገገው የባማኮ ኮንቬንሽን አንቀጽ 4(3)
- እ.ኤ.አ በ 2000 ዓ.ም የተደነገገው የካርታሄና ፕሮቶኮል አንቀጽ 10 እና 11 ውስጥ ይገኛል።

6.3 የመከላከል መርህ (Prevention Principle)

የሳይንስ ኤክስፐርቶች የመከላከል መርህን ከስነመሕዳራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች አንጻር ወርቃማው የአካባቢ መመሪያ በማለት ይገልጹታል።በአንዳንድ ሁኔታዎች አካባቢያዊ ጉዳቶች አንድ ግዜ ከተከሰቱ በኃላ ጉዳት የደረሰበትን አካባቢ ወደ ቀድሞ ይዞታው ለመመለስ ፈጽሞ የማይቻልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል።ለዚህም እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ የሚችሉት አካባቢያዊ ጉዳቶች የእንስሳት እና እጽዋት ዘር መመናመን፣ የአፈር መሸርሸር እና በቀላሉ ሊወገዱ የማይችሉ መርዛማ ኬሚካሎችን ወደ ባህር ማራገፍ እና የመሳሰሉት ናቸው።በአንድ አካባቢ ላይ የደረሰውን ጉዳት ለመጠገን የሚቻል ቢሆን እንኳን አካባቢውን መልሶ ለማቋቋም አጅግ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ ሊያስፈልግ ይችላል።በአብዛኛው በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ሁሉንም አደጋዎችን ሙሉ በሙሉ መከላከል ባይቻልም የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች እየተከናወኑ አስፈላጊ የሆኑ የልማት ሂደቶች እንዲቀጥሉ ለማስቻል በአካባቢ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎችን በተቻለ መጠን መቀነስ ይቻላል።

በአካባቢ ላይ የሚደርስ ጉዳትን ቀድሞ የመመርመር፣ የልቀት መጠንን እና የተለያዩ ምርቶችን ደረጃ የመወሰን እና በቅርብ የሚገኙ ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆኑ የቴክኖሎጂ ምርቶችን መጠቀም

በመከላከል መርህ ውስጥ ጎልተው የሚጠቀሱ ተግባራት ናቸው፡፡በመከላከል መርህ ውስጥ ከሚገኙ ግዴታዎች አንዱ በአካባቢ ላይ ጉዳትን ለማስከተል አቅም ያላቸውን እንቀስቃሴዎች ቀድሞ የመመርመር ሂደት ነው፡፡ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ አካባቢያዊ ጉዳቶች እንዳይከሰቱ ተገቢውን ጥንቃቄ አለማድረግ አለማቀፍ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ሲሆን በተገቢ ሁኔታ የተካሄደ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ተገቢ የሆነ ጥንቃቄ መደረጉን ለማረጋገጥ መለኪያ ይሆናል፡፡

የመከላከል መርህ የአደገኛ ቆሻሻዎች እና የተባይ ማጥፊያዎች ማምረት፣ ማጓጓዝ፣ ማከማቸት እና አወጋገድን ለመቆጣጠር የወጡ ህጎችን ለማዘጋጀት ትልቁን መሰረት የጣለ ሲሆን በተለይም ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ የአደገኛ ቆሻሻዎች ዝውውር እና አወጋገድን የሚቆጣጠረው የባዝል ኮንቬንሽን እንዲደነገግ ትልቁን መሰረት ጥሏል፡፡

6.4. የበከለ ይክፈል መርህ (Polluter Pays Principle)

የበከለ ይክፈል መርህ እ.ኤ.አ ከ 1970 ዎቹ አመታት ጀምሮ በአካባቢ ህግ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ሲያሳድር የቆየ ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡የመጀመሪያው የበከለ ይክፈል መርህ የተዘጋጀው በአለም አቀፉ የኢኮኖሚ ልማት እና ትብብር (Organization for Economic cooperation and Development) ሲሆን ዋና አላማውም መንግስታት ለብክለት ቁጥጥር ተብለው በግሉ ዘርፍ ላይ የሚጣሉ ክፍያዎችን እንዳይደጉሙ ለመገደብ የተዘጋጀ ነበረ፡፡ የዚህ መርህ ዋና አላማ በካዩ ለተጎጂዎች ተገቢውን ካሳ በመክፈል ብቻ የሚያበቃ ሳይሆን ጉዳት የደረሰበትንም አካባቢ መልሶ እንዲያገግም የሚያስችለውንም ወጪ እንዲሸፍን የሚያስገድድ ነው፡፡

የበከለ ይክፈል መርህ አራት መሰረታዊ ጥያቄዎችን የያዘ ሲሆን እነዚህም ብክለትን የሚያስከትሉ እንቅስቃሴዎች ምንድን ናቸው፣ በካይ የሚባሉት እነማን ናቸው፣ በካዩ ላደረሰው ጉዳት ምን ያህል መክፈል አለበት፣ክፍያው ለማን መከፈል አለበት የሚሉ ጥያቄዎችን የያዙናቸው፡፡ በካይ ማለት በአካባቢ ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ጉዳት የሚያደርስ ወይም ጉዳት እንዲደርስ የሚጋብዙ ሁኔታዎችን የሚፈጥር ግለሰብ ወይም ድርጅት ሊሆን ይችላል፡፡በብክለት ምክንያት ለሚደርስ ጉዳት የሚከፈል የጉዳት ካሳ ክፍያ ከደረሰው ጥፋት ጋር እኩል መሆን ያለበት ሲሆን ክፍያውም የሚፈጸመውም ጉዳት ለደረሰበት ግለሰብ ወይም ድርጅት ይሆናል፡፡

የበከለ ይክፈል መርህ በሪዮ ዲክላሬሽን መርህ 16 ላይ የተጠቀሰ ሲሆን መንግስታት በአካባቢ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች የአጠቃላዩን ህዝብ ጥቅም ከግንዛቤ ውስጥ ባስገባ እና የአለም አቀፍ ንግድን እና ኢንቨስትመንት በማያስተጓጉል ሁኔታ በካዩ ላደረሰው ጉዳት ወጪውን እንዲሸፍን

ይደነግጋል፡፡አብዛኛዎቹ አካባቢያዊ ጉዳቶች የሚደርሱት ለኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴያቸው የሚያስፈልጋቸውን ወጪ በማምረት ሂደቱ ውስጥ ተሳትፎ ለሌላቸው አካላት በሚያስተላልፉ አምራቾች ነው፡፡ለምሳሌ ምርት በማምረት ሂደት ያልተጣራ ጭስን ወደ ከባቢ አየር የሚለቅ ወይም ያልተጣሩ ኬሚካሎችን ወደ ወንዞች የሚለቅ ፋብሪካ ቆሻሻዎቹን ምንም ወጪ ሳያወጣ የሚያስወግድ ሲሆን በተቃራኒው በወንዙ ተፋሰስ ዙሪያ የሚኖሩ ነዋሪዎች በወንዙ ለመጠቀም በራሳቸው ወጪ የዉሀ ማጣሪያ ለመገንባት ይገደዳሉ፡፡ በተመሳሳይ የመኪና አሽከርካሪ የነዳጅ እና የጥገና ወጪ የሚሸፍን ሲሆን ከመኪናው የሚወጣውን ጭስ ለማሰወገድ የሚያስፈልገውን ወጪ ወደ ህብረተሰቡ ያስተላልፋል፡፡በመሆኑም የበከለ ይክፈል መርህ ዋና አላማ ምንም እንኳን በአካባቢ ላይ የሚደርስን ብክለት በገንዘብ ለመተመን አስቸጋሪ ቢሆንም ለጉዳቱ ምክንያት የሆነው አካል ሙሉ ወጭ እንዲከፍል የሚገደድበት መርህ ነው፡፡አንድ ተቋም በአካባቢ ላይ ላደረሰው ጉዳት ተገቢውን ክፍያ እንዲከፍል ቢደረግ እንኳን አምራቹ የተጣለበትን ክፍያ በሚያመርታቸው ምርቶች ዋጋ ላይ በመጨመር መልሶ ወደ ተጠቃሚው ያስተላልፋል፡፡

የበከለ ይክፈል መርህን በስራ ላይ ለማዋል ከሚያስችሉ መንገዶች ውስጥ አንዱ በካዩ የብክለት መቆጣጣሪያ መሳሪያዎችን እንዲጠቀም በማድረግ ሲሆን ሌላው አማራጭ የግብር ክፍያ ተመንን ከፍ በማድረግ ነው፡፡አንዳንዴ ይህንን መርህ በተግበር በስራ ላይ ለማዋል አስቸጋሪ የሚሆንበትም ግዜ ሲኖር ለምሳሌ ብክለቱ የተከሰተው በተመሳሳይ ግዜ ከሚከሰቱ የተለያዩ ተያያዥ ምክንያቶች ሲሆን እና በካዩ ላደረሰው ጉዳት ካሳ ለመክፈል አቅም ሳይኖረው ወይም ኪሳራ ላይ ሲወድቅ ነው፡፡

6.5. በአካባቢ ጉዳዮች ላይ ያሉ መረጃዎች፣ የብዙሀን ተሳትፎ እና የፍትህ ተደራሽነት

በአካባቢ ጉዳዮች ላይ ያሉ መረጃዎች የብዙሀን ተሳትፎ እና የፍትህ ተደራሽነት በሪዮ ዲክላሬሽን መርህ አስር ላይ ተዘርዝረው ይገኛሉ፡፡በአጠቃላይ የዜጎች መረጃ የማግኘት ነፃነት፣ ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ እና ፍትህ የማግኘት አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች በብዙ ሀገራት ህገ መንግስቶች እንዲሁም አለም አቀፍ እና አህጉራዊ ስምምነቶች ውስጥ ተካትተው ይገኛሉ፡፡የእነዚህ ሶስት የህግ ድንጋጌዎች ዋና አላማ ሰዎች በአካባቢ አያያዝ ጉዳዮች እና በአካባቢ ላይ በሚደርሱ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎ እንዲያደርጉ በማስቻል የመንግስት አሰራር ግልፅ እንዲሆን በተጨማሪም በአካባቢ አያያዝ ላይ የሚሰሩ ተቋማት እንዲጠናከሩ ይረዳል፡፡

በሪዮ ዲክላሬሽን መርህ አስር ላይ የሚገኘው መረጃ የማግኘት መብት የሚያመለክተው ከአካባቢ ጋር ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮች መረጃ በቅርብ መገኘት እና የመንግስት ተቋማት አካባቢያዊ መረጃዎቹን ለህዝብ የሚያቀርቡባቸው ስልቶችን የሚያብራራ ነው፡፡በተጨማሪም የሪዮ ዲክላሬሽን የድርጊት መርሀ ግብር የሆነው አጀንዳ 21 ምእራፍ 23 ላይ ግለሰቦች፣ ቡድኖች እና ድርጅቶች በብሄራዊ ደረጃ በመንግስት የሚካሄዱ የአካባቢ እና የልማት እንቅቃሴዎች በተለይም በአካባቢ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ እንቅስቃሴዎች ላይ አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች ማግኘት እንዳለባቸው ያስረዳል፡፡

የብዙሀን ተሳትፎ ማለት ግለሰቦች፣ ቡድኖች እና ድርጅቶች በአካባቢ አያያዝ ላይ ተጽእኖ የሚሳድሩ ህጎች በሚዘጋጁበት ወቅት፣ ብሔራዊ ህጎች እና ፖሊሲዎች በሚተገበሩበት ወቅት እንዲሁም የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሥርዐቶች በሚዘጋጁበት ወቅት ግለሰቦች ቡድኖች እና ድርጅቶች ለሚያበረክቱት አስተዋጽኦ የሚኖራቸውን እድል የሚረጋገጥበት ነው[11]፡፡የአጀንዳ 21 ምእራፍ 23 መግቢያ ላይ እንደተገለጸው የህዝቦች ተሳትፎ የዘላቂ ልማትን ለማሳካት አንዱ መሰረታዊ ቅድመ ሁኔታ እንደሆነ ተብራርቷል፡፡ በተጨማሪም ከሰብአዊ መብቶች ድንጋጌዎች መካከል እ.ኤ.አ በ1966 ዓ.ም የተደነገገው United Nations International Covenant on Civil and Political rights በህዝብ ጉዳዮች ውስጥ በቀጥተኛ ወይም በተወካዮች አማካኝነት የሚደረግ ተሳትፎን አካትቶ የያዘ ነው፡፡ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት በልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ የህዝቦችን ተሳትፎ አስፈላጊነት እውቅና የሰጠ ሲሆን በህገ መንግስቱ አንቀፅ 43 (2) ላይ እንደተገለፀው ዜጎች በብሄራዊ ልማት የመሳተፍ በተለይም አባል የሆኑበትን ማህበረሰብ

የፍትህ ተደራሽነት የሚያመለክተው በአካባቢ ላይ በሚደርሱ ጉዳቶች ወይም ወደ ፊት ሊደርሱ በሚችሉ ጉዳቶች ጉዳት የደረሰበት የተፈጥሮ ወይም የህግ ሰውነት ያለው አካል ተገቢውን የጉዳት ካሳ ለማግኘት የሚያስችላቸውን የፍርድ ቤት ወይም አስተዳደራዊ ውሳኔዎች እና ሥነ-ሥርዐቶችን የያዘ ነው፡፡የፍትህ ተደራሽነት አግባብነት ላለው አካል ቅሬታ የሚቀርብበትን ሥርዐት ላይ ብቻ የሚያተኩር ሳይሆን ለደረሰ ጉዳት ካሳ የሚጠይቅባቸውን የህግ መብቶች ጨምሮ የያዘ ነው፡፡ለምሳሌ የተባበሩት መንግስታት በባህር ላይ የተደነገገው ኮንቬንሽን (ኢትዮጵያ የስምምነቱ ፈራሚ ሀገር አይደለችም) (United Nations Convention on the Law of the Sea) በባህር ላይ በተፈጥሮ ወይም በህግ ሰውነት በተሰጠው አካል በሚደርስ ብክለት አባል ሀገራት ወቅታዊ እና በቂ ካሳ መከፈሉን ማረጋገጥ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡

[11] በአለም አቀፍ የአካባቢ ህግ ላይ የሥልጠና ማኑዋል (የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም፣2006) ገፅ 79

በተግባር እንደሚታየው በአካባቢ ጉዳዮች ላይ ያሉ መረጃዎች፣ የብዙሀን ተሳትፎ እና የፍትህ ተደራሽነት በጋራ የሚተገበሩ እና እርስ በእርስ የተሳሰሩ ናቸው።በአካባቢ ላይ ያለ የመረጃ ተደራሽነት ለውሳኔ አሰጣጥ እንዲሁም በመንግስት እና በግሉ ዘርፍ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ለመቆጣጠር እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚያስፈልግ መስፈርት ነው።በተመሳሳይ በአካባቢ ጉዳዮች ላይ ውጤታማ የሆነ የፍትህ ተደራሽነትን ለማስፈን አግባብነት ላለው ተቋም ጉዳዩን አቅርቦ ህጋዊ እርምጃ ለማስወሰድ የሚችል ብቁ ዜጋ ለማፍራት በቅድሚያ በአካባቢያዊ ጉዳዩች ላይ በቂ መረጃ እንዲኖር ያስፈልጋል።

በአካባቢ ጉዳዮች ላይ ውጤታማ የሆነ የመረጃ ተደራሽነትን ለማረጋገጥ፤ በውሳኔ አሰጣጥ የህዝቦች ተሳትፎን ለማረጋገጥ እና የፍትህ ተደራሽነትን ለመወሰን የሚያስችሉ ዋና ዋና ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው

- ሀገራት በተለያየ ደረጃ የሚገኙ የአካባቢ ጉዳዮችን እንዴት እንደሚያስተናግዱ እና ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው ዜጎች አግባብነት ባላቸው የተለያዩ እርከኖች ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ
- በሁሉም ደረጃ የሚገኙ የመንግስት ባለስልጣናት ስለ አካባቢ እና በአካባቢ ላይ አደጋ ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ነገሮች እንዲሁም በግሉ ዘርፍ ስለሚከናወኑ ተግባራት አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን የሚያገኙበት እና የሚሰበስቡት መጠን
- እያንዳንዱ ግለሰብ በሀገር ደረጃ በአካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ በመንግስት ባለስልጣናት የሚገኙ መረጃዎችን በተገቢው ሁኔታ መረጃዎቹን የሚያገኙበትን መጠን
- ግለሰቦች የተለያዩ ቡድኖች እና ድርጅቶች በአካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ በሚደረጉ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ በተገቢ ሁኔታ ለመሳተፍ ያላቸው እድል
- ሀገራት የብዙሀን ተሳትፎን እና ግንዛቤን ለመፍጠር አዋጆችን፣ ደንቦችን፣ ፖሊሲዎችን እና ፕሮግራሞችን ዜጎች በቀላሉ እንዲያገኙዋቸው የሚያደርጓቸው ጥረቶች
- ዜጎች አካባቢያዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አስተዳደራዊ እና በመደበኛ ፍርድቤቶች ጉዳያቸው በተገቢ ሁኔታ መስተናገዱ እና ለደረሰባቸው ጉዳት ተገቢውን የጉዳት ካሳ ማግኘት መቻላቸውን[12]

በአካባቢ ጉዳዮች ላይ ያሉ መረጃዎች፣ የብዙሀን ተሳትፎ እና የፍትህ ተደራሽነት አስፈላጊነት ላይ ከሪዮ ዲክላሬሽን መርህ አስር በተጨማሪ የተባበሩት መንግስታት የምዕተ አመቱ የልማት ግቦች እንዲሁም እ.ኤ.አ በ 2002 ዓ.ም በተካሄደው የአለም የዘላቂ ልማት ስብሰባ (World Summit on Sustainable

[12] ዝኒ ከማሁ ገፅ 80

Development) የአተገባበር እቅድ ላይ ይገኛል።በተለይ እ.ኤ.አ በ1998 ዓ.ም በተባበሩት መንግስታት የአውሮፓ የኢኮኖሚ ኮሚሽን መዋቅር ስር የተደነገገው የአርሀስ አህጉራዊ ኮንቬንሽን ሙሉ በሙሉ በመረጃ ተደራሽነት በብዙሀን ተሳትፎ እና በፍትህ ተደራሽነት ላይ ትኩረት የሚያደርግ ኮንቬንሽን ነው።

6.6. የጋራ ግን የየቅል የሆነ ሀላፊነት መርህ (common but differentiated responsibilities)

የጋራ ግን የየቅል ሀላፊነት መርህ በማደግ ላይ ባሉ እና ባደጉ ሀገራት መካከል ያለውን ለአለም የአካባቢ ችግሮች መፈጠር ያበረከቱትን እና የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ ታሪካዊ ልዩነት እንዲሁም ችግሮቹን በየበኩላቸው ለመፍታት ያላቸውን የቴክኒክ እና የኢኮኖሚ ልዩነት እውቅና የሚሰጥ መርህ ነው።ምንም እንኳን ሀገራት ለአለም አካባቢ ሁኔታ የጋራ የሆነ ሀላፊነት ቢኖርባቸውም ባደጉ እና በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት መካከል የሚኖረው ሀላፊነት የተለያየ ይሆናል።ይህ መርህ በሪዮ ዲክላሬሽን መርህ 7 ላይ የተጠቀሰ ሲሆን ሀገራት የመሬትን ስነ መህድርን ለመጠበቅ እና ለመንከባከብ በአለም አቀፍ ደረጃ መተባበር እንደሚኖርባቸው እና ለአለም አካባቢ ሁኔታ መጎሳቆል ሀገራት የሚኖራቸውን አስተዋጽኦ በሚመለከት የጋራ ግን የየቅል ሀላፊነት እንደሚኖራቸው ያስረዳል።ያደጉ ሀገራት ዘላቂ ልማትን ለማካሄድ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን ተጽእኖ ሀላፊነቱን መሸከም እንዳለባቸው እውቅና እንደሚሰጡ ይጠቅሳል።በተመሳሳይ የጋራ ግን የየቅል ሀላፊነት መርህ በተባበሩት መንግስታት መዋቅራዊ ኮንቬንሽን ውስጥ የተጠቀሰ ሲሆን አባል ሀገራት የአለም አየር ንብረትን ለመጠበቅ እና ለመንከባከብ በእኩልነት መርህ እና በሀገራት የጋራ እና የተለያየ ሀላፊነት እና ችሎታ መሆን እንዳለበት ይጠቅሳል።

ያደጉ ሀገራት ላለፉት ሁለት መቶ አመታት የከባቢ አየር ቦታን (atmospheric space) ያለምንም ተቀናቃኝ ሲጠቀሙ የነበረ ሲሆን በአለም ላይ ለተከሰቱ አካባቢያዊ ችግሮች ትልቁን ሚና ስለተጫወቱ እና ችግሮቹን ለመፍታት የሚያስችል ትልቅ አቅም ስላላቸው በአካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ የመሪውን ቦታ እንዲወስዱ ይጠበቃል።በተጨማሪም ያደጉ ሀገራት የራሳቸውን የዘላቂ ልማት ለማረጋገጥ ከሚያከናውኗቸው እንቅስቃሴዎች ጎን ለጎን በማደግ ላይ የሚገኙ ሀገራት የዘላቂ ልማት ሀላፊነቶቻቸውን ለመወጣት ለሚያከናውኗቸው ተግባራት የገንዘብ፣ የቴክኖሎጂ እና ሌሎች ድጋፎችን እንዲሰጡ ይጠበቅባቸዋል።በአጀንዳ 21 እንደተጠቀሰው ያደጉ ሀገራት በአመት ከሚያገኙት አጠቃላይ አመታዊ ምርት ውስጥ 0.7 በመቶ ለልማት እርዳታ አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ አስታውቀዋል።

የጋራ ግን የየቅል ሀላፊነት መርህ ሁለት መሰረታዊ ሀሳቦችን የያዘ ነው።የመጀመሪያው ሀሳብ አካባቢን ለመንከባከብ ሀገራት በብሄራዊ አህጉራዊ እና አለም አቀፍ ደረጃ ያለባቸውን የጋራ ሀላፊነት ላይ የሚያተኩር ነው።ሁለተኛው በአካባቢ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች የሀገራትን አስተዋጽኦ እና አደጋውን ለመከላከል ለመቀነስ እና ለመቆጣጠር ያላቸውን አቅም ላይ የሚያተኩር ነው።

የጋራ ሀላፊነት:-የሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ሀገራት በአንድ በተወሰነ የተፈጥሮ ሀብት አጠባበቅ ላይ ያላቸውን የጋራ ግዴታ የሚያሳይ ነው።የጋራ ሀላፊነት ተግባራዊ የሚሆነው የተፈጥሮ ሀብቱ በየትኛውም ሉአላዊ ሀገር ቁጥጥር ስር ያልሆነ ነገር ግን በሁሉም ሀገሮች የጋራ የህግ ጥቅም ስር የዋለ ነው።ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው የብዝሀ ህይወት ሀብት ሲሆን የሁሉም የሰው ዘር ጉዳይ (common concern of human kind) በመባል ይታወቃል።

የተለያየ ሀላፊነት:- አካባቢን ለመጠበቅ ሀገራት የሚኖራቸው የተለያየ ሀላፊነት በአብዛኛዎቹ አለም አቀፍ የአካባበቢ ስምምነቶች ውስጥ ተካትተው ይገኛሉ።በሀገራት ላይ የተለያዩ የአካባቢ ሀላፊነት ደረጃዎች የሚዘጋጁት የየሀገራቱን የወደፊት የኢኮኖሚ እድገት ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት እንዲሁም ለአካባቢያዊ ችግሮች መከሰት ሀገራት ያላቸውን ታሪካዊ አስተዋጽኦ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው።የተለያየ ሀላፊነት ጽንሰ ሀሳብ ዋና አላማ ታዳጊ ሀገሮች በአንድ በተወሰነ የህግ መመሪያ ላይ የሥርዐት ተከባሪነትን የሚያረጋግጡበትን ሁኔታ ማረጋገጥ እና በሂደት የህግ ስርአቱ የሚረጋገጥበትን ሁኔታ ማመቻቸት ነው።በተግባር እንደሚታየው ግን የተለያየ ሀላፊነት የተለያየ የህግ ግዴታን አያስከትልም።የተለያዩ ሀላፊነቶች ከሚተገበሩባቸው ዘዴዎች መካከል የችሮታ ግዜ (grace period) የትግበራን ግዜ በማዘግየት እና በጣም ጥብቅ ያልሆኑ ግዴታዎች ናቸው።

7. ብሔራዊ የአካባቢ ፖሊሲዎች እና ህጎች

7.1. የኢትዮጵያ የአካባቢ ፖሊሲ

በአለም አቀፍ ደረጃ አካባቢን የተመለከቱ ህጎች ተለይተው መቀረጽ የጀመሩት ከቅርብ ግዜ ወዲህ እንደሆነ ከላይ ለመግለጽ ተሞክሯል።በኢትዮጵያም አካባቢን የሚመለከቱ ህጎች መዘጋጀት የጀመሩት በተመሳሳይ ሁኔታ ነው። ከአካባቢ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የተለያዩ ህጎች በተለያዩ የህግ ክፍሎች ውስጥ ተበታትነው ይገኙ የነበር ሲሆን በተለይ በ13ኛው ክፍለ ዘመን የነበረው ፍትህ ነገስት በአካባቢዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት የሚያደርጉ ህጎችን በውቅቱ ይዞ እንደነበር የታሪክ መዛግብት ያስረዳሉ።

ኢትዮጵያ እምቅ የተፈጥሮ ሀብት ክምችት እንዳላት የሚታወቅ ሲሆን እነዚህም የግብርና ውጤቶች፣ማእድኖች፣የዱር አራዊቶች እና የውሃ ሀብቶች ናቸው፡፡ሆኖም በሰው ሰራሽ እና በተፈጥሮ አደጋዎች ምክንያት የኢትዮጵያ ህዝብ ከዚህ ሀብት ተገቢውን ጥቅም ሳያገኝ ቆይቷል፡፡ከቅርብ ግዜ ወዲህ በፖለቲካዊ፣ማህበራዊ፣እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ጉልህ የሆነ ለውጥ እየታየ መምጣቱ በአጠቃላይ በግለሰቦች እና በህዝቦች መካከል አካባቢያዊ በሆኑ ጉዳዮች ከፍተኛ የግንዛቤ ለውጥ ሊታይ ችሏል፡፡ ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው በተለያዩ ግዜያት የወጡ ፖሊሲዎች፣በህገ መንግስት ውስጥ የሚገኙ አካባቢን የተመለከቱ አንቀጾች፣የተለያዩ ተቋሞች እና ዝርዝር ህጎች መውጣታቸው ነው፡፡

እ.አ.አ በ1990ዎቹ የመጀመሪያ አመታት የኢትዮጵያ መንግስት በአካባቢ ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችለውን መሰረት የጣለ ሲሆን በተለይም የአካባቢ ጉዳዮችን በብሔራዊ በፖሊሲ ደረጃ እንዲዘጋጅ ያስቻለውን የኢትዮጵያ የእንክብካቤ ስልት ዝግጅት እ.አ.አ በ1989 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን ሂደቱም አስራ ሶስት አመትን ሊወስድ ችሏል፡፡የኢትዮጵያ የእንክብካቤ ስልት አቀራረጽ በሶስት ወቅቶች ተካሄደ ሲሆን ሥራው የተጀመረው በኢትዮጵያ መንግስት እና በዓለም አቀፍ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ማህበር መካከል የመጀመሪያው የፕሮጀክት ስምምነት ከተፈረመ በኃላ ነበር፡፡በአንደኛው ወቅት (እ.ኤ.አ ከ 1989-1990) ለኢትዮጵያ የእንክብካቤ ስልት የጽንሰ ሀሳብ መሰረት የሚሆን ረቂቅ የተዘጋጀበት ሲሆን ረቂቁ ያተኮረው ቁልፍ የሆኑ የአካባቢና የልማት ጉዳዮችን በመለየት ነበር፡፡በሁለተኛው የስልቱ ዝግጅት ወቅት (እ.ኤ.አ ከ 1990-1998) የኢትዮጵያን የእንክብካቤ ስልትን ፖሊሲ፣ተቋማዊ መዋቅርና እና የድርጊት መርሀ ግብር በማዘጋጀት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ሶስተኛው ወቅት ትኩረት አድርጎ የነበረው የክልልሎችን አቅም መገንባት ሲሆን የክልል መስተዳድሮች የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ የድርጊት መርሀ ግብሮችና የልማት ፕሮግራሞች የሚጠናቀቁበትና ሥራ ላይ መዋል የሚጀምሩበት ክፍል ነው፡፡

የኢትዮጵያ እንክብካቤና ስልት ሰነድ በአምስት ጥራዞች የተዘጋጀ ሲሆን ጥራዝ አንድ፣ የተፈጥሮ ሀብት መሰረት፣ ጥራዝ ሁለት፣ ፖሊሲና ስልት፣ ጥራዝ ሶስት፣ ተቋማዊ መዋቅር፣ ፣ጥራዝ አራት፣ የድርጊት መርሀ ግብር እና ጥራዝ አምስት የኢንቨስትመንት መርሀ ግብር ጥንቅር ናቸው፡፡የ ኢትዮጵያ የአካባቢ ፖሊሲ ከኢትዮጵያ እንክብካቤ ስልት ሰነድ ጥራዝ ሁለት የተወሰደ ሲሆን በአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣንና በተለያዩ ዘርፎች የሚካሄዱትንና መካሄድ ያለባቸውን አካባቢ ነክ ተግባራት ለመምራት ታስቦ የተዘጋጀ ሲሆን ፖሊሲው መጋቢት 24 ቀን 1989 በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሚንስትሮች ምክር ቤት ፀደቋል፡፡

የኢትዮጵያ የአካባቢ ፖሊሲው ግብ የኢትዮጵያውያንን ጤንነት እና የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል፣ለማሳደግና የወደፊት ትውልዶች ፍላጎቶቻቸውን መሟላት የሚኖራቸውን አቅም ከአሁኑ ትውልድ ፍላጎቶች መሟላት ጋር ለማቻቻል፣በአጠቃላይ አስተማማኝ በሆነ የተፈጥሮአዊ፣የሰው ሰራሽ፣የባህላዊ ሀብትና የአካባቢ አያያዝና አጠቃቀም አማካኝነት ዘላቂ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ልማትን ማራመድ ነው።

7.2. የአካባቢ ጉዳዮች በሕገ መንግስት ውስጥ

የኢትዮጵያ የአካባቢ እንክብካቤ ስልት በ1995 ዓ.ም በፀደቀው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ህገ መንግስት ውስጥ የተለያዩ ከአካባቢ አያያዝ እና አጠባበቅን የሚመለከቱ ህጎች እንዲካተቱ ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል።ለምሳሌ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 44 መሰረት ሁሉም ሰዎች ንፁህ እና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት እንዳላቸው ያረጋግጣል።በተመሳሳይ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 92 መሰረት የሚከተሉትን የአካባቢ ደህንነት ጥበቃ ዓላማዎችን አስቀምጧል

1) መንግስት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ንጹህና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረው የመጣር ኃላፊነት አለበት።
2) ማንኛውም የኢኮኖሚ ልማት እርምጃ የአካባቢውን ደህንነት የማያናጋ መሆን አለበት።
3) የህዝብን የአካባቢ ደህንነት የሚመለከት ፖሊሲና ፕሮግራም በሚነደፍበትና ሥራ ላይ በሚውልበት ግዜ የሚመለከለተው ህዝብ ሁሉ ሀሳቡን እንዲገልፅ መደረግ አለበት።
4) መንግስትና ዜጎች አካባቢያቸውን የመንከባከብ ግዴታ አለባቸው።

7.3. የአካባቢ ፖሊሲውን ለማስፈፀም የወጡ ዝርዝር ሕጎች

በአካባቢ ፖሊሲው ውስጥ የተዘረዘሩትን የአካባቢ አያያዝ ግቦች ለማስፈፀም የሚያስችሉ አዋጆችና ደንቦች ወጥተዋል።ዋና ዋናዎቹም ቀጥለው የተዘረዘሩት ናቸው።

የአካባቢ ጥበቃ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ (አዋጅ ቁጥር 295/2002) ፡-ይህ አዋጅ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣንን ስልጣን እና ተግባር የሚያብራራ ሲሆን በተጨማሪም እያንዳንዱ አግባብ ያለው መሥሪያ ቤት የሥራ እንቅስቃሴዎቹ ከማቋቋሚያ አዋጁ እና ከሌሎች የአካባቢ ጥበቃ ግዴታዎች ጋር ተጣጥመው መካሄዳቸውን የመከታተልና የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለው የአካባቢ አሀድ በስሩ ማቋቋም እንዳለበት ይደነግል።በፌደራልና በክልል የአካባቢ ጥበቃ መስሪያ ቤቶች መሀል የተቀናጀ ነገር ግን የየቅል የሆነ ኃላፊነትን የሚያጠናክር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱም ገለልተኛ የሆኑ

የክልል የአካባቢ መስሪያ ቤቶች እንዲቋቋሙ ተደርጓል።በመሆኑም እያንዳንዱ ብሔራዊ ክልልላዊ መንግስት በኢትዮጵያ የአካባቢ ፖሊሲና እንክብካቤ ስልት በመመስረትና በውሳኔ ሂደት ሕዝቡን በማሳተፍ

- የክልሉን የአካባቢ እንክብካቤ ስልት የሚያዘጋጅ፣እንዲሁም የአተገባበር፣የግምገማና የክለሳ ስራዎችን የሚያስተባብር፣የክልሉን አካባቢ ሁኔታ ክትትል፣ጥበቃና ቁጥጥር ተግባር የሚያከናውን ራሱን የቻለ የአካባቢ መስሪያ ቤቶች መካከል አንዱን ለዚሁ ተግባር ይሰይማል።
- የክልል የአካባቢ መስሪያ ቤቶች የፌደራል የአካባቢ ደረጃዎች በስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣሉ፣እነደ አስፈላጊነቱም ከፌደራሉ የጠበቁ ደረጃዎችን በማውጣት ስራ ላይ ሊያውሉ ይችላሉ።
- የክልል የአካባቢ መስሪያ ቤቶች የየክልላቸውን የአካባቢና የዘላቂ ልማት ሁኔታ በተመከለተ ዘገባ በማዘጋጀት ለባለስልጣኑ ያቀርባሉ።

የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/2002- ይህ አዋጅ የልማት ሀሳብ ንድፍ ሲዘጋጅ፣ ቦታው ሲመረጥ፣ሲገነባ ወይም ሲተገበር እንደዚሁም በመተግበር ላይ ያለ እንቅስቃሴ ሲሻሻል ወይም ሲቋረጥ የሚያስከትለውን ተፅእኖ በመተንበይና አስቀድሞ በማረም በውል የታሰበበትን ልማት ለማምጣት ያግዛል።በተጨማሪም አንድ ፕሮጀክት በአካባቢ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ተፅእኖ ለመለየት ገና ከመፅደቁ በፊት መገምገም፣የመፅደቂያው ውሳኔ በሚሰጥበት ወቅት አካባቢያዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ባህላዊና ማህበራዊ ታሳቢዎችንና ግቦችን ዘላቂ ልማትን ለማምጣት በሚያመች ሁኔታ እንዲዋሀዱና እንዲቀናጁ ለማድረግ ያስችላል።

የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/2002 - ይህ አዋጅ ከኢንዱስትሪ ተቋሞች፣ከግለሰብ ወይም ከማህበረሰብ የመገልገያ ዕቃዎች ወይም ከማናቸውም ምንጮች የሚለቀቁ ሊጎዱ የሚችሉ ንጥረ ነገሮችን፣ህይወት ያላቸውን ነገሮችን ወይም ቅሪቶቻቸውን የመቀነስ ወይም ሲቻል የማቆም፣በጣም ጎጂ የሆኑቱን ንጥረ ነገሮች ደግሞ እንዳይለቀቁ የሚደነግግ ህግ ነው።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. አካባቢ ማለት ምን ማለት ነው?
2. የአካባቢ ሕግን ታሪካዊ አመጣጥ ከአለም አቀፍ ህግ አኳያ አብራሩ?
3. ከአለም አቀፍ የአካባቢ ህግ መርሆች ውስጥ የመከላከል መርህን እና የቅድመ ጥንቃቄ መርህን መሰረታዊ ልዩነት ግለፁ?

ምዕራፍ ሁለት

ቁልፍ የአካባቢ ጉዳዮችን የሚመሩ አለም አቀፍ እና ብሔራዊ ህጎች

ሠልጣኞች በዚህ ምዕራፍ ማብቂያ ላይ

- አለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ምን ማለት እንደሆነ ያብራራሉ
- አለም አቀፍ አየር ንብረት ለውጥ ስምምነቶችን ይለያሉ
- የአየር ንብረት ለውጥ ተፅእኖና የኢትዮጵያ ምላሽ ምን እንደሆነ ያስረዳሉ
- የከባቢ አየር ሽፋን መሳሳት አለም አቀፍ ስምምነት እና ሀገራዊ ህጎችን ይገነዘባሉ
- የአደገኛ ቆሻሻዎች እና ኬሚካሎች አለም አቀፍ ስምምነት እና ሀገራዊ ህጎችን ይለያሉ
- የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ እና የደህንነተ ሕይወት አለም አቀፍ ስምምነቶች እና ሀገራዊ ህጎችን ያብራራሉ
- በርሀማነት፣የተራራዎች፣የጫካዎች እና የዋልታዎች ስነ-ምህዳር አያያዝ እና ተያያዥ ህጎችን ያስረዳሉ

1) አለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ

የአየር ፀባይ (weathere) እና የአየር ንብረት (climate) እጅግ የተሳሰሩ ቢሆኑም መሰረታዊ ልዩነት አላቸው፡፡የአየር ፀባይ ማለት የአንድ የተወሰነ አካባቢን የእለት ተእለት የአየር ፀባይ ለውጥን የሚያሳይ ሲሆን ዋና ዋና የሚይዛቸው ነገሮችም ሙቀት ፣ርጥበት፣ወበቅ፣የንፋስ ፍጥነት እና አቅጣጫ የመሳሰሉትን ነው፡፡በሌላ አገላለፅ የአየር ፀባይ የከባቢ አየርን የአጭር ግዜ ሁኔታን የሚያስረዳ ነው፡፡በሌላ በኩል የአየር ንብረት ማለት በአንድ በተወሰነ አካባቢ ወይም ክልል የሚታይ አማካይ የአየር ፀባይ ሲሆን በአብዛኛው በ30 አመታት ውስጥ የሚታይ አማካይ የአየር ሁኔታ ውጤት ነው፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ ማለት አማካይ የአየር ንብረት በጊዜና በቦታ ሽፋን በፊት ከነበረበት የመቀያየር ሁኔታን የሚያመለክት ለውጥ ሲሆን እነዚህም የሙቀት መጨመር፣የዝናብ መጠን መለዋወጥ፣የበረዶ ግግር መቅለጥና መጥፋት፣የባህር ዳርቻ ውሀ መጨመር የመሳሰሉት ናቸው፡፡በአሁኑ ሰአት በሳይንቲስቶች እና በፖሊሲ አውጪዎች ከፍተኛ ትኩረትን እያገኘ የመጣው አለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ነው፡፡የአለም ሙቀት መጨመር (Global warming) በዋናነት የመሬት ውጫዊ ክፍል

ሙቀት መጨመርን የሚያሳይ ሲሆን የመሬት ሽፋን አካላት የሚባሉት ከባቢ አየር፣ሁሉንም በመሬት ላይ እና በመሬት ውስጥ የሚገኙ የውሀ አካላትን እንዲሁም በበረዶ ግግር መልክ የሚገኙ የውሀ አካለትን እና የመሳሰሉትን ጨምሮ የያዘ ክፍል ነው፡፡

መሬት በታሪክ ሂደት ውስጥ የተለያዩ የአየር ንብረት ለውጦችን ያስተናገደች ሲሆን ከበረዶ ዘመን አንስቶ እስከ ሙቀት መጨመር ያሉ ለውጦች ታይተዋል፡፡ከኢንዱስትሪው አብዮት በፊት ዋና ዋናዎቹ በመሬት የአየር ንብረት ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ የሚያሳድሩ የነበሩት የእሳተ ገሞራ ፍንዳታዎች እና የመሬት ዛቢያ ለውጥ ነበሩ፡፡ነገር ግን ከ18ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ጀምሮ የኢንዱስትሪውን አብዮት ተከትለው ሲካሄዱ የቆዩት የሰዎች እንቅስቃሴዎች በከባቢ አየር ላይ ከፍተኛ ለውጥ ሊያስከትሉ ችለዋል፡፡

1.1) የግሪን ሀውስ ኢፌክት

የመሬት አየር ንብረት ከፀሀይ በቀጥታ በሚመጣ ጨረር እና ምድርን ሸፍኖ በሚገኘው ከባቢ አየር መካከል በሚደረግ መስተጋብር ምክንያት የተለያዩ ተፅዕኖዎች ይታዩበታል፡፡ከባቢ አየር በውስጡ ናይትሮጅን፣ ኦክሲጅን እና የግሪን ሀውስ ጋዞችን ማለትም ካርቦንዳይኦክሳይድ፣ሚቴን፣ናይትረስኦክሳይድ፣ኦዞን እና ፍሎሮካርበኖችን የያዘ ነው፡፡ግሪን ሀውስ ጋዞች ከፀሀይ የሚመጣውን ሙቀት በመቀበልና አምቆ በመያዝ እና እንደገና በመልቀቅ ሙቀትን በተመጣጣኝ ሁኔታ ይለቃሉ፡፡የግሪን ሀውስ ጋዞች ከከባቢ አየር እና ከመሬት የላይኛው ሽፋን አካል ተንፀባርቆ የሚመለሰውን የፀሀይ ነፀብራቅ በታችኛው የከባቢ አየር ሽፋን ይዘው ያስቀራሉ፡፡ይህም ሂደት የግሪን ሀውስ ኢፌክት በመባል ይታወቃል፡፡የግሪን ሀውስ ኢፌክት የአለምን ሙቀት ለማመጣጠን በእጅጉ የሚረዳ ሲሆን የግሪን ሀውስ ጋዞች በከባቢ አየር ውስጥ ባይኖሩ ኖሮ መሬት ልክ እንደ ጨረቃ ቀዝቃዛ ትሆን የነበረ ሲሆን የመሬት ሙቀት አሁን ካለበት 14 ዲግሪ ሴንቲግሬድ በመውረድ ከዜሮ በታች 18 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ይሆን ነበር፡፡ በመሆኑም የግሪን ሀውስ ኢፌክት በራሱ ችግር ሳይሆን የግሪን ሀውስ ጋዞች በተለያዩ የሰው ልጆች እንቅስቃሴዎች ምክንያት መጠናቸው ከግዜ ወደ ግዜ መጨመሩ ለአየር ንብረት ለውጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

1.2. የሙቀት ሳቢ ጋዞች

ሙቀት አምጭ ጋዞች ማለት በመሬት ከባቢ አየር የሚገኙና ሙቀትን አምቀው የሚያስቀሩ ከተፈጥሮና ከኢንዱስትሪ የሚመነጩ ጋዞች ሲሆኑ በኪዮቶ ፕሮቶኮል Annex A ላይ የተዘረዘሩት ማለትም ካርበን ዳዮክሳይድን፣ሚቴን፣ ሰልፈርሄክሳፈሎራይድን፣ ናይትረስኦክሳይድን፣ ሃይድሮፍሎሮካርበንን፣ ፐርፍሎሮካርበንን እንዲሁም በተባበሩት መንግስታት በአየር ንብረት ለውጥ ማእቀፍ ወደፊት ሊጨመሩ የሚችሉትንም ይጨምራል፡፡

ካርቦን ዳይኦክሳይድ (CO2):- ካርቦንዳይኦክሳይድ በስፋት በከባቢ አየር ወስጥ የሚገኝ ጋዝ ሲሆን ለአለም ሙቀት መጨመር 60 በመቶ አስተዋፅኦ ያደርጋል[13] ፡፡ ካርቦንዳይኦክሳይድ በከባቢ አየር ውስጥ ከ አምስት እስከ ሁለት መቶ አመት ሊቆይ የሚችል ሲሆን አፈጣጠሩም በዋናነት ከሰል፣ነዳጅ እና፣የተፈጥሮ ዘይት በሚቀጣጠሉበት ግዜ ነው፡፡ በሌላ በኩል የተወሰኑ የግብርና ስራዎች እና የደን መመንጠር ለካርቦንዳይኦክሳይድ መፈጠር ምክንያት ይሆናሉ፡፡ ውቅያኖሶች እና ደኖች ካርቦንዳይኦክሳይድ እና ሌሎች በካይ ጋዞችን ወደ ከባቢ አየር እንዳይቀላቀሉ ስበው የሚያስቀሩ ሲሆን በዚህም ምክንያት “የበካይ ጋዞች ማስረጊያ”(green house sinks) በመባል ይታወቃሉ፡፡በሌላ በኩል የደን መመንጠር በዛፎች ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ በካይ ጋዞች ወደ ከባቢ አየር እንዲቀላቀሉ የሚያደርግ ሲሆን የበካይ ጋዞች መጠንም በከባቢ አየር ውስጥ በእጅጉ እንዲጨምር ያደርጋል፡፡

ሚቴን (CH$_4$) :-ሚቴን በዋናነት የሚመነጨው ከሰል፣የተፈጥሮ ጋዝ እና የነዳጅ ዘይት በሚመረቱበት እና በሚጓጓዙበት ወቅት ነው፡፡ በተጨማሪም ሚቴን ከከብቶች እርባታ እና ከሌሎች የግብርና ስራዎች ሊመነጭ የሚችል ሲሆን የከተማ ቆሻሻ ማከማቻ አካባቢዎች ኦርጋኒክ የሆኑ ቆሻሻዎች በሚበሰብሱበት ወቅት እና በፈሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ አካባቢዎች ይፈጠራል፡፡ሚቴን ለአለም ሙቀት መጨመር የ 20 በመቶ አስተዋፅኦ ያለው ሲሆን በከባቢ አየር ውስጥም ለ12 አመታት መቆየት ይችላል[14]፡፡

ናይትረስ ኦክሳይድ (N$_2$O):- ናይትረስ ኦክሳይድ የሚመመነጨው ከግብርና እና ከኢንዱስትሪዎች እንዲሁም ከከሰል፣ከነዳጅ ዘይት፣ ከተፈጥሮ ጋዝ እና የደረቅ ቆሻሻዎች በሚቃጠሉበት ወቅት እንዲሁም

[13] የግሪን ሀውስ ተፅእኖ እና አለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ (Environmental Literacy Council National Science Teachers Association , 2007) ገፅ 9
[14] ዝኒ ከማሁ

ቆሻሻ ውሀ በሚጣራበት ወቅት ነው።ናይትረስ ኦክሳይድ ለአለም ሙቀትመጨመር የ 6 በመቶ አስተዋፅኦ ያለው ሲሆን በከባቢ አየር ውስጥ ለ114 አመታት መቆየት ይችላል[15]።

ፍሎሪኔትድ ጋዞች፡- ሀይድሮፍሎሮካርቦን(HFCs)፣ፐርፍሎሮካርበን(PFC$_s$) እና ሰልፈርሄክሳፍሎራይድ (SF_6) በጣም ከፍተኛ ሀይል ያላቸው በካይ ጋዞች ሲሆኑ የሚመነጩትም ከተለያዩ የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴዎች ነው።ምንም እንኳን እነዚህ ጋዞች የሚመነጩት በአነስተኛ መጠን ቢሆንም ሙቀትን በከባቢ አየር ውስጥ ስቦ የማስቀረት ከፍተኛ ሀይል አላቸው። ፍሎሪኔትድ ጋዞች የሚመነጩት ከተለያዩ የኢንዱስትሪ ምርቶች ሲሆን በዋናነትም በማቀዝቀዣ መሳሪያዎች ውስጥ፣በእሳት ማጥፊያ መሳሪያዎች ውስጥ እንዲሁም በስፖንጅና በፕላስቲክ ፋብሪካዎች ውስጥ ይገኛሉ። እነዚህ ጋዞች ለአለም ሙቀት መጨመር የ 14 በመቶ ድርሻ ያላቸው ሲሆን በከባቢ አየር ውስጥ ከሁለት አመት እስከ ሀምሳ ሺህ አመት መቆየት ይችላሉ[16]።

ለእነዚህ በካይ ጋዞች መመንጨት በዋናነት እንደምክንያት የሚጠቀሰው ከኢንዱስትሪ አብዮት በተለየም እ.ኤ.አ ከ1950 ዎቹ ጀምሮ የነበረው የኢኮኖሚ እድገት ሲሆን ይህንንም ተከትሎ የተከሰተው የኤሌክትሪክ ፍጆታ እና የመኪና ተጠቃሚዎች ቁጥር መጨመር ነው። እነዚህ በካይ ጋዞች በካባቢ አየር ውስጥ ለረጅም አመታት የሚቆዩ መሆናቸው በተለያዩ የሰዎች እንቅስቃሴዎች የሚመነጨው የበካይ ጋዝ መጠን ቢቆም እንኳን በከባቢ አየር ውስጥ ቀደም ብለው ተቀላቅለው የሚገኙት በካይ ጋዞች ለብዙ አመታት መኖራቸውን ይቀጥላሉ።

ይህ በእጅጉ እየጨመረ የሚገኘው የአለም ሙቀት በአካባቢ ላይ ከፍተኛ የሆነ ተፅእኖ ማሳደር ጀምሯል።የአየር ንብረት ኤክስፐርቶች እንደሚተነብዩት የአለም ሙቀት መጨመር በብዙ ቦታዎች የዝናብ መጠን መጨመርን፣የበርሀማነት መስፋፋትን እና በዋልታዎች አካባቢ የሚገኝ የበረዶ ሽፋንን ሊያጠፋ ይችላል።በተጨማሪም አማካይ የባህሮች ከፍታ በ21ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ በ88 ሳንቲሜትር ከፍ ይላል ተብሎ የሚገመት ሲሆን ይህም ለአነስተኛ የደሴት ሀገሮች ላይ ስጋት የሚፈጥር ይሆናል።

የአለም ሙቀት መጨመር በተክሎች እና በእንስሳት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ያሳድራል።የወቅቶች መፈራረቅ ላይ ከተለመደው ውጭ ለውጥ ስለሚኖር ይህም ረጅም የሙቀት ግዜን የሚያስከትል

[15] ዝኒ ከማሁ
[16] ዝኒ ከማሁ

ይሆናል፡፡በዚህም ምክንያት አንዳንድ የዕፅዋት እና የእንስሳት ዝርያዎች የሙቀቱን መጠን መላመድ ባለመቻላቸው ቀስ በቀስ ሊጠፉ ይችላሉ፡፡

እነደ አለም አቀፉ የአየር ንብረት ለውጥ ፓነል ሪፖርት መሰረት የአለም አማካይ የሙቀት መጠን መጨመር በዝናብ መጠን እና በከባቢ አየር እርጥበት ላይ ለውጥ ያስከትላል፡፡የአየር ሙቀት መጨመር የከባቢ አየር ዝውውር ላይ እና የውሀ ትነት መጠን ላይ ለውጥ የሚስከትል ሲሆን ይህም የዝናብ መጠን እና የባህር ከፍታ ላይ ለውጥ ያስከትላል፡፡እንደ አለም አቀፉ የአየር ንብረት ለውጥ ፓነል ግምት መሰረት እ.ኤ.አ በ 2100 የአለም አማካይ የባህር ከፍታ ከ 7.2-23.6 ኢንች (18-59 ሳ.ሜ) እንደሚጨምር ተገምቷል፡፡

2. አለም አቀፍ አየር ንብረት ለውጥ ስምምነቶች

አለም አቀፍ የሙቀት መጨመርን በሚመለከት አለም አቀፍ ስብሰባዎች መካሄድ የጀመሩት እ.ኤ.አ ከ1980 ዎቹ ዓ.ም ጀምሮ ነው፡፡እ.ኤ.አ በ1988 ዓ.ም በተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ እንደተገለፀው የአየር ንብረት ለውጥ የሁሉም የሰው ልጆች ጉዳይ መሆኑን እና የሁሉንም ሀገሮች አፋጣኝ እርምጃ የሚጠይቅ መሆኑ የተገለፀ ሲሆን ይህም አለም አቀፍ የአየር ንበረት ለውጥ ስምምነቶች እንዲዘጋጁ ፖለቲካዊ ድርድሮች እንዲጀመሩ አስችሏል፡፡በተመሳሳይ ወቅት የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም እናየአለም የሚትዮሮሎጂ ድርጅት በጋራ የመሰረቱት ገለልተኛ የሳይንስ ቡድን የሆነው አለም አቀፉ የአየር ንብረት ለውጥ ፓነልን አቋቁሟል፡፡ይህ ፓነል 2000 የሳይንስ እና የቴክኒክ ኤክስፐርቶችን ከአለም ዙሪያ አሰባስቦ የያዘ ሲሆን ዋና የስራ ድርሻውም የአየር ንብረት ለውጥን በተመለከተ ሳይንሳዊ መረጃዎችን ማሰባሰብ፣የሚያስከትለውን ተፅእኖ እና ተፅእኖዎቹን ለመቀነስ የሚቻልባቸውን መንገዶች ማፈላለግ ነው፡፡ፓነሉም የመጀመሪያውን የግምገማ ሪፖርት እ.ኤ.አ በ1990 ያቀረበ ሲሆን በመቀጠልም እ.ኤ.አ በ1995 እና 2001 እና በ2007 ዓ.ም ተከታታይ ሪፖርቶችን አቅርቧል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥን በሚመለከት የተካሄዱ የድርድር ሂደቶች በመልቲላተራል የአካባቢ ስምምነቶች ታሪክ ውስጥ እጅግ ፈታኝ የሆኑ ሂደቶች ታልፎባቸዋል፡፡አብዛኛዎቹ ታዳጊ ሀገራት ከባድ ግዴታዎችን ለመቀበል ፈቃደኛ ለመሆን ያልቻሉ ሲሆን እንደ ምክንያት የሚያቀርቡትም ያደጉት ሀገራት ኢኮኖሚያቸውን ለማሳደግ በሚያደርጉት ሂደት ለአለም ሙቀት መጨመር ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳሉ በሚል ነው፡፡በአለም ሙቀት መጨመር ምክንያት ለአደጋ በሰፊው የተጋለጡ እንደ ትናንሽ የደሴት ሀገራት የመሳሰሉት ጠንካራ እና ውጤታማ የሆኑ ግዴታዎች እንዲወሰኑ የሚፈልጉ ሲሆን

በተቃራኒው ያደጉ ሀገራት የአየር ንብረትን አስመልክተው የሚወሰኑ ግዴታዎች በኢኮኖሚያቸው ላይ የሚያስከትለው ተፅእኖ በእጅጉ ያሳስባቸዋል፡፡ምንም እንኳን በሀገራት መካከል እነዚህ ልዩነቶች ቢኖሩም በአለም አቀፉ ህብረተሰብ ዘንድ የችግሩ አሳሳቢነት ላይ ያለው ግንዛቤ መጨመር የፖለቲካ መሪዎች ችግሩን በአለም አቀፍ ደረጃ የሚፈታበትን መንገድ ግፊት እንዲፈጠር አድርጓል፡፡

እ.ኤ.አ በ1992 ዓ.ም በቂ የሆነ የሳይንስ እና የፖለቲካ ስምምነት ላይ መደረሱ በአለም ላይ የሚገኙ 154 ሀገራት የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ መዋቅራዊ ስምምነት እንዲፈረሙ አስችሏል፡፡ይህ ስምምነት በዋናነት የጋራ ግን የየቅል ሀላፊነት በሚለው መርህ ላይ የተመሰረተ ሲሆን በዚህ ፅንሰ ሀሳብ መሰረት በሀገራት ላይ ግዴታ የሚጣለው እንደየ ሀገራቱ የኢኮኖሚ ሁኔታ ሲሆን ያደጉ ሀገራት እና በኢኮኖሚ በሽግግር ላይ የሚገኙ ሀገራት የልቀት መጠንን ለመቀነስ የሚያስችል ቋሚ የሆነ ግዴታ አለባቸው፡፡እነዚህ ሀገሮች በተባበሩት መንግስታት መዋቅራዊ ስምምነት Annex 1 ላይ ተዘርዝረው የሚገኙ ሲሆን በተቃራኒው በማደግ ላይ የሚገኙ ሀገራት የልቀት መጠንን ለመቀነስ በፈቃደኝነት ግዴታ ውስጥ መግባት ይችላሉ፡፡ነገር ግን ሁሉም ለመዋቅራዊ ስምምነቱ አባል የሆኑ ሀገራት ለአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሆኑ ጉዳዮችን እና ተፅእኖዎችን ለመቀነስ የሚያስችሉ ብሔራዊ ፕሮግራሞችን እንዲያዘጋጁ ይጠበቅባቸዋል፡፡

2.1) የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ መዋቅራዊ ኮንቬንሽን

የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ መዋቅራዊ ኮንቬንሽንዋና አላማ በስምምነቱ አንቀጽ ሁለት ላይ እንደተገለፀው የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን አሉታዊ ተጽእኖ ማስቀረት ሲሆን በዋናነት በከባቢ አየር ውስጥ የሚገኘውን የግሪን ሀውስ ጋዝ ክምችት በማመጣጠን ስነ መሀድሮች ከአየር ንበረት ለውጥ ጋር በመጣጣም የእርሻ ምርት እንዲሁም የኢኮኖሚያዊ ልማቶች በዘላቂነት የሚቀጥሉበትን ሁኔታ ማረጋገጥ ነው፡፡ይህንንም ለማሳካት አባል ሀገራት በተለያዩ አለም አቀፍ አካባቢያዊ ሀላፊነቶችን በሚያንጸባርቁ መርሆች የሚመሩ ሲሆን እነዚህም በሪዮ የአካባቢ እና ልማት ዲክላሬሽን እንዲሁም በአጀንዳ 21 ላይ ተብራርተው ይገኛሉ፡፡

በስምምነቱ መሰረት አባል ሀገራት አጠቃላይ ግዴታዎችን እንዲወጡ የሚደነግግ ሲሆን እነዚህም

- ብሄራዊ የግሪን ሀውስ ጋዝ ልቀት ቆጠራ የሚያካሂድ ተቋም ማቋቋም፣
- የሳይንስ እና የቴክኒክ ትብብሮችን ማሳደግ፣
- ዘላቂ የደኖች፣ውቅያኖሶች እና የስነ መሀድር አያያዝ፣

- የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዩችን ከማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ፖሊሲዎች ጋር አዋህዶ መስራት ናቸው፡፡

በመዋቅራዊ ስምምነቱ ውስጥ በ Annex 1 ላይ የተዘረዘሩት በኢንዱስትሪ የበለፀጉ ሀገራት ተጨማሪ ግዴታዎች ያሉባቸው ሲሆን በዚሁ መሰረት ሀገራቱ አጠቃላይ የበካይ ጋዝ ልቀት መጠናቸውን ወደ 1990 ለማድረስ ተስማምተው ነበር፡፡ ፡፡ይህንንም ለማሳካት የበለፀጉት ሀገራት የአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተፅእኖን ለመቋቋም የሚያስችሉ ማለትም የበካይ ጋዝ ልቀት መጠንን ለመቆጣጠር እንዲሁም ካርቦንን ስቦ ለማስቀረት የሚያስችሉ ብሄራዊ ፖሊሲዎችን እንዲያዘጋጁ ግዴታን አስቀምጧል፡፡እነዚህን ግዴታዎች በአግባቡ ለመወጣት አባል ሀገራት ያላቸውን ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ ማስገባት ያለባቸው ሲሆን በተጨማሪም ሀገራት ግዴታቸውን ከሌሎች ሀገራት ጋር በጋራ መተግበር ይችላሉ፡፡ሀገራት ግዴታቸውን በተገቢው ሁኔታ እየተወጡ እንዳሉ ለማረጋገጥ እንዲቻል አባል ሀገራት የወሰዱዋቸውን እርምጃዎች የሚያሳይ ሪፖርት ማቅረብ እንዳለባቸው በመዋቅራዊ ስምምነቱ አንቀፅ 12(1) ላይ ተደንግጓል፡፡

የአባል ሀገራት ስብሰባ (conference of the parties (COP) መዋቅራዊ ስምምነቱን በዋናነት የሚቆጣጠር ሲሆን ስብሰባውም በመደበኛነት ስምምነቱ በበቂ ሁኔታ መተግበሩን እና ውጤታማነቱን ይከታተላል፡፡የአባል ሀገራት ስብሰባ (COP) የሳይንስ እና የቴክኒክ ጉዳዮች ላይ ምክር ከሚሰጠው Subsidiary Body for Scientific and Technological advice (SBSTA) እና በፖሊሲዎች አተገባበር ላይ አስተያየት የሚሰጠው Suplimentary Body for Implimentation የማማከር አገልግሎት ያገኛል፡፡የመዋቅራዊ ስምምነቱ ሴክሬታሪያት አባል ሀገራት ለሚያደርጉት ድርድር ተቋማዊ እና የኤክስፐርት ድጋፍ ያደርጋል፡፡

2.2 የኪዮቶ ፕሮቶኮል

የመጀመሪያው የተባበሩት መንግስታት መዋቅራዊ ስምምነት አባል የሆኑ ሀገራት ስብሰባ (COP-1) የተካሄደው እ.አ.አ በ1995 ዓ.ም በበርሊን ከተማ ነበር፡፡በወቅቱ ሁለተኛው የአለም አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ፓነል የግምገማ ሪፖርት የቀረበ ሲሆን ይህንንም መሰረት በማድረግ አባል ሀገራቱ በመዋቅራዊ ስምምነቱ ውስጥ የተቀመጠውን ግብ ለመምታት የተቀመጡት ግዴታዎች በቂ አለመሆናቸውን ከስምምነት ላይ ሊደርሱ ችለዋል፡፡የዚህ ስብሰባ ውጤትም በመዋቅራዊ ስምምነቱ ውስጥ የተቀመጡትን ግዴታዎች ሊያጠናክር የቻለውን ለመዋቅራዊ ስምምነቱ የመጀመሪያ የሆነው የኪዮቶ ፕሮቶኮል እ.ኤ.አ

ታህሳስ 11 ቀን 1997 ዓ.ም በ የጃፓን ሀገር ኪዮቶ ከተማ በተካሄደው ሶስተኛው የአባል ሀገራት ስብሰባ (COP 3) ሊደነገግ ችሏል፡፡

የኪዮቶ ፕሮቶኮል በአለም አቀፍ ደረጃ የግሪን ሀውስ ልቀትን ለመቀነስ ህጋዊ ግዴታን የሚጥል አለም አቀፍ ፕሮቶኮሉ ሲሆን በስራ ላይ የዋለው እ.ኤ.አ የካቲት 16 ቀን 2005 ዓ.ም ነው፡፡ፕሮቶኮሉን ለመተግበር የሚያስችሉ ዝርዝር መመሪያዎች የወጣው በሰባተኛው በማራካሽ ከተማ በተካሄደው የአባል ሀገራት ስብሰባ (COP 7) እ.ኤ.አ በ2001 ዓ.ም ሲሆን ይህም የማራካሽ ስምምነት በመባል ይታወቃል፡፡

ይህ ፕሮቶኮል ከተባበሩት መንግስታት መዋቅራዊ ስምምነት ጋር ተያይዞ የተደነገገ ስምምነት ሲሆን ዋና አላማውም 37 ለሚሆኑ በኢንዱስትሪ ለበለፀጉ እና የአውሮፓ ህብረት ሀገሮች ላይ አስገዳጅ የሆነ የልቀት መጠን ቅነሳ ግቦችን የያየዘ ሲሆን ይህም ሊለካ የሚችል እና በግዜ የተወሰነ የልቀት ቅነሳ ግቦችን የያዘ ነው፡፡ግዴታው በፕሮቶኮሉ Annex A ላይ የተዘረዘሩትን ስድስቱን የበካይ ጋዞች ማለትም ካርበንዳይኦክሳይድ፣ሚቴን፣ናይትረስኦክሳይድ ሀይድሮፍሉሮካርበን፣ፐርፍሉሮካርበን፣እና ሰልፈርሄክሳፍሉራይድ የሚሸፍን ሲሆን በመዋቅራዊ ስምምነቱ Annex B ላይ የተዘረዘሩት ሀገራት የእያንዳቸውን የተሰላ የልቀት ቅነሳ ግብን ዘርዝሮ ይዞ ይገኛል፡፡ በመሆኑም በ Annex B ላይ የተዘረዘሩት ሀገራት የሙቀት አምጪ ጋዞች የልቀት መጠናቸውን በ 1990 ዓ.ም ከነበረው ቢያንስ በአምስት በመቶ ለመቀነስ ተስማምተዋል፡፡ በመዋቅራዊ ስምምነቱ እና በፕሮቶኮሉ መካከል ያለው ዋና ልዩነት መዋቅራዊ ስምምነቱ በኢንዱስትሪ የበለፀጉ ሀገራት የግሪን ሀውስ ጋዝ ክምችት መጠንን እንዲቀንሱ የሚያበረታታ ሲሆን በተቃራኒው የኪዮቶ ፕሮቶኮል በአንዣሩ በሀገራቱ ላይ ግዴታን የሚጥል ነው፡፡ፕሮቶኮሉ ያደጉ ሀገራት ላለፉት 150 አመታት ባካሄዱት የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴ ምክንያት በአሁኑ ወቅት በከባቢ አየር ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ ተከማችቶ ለሚገኘው የበካይ ጋዝ ክምችት በዋናነት ተጠያቂ መሆናቸውን እውቅና የሰጠ ሲሆን በዚህም ምክንያት ፕሮቶኮሉ በኢንዱስትሪ በበለፀጉ ሀገሮች ላይ በጋራ ግን የየቅል ሀላፊነት በሚለው የአካባቢ መርህ መሰረት ከባድ ሀላፊነትን ጥሎባቸዋል፡፡

ፕሮቶኮሉን በአጠቃላይ በአለማችን ላይ የሚገኙ 141 ሀገራት ያፀደቁት ሲሆን በአለማችን ላይ ትልቁን የበካይ ጋዝ ልቀት መጠን የምታመነጨው አሜሪካ ግን ስምምነቱን አላፀደቀችውም፡፡ የአሜሪካን የህግ መወሰኛ ምክር ቤት እ.ኤ.አ ሰኔ 25 ቀን 1997 ዓ.ም ባሰለፈው ውሳኔ በኢንዱስትሪ በበለፀጉም ሆነ ታዳጊ በሆኑ ሀገራት ላይ አስገዳጅ የልቀት መጠን ቅነሳን ያላስቀመጠ እና በአሜሪካ ኢኮኖሚ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ማንኛውንም ፕሮቶኮል ላለመፈረም ውሳኔ አሳልፏል፡፡

በኪዮቶ ፕሮቶኮል Annex 1 ላይ የተዘረዘሩት ሀገራት የተቀመጠላቸውን ግብ የሚያሳኩት በዋናነት ብሔራዊ እርምጃዎችን በመውሰድ ነው።ነገር ግን ፕሮቶኮሉ ሀገራት ግዴታቸውን ለመወጣት የሚያስችላቸውን ስልቶች ያስቀመጠ ሲሆን እነዚህም

- የካርበን ንግድ፣
- የንፁህ ልማት ዘይቤ ስልት እና
- የጋራ ትግበራ ስልት ናቸው

የካርበን ንግድ (Emission trading)

በኪዮቶ ፕሮቶኮል በ Annex B ላይ የተዘረዘሩት በኢንዱስትሪ የበለፀጉ ሀገራት የተሰላ የልቀት መጠን የተቀመጠላቸው እንደሆነ ከላይ ለመጥቀስ ተሞክሯል። በኪዮቶ ፕሮቶኮል አንቀፅ 17 መሰረት የተቀመጠላቸውን የልቀት መጠን ሙሉ በሙሉ ያልተጠቀሙ ሀገራት ትርፉን የልቀት መጠናቸውን በተቃራኒው ከተቀመጠላቸው የልቀት መጠን በላይ ለተጠቀሙ ሀገራት መሸጥ ይችላሉ።

የንጹህ ልማት ዘይቤ

የንጹህ ልማት ዘይቤ" ማለት በኪዮቶ ፕሮቶኮል አንቀፅ 12 ላይ በተገለፀው መሰረት በሰው ልጆች እንቅስቃሴ ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን የሙቀት አምጪ ጋዞች ልቀት የሚቀንስ ገበያ መር የሆነ ዘዴ ነው።ይህ ዘዴ በታዳጊ ሀገሮች የሚካሄደውን ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ የሚያግዙ የልቀት ቅነሳ ፕሮጀክቶችን የሚያበረታታ ሲሆን በስልቱ በመጠቀምም በ Annex 1 ላይ የተዘረዘሩት በኢንዱስትሪ የበለፀጉ እና በሽግግር ላይ የሚገኙ ሀገራት አግባብነት ያላቸው ፕሮጀክቶችን በማደግ ላይ በሚገኙ ሀገራት ላይ ገንዘባቸውን ኢንቨስት በማድረግ የተረጋገጠ የልቀት ቅነሳ (Certtified emission reduction) ማመንጨት ይችላሉ።የተረጋገጠ የልቀት ቅነሳ ማለት ለንጹህ ልማት ዘይቤ አስፈላጊ ለሆነ የካርበን ሀብት የተሠጠ ስያሜ ሲሆን የካርበን ሀብት ማለት ለተወሰነ ጊዜ ከተመዘገበ የፕሮጀክት እንቅስቃሴ የሚመነጭ እና ሊቆጣጣጠሩት የሚችል ሀብት ነው።

የጋራ ትግበራ (Joint Implimentation)

የጋራ ትግበራ በኪዮቶ ፕሮቶኮል የሙቀት አምጪ ጋዞችን ለመቀነስ ከተቀመጡት ስልቶች አንዱ ሲሆን በመዋቅራዉ ስምምነቱ በ Annex 1 ላይ የተዘረዘሩ ሀገራት በፕሮቶኩሉ መሰረት የልቀት መጠንን ለመቀነስ የተጣለባቸውን ግዴታ እንዲወጡ የሚያስችል ስልት ነው። በኪዮቶ ፕሮቶኮል አንቀፅ 6 ላይ

እንደተገለፀው አንድ በ Annex 1 ላይ የሚገኝ አባል ሀገር በሌላ በ Annex 1 ላይ ለሚገኝ ሀገር የግሪን ሀውስ ልቀት መጠንን ለመቀነስ የሚያስችሉ ፕሮጀክቶችን የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ በኪዮቶ ፕሮቶኮል የተቀመጠውን የልቀት መጠን ቅነሳ ግብን ለማሳካት የሚያስችለውን emission reduction unit (ERU) ለማመንጨት ይችላል።የአንድ emission reduction unit ከአንድ ቶን ካርበን ጋር እኩል ዋጋ ይኖረዋል። አብዛኛዎቹ የጋራ ትግበራ ፕሮጀክቶች የሚካሄዱት በኢኮኖሚ ሽግግር ላይ በሚገኙ ሀገራት ሲሆን በዋናነትም ራሺያ እና ዩክሬን በርካታ የጋራ ትግበራ ፕሮጀክቶችን ያስተናግዳሉ ተብሎ ይጠበቃል ። በጋራ ትግበራ ፕሮጀክቶች ውስጥ ተሳታፊ ለመሆን አንድ ሀገር

- በኪዮቶ ፕሮቶኮል Annex 1 ላይ የሚገኝ እና ለኪዮቶ ፕሮቶኮል አባል መሆን ይኖርበታል
- የተሰላ እና የተመዘገበ የልቀት መጠን ያለው
- ብሄራዊ የልቀት ምዝገባ ያለው
- የሙቀት አምጪ ጋዞች የልቀት መጠንን መገመት የሚያስችል ዘዴ
- አመታዊ የሙቀት አምጪ ጋዞች ምዝገባ ሪፖርት ማድረግ ይኖርበታል።

3. የአየር ንብረት ለውጥ ተፅእኖና የኢትዮጵያ ምላሽ

በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት በአለማችን ላይ አዳዲስ ክስተቶች እየተፈጠሩ ነው።የባህር ከፍታ ጨምሯል፣በዋልታዎች አካባቢ የነበረው የበረዶ ግግር እየቀለጠ ነው።እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ደረቃማ አካባበቢዎች ደግሞ የዝናብ መጠን ቀንሶ ተደጋጋሚና አደገኛ ድርቅ በመከሰት ላይ ይገኛል።በአንዳንድ አካባቢዎች የጎርፍ መጥለቅለቅ አደጋዎች ባልተጠበቀ ሁኔታ እየተከሰቱናቸው።ድርቅ፣ጎርፍ፣ከባድ ዝናብ፣ኃይለኛ ነፋስ፣ከፍተኛ ሙቀት፣መብረቅ ወዘተ በሰው ህይወትና በተፈጥሮ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱና ለውጡ ያስከተላቸው ክስተቶች ሲሆኑ ከነዚህ ሁሉ የከፉት ድርቅና ጎርፍ ናቸው።ክሰተቶቹ በሰው እና በእንስሳት ሕይወት፣በግብርና ስራ፣ በኢንዱስትሪና በመሰረተ ልማት ግንባታ ላይ ተፅእኖ የደርጋሉ።ስለዚህም በብዙ አካባቢዎች የጤና ችግሮች፣ለምሳሌ የወባ መስፋፋት፣የምርት መቀነስ፣የከብት ሀብት መጥፋት፣የደን መመናመን፣እንዲሁም የዱር እንስሳት ሞት በተጨባጭ የሚታዩ ችግሮች ሆነዋል።የውሀ እጥረትና ጥራት ጉድለትም ብዙዎችን እያሳሰበ ያለ ጉዳይ ነው።

ኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ የምታደርገው አሉታዊ አስተዋፅኦ ይህ ነው የሚባል አይደለም።ይሁን እንጂ በተፅእኖው በከፍተና ደረጃ ተጎጂ ከሆኑት ሀገሮች አንዷ ናት።በመጀመሪያው የአገሪቱ የአየር ንብረት ለውጥ ዘገባ (First National Communication to the UNFCC) ላይ እንደተገለፀው እ.ኤ.አ በ2007

የአገሪቱ ሙቀት ከ 0.5 እስከ 3.6 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ድረስ እንደሚጨምር ተተንብዮ ነበር፡፡ እንደትንበያው ዓመታዊ የሙቀት መጠን ሲጨምር፣ዓመታዊው የዝናብ መጠን ደግሞ እየቀነሰ መጥቷል፡፡

በዚህም ምክንያት ፣ኢትዮጵያ በከፍተና ደረጃ በድርቅ ከሚመቱና ድረቅ በሚያስከትላቸው አደጋዎች ከሚጎዱ አገሮች አንዷ ናት፡፡አሁን እንኳን በተደጋጋሚ እየተከሰተ ባለው ድርቅና ረሀብ የእንስሳት ሞት፣የምርት መቀነስ እና የምግብ ዋስትና እጦት ኢትዮጵያን በከፍተና ደረጃ የሚፈታተኑ ችግሮች ናቸው፡፡የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የተመሰረትበትና በዝናብ ላይ የተደገፈ ግብርና ለአየር ንብረት ለውጥና ተለዋዋጭነት በከፍተኛ ደረጃ የተጋለጠ ነው፡፡ለውጡ በአገር ደረጃ ብቻ ሳይሆን በግለሰብና በቤተሰብ ደረጃም ጉዳትን ያስከትላል፡፡የመተዳደሪያ ጥሪቶች (livelihood assets) በሆኑት ሀብቶች ማለትም በመሬት፣በውሀ፣በመሰረተ ልማቶች በገቢ ማግኛ ምንጮች ላይ የሚደርሰው ጉዳት ግለሰቦችንና ቤተሰቦችን ላልተጠበቁ ችግሮች ይዳርጋል፡፡በተለይ በዝናብ ላይ የተመሰረተና ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ግብርናን የሚያካሂዱ አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች በችግሩ ይበልጥ ተጎጂ ናቸው፡፡

የመጀመሪው የአገሪቱ አየር ንበረት ለውጥ ዘገባ (First National Communication to UNFCC, 2001) ከአየር ንብረት ለውጥና ተለዋዋጭነት ጋር የተያያዙ ችግሮች በኢትዮጵያ በግልፅ መታየታቸውን ጠቁሟል፡፡ለምሳሌ

- ባለፉት ሀምሳ አመታት የአገሪቱ አማካይ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በየአስር ዓመቱ በ0.2 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ያህል ጨምሯል
- ተደጋጋሚና የአገሪቱን በርካታ ክፍል የሚሸፍን ድርቅ በቅርብ አስርት አመታት ውስጥ ተከስቷል፡፡ይህም ብዙዎችን ለምግብ እጦትና ለረሀብ አጋልጧል፡፡የቤትና የዱር እንስሳትን ሞትና ስደት አስከትሏል፡፡
- የወባ በሽታ ቀድሞ ወዳልነበረባቸው ከፍተኛ የአገሪቱ አካባቢዎች ተስፋፍቷል፡፡
- ብዝሀ ሕይወት በመመናመን ላይ ይገኛል፡፡

ኢትዮጵያ አንድም እያስመዘገበች ያለችው የኢኮኖሚ ልማት እንዳይደናቀፍባት ሁለትም የአየር ንብረት ለውጡ ያልተጠበቁና አውዳሚ የሆኑ አደጋዎችን እንዳያደርስባት ተገቢ ምላሽ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡በተለይ ኢትዮጵያ ሊያጋጥማት የሚችለው ደረቅ የአየር ጠባይና ተለዋዋጭ የሆነው የዝናብ ሁኔታ የምግብ ዋስትና ችግሮችን እንዳያባብስባትና በግብርና ላይ የተመሰረተውን ኢኮኖሚዋን እንዳይጎዳው መፍትሄ መፈለግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያ በሁለት መልኩ ምላሽ

በመስጠት ላይ ትገኛለች፡፡በመጀመሪያ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚካሄዱት የአየር ንብረት ለውጥ ድርድሮች ላይ በንቃት ትሳተፋለች፡፡የአየር ንብረት ለውጥ ችግሮችን የፈጠሩት የበለጸጉት አገሮች መፍትሄ በመፈለጉም ረገድ ኃላፊነቱን መውሰድ አለባቸው በማለት በዓለም አቀፍ መድረኮች ድምጻን ታሰማለች፡፡ለዚህም በዴንማርክ ዋና ከተማ በኮፐን ሀገን በተካሄደው ድርድር ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የአፍሪካን ችግሮች በመወከል የተጫወቱት ሚና ለአብነት የሚጠቀስ ነው፡፡እንዲሁም ዲሴምበር 2010 እ.ኤ.አ በካንኩን ሜክሲኮ ለተካሄደው ጉባኤ ሪፖርት ያዘጋጀውንና በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተመሰረተውን 21 አባላት የሚገኙበትን ሀይል ሌቭል አድቫይዘሪ ግሩፕ ኦን ክልይሜት ቼንጅ ፋይናንሲንግ (High-Level Advsiory Group on Climate Change Financing) ከኖርዌይ ከጠቅላይ ሚኒስትር ጋር በጋራ በመምራት ወሳኝ ተግባሮችን ማከናወናቸው አይዘነጋም፡፡

ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ ችግሮችን ለመቀነስ የተደረጉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ፈርማለች፡፡በዚህም መሰረት የሙቀት ሳቢ ጋዞችን ክምችት የመቀነስ ዓላማ ያለው የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ የማዕቀፍ ስምምነትንና እና የስምምነቱን ቀጣይ አካል የሆነውን የኪዮቶ ፕሮቶኮል ፈራሚ ናት፡፡ስምምነቶቹ በአገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ የሚሆኑበትን ህግም አውጥታለች፡፡ይህም አገሪቱ የአየር ንብረት ለውጥ ተጽእኖዎችን ለመቋቋም ያላትን ዝግጁነት የሚያመላክት ሲሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚካሄደው ጥረት የበኩላን አስተዋጽኦ ለማበርከትም ያስችላታል፡፡በዚህም መሰረት የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳይ በኢትዮጵያ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ውስጥ የተካተተ ሲሆን አገሪቱ በሚቀጥሉት አምስት የእቅድ አመታት ትኩረት የምትሰጠው ይሆናል፡፡

3.1. ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በቀጥታ ተያያዥነት ያላቸው ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች እና መርሀ ግብሮች

3.1.1. የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲውና የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዮች

ከአየር ንብረት ለውጥ አንፃር ሲቃኝ የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲው በዝርዝር ካቀፋቸው አስር ንኡሳን ዘርፎች ውስጥ የአየር ንብረት ለውጥና የአካባቢ የአየር ብክለት ጉዳይ በቀጥታ ተካትተዋል፡፡ፖሊሲው የኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነትን በማውሳት ተፅእኖዎችን ለመቀነስና የአየር ንብረት ለውጥ ተፅእኖዎችን ለመቋቋም የአየር ንብረት ክትትል መርሀ ግብርን የማስፋፋት ፣የአዞን ሽፋንን የመከላለከልና የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና እንክብካቤ (ደን ተከላ፣ጥምር ግብርና፣ልቅ ግጦሽ ቁጥጥር፣የተጎዱ መሬቶችን የማከም) ስራዎችን ለመስራት የሥነ-ምህዳርን ይዞታ ማጠናከር እንደሚገባ

ያስረዳል፡፡በተጨሪም እነዚህን ስራዎች ለማስፈጸም የሚያስችል የገንዘብ ድጋፍ ከበለፀጉ ሀገሮች ማፈላለግ እንደሚያስፈልግ በግልፅ አስፍሯል፡፡

3.1.2. ብሄራዊ የማጣጣሚያ የድርጊት መርሐ-ግብር (Nationally Appropriate Programme of Action)

ኢትዮጵያ የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ማእቀፍ ስምምነት ፈራሚና አባል ሀገር ናት፡፡በመሆኑም በአየር ንብረት ለውጥ አደጋዎች ተጠቂ ከሆኑ ገና በመልማት ላይ ካሉ ሀገራት ውስጥ ስለምትመደብ የስምምነት ማእቀፉ በሚያዘው መሰረት የአየር ንብረት ለውጥ የማጣጣሚያ የድርጊት መርሀ ግብር በማዘጋጀት የገንዘብ እና ተስማሚ ቴክኖሎጂ ድጋፍ የመጠየቅና የማግኘት መብት አላት፡፡በዚሁ መሰረት የኢትዮጵያ ብሄራዊ የማጣጣሚያ መርሐ-ግብር እ.ኤ.አ በ2007 ዓ.ም ተዘጋጅቶ ለተባበሩት መንግስታት ማእቀፋዊ ስምምነት ሴክሬታሪያት ቀርቧል፡፡

3.1.3. ብሄራዊ የአየር ንብረት ለውጥ ስርየት ተግባሮች (Nationally Apprropriate Mitigation of Action)

የኮፐን ሀገን ስምምነት (Copenhagen Accord) በሚያዘው መሰረት ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚደረገው የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት እቀባ የበኩሏን አስተዋፅኦ ለማበርከት ብሄራዊ የስርየት የፕሮጀክት ተግባሮችን የያዘ ሰነድ እ.አ.አ በ 2010 ዓ.ም አዘጋጅታለች፡፡ይህ የፕሮጀክት ትግበራ ሰነድ የተለያዩ ዘርፎችንና ሰባ አምስት የሚሆኑ ተጨባጭ የፕሮጀክት ሀሳቦችን ይዟል፡፡ የፕረጀክት ሀሳቦቹ በተለይ በውሀና ሌሎች ታዳሽ የሀይል ምንጮች፣በትራንሰፖርት፣በደን ሀብት ልማት፣በእርሻና በከተማ የቆሻሻ አያያዝና አጠቃቀም ዙሪያ ትኩረት ያደርጋሉ፡፡

3.1.4. የኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ መርሐ-ግብር (Ethiopian Programme of Adaptation to Climate Change)

በፌደራል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ተዘጋጅቶ የቀረበው የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ መርሀ ግብር ኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭ መሆኗን በግልፅ በማስቀመጥ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ መርሐ- ግብርን ማዘጋጀት እና መተግበር የሀገሪቱ የህልውና ግዴታ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡የዚህ መርሐ- ግብር ዋና አላማ በሀገሪቱ በሙሉ የተለያዩ የማጣጣሚያ መርሐ -ግብሮችን በየዘርፉ በተቀናጀ፣ አዋጭ፣ ዘላቂ እና ሁሉን የህብረተሰብ ክፍል አሳታፊ በሆነ መልኩ በመተግበር

ሀገሪቱ በ2018 ዓ.ም አየርን ከካርበን ሱስ ከመበከል ሙሉ ለሙሉ ነጻ ትሆናለች የሚለውን ራዕይ እውን ማድረግ ነው፡፡

መርሐ-ግብሩ የአየር ንብረት ለውጥ የሚያመጣቸው ወይም የሚያባብሳቸው ችግሮች ብዙ መሆናውን በመግለፅ 20 የሚሆኑ ዋና ዋና የመፍትሄ ተግባሪ መስሪያ ቤቶችንና አካላትን ዘርዝሮ አስቀምጧል፡፡ከተዘረዘሩት ዋና ዋና ችግሮች ውስጥ የሰው ጤና፣የሰብል በሽታዎች እና ተባዮች፣የብዝሀ-ሕይወት መመናመን፣የመሬት መጎሳቆል፣የግብርና ምርት ማሽቆልቆል፣የውሀ አቅርቦት ስጋት፣የከተማ ቆሻሻና በመሰረት-ልማት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ አደጋዎችን በመዘርዘር ጉዳዩ የሚመለከታቸው መስሪያ ቤቶች የጉዳዩ ባለቤት ሆነው የማጣጣም ሂደቱን የሚመሩትንና ችግሮቹን የሚፈቱትን አካላት ከችግሮቹ ጋር በማያያዝ አስፍሯል፡፡

3.1.5. የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዱና የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዮች

የኢትዮጵያ መንግስት በቀጣዮቹ አምስት አመታት (2003- 2007 ዓ.ም.) የልማት እቅድን በቅርቡ ይፋ አድረጎ ስራ ላይ ማዋል ጀምሯል፡፡ የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅዱ ዋና አላማ ባለፉት አመታት ተፈፃሚ የሆኑ የልማት እቅዶች ያስገኟቸውን ውጤቶች አጠናክሮ በመቀጠል ድህነትን በሂደት ማስወገድ ነው፡፡ከዚህ አንፃር በአካባቢ እንክብካቤ መስክ በ5 አመት ውስጥ ታቅደው እንዲተገበሩ ትኩረት የተሰጣቸው ጉዳዮች ተዕእኖ የማያስከትል የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታና በስራ ላይ ያሉ የአካባቢ ህጎች ትግበራ ናቸው፡፡ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኤኮኖሚ ግንባታ ሁለት ዘርፎችን ያካትታል፡፡እነርሱም ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር መጣጣምና (Adaptation to Climate Change) የከባቢ አየር በካይ ወይም ሙቀት ሳቢ ጋዞች ልቀት ስርየት (Mitigation of Greenhouse gases) ናቸው፡፡በተጨማሪም በዕቅድ ዘመኑ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያና ለስርየት ማስፈፀሚያ የሚረዱ ርምጃዎችን ከዝቅተኛው የአስተዳደር እርከን አንስቶ በሁሉም ደረጃዎች ከልማት እንቅስቃሴዎች ጋር በማዋሀድ ለማቀድና ለመተግበር የሚያስችል ሀገራዊ አቅም እንደሚጠናከር ተገልጿል፡፡

በእቅድ ዘመኑ የአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነትን ለመቀነስ የሚያስችሉ ፖሊሲዎችን፣ህጎችንና ስልቶችን በመለየት ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር እንዲጣጣሙ ማድረግ፤ለአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭ የሆኑ ግድቦችን፣የውሀ አካላትን፣መንገዶችን፣የመገናኛ አውታሮችን፣የመስኖ ካናሎችን፣የሀይል ማሰራጫ መሰረተ ልማቶችን በመለየት ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የማጣጣም እርምጃ እንደሚወሰድ አስቀምጧል፡፡በተጨማሪም የተራቆቱ መሬቶችን በደን መሸፈን፣ምርታማ ደን ማልማት ፣የብሄራዊ ፓርኮችና የውሀ አዘል መሬቶችን ልማት ማካሄድ፣የእርሻ መሬትን በቀልዝ (compost) በማዳበርና

የጥምር ደን ሥራን ማስፋፋት፣የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አጠቃቀምን ማሻሻል፣የከባቢ አየር በካይ ጋዝ ልቀት ስርየት ማካሄድ የሚሉ ግቦችንም ይዟል።ለዚሁ ጉዳይ ከተዘረዘሩ የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎች መካከል የድርጊት መርሀ ግብር ዝግጅት፣የትምህርትና የአቅም ግንባታ ስራ፣የተስማሚ ቴክኖሎጂ ዳሰሳ ጥንቅርና ስርጭት፣መልካም ተሞክሮዎችን ለህዝብ ማሳወቅ፣የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ደረጃ ማውጣት፣የአካባቢ ድንጋጌን የሚጥሱ አካላትን ወደ ህግ አክባሪነት የመለወጫ እርምጃ መውሰድ ከሚተኮርባቸው የማስፈፀሚያ ስልቶች የሚጠቀሱ ናቸው።

ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የኢኮኖሚ ልማት አገሮች የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም የተከተሉት አዲስ የእድገት አቅጣጫ ነው።ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚ ግንባታ ከካርበን ልቀት ነጻ የሆነና ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የሚጣጣም የኢኮኖሚ ግንባታ ሲሆን ከተለመደው የልማት አካሄድ በመውጣትና ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተያያዙ ስጋቶችን ትርጉም ባለው ሁኔታ በመቀነስ አካባቢያዊ ተቀባይነት ያላቸውን ስራዎች መስራትን የሚጠይቅ ነው።ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የኢኮኖሚ ልማት የአየር ንብረት ለውጥን ለማስተሰረይ (mitigation) የሚያስችሉ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተጣጥመው መሄድ የሚችሉ የመተዳደሪያ ስራዎችን የሚፈጥርና ያሉትንም ጠብቆ የሚያቆይ የኢኮኖሚ ልማት አቅጣጫ ነው።

በአለም አቀፍ ደረጃ ሲታይ በከባቢ አየር ውስጥ ያለውን የሙቀት ጋዝ ቋጣሪ ጋዞች ክምችት የሚያረጋጋ ወይም የሚቀንስ የልማት መንገድ ነው።በመልማት ላይ ካሉት አገሮች አንጻር ሲታይ አዳዲስ ኢንቨስትመንቶች የደን መመናመንን የማያስከትሉና ኢንዱስትዎች የተፈጥሮ ነዳጅ በመጠቀም በካይ ጋዞችን ወደ አካባቢ በተለይም ወደ አየር የማይለቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ ማለት ነው።ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የኢኮኖሚ ልማት በከፍተኛ ደረጃ በማጣጣሚያ ስራዎች (adaptation) ላይ ትኩረት እንዲያደርግ ይጠበቃል።

በኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ መርሀ ግብር ላይ እንደተጠቀሰው ኢትዮጵያ በአዲሱ የኢኮኖሚ ልማት እሳቤ መሰረት በታዳሽ ኃይል ምንጮች ላይ የተመሰረተ የኢኮኖሚ እድገቷን በማፈጠንና የእጽዋት ሽፋኗን በማሳደግ እንደ አውሮፓውያን ዘመን አቆጣጠር በ 2025 ራሷን ሙሉ በሙሉ ከተጨማሪ የካርቦንዳይኦክሳይድ ለቃቂነት (net emission) ነጻ ለማድረግ እቅድ አውጥታ በመተግበር ላይ ትገኛለች።

4. የከባቢ አየር ሽፋን መሳሳት አለም አቀፍ ስምምነት እና ሀገራዊ ህጎች

መሬትን ሽፍኖ የሚገኘው ከባቢ አየር ሶስት ሽፋኖች ያሉት ሲሆን እነዚህም ትሮፖስፌር (ከመሬት የላይኛው ሽፋን አስር ኪሎሜትር በላይ ይገኛል)፣ስትራቶስፌር (ከመሬት የላይኛው ሽፋን በግምት ከአስር እና አስራ አምስት ኪሎሜትር ርቀት ላይ ይገኛል) እና አዮኖስፌር (ከመሬት የላይኛው ሽፋን ሶስት መቶ ሀምሳ ኪሎሜትር ርቀት ላይ ይገኛል) በመባል ይታወቃሉ፡፡

አዞን የተባለው የኬሚካል ውህድ (O_3) ከሶስት የኦክስጅን ሞለኪዩሎች የተሰራ ሲሆን በዋናነትም የሚገኘው በሁለቱ የከባቢ አየር ሽፋኖች ውስጥ ነው፡፡ዘጠና በመቶ የሚሆነው የኦዞን ክምችት የሚገኘው በስትራቶስፌር ውስጥ ሲሆን ይህም የኦዞን ሽፋን በመባል ይታወቃል፡፡የተቀረው የኦዞን ክምችት በትሮፖስፌር ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ይህም Surface level ozone በመባል ይታወቃል፡፡በሁለቱ የከባቢ አየር ውስጥ የሚገኘው የኦዞን ኬሚካል ውህድ ተመሳሳይ ሲሆን ምንጫቸው እንዲሁም በሰዎች እና በሌሎች ህይወት ባላቸው ፍጥረታት ላይ ያላቸው ተጽእኖ የተለያየ ነው፡፡

Surface level ozone የሚፈጠረው ከመኪናዎች እና ከኢንዱስትሪዎች በሚወጣው ጭስ እና ከፀሀይ ብርሀን ጋር በሚደረግ ኬሚካላዊ ውህደት ነው፡፡የኦዞን ኬሚካል በባህሪው ከሌሎች ሞለኪዩሎች ጋር የመዋሀድ ተፈጥሮ ስላለው በከፍተኛ ደረጃ የሚገኝ የኦዞን መርዛማ በመሆኑ ህይወት ባላቸው ፍጥረታት ላይ በተለይም በሰብሎች ላይ፣በደኖች እድገት እና በሰዎች ጤና ላይ አሉታዊ ተፅእኖን ያስከትላል፡፡

በተቃራኒው በስትራቶስፈተር ውስጥ የሚገኘው የኦዞን ሽፋን በአጠቃላይ በምድር ላይ ህይወት ላላቸው ፍጥረታት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ሽፋኑ በዋናነት ከፀሀይ በቀጥታ የሚመጣውን ህይወት ባላቸው ፍጥረታት ላይ ጉዳት የሚያደርሰውን አልትራቫዮሌት ጨረር ስቦ በማስቀረት በመጠን አነስተኛ የሆነውን የፀሀይ ብርሀን ወደ መሬት እንዲደርስ ያደርጋል፡፡የኦዞን ሽፋን ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ ከፀሀይ የሚመጣውን አደገኛ ጨረር የሚከላከል ሲሆን በዚህም ምክንያት earths sunscreen በመባል ይታወቃል፡፡በመሬት ከባቢ አየር ውስጥ የሚገኘው የኦዞን ሽፋን መጠን በአካባቢ፣በሰዎች ጤና እና በኢኮኖሚ ላይ ቀጥተኛ የሆነ ተጽእኖ የሚያደርግ በመሆኑ በአለም አቀፍ የአካባቢ ህግ ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡

እ.ኤ.አ በ1970ዎቹ ገደማ ሳይንቲስቶች በስትራቶስፌር የሚገኘው የኦዞን ሽፋን መሳሳቱን ሊያስተውሉ ችለው ነበር፡፡በተለይም ችግሩ ጎልቶ ሊታይ የቻለው እ.ኤ.አ በ1985 ዓ.ም በላይኛው የአንታርክቲካ

ክፍል በመጠኑ ትልቅ የሆነ ቀዳዳ መታየቱ ሲሆን ይህ ቦታ እ.ኤ.አ በ1992 በተካሄደ ጥናት የኦዞን ሽፋኑ በፊት ከነበረበት ስልሳ በመቶ መሳሳቱ ጨምሮ የተገኘ ሲሆን የቀዳዳው ስፋትም ሀያ ሶስት ስኩዌር ማይል የሸፈነ ነበር፡፡በአጠቃላይ ሽፋኑ በየአስር አመቱ በሶስት በመቶ ይቀንስ እንደነበረ የሚገመት ሲሆን እ.ኤ.አ በ1990ዎቹ አጋማሽ የኦዞን ሽፋን መሳሳቱ በሰሜን አሜሪካ፣በአውሮፓ፣በኤሽያ፣በአብዛኛው የአፍሪካ አህጉር፣በ አውስትራሊያ፣እና በደቡብ አሜሪካ ተስተውሏል፡፡ከችግሩ ስፋትም አኳያ የኦዞን ሽፋን መሳሳት አለም አቀፍ ጉዳይ ሊሆን ችሏል፡፡

ይህ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው የኦዞን ንጣፍ ሙሉ በሙሉ ሰው ሠራሽ ከሆኑ ኬሚካሎች ጋር በሚያደርገው ኬሚካላዊ ውህደት በከፍተኛ ፍጥነት እየሳሳ በመሄድ ላይ ይገኛል፡፡ እነዚህ የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሱ ኬሚካሎች በማቀዝቀዣ መሳሪያዎች ውስጥ እንደ ማቀዝቀዣ ፈሳሽነት (Refrigant)፣ በተለያዩ ፋብሪካዎች ውስጥ እንደማጠቢያነት (Solvent)፣በእሳት ማጥፊያነትና በስፖንጅና በፕላስቲክ ፋብሪካዎች ውስጥ ለተለያዩ ጠቀሜታ የሚያገለግሉ ሲሆኑ በዋናነት የሚታወቀው ኬሚካልም ክሎሮፍሉሮካርበን ይባላል፡፡ ክሎሮፍሉሮካርበን ከፀሀይ በሚመጣው አልትራቫዮሌት ጨረር በሚጋለጥበት ወቅት የኬሚካል ውህዶቹ የሚበታተኑ ሲሆን በዚህም ወቅት የክሎሪን አተሞች ይለቀቃሉ::አንድ የክሎሪን አተም በ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ኬሚካሎችን የመበታተን አቅም አለው፡፡በስትራቶስፌር የሚገኘው የክሎሪን ሞለኪዩል በተፈጥሮ ክስተቶች ምክንያት ማለትም በእሳተ ገሞራ ፍንዳታ እንዲሁም በከፍተኛ የእሳት ሰደድ ሊፈጠሩ የሚችሉ ቢሆንም በእነዚህ ምክንያቶች የሚፈጠሩ ክሎሪኖች በስትራቶስፌር ውስጥ አስራ አምስት በመቶ ብቻ ሲሆኑ የኦዞን ሽፋንንም የማሳሳት አቅማቸው አነስተኛ ነው፡፡

ማንኛውም በኦዞን ሽፋን ላይ የሚደርስ ጉዳት ከፀሀይ ወደ መሬት የሚመጣውን አልትራቫዮሌት ጨረር መጠን የሚጨምር ሲሆን ይህም በሰዎች ጤና ላይ የተለያየ ችግር የሚያስከትል ሲሆን እነዚህም የቆዳ ካንሰርን፣የአይን በሽታ እና የሰውነትን ከበሽታ የመከላከል አቅም ያዳክማል፡፡የአንድ በመቶ የኦዞን ሽፋን መቀነስ የቆዳ ካንሰር በሽታን በአራት በመቶ የሚጨምር ሲሆን ከመቶ እስከ መቶ ሀምሳ ሺህ የአይነስውርነትን በሽታ ይጨምራል፡፡በተጨማሪም የአልትራቫዮሌት ጨረር በተክሎች አስተዳደግ ላይ፣ በደኖቸ ላይ፣በሰብሎች ላይ፣በአሳ ዝርያዎች እንዲሁም በባህር ውሰጥ በሚገኙ ተክሎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል፡፡

4.1. የቬና ኮንቬንሽን

እ.ኤ.አ በ1975 የአለም ሚትዮሮሎጂካል ኤጀንሲ የመጀመሪያውን አለም አቀፍ የኦዞን ሽፋን ግምገማ ያካሄደ ሲሆን በውጤቱም የኦዞን ሽፋን በአሳሳቢ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ እና አፋጣኝ እርምጃ እንደሚያስፈልገው ተገልፃል፡፡እ.ኤ.አ በ1981 ዓ.ም የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም የኦዞን ሽፋንን ለመጠበቅ የሚያስችል አለም አቀፍ መዋቅራዊ ስምምነት እንዲዘጋጅ አለም አቀፍ ድርድሮች እንዲዘጋጁ ሀሳብ አፍልቋል፡፡

የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሱ ኬሚካሎች ተፅእኖ የሚያሳድሩት በሁሉም ሀገራት ላይ መሆኑ በአለም አቀፍ ደረጃ ተፈጻሚ የሚሆን ህግ መዘጋጀት እንዳለበት ታምኖበታል፡፡ይህንንም ለማሳካት የተለያዩ ሀገራት ፍላጎቶቻቸውን እንዲያንሸራሽሩ የተደረገ ሲሆን በወቅቱ ታዳጊ ሀገሮች የተወሰኑ የኦዞን ሽፋንን የሚያሳሱ ኬሚካሎች ላይ የሚደረገው ገደብ የኢንዱስትሪ እድገታቸው ላይ ተፅእኖ ያሳድራል የሚል ስጋት አድሮባቸው ነበር፡፡ በሌላ በኩል ኢንዱስትሪዎቻቸው በዋናነት ኦዞንን በሚያሳሱ ኬሚካሎች ላይ ጥገኛ የሆኑት እንደ አውሮፓ ህብረት ያሉ ሀገራት የእነዚህን ኬሚካሎች አመራረት እና አጠቃቀም ለመቆጣጠር የሚያስፈልገውን ወጪ ለመቀበል ቸልተኝነትን አሳይተው ነበር፡፡በአንፃሩ ኦዞንን የሚያሳሱ ኬሚካሎችን ማምረት እና መጠቀም የቀነሱ ሀገራት ሌሎች ሀገራት በተመሳሳይ ኬሚካሎቹን እንዲጠቀሙ አይፈልጉም፡፡

በመጨረሻም የኦዞን ሽፋንን ለመጠበቅ የተደነገገው የቬና ኮንቬንሽን እ.ኤ.አ ሚያዝያ 22 ቀን 1985 ዓ.ም በሀገራት መካከል ስምምነት ላይ ከተደረሰ ቦሀላ ሊደነገግ ችሏል፡፡የኮንቬንሽኑ አጠቃላይ ዋና አላማ የሰዎችን ጤና እና አካባቢን የኦዞን መሳሳት ከሚያስከትለው ተፅእኖ መጠበቅ ሲሆን መዋቅራዊ ስምምነት እንደመሆኑ ኦዞንን የሚያሳሱ ኬሚካሎችን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ዝርዝር የመቆጣጠሪያ ዘዴዎችን ይዞ ባይገኝም አባል ሀገራት የኦዞን ሽፋንን ለመጠበቅ ያለባቸውን አጠቃላይ ግዴታ እና አለም አቀፍ ትብብር ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡በተጨማሪም አባል ሀገራት በሰው ሰራሽ ምክንያት የሚደርስ የኦዞን መሳሳትን ለመከላከል የሚያስችል ተገቢ እርምጃ እንዲወስዱ የሚጠይቅ ሲሆን እነዚህም ህጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃዎች፣ሳይንሳዊ ግምገማዎች እና የምርምር ትብብሮች፣የኢንፎርሜሽን ልውውጦች እና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲካሄድ ይደነግጋል፡፡

ኮንቬንሽኑ በመደበኛነት የሚሰበሰብ የአባል ሀገራት ስብሰባ እና ሴክሬታሪያት እንዲቋቋም አድርጓል፡፡ የአባል ሀገራቱ ስብሰባ የኮንቬንሽኑን አተገባበር እና አስፈላጊ የሆኑ መርሀ ግብሮች እና ፖሊሲዎችን ማዘጋጀት እንዲሁም ኮንቬንሽኑን ማሻሻል እንዲሁም አዳዲስ ፕሮቶኮሎች እና Annex

ያዘጋጃል፡፡ሴክሬታሪያቱ የአባል ሀገራቱን ስብሰባ ማዘጋጀት እንዲሁም በአባል ሀገራቱ የሚከናወኑ የአተገባበር እና የተወሰዱ እርምጃዎች ሪፖርቶችን የሚያስተላልፍ ሲሆን በተጨማሪም ሌሎች አግባብነት ካላቸው አለም አቀፍ ተቋሞች የሚደረግ ግንኙነትን ያስተባብራል፡፡

4.2. የሞንትሪያል ፕሮቶኮል

የቬና ኮንቬንሽን አባል ሀገራት ተጨባጭ የሆኑ እርምጃዎች እንዲወሰዱ በሚደነግገው መሰረት ሀገራት የኦዞን ሽፋንን የሚያሳሱ ኬሚካሎችን ከጥቅም ላይ እንዳይውሉ የሚያስችለውን ፕሮቶኮል እንዲደነገግ ሀገራት እ.ኤ.አ በ1987 ዓ.ም በሞንትሪያል ከተማ ስብሰባ አካሂደው ነበር፡፡ፕሮቶኩሉን በሚመለከት በተካሄደው ድርድር ሶስት ጉዳዮች በዋናነት ተነስተው የነበረ ሲሆን እነዚህም

1. የፕሮቶኩሉን ተከባሪነት በስፋት መረጋገጥ እንዳለበት እና ታዳጊ ሀገሮች ፕሮቶኩሉን ለመተግበር ያላቸውን የገንዘብ አቅም ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ መሆን እንዳለበት
2. ፕሮቶኮሉ በተለያዩ ግዜያት የሚገኙ ሳይንሳዊ ግኝቶችን እና የተለያዩ የአባል ሀገራትን ፍላጎት ለማካተት በሚያስችል መልኩ እንዲዘጋጅ
3. የኦዞንን ሽፋን የሚያሳሱ ኬሚካሎች ከጥቅም ላይ እንዳይውሉ የሚያስችል ኢኮኖሚያ ሁኔታዎችን ከግንዛቤ ወስጥ ያስገባ እና ዝርዘር የድርጊት መርሀ ግብር እንዲዘጋጅ የሚሉ ነበሩ፡፡

የሞንትሪያል ፕሮቶኮል በአለም አቀፉ የአካባቢ ህግ እድገት ላይ እንደትልቅ ስኬት የሚቆጠር ሲሆን የኦዞን ሽፋንን የሚያሳሱ ኬሚካሎች እንዲቀነሱ እና ቀስ በቀስ እንዲወገዱ በአንጻሩ ጠንከር ያሉ ግቦችን አስቀምጧል፡፡እነዚህ ኬሚካሎች በፕሮቶኮሉ ከ Annex A-E የተዘረዘሩ ሲሆን የሚወገዱበትም ግዜ በፕሮቶኮሉ አንቀጽ 2A-21 ተዘርዝሮ ይገኛል፡፡ፕሮቶኮሉ የታዳጊ ሀገሮችን ፍላጎት መሰረተ ያደረገ የተለዩ አንቀጾችን አካትተቶ የያዘ ሲሆን ይህም የሆነበት ዋና ምክንያት ታዳጊ ሀገሮች ለኦዞን ሽፋን መሳሳት ያበረከቱት አስተዋጽኦ እጅግ በጣም አነስተኛ መሆኑ ሲሆን በዚህም ምክንያት ታዳጊ ሀገሮች ኬሚካሎቹን ለመቀነስ ያለባቸው ግዴታ በአስር አመት እንዲዘገይላቸው ተደርጓል፡፡በተጨማሪም ታዳጊ ሀገራት በፍጥነት ከነዚህ ኬሚካሎች ተላቅቀው በሌሎች አማራጭ ኬሚካሎች መጠቀም እንዲችሉ የገንዘብ እና የቴክኖሎጂ ድጋፍ እንዲደረግላቸው ያበረታታል፡፡

ኢትዮጵያም የቪየና ኮንቬንሽን እና የሞንትሪያል ፕሮቶኮል እ.ኤ.አ ኦክቶበር 1994 የፊረመች ሲሆን በቅርቡም በሞንትሪያል ፕሮቶኮል ላይ የተደረጉ የተለያዩ ማሻሻያዎችን ተቀብላ በአዋጅ ቁጥር

656/2001 በማዕደቅ ለከባቢ አየር ጥበቃ የምትሰጠውን ከፍተኛ ትኩረት አሳይታለች።በሌላ በኩል እ.ኤ.አ በ1997 በተካሄደው ዘጠነኛው የሞንትሪያል ፕሮቶኮል አባል ሀገራት ስብሰባ ላይ የፀደቀውና ኢትዮጵያም ከላይ በተጠቀሰው አዋጅ ካፀደቀቻቸው ማሻሻያዎች አንዱ የሆነው የሞንትሪያል ፕሮቶኮል ማሻሻያ አባል ሀገራት በፕሮቶኮሉ ቁጥጥር የሚደረግባቸው ኬሚካሎች ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡና ሲወጡ ለመቆጣጠር ክትትል ለማድረግ የሚያስችል የፈቃድ ሥርዐት የመዘርጋትን ግዴታ በአባል ሀገራት ላይ የሚጥል ሲሆን ኢትዮጵያም ይህንኑ ግዴታዋን እንድትወጣ የኦዞን ንጣፍን የሚያሳሱ ኬሚካሎችን ለመቆጣጠር የሚያስችል ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅታለች።

5. የአደገኛ ቆሻሻዎች እና ኬሚካሎች አለም አቀፍ ስምምነት እና ሀገራዊ ህጎች

አለም አቀፍ የአደገኛ ቆሻሻዎች ኮንቬንሽኖች እና ሌሎች ስምምነቶች እንደሚያሳዩት "ቆሻሻ" የሚለው ቃል በአለም አቀፍ ደረጃ የተሰጠው ትርጉም የተወገዱ፣ሊወገዱ የተዘጋጁ ወይም እንዲወገዱ የሚፈለጉ ነገሮችን ነው[17]።በሌላ በኩል አደገኛ ቆሻሻዎች የሚባሉት ደግሞ በሰዎች ጤና እና በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚስከትሉ የተለያዩ አይነት ቆሻሻዎች ሲሆኑ እነዚህም ተረፈ ምርት የሆኑ ተቀጣጣዮች ፣ ፈንጂዎች፣ራድዮአክቲቮች ፣መርዞች እና የመሳሰሉት ናቸው[18] ።እነዚህ ቆሻሻዎችም መርዛማ የሆኑ ንጥረ ነገሮችን የሚይዙ ሲሆን ዋና ዋናዎቹም አርሰኒክ፣ካድሚየም፣ሜርኩሪ፣ሊድ፣ኦርጋኒክ ፎስፎረስ እና የመሳሰሉት ሲሆኑ እነዚህም ቆሻሻዎች የሚፈጠሩት ከተለያዩ ምንጮች ሲሆኑ በዋናነትም ከሰፋፊ የምርት ሂደቶች፣ከተለየዩ ሆስፒታሎች እና ከመኖሪያ ቤቶች ከሚወገዱ ቆሻሻዎች ነው።

አለማችን ይበልጡን እያደገች መሄድዋ እና የነዋሪዎችዋም ቁጥር እያደገ መሄዱ፣የተለያዩ አይነት የኢንዱስትሪ፣የንግድ፣የኮንስትራክሽን፣የግብርና፣የጤና እንቅስቃሴዎች በከፍተኛ ሁኔታ ማደግ የሚመነጩ ቆሻሻዎች መጠን እንዲጨምር አድርጓል።ለምሳሌ መረጃዎች እንደሚያሳዩት የአውሮፓ ህብረት ሀገራት በየአመቱ 1.3 ቢሊዮን ቶን ቆሻሻ ሲያመነጩ ከዚህ ውስጥ 36 ሚሊዮን ቶን የሚሆነው አደገኛ ቆሻሻዎች ናቸው።በመሆኑም ቆሻሻዎች በተለያየ መንገድ ከመነጩ በኃላ በሰው ጤና እና በአካባቢ ላይ የሚያደርሱትን አሉታዊ ተፅእኖ ለማስቀረት የሚያስችል ተገቢ የሆነ አያያዝ እና አወጋገድ እንዲኖር ያስፈልጋል።

በአብዛኛዎቹ በአለም ላይ የሚገኙ ሀገራት አንድ ሀገር በተገቢ ሁኔታ ሊያስወግደው ከሚገባው መጠን በላይ ቆሻሻ የሚያመነጩ ሲሆን በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ የቆሻሻ መጣያ ቦታዎች በመሙላታቸው

[17] እ.ኤ.አ በ1989 የተደነገገው የባዝል ኮንቬንሽን አንቀፅ 2 (1)
[18] ዝኒ ከማሁ

ኢንዱስትሪዎች እና ሌሎች ዘርፎች አማራጭ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታዎችን በመፈለግ ላይ ይገኛሉ።ሳይንሳዊ ጥናቶች እና ምርምሮች አደገኛ ቆሻሻዎችን ለመቆጣጠር የወጡ ህጎች እና ስምምነቶች እንዲዘጋጁ ትልቁን ሚና ተጫውተዋል።ምንም እንኳን የሁሉንም የቆሻሻ አይነቶች አደገኝነት የሚያሳይ የሳይንስ ማረጋገጫዎች ባይኖሩም ጥናቶቹ እና ምርምሮቹ የቆሻሻዎቹ ተፈጥሮአዊ ባህርይ በአካባቢ እና በጤና ላይ ሊያደርሱ የሚችሉትን አደጋ ይፋ እንዲወጣ አድርገዋል።እነዚህ የጥናት ውጤቶችም በኢንዱስትሪ በበለፀጉ ሀገሮች ላይ የጠበቀ የአካባቢ ደንቦች እንዲወጡ መሰረት የጣለ ሲሆን እ.ኤ.አ ከ 1970ዎቹ ጀምሮ የአደገኛ ቆሻሻዎችን ለማስወገድ የሚያስፈልገው ወጪ እንዲጨምር አድርጓል፡ይህም ሁኔታ ቆሻሻዎች በመነጩበት ወይም በሌላ ሀገር ቀለል ባለ ወጪ እንዲወገዱ የሚቻልበትን አማራጭ እንዲፈለግ ረድቷል።

በአንዳንድ አጋጣሚዎች ቆሻሻን በማስወገድ ላይ የተሰማሩ ተቋሞች ባልተፈቀዱ ቦታዎች ላይ ደህንነቱ ባልተጠበቀ ሁኔታ አደገኛ ቆሻሻዎችን በባህር ዳርቻዎች እና በትላልቅ የውሀ አካላት ላይ በማስወገድ በውሀ ላይ በሚኖሩ ህይወት ያላቸው ፍጥረታት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሱ ይገኛል።በተለይም አደገኛ ቆሻሻን በአንጻሩ ርካሽ በሆነ መንገድ በኢንዱስትሪ የበለፀጉ ሀገሮች የውጭ ምንዛሪን በእጅጉ ወደሚፈልጉ ነገር ግን ስለ ቆሻሻዎቹ በቂ እውቀት በሌላቸው እና ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ለማስወገድ አቅሙ ወደ ሌላቸው ታዳጊ ሀገሮች ኤክስፖርት ያደረጋሉ።ብዙዎቹ እነዚህን ቆሻሻዎች የሚቀበሉ ሀገራት የሚገኙት በአፍሪካ፣በምስራቅ አውሮፓ እና የካሪቢያን ሀገራት ሲሆኑ ወደ እነዚህም ሀገራት የሚላከውም አደገኛ ቆሻሻ ስለ ቆሻሻዎቹ ምንም አይነት ጥርጣሬ እና እውቀት በሌላቸው ነዋሪዎቻቸው ላይ ከፍተኛ የጤና እና የአካባቢ ጉዳት አስከትሏል።ለችግሩ መወሳሰብም በዋናነት እንደምክንያት የሚጠቀሰው በኢንዱስትሪው ዘርፍ የተሰማሩ አምራቾች በማምረት ሂደት ወቅት ስለሚመነጩት አደገኛ ቆሻሻዎች ምንነት የሚያስረዱ መረጃዎችን የንግድ ሚስጥር በሚል ሸፋን የሚደብቁ መሆኑ ሲሆን ይህም ቆሻሻዎቹን የሚረከቡ ሀገራት ቆሻሻዎቹን በተገቢው መንገድ ለመያዝ እና ለማስወገድ እንዳይችሉ አድርጓል።የችግሩ ስፋት እና መጠን በሀገራት ዘንድ ትኩረትን በማግኘቱ አደገኛ ቆሻሻዎችን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ አስገዳጅ እና አስገዳጅ ያልሆኑ አለም አቀፍ ስምምነቶች፣ድንበር ዘለል የሆኑ የቆሻሻ እንቅስቀሴዎችን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ስታንዳርዶች እንዲዘጋጁ ምክንያት ሆኗል።

5.1. የአደገኛ ቆሻሻዎችን ለመቆጣጠር የተደነገጉ አለም አቀፍ ስምምነቶች

5.1.1. የባዝል ኮንቬንሽን

የአደገኛ ቆሻሻዎችን ለመቆጣጠር ከተደነገጉ ድንጋጌዎች ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሰው ድንበር ዘለል የአደገኛ ቆሻሻዎች ዝውውር እና አወጋገድን ለመቆጣጠር የተደነገገው የባዝል ስምምነት ነው፡፡የባዝል ስምምነት መነሻውን ያደረገው ብክለትን በሚመለከት እና በሰዎች ጤና እና ደህንነት፣በስነ መህድር እና በተለያዩ ዝርያዎች ላይ የሚደርሱ አካባቢያዊ ችግሮች ላይ ለመምከር እ.ኤ.አ በ1972 ዓ.ም በተካሄደው የተባበሩት መንግስታት የሰዎች እና የአካባቢ ስብሰባ (የስቶክሆልም ስብሰባ) ወቅት ጀምሮ ነው፡፡ከስቶክሆልም ስብሰባ ቀደም ብሎ የተለያዩ አለምአቀፍ እና ብሔራዊ የሳይንስ ምርምር ተቋማት በተለያዩ የሰው ልጆች እንቅስቃሴዎች ምክንያት በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶች ላይ በተለይም አለም አቀፍ አካባቢያዊ ችግሮችን በአለም አቀፍ ትብብሮች መፈታት እንደሚኖርባቸው ሰፋ ያለ ግንዛቤ እንዲፈጠር አድርገዋል፡፡

ከስቶክሆልም ስብሰባ ውጤቶች አንዱ የሀገራት ተወካዮች በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ትኩረት ለመስጠት የተስማሙ ሲሆን ይህም በዋናነት ወደ አካባቢ የሚለቀቁ አደገኛ ቆሻሻዎችን ለማቆም ነበር፡፡የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም እ.ኤ.አ በ1981 ዓ.ም የአለም አካባቢን ለመጠበቅ ከሚያስፈልጉ ጉዳዮች አንዱ የአደገኛ ቆሻሻዎች አያያዝ እና ድንበር ዘለል ዝውውር ቁጥጥር መሆኑን ተገንዝቧል፡፡በወቅቱም ህገ ወጥ በሆነ መንገድ አደገኛ ቆሻሻዎች በሀገር ውስጥ እና በባህሮች ላይ የሚራገፉበት እንዲሁም ከበለፀጉት ሀገራት ወደ ታዳጊ ሀገራት ተልከው የሚወገዱበት በርካታ አጋጣሚዎች ነበሩ፡፡ የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራምም አደገኛ ቆሻሻዎች ከአካባቢ ጋር ተስማሚ በሆነ ሁኔታ የሚወገዱበትን የካይሮ መመሪያ እ.ኤ.አ በ1987 ዓ.ም ያዘጋጀ ሲሆን የተዘጋጀበትም ዋና ምክንያት ሀገራት የአደገኛ ቆሻሻዎችን አያያዝ እና አወጋገድ በሚመለከት ለሚያዘጋጁዋቸው ብሄራዊ ፖሊሲዎች ድጋፍ እንዲያደርግ በማሰብ ነበር፡፡መመሪያው ከወጣ በኃላ የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም ዋና ካውንስል ቁጥጥር ያልተደረገበት የአደገኛ ቆሻሻዎች ዝውውርን ስለሚያስከትለው አሉታዊ ተፅእኖ በተመለከተ በህዝቦች ዘንድ እያደገ የመጣውን ግንዛቤ ከግምት ውስጥ በማስገባት አንድ አለም አቀፍ ስምምነት እንዲዘጋጅ ሊወስን ችሏል፡፡የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም የህግ እና የቴክኒክ ኤክስፐርቶችን የያዘ አንድ ቡድን አቋቁሞ ረቂቅ ኮንቬንሽኑን ያዘጋጀ ሲሆን ረቂቁም ከተጠናቀቀ በኃላ ከተለያዩ ሀገራት ለመጡ ተወካዮች በረቂቅ ኮንቬንሽኑ ላይ እንዲወያዩ ስብሰባ አዘጋጅቶ ነበር፡፡በመጨረሻም የባዝል ኮንቬንሽን እ.ኤ.አ በ1989 ዓ.ም

የወጣ ሲሆን በስራ ላይ የዋለውም እ.ኤ.አ ግንቦት 5 ቀን 1992 ዓ.ም ሲሆን እ.ኤ.አ ከ ህዳር 2005 ዓ.ም ጀምሮ 166 ሀገሮች በአባልነት ይገኙበታል፡፡

የባዝል ኮንቬንሽን ድንበር ተሻጋሪ የአደገኛ ቆሻሻዎችን ዝውውር እና ሌሎች ቆሻሻዎችን ጥብቅ በሆነ መንገድ ለመቆጣጠር የተደነገገ የመጀመሪያው እና ዋነኛው ስምምነት ሲሆን ስምምነቱም በአባል ሀገራቱ ላይ አስገዳጅ ግደታዎችን የሚጥሉ አንቀፆችን የያዘ ነው፡፡በኮንቬንሽኑ አንቀፅ ሁለት መሰረት ቆሻሻ ማለት የተወገዱ ወይም ሊወገዱ የተዘጋጁ ወይም እንዲወገዱ የሚፈለጉ ነገሮች በማለት ይተረጉመዋል፡፡ኮንቬንሽኑ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ ቆሻሻዎችን እንዲሁም ቆሻሻዎቹ ሊመነጩባቸው የሚችሉባቸውን እንቅስቃሴዎች (ከሆስፒታሎች እና ከክሊኒኮች የሚወጡ ቆሻሻዎች፣የመድሀኒት ቅመማ በሚዘጋጅበት ወቅት የሚወገዱ ቆሻሻዎች እና የመሳሰሉት) በ Annex 1 እና 3 ላይ ተዘርዝረው ይገኛሉ፡፡ከአደገኛ ቆሻሻዎች በተጨማሪም ኮንቬንሽኑ በ Annex 2 ላይ ሌሎች ቆሻሻዎች በሚል ዝርዝር ስር ለድንበር ዘለል የቆሻሻዎች እንቅስቃሴ ሊጋለጡ የሚችሉ ከመኖርያ ቤቶች የሚሰበሰቡ ቆሻሻዎችን እና የቤት ቆሻሻዎች በሚቃጠሉበት ወቅት የሚቀሩ ቅሪቶችን ይዞ ይገኛል፡፡

በባዝል ኮንቬንሽን አንቀፅ 1(3) እና 4 መሰረት የተወሰኑ የቆሻሻ አይነቶችን ከኮንቬንሽኑ ወሰን ውጭ አድረጓቸዋል፡፡ በአንቀፅ 1(3) መሰረት ኮንቬንሽኑ ራድዮአክቲቭ የሆኑ ቁስ ነገሮች ላይ ተፈፃሚ እንደማይሆን ሲያስቀምጥ ለዚህም እንደ ምክንያት ሊጠቀስ የሚችለው ራዲዮአክቲቭ ቆሻሻዎች በተፈጥሮአቸው እና በኬሚካላዊ አወቃቀራቸው በጣም የተለዩ በመሆኑ በእጅጉ የተለየ የቴክኒክ እና የሌሎች የአያያዝ ስርአቶች ስለሚያስፈልጋቸው ነው፡፡በዚህም ምክንያት የራድዮአክቲቭ ቆሻሻዎች በአለም አቀፉ የአቶሚክ ኤነርጂ ኤጀንሲ ቁጥጥር ይደረግባቸዋል፡፡በተጨማሪም በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 1(4) ላይ እንደተጠቀሰው ከመርከቦች መደበኛ አሰራር ጋር በተያያዘ የሚመነጩ ኬሚካሎች በዚህ ኮንቬንሽ ውስጥ አልተካተቱም፡፡

የባዝል ኮንቬንሽን በመግቢያው ላይ እንደተገለፀው ኮንቬንሽኑ በድንበር ተሻጋሪ አደገኛ ቆሻሻዎች እና ሌሎች ቆሻሻዎች አማካኝነት በሰዎች ጤና እና በአካባቢ ላይ ሊደርስ የሚችለውን አደጋ እውቅና የሰጠ ሲሆን አላማውም በእነዚህ ቆሻሻዎች አማካኝነት ሊደርስ የሚችለውን አደጋ መከላከል እንደሆነ በግልፅ ተቀምጧል፡፡ይህንንም ግብ ለማሳካት ኮንቬንሽኑ ሶስት በአባል ሀገራት ላይ ፅኑ ግዴታን የሚጥሉ ቁልፍ እርምጃዎችን ያስቀመጠ ሲሆን እነዚህም

1) ጥብቅ የሆነ ድንበር ዘለል የአደገኛ ቆሻሻዎች ቁጥጥር፣
2) ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆነ የአደገኛ ቆሻሻዎች አያያዝ እና

3) በኮንቬንሽኑ ውስጥ የሚገኙ አንቀፆች በአለም አቀፍ ሁኔታ መተግበር የሚሉ ናቸው፡፡

1) ጥብቅ የሆነ ድንበር ዘለል የአደገኛ ቆሻሻዎች ቁጥጥር

ድንበር ዘለል የአደገኛ ቆሻሻዎች ዝውውር ማለት አለም አቀፍ ድንበርን ተሻግረው የሚጓዝ ቆሻሻዎችን ለማመልከት ነው፡፡የኮንቬንሽኑ አንቀጽ 4(1)(ሀ) ላይ እንደተጠቀሰው እያንዳንዱ አባል ሀገር አደገኛ ቆሻሻዎች ወይም ሌሎች ቆሻሻዎች ወደ ሀገር ውስጥ ለማራገፍ እንዳይገቡ የመከልከል መብት እንዳለው እውቅና ይሰጣል፡፡በመሆኑም ማንኛውም አባል ሀገር በባዝል ኮንቬንሽን Annex ላይ የተዘረዘሩት ቆሻሻዎችን ወይም በብሄራዊ ህጎች አደገኛ የተባሉ ቆሻሻዎች ወደ ሀገር ውስጥ እንዳይገቡ ሊከለክሉ ይችላሉ፡፡እንደዚህ አይነት ክልከላንም የሚያደርግ አባል ሀገር ውሳኔውን ለባዝል ሴክሬታሪያት እና ለሌሎች አባል ሀገሮች ማሳወቅ እንዳለበት በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 4(1) (ሀ) እና አንቀፅ 13 ላይ ተደንግጎ ይገኛል፡፡በሌላ በኩል የኮንቬንሽኑ አንቀፅ 4(2)(ረ) መሰረት እያንዳንዱ አባል ሀገር በተለይም የባዝል ኮንቬንሽን አባል በሆኑም ሆነ ባልሆኑ ታዳጊ ሀገራት ቆሻሻዎቹ በተገቢው እና ደህንነቱ በተጠበቀ መንገድ ሊወገዱ እንደማይችሉ የሚታወቅ ሲሆን የቆሻሻ ዝውውር ክልከላ እንዲደረግ ያስገድዳል፡፡

2) ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆነ የአደገኛ ቆሻሻዎች አያያዝ

የሰዎች ጤናን እና አካባቢን አደገኛ ቆሻሻዎች ከሚያደርሱት አሉታዊ ተፅእኖ መከላከል ይቻል ዘንድ የባዝል ኮንቬንሽን አባል ሀገራት ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆነ የቆሻሻ አያያዝ እንዲኖራቸው ይደነግጋል፡፡በባዝል ኮንቬንሽን አንቀፅ ሁለት ላይ እንደተጠቀሰው ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆነ የአደገኛ ቆሻሻዎች አያያዝ ማለት በአደገኛ ቆሻሻዎች ምክንያት በሰው ጤና እና በአካባቢ ላይ ሊከሰት የሚችል አደጋን በማንኛውም ሊተገበር በሚችል እርምጃ ቆሻሻዎቹን በተገቢ ሁኔታ የመያዝ ሂደት በማለት ተርጉሞታል፡፡አብዛኛዎቹ በኮንቬንሽኑ ውስጥ ቆሻሻ አያያዝን በተመለከተ የተዘረዘሩት አንቀፆች በሙሉ አደገኛ ቆሻሻዎቹ ከሚመነጩበት ሂደት ጀምሮ እስከ ማንጓዝ፣መልሶ ጥቅም ላይ የሚውሉበት እና ሙሉ በሙሉ የሚወገዱበት ሂደት ጠንከር ባለ ቁጥጥር መከናወን እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡

በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 4(2)(ሀ) እንደተጠቀሰው አባል ሀገራት በግዛታቸው ውስጥ የሚመነጩ አደገኛ ቆሻሻዎች እንዲቀንሱ ይደነግጋል፡፡በተለያየ ምክንያት የሚመነጩ የቆሻሻዎችን መቀነስ ሁለት ጠቃሚ ጎኖች ያሉት ሲሆን እነዚህም አንደኛው የቆሻሻዎቹን መጠን መቀነስ ሲሆን ሌላኛው የአደገኛ ቁሶችን አጠቃቀም መቀነስ እንዲሁም ሙሉ በሙሉ አለመጠቀም መቻል ነው፡፡ለምሳሌ በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 13(3) ላይ እንደተጠቀሰው አባል ሀገራት አደገኛ ቆሻሻዎችን ለመቀነስ እንዲሁም ለማስወገድ

የተጠቀሙባቸውን ቴክኖሎጂዎች ለሌሎች አባል ሀገራት እንዲያጋሩ ይደነግጋል፡፡ከዚህም በተጨማሪ የአደገኛ ቆሻሻዎችን መጠን ለመቀነስ ተጠቃሚዎች የሚገለገሉባቸው እቃዎች ተረፈ ምርት ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ እና ሌሎች አማራጮችን በሚመለከት የግንዛቤ ትምህርት ለተጠቃሚዎች ማስተማር እንደ አንድ አማራጭ ሊወሰድ ይችላል፡፡

በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 4(2) ላይ እንደተገለፀው አባል ሀገራት በቆሻሻዎች አያያዝ ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ግለሰቦች ማለትም ቆሻሻዎችን የሚሰበስቡ እና የሚያጓጉዙ በቆሻሻ ምክንያት የሚደርስ ብክለትን በተቻለ መጠን መቆጣጠር እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ይህንንም ለማሳካት የፈሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻዎች እንዳይፈስሱ ተገቢ የማሸጊያ መሳሪያ መጠቀም እንዳለባቸው እንዲሁም የቆሻሻዎቹ አደገኛ ንጥረ ነገሮች ቆሻሻዎቹ ሙሉ በሙሉ ከመወገዳቸው በፊት መለየት እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 4(2)(ለ) ላይ እንደተገለፀው አባል ሀገራት ቆሻሻዎቹ በተቻለ መጠን በመነጨበት ቦታ መወገዳቸውን እንዲያረጋግጡ የሚደነግግ ሲሆን ቆሻሻዎቹ ኤክስፖርት በሚደረጉበትም ወቅት በአለም አቀፍ ደረጃ እውቅና በተሰጣቸው ደረጃዎች እና ደንቦች መሰረት መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

በባዝል ኮንቬንሽን ውስጥ የተዘረዘሩ መመሪያዎች እና ደረጃዎች የሚተገበሩት በብሔራዊ እና በአለም አቀፍ ደረጃ ነው፡፡በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 9(5) መሰረት አባል ሀገራት የህገ ወጥ የአደገኛ ቆሻሻዎች ዝውውርን የሚከላከል እና ተገቢውን ቅጣት ለማስተላለፍ የሚያስችሉ አግባብነት ያላቸው ህጎችን እንዲያወጡ ያስገድዳል፡፡ለምሳሌ አባል ሀገራት የቅድመ ማስጠንቀቂያ እና ስምምነት በሌለበት ሁኔታ የሚደረጉ የአደገኛ ቆሻሻዎች ዝውውርን በግልፅ የሚከለክል ህግ ሊያወጡ ይችላሉ፡፡በተመሳሳይ አባል ሀገራት ህገ ወጥ የአደገኛ ቆሻሻዎች ዝውውርን የሚቆጣጠር ልዩ የፖሊስ ሀይል ሊያቋቁሙ እንደሚችሉ ይደነግጋል፡፡

በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 15 እና 16 መሰረት ኮንቬንሽኑ የአባል ሀገራት ስብሰባ እና ሴክሬታሪያት ያቋቋመ ሲሆን የተለያየ ሀላፊነትም ይኖራቸዋል፡፡የአባል ሀገራቱ ስብሰባ (COP) የውሳኔ ሰጪ አካል ሲሆን ከሁሉም አባል ሀገራት የተውጣጡ ተወካዮችን የያዘ ነው፡፡ሴክሬታሪያቱ በተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም የሚተዳደር ሲሆን ዋና ሀላፊነቱም የኮንቬንሽኑን አተገባበር መከታተል ሲሆን ከአባል ሀገራት በሚደርሰው መረጃዎች መሰረትም ድንበር ዘለል የአደገኛ ቆሻሻዎችን ዝውውር ይቆጣጠራል፡፡ከዚህ በተጨማሪም ሴክሬታሪያቱ ቴክኒካል በሆኑ ጉዳዮች ላይ ለአባል ሀገራቱ ድጋፍ ሙያዊ ድጋፍ የሚያደርጉ ባለሙያዎችን እና መሳሪዎችን ይመድባል፡፡

5.2. አደገኛ ቆሻሻዎችን በሚመለከት የተደነገጉ አህጉራዊ ስምምነቶች

5.2.1 የባማኮ ኮንቬንሽን

የባዝል ኮንቬንሽን አባል ሀገራት በኮንቬንሽኑ ላይ የተቀመጡ አላማዎችን ለማሳካት እንዲቻል በባይላተራል፣መልቲላተራል፣እና አህጉራዊ ስምምነቶች ላይ እንዲሳተፉ የሚያበረታታ ሲሆን የአደገኛ ቆሻሻዎችን አያያዝ በሚመለከት ለተደነገጉ ሌሎች ተጨማሪ አህጉራዊ ስምምነቶች እንዲደነገጉ ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል። በዚህም ምክንያት እ.ኤ.አ ጥር 30 ቀን በ1991 ዓ.ም አደገኛ ቆሻሻዎች ወደ አፍሪካ እንዳይገቡ ለማገድ እና በአፍሪካ አገሮች መካከል የአደገኛ ቆሻሻዎችን ድንበር ዘለል ዝውውር እንዲሁም አወጋገድ ለመቆጣጠር የባማኮ ኮንቬሽን እ.ኤ.አ ጥር 30 ቀን በ1991 ዓ.ም ወጥቷል። በስራ ላይ የዋለውም እ.ኤ.አ በ1998 ዓ.ም ሲሆን ሴክሬታሪያቱም በአፍሪካ ዩኒየን ውስጥ ይገኛል።የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ 26 ቀን 1998 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ የባማኮ ኮንቬንሽንን አፅድቆታል።

የባማኮ ኮንቬንሽን በዋናነት የሚቆጣጠረው በጤና እና በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ የተባይ ማጥፊያዎችን፣ማዳበሪያዎች እና ሌሎች ኬሚካሎች ላይ ሲሆን ከባዝል ስምምነት በተለየ ሁኔታም አደገኛ ቆሻሻዎች የሚለው ትርጓሜ የራዲዮአክቲቭ ቆሻሻዎችንም ጨምሮ እንዲይዝ ተደርጓል።ሌላው በባማኮ ኮንቬንሽን ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሰው አንቀፅ ከሌሎች አባል ባልሆኑ ሀገራት ኢምፖርት የሚደረጉ አደገኛ ቆሻሻዎችን ወደ አፍሪካ ሀገራት እንዳይገቡ በግልፅ የሚከለክል ሲሆን ይህንንም ለማስፈፀም እንዲቻል በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 4፣6፣8 እና 9 መሰረት አባል ሀገራት የአደገኛ ቆሻሻዎቹ ወደ ግዛታቸው እንዳይገቡ ህጋዊ እናአስተዳደራዊ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ያስገድዳል። ህገወጥ የሆነ የአደገኛ ቆሻሻዎች ዝውውር በሚያጋጥምበት ግዜ በህገወጥ መንገድ የገቡት ቆሻሻዎች ወደ መጡበት ሀገር እንዲመለሱ እና አባል ሀገራት ስለተፈጠረው ጉዳይ ለባማኮ ሴክሬታሪያት እና ለሌሎች አባል ሀገራት ማሳወቅ እንዳለባቸው ኮንቬንሽኑ ያስገድዳል።በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 9 መሰረት በአባል ሀገራት መካከል የአደገኛ ቆሻሻዎች ዝውውር ማድረግ የሚቻል ሲሆን ነገር ግን የቆሻሻዎቹ መድራሻ የሆነው ሀገር ቆሻሻዎቹ ከመላካቸው በፊት በፅሁፍ ፈቃደኝነቱን መግለፅ ይኖርበታል።በተጨማሪም በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 8 መሰረት በአባል ሀገራት መካከል ቆሻሻዎችን ለማዘዋወር ስምምነት ላይ ከተደረሰ በኃ ዝውውሩ ሙሉ በሙሉ መፈፀም የማይችል ከሆነ ወይም የተወሰኑት ኤክስፖርት የተደረጉት ቆሻሻዎች በተቀባዩ ሀገር አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ መወገድ የማይችሉ ከሆነ ቆሻሻዎቹ ወደ መጡበት ሀገር እንዲመለሱ ይደነግጋል።

5.3. ኬሚካሎች

ኬሚካሎች በእለት ተእለት ኑሮአችን ውስጥ ትልቅ ሚና የሚጫወቱ ሲሆን ለሰዎች ደህንነትም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል፡፡ለእርሻ ስራ የሚውሉ ኬሚካሎች የሰብል ተባዮችን በማጥፋት የእርሻ ምርት እንዲጨምር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ ሲሆን የኢንዱስትሪ ኪሚካሎች በአንጻሩ ደግሞ የተለያዩ ምርቶች እንዲመረቱ ምክንያት ሆነዋል፡፡ኬሚካሎች በዘመናዊው አለም በሁሉም ምርቶች ውስጥ የሚገኙ ሲሆኑ እነዚህም በኢንዱስትሪ እና በትራንስፖርት ዘርፍ፣በአገልግሎት ዘርፍ ማለትም በቴሌኮሚዩኒኬሽን፣በባንኮች እንዲሁም በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች ውስጥ ይገኛሉ፡፡

ነገር ግን አንድ ግዜ ወደ አካባበቢ ከተቀላቀሉ ለረጅም ግዜ ምንም ሳይሆኑ የሚቆዩ ሲሆን ይህም በሰዎች ጤና እና በስነ መሕድር ላይ ያልተጠበቀ እና ለረጅም ግዜ የሚቆይ ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ፡፡የሳይንሳዊ እውቀት እና ግንዛቤ በኬሚካሎች ላይ እየጨመረ መሄዱ በዚያው መጠን በሰዎች እና በአካባቢ ላይ የሚያሳድሩት ተጽእኖ እንዲታወቅ አስችሏል፡፡በአሁኑ ወቅት ከመቶ ሺህ በላይ የሚሆኑ ኬሚካሎች በሰፊው ተመርተው የሚገኙ ሲሆን ከእነዚህም ምርቶች ጋር ተያይዘው የሚከሰቱ አደጋዎች ብዙውን ግዜ ዘግይተው የሚስተዋሉ ናቸው፡፡ኬሚካሎች በኢንዱስትሪዎች አካባቢ ብቻ ተወስነው የሚገኙ ሳይሆን ለረጅም ግዜ ምንም ሳይሆኑ የሚቆዩ ሲሆን ከነበሩበት ቦታ በብዙ ሺህ ኪሎ ሜትር የሚቆጠር ርቀት ተጉዘው በምግብ ሰንሰለት ውስጥ በመግባት በሰዎች እና በእንስሳት አካላት ውስጥ ሊገኙ ይችላሉ፡፡

እ.ኤ.አ በ1992 ዓ.ም በተካሄደው የተባበሩት መንግስታት አካባቢ እና የልማት ስብሰባ ወቅት በ የዘላቂ ልማትን ለማሳካት በወጣው በአጀንዳ 21 ላይ እንደተጠቀሰው በኬሚካል ብክለት ምክንያት የሚደርስ ብክለት ከቅርብ አመታት ወዲህ በአለማችን ላይ በተለይም ዋና ዋና በሚባሉ የኢንዱስትሪ አካባበቢዎች በሰዎች ጤና ፣ በስነ ባህርይ (genetic) አወቃቀር ፣ በመራባት ሥርዐት እንዲሁም በአካባቢ ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ እያደረሱ እንደሆኑ ተገልጻል፡፡ በአሁኑ ወቅት እነዚህ ኬሚካሎች ከመቼውም ግዜ በበለጠ ሁኔታ እተመረቱ የሚገኙ ሲሆን ወደ ፊትም ከዚህ በበለጠ ሁኔታ ይመረታሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡መረዛማ የሆኑ ኬሚካሎች በመላው አለም በማደግ ላይ በሚገኙትም ሆነ በኢንዱስትሪ በበለጸጉት ሀገሮች የሚመረቱ ሲሆን በአለም አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ አለም አቀፍ ንግዶችም ግሎባላይዝድ በሆነው አለም ውስጥ ትልቅ ቦታ ይኖራቸዋል፡፡

ሆኖም ጥብቅ በሆነ ሁኔታ በጥቅም መዋል ያለባቸውን ኬሚካሎችን አምርተው ኤክስፖርት በሚያደርጉ እና እነዚህን ምርቶች ወደ ሀገራቸው የሚያስገቡ ነገር ግን ምርቶቹን በተገቢው ሁኔታ ለመጠቀም በአነስተኛ የእድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ ሀገራት መካከል ያለው ሁኔታ በአለም አቀፍ ደረጃ አሳሳቢ ሊሆን ችሏል፡፡ይህም ስጋት በይበልጥ ጎልቶ የሚታየው ወደ ሀገር ውስጥ በሚያስገቡት መርዛማ ኬሚካሎች ላይ በቂ የሆነ መረጃ በሌላቸው እና አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ለመያዝ የሚያስችል መሰረተ ልማት በሌላቸው በማደግ ላይ በሚገኙ ሀገራት እና በኢኮኖሚ ሽግግር ላይ በሚገኙ ሀገራት ላይ ነው፡፡

5.3.1) ኬሚካሎችን በሚመለከት የተደነገጉ አለም አቀፍ ስምምነቶች

በአለም አቀፍ ደረጃ የኬሚካሎች ንግድ መጠን መጨመር እንዲሁም የሚያሳድሩትም ተጽእኖ ኬሚካሉን በሚያስገቡት ሀገሮች ላይ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በአህጉር ደረጃ እንዲሁም በአለም አቀፍ ደረጃ መሆኑ ኬሚካሎቹን በተገቢው ሁኔታ ለመያዝ የሚያስችል አለም አቀፍ እና መልቲላተራል ትብብር እንዲመሰረት አስችሏል፡፡ለመጀመሪያ ግዜ መርዛማ ኬሚካሎችን ለመቆጣጠር ህጎች የተደነገጉት በብሄራዊ ደረጃ ሲሆን ትኩረት ያደርጉ የነበረውም ከተመረቱ በኃላ አደገኛ ተብለው በሚመደቡ ምርቶች ላይ ነበር፡፡እነዚህም ህጎች በዋናነት ትኩረት ያደርጉ የነበረውም በሰዎች ጤና አጠባበቅ፣በስራ ቦታ ደህንነት እና በሸቀጥ እቃዎች ላይ የሚኖር የተጠቃሚዎች ደህንነት ላይ ነበሩ፡፡

ከኬሚካሎች ጋር በተያያዘ የሚደርሱ አካባቢያዊ እና የህዝብ ጤንነት ችግሮችን ለማሰወገድ የተደረጉ ቀደምት አለም አቀፍ ስምምነቶች ትኩረት ያደርጉ የነበረው አደገኛ ኬሚካሎችን በሚመለከት በቂ መረጃዎች መኖራቸው ላይ ነበር፡፡ለዚህም በዋናነት የሚጠቀሰው እ.ኤ.አ በ 1976 ዓ.ም የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም አለም አቀፍ መርዛማ የሆኑ ኬሚካሎች መዝገብ (International Register of Potentially Toxic Chemicals (IRTPC)) አዘጋጅቶ በኬሚካሎቹ የሚደርሱ ጉዳቶችን የያዘ ጥራዝ አዘጋጅቶ አሰራጭቷል፡፡

በፍጥነት በማደግ ላይ የሚገኘውን የኬሚካል ምርት እና ንግድ በማስመልከት የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም እና የተባበሩት መንግስታት የምግብ እና የእርሻ ድርጅት (United Nations Food and Agricalture Organization) በፈቃድ ላይ የተመሰረተ ኬሚካሎችን በሚመለከት መረጃዎችን የመለዋወጥ መርሀ ግብሮችን እ.ኤ.አ በ1980 ዎቹ አጋማሽ ላይ ጀምረው ነበር፡፡እ.ኤ.አ በ1985 ዓ.ም የተባበሩት መንግስታት የእርሻ እና የምግብ ድርጅት የተባይ ማጥፊያዎችን አጠቃቀም እና ስርጭትን በሚመለከት

የስነ ምግባር ደንብ ያዘጋጀ ሲሆን አላማውም የተባይ ማጥፊያዎችን በማሰራጨት ላይ ለተሰማሩ የግልም ሆነ የመንግስት አካላት በፍቃድ ላይ የተመሰረተ የስነ ምግባር ደረጃዎችን እና ያለባቸውን ሀላፊነት ለማሳወቅ ነበር፡፡በተጨማሪም በአለም አቀፍ ደረጃ የኬሚካሎችን ንግድ ለማካሄድ የመረጃ ልውውጥ መመሪያ የሆነው የለንደን መመሪያ የተዘጋጀ ሲሆን ይህም እ.ኤ.አ በ1987 ዓ.ም በተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም ምክር ቤት የጸደቀ ሲሆን አላማውም ሀገራት መመሪውን በመጠቀም በኬሚካሎች ሊደርስ የሚችለውን አደጋ ለመቀነስ የሚስችሉ ሳይንሳዊ፣ ቴክኒካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ህጋዊ መረጃዎችን እንዲለዋወጡ የሚያስችል ነው፡፡እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ደንቦች በአንድነት ተዋህደው የተወሰኑ አደገኛ ኬሚካሎችና ፀረ ተባዮች ዓለም አቀፍ ንግድ በቀዳሚ ግንዛቤ ላይ በተመሰረተ የእሽታ ሥርዐት እንዲተገበር የሚደነግገው የሮተርዳም ኮንቬንሽን እ.ኤ.አ በ1998 እንዲወጣ አስችሏል፡፡

5.3.1.1) የሮተርዳም ኮንቬንሽን

የሮተርዳም ኮንቬንሽንን ለማዘጋጀት ድርድሩ የተጀመረው እ.ኤ.አ በሚያዝያ 1996 ዓ.ም ሲሆን ድርድሩም በተፋጠነ ሁኔታ በሁለት አመታት ውስጥ ሊያልቅ ችሏል፡፡በመሆኑም ኮንቬንሽኑ እ.ኤ.አ መስከረም 10 ቀን 1998 ዓ.ም የወጣ ሲሆን በስራ ላይ የዋለውም እ.ኤ.አ የካቲት 24 ቀን 2004 ዓ.ም ነው፡፡ ኢትዮጵያም የሮተርዳም ኮንቬንሽንን የፈረመች ሲሆን የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ 23 ቀን 1994 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ አፅድቆታል፡፡

ኮንቬንሽኑ በአባል ሀገራቱ ላይ ጽኑ የሆነ ግዴታን የሚስከትል ሲሆን በዋናነትም በቀዳሚ ግንዛቤ ላይ የተመሰረተ የእሽታ ሥርዐት እንዲተገበር የሚደነግግ ሲሆን አላማውም የተለያዩ ኬሚካሎችን ወደ ተለያዩ ሀገራት የሚልኩ ሀገራት ከተቀባይ ሀገራት በቅድሚያ እሽታን ወይም ፈቃድ ማግኘት እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ኮንቬንሽኑ ኤክስፖርት ስለሚደረጉት ኬሚካሎች የመረጃ ልውውጥ እንዲደረግ ሁኔታዎችን የሚያመቻች ሲሆን ኬሚካሎቹንም ወደ ሀገራቸው ለማስገባት ለሚፈልጉ ሀገራት በኬሚካሎቹ ላይ ብሄራዊ ውሳኔ እንዲወሰኑ ያሳውቃል፡፡ሆኖም ኮንቬንሽኑ በአለም አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ የኬሚካል ንግዶችን እና የተወሰኑ ኬሚካሎችን ከመጠቀም የሚከለክል አንቀጽ አልያዘም፡፡

በኮንቬንሽኑ አንቀጽ ሁለት መሰረት ኬሚካል ማለት በራሱ ወይም በውህድ መልክ በፋብሪካ የተመረተ ወይም በተፈጥሮ የተገኘ ህይወት ያላቸውን ፍጥረቶች የማይጨምር ነገር ነው፡፡ በኮንቬንሽኑ ውስጥ ሽፋን ያገኙት ኬሚካሎች በሁለት የተከፈሉ ሲሆን እነዚህም በጤና እና በአካባቢ ላይ በሚያደርሱት

ጉዳት ምክንያት የታገዱ ወይም በጥብቅ የተከለከሉ የኢንዱስትሪ ኬሚካሎች እና በማደግ ላይ በሚገኙ ሀገራት እንዲሁም በኢኮኖሚ ሽግግር ላይ በሚገኙ ሀገራት ላይ ቸግር ሊያደርሱ የሚችሉ አደገኛ የፀረ-ተባይ ማጥፊያዎች ናቸው፡፡ኮንቬንሽኑ በአጠቃላይ በ 41 ኬሚካሎች ላይ ትኩረት የሚያደርግ ሲሆን እነዚህም 24 በፀረ-ተባይ ኬሚካሎች ላይ፣6 በአደገኛ ፀረ ተባዮች ላይ እንዲሁም 11 በኢንዱስትሪ ኬሚካሎች ላይ ነው፡፡በተጨማሪም በሮተርዳም ኮንቬንሽን የማይሸፈኑ ነገር ግን በሌሎች አለም አቀፍ ስምምነቶች የሚሸፈኑ ኬሚካሎች ሲኖሩ እነዚህም ራድዮ አክቲቭ ኬሚካሎች፣የኬሚካል ጦር መሳሪዎች እንዲሁም ምግብ ለማዘጋጀት የሚውሉ ኬሚካሎች ናቸው፡፡በሌላ በኩል ለምርምር እና ለግል ጥቅም የሚውሉ በሰው ጤና እና በአካባቢ ላይ ጉዳት የማያደርሱ ኬሚካሎችም በዚህ ኮንቬንሽን አይሸፈኑም፡፡

የሮተርዳም ኮንቬንሽን በአንቀፅ 18 መሰረት የኮንቬንሽኑን አተገባበር የሚከታተል የአባል ሀገራት ስብሰባ (COP) ያቋቋመ ሲሆን የመጀመሪያውንም የአባል ሀገራት ስብሰባ እ.ኤ.አ በመስከረም ወር 2004 ዓ.ም አካሂዷል፡፡በመጀመሪያው ስብሰባውም የኬሚካል ግምገማ ኮሚቴ (Chemical Review Comitte) የተቋቋመ ሲሆን ኮሚቴውም ከአባል ሀገራት የሚደርሱትን ማስታወቂያዎች በመገምገም በቅድመ እሺታ ሥርዐት ማለፍ የሚገባቸው ኬሚካሎች ላይ አስተያየቱን ይሰጣል፡፡

የአባል ሀገራት ስብሰባ እና በስሩ የሚገኙ ተቋማት በዋናነት የሚንቀሳቀሱት በሴክሬታሪያቱ ነው፡፡የሴክሬታሪያቱ ዋና ሀላፊነትም ለአባል ሀገራቱ እና በስሩ ለሚገኙ አካላት ኮንቬንሽኑን ለመተግበር የሚያስችል እገዛዎችን ማድረግ እና ከሌሎች አግባብነት ካላቸው አለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ትብብር ለመፍጠር የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው ፡፡ሴክሬታሪያቱ ዋና መቀመጫውን ያደረገው በስዊትዘርላንድ ዋና ከተማ ጄኔቭ ሲሆን ዋና ዋና ሀላፊነቶቹም የሚከናወነው በተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም ስራ አስፈፃሚ እና በአለም የእርሻ እና የምግብ ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ጄነራል ነው፡፡

5.3.1.1.1) የቅድመ እሺታ ሥርዐት

የቅድመ እሺታ ሥርዐት በሁለት ደረጃዎች የሚከፈል ሲሆን እነዚህም

1) የኢንፎርሜሽን ልውውጥ ደረጃ እና
2) በኮንቬንሽኑ Annex ሶስት ላይ አዳዲስ ኬሚካሎችን ማካተት እና እነዚህን ኬሚካሎች ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባት የሚያስችሉ አሰገዳጅ ሥርዐቶችን ማዘጋጀት ነው፡፡

በኮንቬንሽኑ አንቀፅ አራት መሰረት አባል ሀገራት መረጃዎችን ለመለዋወጥ እና በቅድመ እሽታ ሥርዐት መሰረት ፍቃድን ለማግኘት ግንኙነት ለመፍጠር የሚያስችል የተወከለ ብሄራዊ ተቋም (Designated National Authority) እንዲመሰርቱ ይጠይቃል፡፡ለምሳሌ አንድ አባል ሀገር በህግ አንድን ኬሚካል ወደ ግዛቱ እንዳይገባ ቢያግድ ወይም ጥብቅ ቁጥጥር ቢያደርግ በኮንቬንሽኑ አንቀፅ አምስት መሰረት ውሳኔውን ያስተላለፈው ሀገር በተወከለ ብሄራዊ ተቋሙ አማካኝነት ውሳኔውን ለሴክሬታሪያቱ በዘጠና ቀናት ውስጥ ማሳወቅ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ለሴክሬታሪያቱ የሚላከው ማስታወቂያ የተወሰደውን እርምጃ እና የኬሚካሉን አይነት በኮንቬንሽኑ Annex 1 ላይ በተገለፀው መሰረት መሆን ይኖርበታል፡፡በመቀጠልም ሴክሬታሪያቱ የተላከው ማስታወቂያ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን መያዙን በስድስት ወራት ውስጥ አረጋግጦ ውጤቱን ለሁሉም አባል ሀገራት ያሳውቃል፡፡በተመሳሳይ ወደ አንድ ሀገር እንዳይገቡ ክልከላ የሚደረግባቸውን ኬሚካሎች ለሴክሬታሪያቱ ማስታወቅ እንደሚያስፈልግ ሁሉ በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 12 መሰረት ወደ አባል ሀገራት ኬሚካሎች ከመግባታቸው በፊት በቅድሚያ ለተወከለ ብሄራዊ ባለስልጣን ማስታወቅ እንዳለበት የሚደነግግ ሲሆን ማስታወቂያውም መላክ የሚኖርበት የመጀመሪያ ኤክስፖርት ከመላኩ በፊት ይሆናል፡፡

በቅድመ እሺታ ሥርዐት ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሰው ቀጣዩ ስራ የተለያዩ ኬሚካሎችን በአምስተርዳም ኮንቬንሽን Annex ሶስት ላይ ማስፈር ነው፡፡በመሆኑም አባል ሀገራት በሴክሬታሪያቱ በአንድ በተወሰነ ኬሚካልን በሚመለከት የተላከላቸውን መረጃ ላይ ተመስርተው ኬሚካሉን ወደ ሀገራቸው ውስጥ ለማስገባት እንደሚፈልጉ ወይም እንደማይፈልጉ ፈቃዳቸው ይረጋገጣል፡፡ከዚህም በመቀጥል በሴክሬታሪያቱ በቂ መረጃ ለአባል ሀገራቱ ከተላከ ቦሀላ ኬሚካሉን ወደ ግዛቱ ውስጥ ማስገባት የሚችለው ሀገር ኬሚካሉ ወደ ግዛቱ እንዲገባ በግልፅ ለፈቀደው ሀገር ብቻ ይሆናል፡፡

የሮተርዳም ኮንቬንሽን በአባል ሀገራት ላይ አጠቃላይ ግዴታዎችን የሚጥል ሲሆን በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 15 መሰረት እያንዳንዱ አባል ሀገር ኮንቬንሽኑን በተገቢ ሁኔታ ለመተግበር የሚያስችሉ ብሄራዊ ተቋሞችን እና መሰረተ ልማቶችን ማቋቋም እንዲሁም ማጠናከር እንደሚያስፈልግ ይደነግጋል፡፡በብሄራዊ ደረጃ ኮንቬንሽኑን ለመተግበር የሚያስችሉ ዝርዝር ህጎች እና አስተዳደራዊ አደረጃጀቶችን (በብሄራዊ ደረጃ የተለያዩ ኬሚካሎችን የሚመዘግብ ተቋም እንዲሁም ዳታቤዝ) ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

በሮተርዳም ኮንቬንሽን በአንቀፅ 16 ላይ እንደተጠቀሰው ኮንቬንሽኑ በማደግ ላይ ለሚገኙ ሀገራት እና በኢኮኖሚ ሽግግር ላይ ለሚገኙ ሀገራት የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፡፡የዚህ ድጋፍ ዋና አላማም ታዳጊ ሀገሮች በኮንቬንሽኑ የተቀመጡ ግዴታዎችን ለማሳካት ኬሚካሎችን በተገቢ ሁኔታ ለመያዝ

የሚያስችሉ መሰረተ ልማቶችን እንዲሁም በቂ አቅም እንዲገነቡ ያስችላቸዋል፡፡ሴክሬታሪያቱም የኮንቬንሽኑን አተገባር ለማሳካት የሚያስችሉ የቴክኒክ ድጋፎችን እንዲያከናውን ስልጣን እና ሀላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ይህንንም ሀላፊነት ለመወጣት እንዲያስችለው ሴክሬታሪያቱ የተለያዩ ገንዘብ የሚያፈላልግበት ዘዴዎችን እንዲያመቻች በመጀመሪያው የአባል ሀገራት ስብሰባ ወቅት (COP-1) ሀላፊነት ተጥሎበታል፡፡

5.3.1.2. የስቶክሆልም ኮንቬንሽን

ለረጅም ግዜ ሳይረክሱ የሚቆዩ ከካርበን የተሰሩ ኬሚካሎች (Persistent Organic Pollutants) በአብዛኛው ከፍተኛ ሀይል ያላቸው የፀረ-ተባይ ማጥፊያዎች ሲሆኑ በአካባቢ እና በሰዎች ጤና ላይ ከፍተኛ ስጋትን ፈጥረው ይገኛሉ፡፡እነዚህ ኬሚካሎች በዋናነት የተዘጋጁት ለረጅም ግዜ ሳይረክሱ በመቆየት የተወሰኑ ስነ ምህዳሮችን ለመመረዝ እና ለማጥፋት ነው፡፡ምንም እንኳን ለረጅም ግዜ ሳይረክሱ በሚቆዩ ኬሚካሎች የሚደርስ አካባቢያዊ አደጋ እንደ ኬሚካሉ አይነት የተለያየ ቢሆንም አብዛኛዎቹ ኬሚካሎች ቀጥለው የተዘረዘሩትን አራት መሰረታዊ ባህሪያት ይዘው ይገኛሉ፡

- መርዛማነት፣
- ለአመታት ወይም ለአስርት አመታት ሳይረክሱ ወይም በአንፃሩ አነስተኛ ጉዳት ወደሚያደርስ ደረጃ እስኪለወጡ ይቆያሉ፣
- በሚተንኑበት ወቅት በአየር እና በውሀ አማካኝነት ረጅም ርቀቶችን ይጓዛሉ፣
- በተክሎች አካላት ውስጥ ተከማችተው ይገኛሉ[19]፡፡

ለረጅም ግዜ ሳይረክሱ የሚቆዩ ኬሚካሎች በሰፊው ተሰራጭተው የሚገኙ ሲሆን በአብዛኛው በውቅያኖሶች ሞገድ አማካኝነት በስፋት ከሚገኙበት ከሀሩሩ (Tropical) እና ቴምፕሬት አካባቢዎች ቀዝቃዛ ወደሆኑት ዋልታዎች አካባቢ ተወስደው ይከማቻሉ፡፡በዋልታዎች አካባቢ የእነዚህ ኬሚካሎች በስፋት ሊገኙ የቻሉበት ምክንያት አነስተኛ ትነት መኖሩ ነው፡፡በዚህም ምክንያት በዋልታዎች አካባቢ የሚኖሩ ቀደምት ነዋሪዎች ከኬሚካሎቹ ዋና አገልግሎት ብዙም ተጠቃሚ ባይሆኑም በኬሚካሎቹ በሚደርስ ጉዳት ዋና ተጠቂ ሆነዋል፡፡

እ.ኤ.አ በ1995 ዓ.ም የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም ዋና ምክር ቤት አስራ ሁለት ለሚሆኑ ለረጅም ግዜ ሳይረክሱ የሚቆዩ ኬሚካሎች ላይ ምርመራ እንዲደረግ አድርጓል፡፡ለዚህም

[19] Ridding The World of Persistent Organic Pollutants: A guide To The Stockholme Convention On persistent Organic Pollutants (United Nations Environmental Programme ገፅ 5

እንዲረዳ ለረጅም ግዜ ሳይረክሱ የሚቆዩ ኬሚካሎችን በተመለከተ ግዜያዊ ኮሚቴ ተቋቁሙ የነበረ ሲሆን ኮሚቴውም የኬሚካሎቹን ውህዶች፣ምንጮች፣መርዛማነት እና በማህበረሰብ እና በኢኮኖሚ ላይ የሚያደርሱትን ተፅእኖ ላይ ሰፊ ምርመራ አድርጓል።ግዜያዊ ኮሚቴውም የደረሰበት ውጤትም አፋጣኝ እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ያስገነዘበ ሲሆን በምላሹም ከተለያዩ ሀገራት የተውጣጡ ተደራዳሪዎችን የያዘ አንድ ኮሚቴ ሊቋቋም ችሏል።ኮሚቴው የስቶክሆልም ኮንቬንሽንን የቀረፀ ሲሆን ኮንቬንሽኑ እ.ኤ.አ በግንቦት ወር 2000 ዓ.ም ለፊርማ የቀረበ ሲሆን በስራ ላይ የዋለውም እ.ኤ.አ ግንቦት ወር 2004 ዓ.ም ነበር።ኢትዮጵያም የስቶክሆልም ኮንቬንሽንን ፈርማ የተቀበለች ሲሆን የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ 23 ቀን 1994 ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ይህንን ኮንቬንሽን አፅድቆታል።

በስቶክሆልም ኮንቬንሽን አንቀፅ አንድ ላይ እንደተጠቀሰው የኮንቬንሽኑ ዋና አላማ የሰዎች ጤንነትን እና አካባቢን ለረጅም ግዜ ሳይረክሱ ከሚቆዩ ኬሚካሎች መጠበቅ ነው። ይህንንም ለማሳካት የተለያዩ ስራዎች የሚከናወኑ ሲሆን በጣም አደገኛ የተባሉትን አስራ ሁለት ኬሚካሎች በኮንቬንሽኑ ውስጥ የተዘረዘሩ ሲሆን እነርሱም ፡

1) ሆን ተብለው የተመረቱ ኬሚካሎች
2) ታቅደው ያልተመረቱ ኬሚካሎች (የሌሎች ኬሚካላዊ ሂደቶች ተረፈ ምርቶች) እና
3) ተከማችተው የሚገኙ ኬሚካሎች (Stockpiles) ናቸው።

1) ሆን ተብለው የሚመረቱ ለረጅም ግዜ ሳይረክሱ የሚቆዩ ኬሚካሎች

ሆን ተብለው የሚመረቱ ለረጅም ግዜ ሳይረክሱ የሚቆዩ ኬሚካሎች ዝርዝር በኮንቬንሽኑ Annex A (መወገድ ያለባቸው ኬሚካሎች) እና Annex B (በገደብ ጥቅም ላይ መዋል ያለባቸው ኬሚካሎች) ውስጥ ይገኛሉ።ዘጠኙ ሆን ተብለው የሚመረቱ ኬሚካሎች ለረጅም ግዜ ሳይረክሱ የሚቆዩ የፀረ- ተባይ ኬሚካሎች ሲሆኑ aldrin, Chlorade, DDT, diedrin, endrin, heptachlor,hexachglorobenzene, mirex እና toxaphene ናቸው።ሌላው ሆን ተብለው ከሚመረቱ ለረጅም ግዜ ሳይረክሱ የሚቆዩ ኬሚካሎች ውስጥ የሚመደበው Polychlorinated biphenyls የተባለው ኬሚካል ነው።በሌላ በኩል ኮንቬንሽኑ ሆን ተብለው የማይመረቱ ወይም የሌሎች ኬሚካላዊ ሂደቶች ተረፈ ምርት ውጤት የሆኑ ሁለት የኬሚካል ክፍሎችን በ Annex C ላይ የያዘ ሲሆን እነዚህም Polychlorinated biphenyls እና Furans የሚባሉ ሲሆን

እነዚህም ኬሚካሎች በዋናነት የካንሰር በሽታን የሚያስከትሉ ሲሆን የሚገኙትም ከተለያዩ የኢንዱስትሪ ምርት ሂደቶች ነው፡፡

በስቶክሆልም ኮንቬንሽን አንቀፅ 3 መሰረት endrin እና toxaphene የተባሉ የፀረ-ተባይ ማጥፊያ ኬሚካሎችን ማምረትን ሙሉ በሙሉ የሚያግድ ሲሆን aldrin, dieldrin እና heptachlor የተባሉትን ኬሚካሎች አባል ሀገራት ማምረት እንዲያቆሙ ያስገድዳል፡፡ ሆኖም በመጨረሻ የተጠቀሱትን ሶስት ኬሚካሎች መጠቀም የሚፈልግ ሀገር በጣም ለተወሰኑ ጉዳዮች እና ለተወሰነ ግዜ ለመጠቀም በቅድሚያ ለህዝብ ግልፅ በሆነ መንገድ በመመዝገብ ክልከላው እንዲነሳ ማድረግ እንደሚቻል በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 4 ላይ ተጠቅሷል፡፡በተመሳሳይ chlordane,hexachlorobenzene እና mirex የተባሉ ኬሚካሎችን ማምረትም ሆነ በጥቅም ላይ ማዋል የሚቻለው በጣም ውስን ለሆኑ ጉዳዮች ሲሆን ይህንንም ማድረግ የሚችሉት ክልከላው እንዲነሳላቸው የተመዘገቡ ሀገራት ብቻ ነው፡፡

Polychlorinated biphenyls የተባሉት ኬሚካሎች በአብዛኛው የሚገኙት በኤሌክትሪክ መሳሪያዎች ውስጥ በዋናነትም የኤሌክትሪክ ትራንስፎርመሮች እና ካፓሲተሮች ውስጥ ሲሆንየስቶክሆልም ኮንቬንሽን እነዚህ ኬሚካሎች እንዳይመረቱ አግዷል፡፡ ሆኖም ኮንቬንሽኑ ሀገራት ኬሚካሉን የያዙ ምርቶችን እ.ኤ.አ እስከ 2025 ድረስ መጠቀም እንዲያቆሙ የሚደነግግ ሲሆን ነ በተጨማሪም አባል ሀገራት እነዚህ ኬሚካሎች የያዙ መሳሪያዎችን እንዲለዩ፣ምልክት እንዲያደርጉ እና እንዲያስወግዱ ያስገነዝባል፡፡

በሌላ በኩል የ DDT ምርት ጥቅም ላይ የሚውለው የወባ ትንኝን ለማጥፋት ሲሆን ይህም አለም አቀፉ የጤና ድርጅት ባዘጋጀው መመሪያ መሰረት የአካባቢ ደህንነትን በጠበቀ መልኩ እና ሌሎች አማራጮች በበቂ ሁኔታ በማይገኙበት ወቅት ነው ፡፡በስቶክሆልም ኮንቬንሽን መሰረት አባል ሀገራት DDT ን መጠቀም የሚችሉት በሁለት ውሱን ጉዳዮች ነው፡፡አንደኛው አባል ሀገራት በቅድሚያ በስራ ላይ ለማዋል ያቀዱትን የ DDT መጠን ሪፖርት ማድረግ ያለባቸው ሲሆን በተጨማሪም ኬሚካሉን የሚጠቀሙበትን ሁኔታ እና ለበሽታ ቁጥጥር ያለውን ጠቀሜታ ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ከዚህ በተጨማሪም አባል ሀገራት የ DDT ኬሚካል አጠቃቀምን ለመገደብ የሚያስችል ብሄራዊ የድርጊት መርሀ ግብር ማዘጋጀት እንዳለባቸው እና DDTን የሚተኩ ሌሎች አማራጮችን ለማግኘት የሚስችሉ ምርምሮችን እንዲያካሂዱ ያስገድዳል፡፡ በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ DDT ን መጠቀም ሙሉ በሙሉ የታገደ ሲሆን በአማራጭነትም ዴልታሜትሪን የተባለ ኬሚካል በጥቅም ላይ ውሎ ይገኛል፡፡

2) ሳይታቀዱ የሚመረቱ ለረጅም ግዜ ሳይረክሱ የሚቆዩ ኬሚካሎች

መንግስታት dioxins, furans, hexachlorobenzene እና Polychlorinated biphenyls የተባሉ ከኢንዱስትሪዎች በተረፈ ምርት መልክ የሚገኙ ኬሚካሎችን መጠን ለመቀነስ እንዲሁም ቀስ በቀስ ለማስወገድ የሚያስችሉ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ያስገድዳል፡፡የስቶክሆልም ኮንቬንሽን በስራ ላይ ከዋለ በኃላ በሁለት አመት ግዜ ውስጥ አባል ሀገራት በኮንቬንሽኑ Annex C ላይ የተዘረዘሩት ኬሚካሎችን መለየት፣ባህሪያቸውን ማጥናት እና መመርመር፣የኬሚካሎቹን ወቅታዊ እና የወደፊት ልቀት ሁኔታ መገምገም የሚያስችል ብሄራዊ የአተገባበር ዕቅድ (National Implimentation Plan) ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

3) ተከማችተው የሚገኙ ኬሚካሎች

የስቶክሆልም ኮንቬንሽን አባል ሀገራት ለረጅም ግዜ ሳይረክሱ ተከማችተው የሚገኙ ኬሚካሎች ተለይተው ከአካባቢ ጋር ተስማሚ በሆነ ሁኔታ የሚያዙበትን ስልት እንዲያዘጋጁ ኮንቬንሽኑ አንቀፅ 6 ላይ ተደንግጎ ይገኛል፡፡በመሆኑም እነዚህን ኬሚካሎች የያዙ ቆሻሻዎች በባዝል ኮንቬንሽን ምዕራፍ 11 ላይ እንደተጠቀሰው ከአካባቢ ጋር ተስማሚ በሆነ መንገድ መያዝ፣መሰብሰብ፣መጓጓዝ እንዲሁም መከማቸት ይኖርባቸዋል፡፡በተጨማሪም ኮንቬንሽኑ ለረጅም ግዜ ሳይረክሱ የሚቆዩ ኬሚካሎችን መልሶ መጠቀም እንዲሁም ተገቢ ያልሆነ ድንበር ዘለል ዝውውር የተከለከለ ነው፡፡

በስቶክሆልም ኮንቬንሽን አንቀፅ 7 ላይ እንደተገለፀው አባል ሀገራት ኮንቬንሽኑን ለመተግበር የሚያስችል ብሄራዊ የትግበራ እቅድ ማዘጋጀት ያለባቸው ሲሆን በአንቀፅ 9 ላይ እንደተጠቀሰውም National Focal point መወከል እንደሚኖርባቸው ተግልጿል፡፡በተጨማሪም አባል ሀገራት ለረጅም ግዜ ሳይረክሱ የሚቆዩ ኬሚካሎችን የተመለከቱ የተለያዩ መረጃዎችን ለህዝብ ግልፅ ማድረግ የሚኖርባቸው ሲሆን ከዚህም ጋር ተያያዥ የሆኑ የግንዛቤ ማስጨበጫ እና ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን እንዲያዘጋጁ በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 11 ላይ ተገልጿል፡፡በሌላ በኩል አባል ሀገራት ኮንቬንሽኑን ለመተግበር የወሰዱዋቸውን የተለያዩ እርምጃዎች፣የተወሰዱ እርምጃዎች ውጤማነታቸውን እንዲሁም በተለያዩ ግዜያት ለረጅም ግዜ ሳይረክሱ የሚቆዩ ኬሚካሎችን የተመለከቱ ግብይቶችን የያዘ ዳታ እና በግብይቱ የተሳተፉ ሀገራትን የያዘ ሪፖርት በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 15 መሰረት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ የሚቀርበቀው ሪፖርት በመጀመሪያው የአባል ሀገራቱ ስብሰባ ወቅት እንደተወሰነው በየአምስት አመት አንድ ግዜ የሚቀርብ ይሆናል፡፡

የአባል ሀገራቱ ስብሰባ (COP) የኮንቬንሽኑን አተገባበር የሚከታተል እና የሚገመግም ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱም ሌሎች ተያያዥ የሆኑ አካላትን ማቋቋም እንደሚችል በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 19 ላይ ተጠቅሷል፡፡የአባል ሀገራቱ በመደበኛነት የሚገናኙ ሲሆን የመጀመሪያውም ስብሰባ የተካሄደው እ.አ.አ በግንቦት ወር 2005 ዓ.ም ነበር፡፡ኮንቬንሽኑ የራሱ የሆነ ሴክሬታሪያት ያለው ሲሆን ዋና መቀመጫውንም በስዊትዘርላንድ ዋና ከተማ በጄኔቭ አድርጓል፡፡ሴክሬታሪየቱ ኮንቬንሽኑን ለመተግበር የሚያስችሉ ሁኔታዎችን የሚያመቻች ሲሆን ሌሎች አግባብነት ካላቸው አለም አቀፍ ተቋማት በተለይም ከባዝል ኮንቬንሽን ሴክሬታሪያት ጋር ቅንጅትን ይፈጥራል፡፡

5.4 የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ እና የደህንነተ ሕይወት አለም አቀፍ ስምምነት እና ሀገራዊ ህጎች

5.4.1 የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ

ሁሉም በምድር ላይ የሚኖር ፍጥረት ሁሉ እርስ በእርሱ የተሳሰረ የአንድ ክፍል አካል ነው፡፡ ሁሉም ህይወት ያለው ፍጥረት በምድሪቱ ላይ ከሚገኙ ህይወት ከሌላቸው ፍጥረታት ጋር ማለትም ከከባቢ አየር፣ውቅያኖሶች፣አለቶች፣አፈሮች እንዲሁም ከመሳሰሉት ጋር ተሳስረው ይገኛሉ፡፡ብዝሀ ሕይወት የሚለው ቃል እ.ኤ.አ በ 1992 ዓ.ም የተደነገገው የብዝሀ ህይወት ኮንቬንሽን ላይ የሚከተለው ትርጓሜ ተሰጥቶታል ፡

> “Biological diversity means the variability among living organisms from all sources including, inter alia, teresterial, marine and other aquatic ecosystems and the ecological complexes of which they are part; this includes diversity within species, between species and of ecosystems[20].”

ብዝሀ ህይወት የዘረመል፣የህያውያንና የሥርዐተ ምህዳር ዓይነቶችንና መጠንን ያጠቃልላል፡፡ስለዚህ የብዝሀ ሕየወት ይዘት ሕያዋን እንስሳትን፣እፅዋትንና ጥቃቅን ተህዋስያንን ይጨምራል፡፡የህያዋን እና ህይወት አልባዎች ተስተጋብሮት ደግሞ የህይወት ሂደት ይወስናል፡፡የብዝሀ ህይወት ሀብት የግብርና ስራን በተለያዩ ስነ ምህዳሮች በአጥጋቢ ሁኔታ ለማካሄድ ያስችላል፡፡በሽታን እንደዚሁም ድርቅን ለመቋቋም ችሎታ ያላቸውን ዝርያዎች ያስገኛል፡፡በተለይም የአርሶ አደሩ ማህበረሰብ የሚፈልገውን የሰብል ወይም የቤት እንስሳት ባህርይ በማጎልበት የተሻለ ዝርያን አስገኝቷል፡፡ ብዝሀ ህይወት ለብዙ

[20] የብዝሀ ህይወት ኮንቬንሽን አንቀፅ 2

አይነት ኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃነት፣ህያውያን በካዮችን ጉዳት አልባ ለማድረግ እንደዚሁም የተበከለ አካባቢንም ለማፅዳት ያገለግላሉ።ብዝሀ ህይወት ሀብት የማይታደስ የተፈጥሮ ሀብት ሲሆን በአንድ አጋጣሚ የሚደርስ አደጋ በቀላሉ ለመመለስ የማይቻል ጉዳት ሊያስከትል ይችላል።

5.4.1.1. የብዝሀ ሕይወትን የተመለከቱ አለም አቀፍ መዋቅሮች

የሰው ልጆች የኢንዱስትሪውን አብዮት ሲቀላቀሉ በቁጥር 850 ሚሊየን የነበሩ ሲሆን በወቅቱም መሬት በጣም ሰፊ የሆነ የብዝሀ ህይወት ሽፋን ነበራት።በአሁኑ ወቅት የአለም ህዝብ ቁጥር ከኢንዱስትሪው አብዮት ከነበረው አንጻር በስምንት እጥፍ የጨመረ ሲሆን በዛው መጠን የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ፍጆታውም ጨምሯል።በተለያዩ የሰዎች እንቅስቃሴዎች ምክንያትም በተለያዩ ዝርያዎች እና በአጠቃላይ በስነምህዳር ላይ በታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ጉዳት እየደረሰበት ይገኛል።አብዛኛው የብዝሀ ህይወት ጥፋት በዋናነት እየደረሰ የሚገኘውም ትሮፒካል በሆነው የጫካ አካባቢ ሲሆን ይህም ስፍራ ከ 50 እስከ 90 በመቶ የሚሆኑ የተለዩ ዝርያዎች የሚኖሩበት ስፍራ ሲሆን በተጨማሪም በወንዞች፣ሐይቆች፣ በርሀዎች፣ተራራዎች እንዲሁም በደሴቶች አካባቢ የሚገኝ የብዝሀ ህይወት ሀብት በእጅጉ እየተመናመነ ይገኛል።ምንም እንኳን የዝርያዎች ቁጥር መመናመንና በስነ ምህዳር ላይ እየተከሰተ ያለው መዛባት እንዳለ ሆኖ በኢኮኖሚ እና በማህበራዊ እድገት ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ አሳድሯል።የብዝሀ ህይወት መቀነስ በሌላ በኩል በሰዎች ባህላዊ አኗኗር ላይ ተፅእኖ ያሳድራል።ተክሎች እና እንስሳት በሰዎች ኑሮ ውስጥ ትልቅ ቦታ የሚኖራቸው ሲሆን ይህም በተለያየ መንገድ የሚገለፅ ሲሆን ለምሳሌ በሰንደቅ አላማዎች፣በቅርጻ ቅርጾች እንዲሁም በተለያዩ ምስሎች ላይ የሰዎችን አኗኗር በሚገልፅ መንገድ ተቀምጠው ይገኛሉ።ብዝሀ ህይወት ምግብ፣መድሀኒት እና መጠለያቸውን ለማግኘት በሚኖሩበት አከባቢ ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ጥገኛ ለሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ትልቅ ቦታ ይኖረዋል።በሌላ በኩል አንዳንድ የማህበረሰብ ክፍሎች የመንፈሳዊው አለም በተፈጥሮ ውስጥ ይገኛል ብለው ስለሚያምኑ ለተፈጥሮ ያላቸው ቦታ በእጅጉ ከፍተኛ ነው።በመሆኑም በአካባቢ ላይ እና በብዝሀ ህይወት ላይ የሚደርስ አደጋ በሰዎች የአኗኗር ዘይቤ እና ባህል ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ ያሳድራል።

የተወሰኑ የብዝሀ ህይወት ክፍሎች ላይ ትኩረት ያደረጉ ቀደምት አለም አቀፍ ስምምነቶች የተደነገጉ ሲሆን ለምሳሌ ያህል እ.ኤ.አ በ1972 ዓ.ም የተደነገገው የአለም የባህል እና የተፈጥሮ ሀብት ኮንቬንሽን ሲሆን ኮንቬንሽኑም በአለም አቀፍ ደረጃ ጠቀሜታ ያላቸው የተፈጥሮ እና ጥንታዊ ቦታዎችን ይሸፍናል።ዝርያቸው በመመናመን ላይ የሚገኙ የእንስሳት እና የእፅዋት ዝርያዎችን ንግድ ለመቆጣጠር እ.ኤ.አ በ1973 ዓ.ም የተደነገገው ኮንቬንሽን፣የውሀ አዘል መሬቶችን ለመንከባከብ እ.ኤ.አ በ1979

ዓ.ም የተደነገገው የራምሳር ኮንቬንሽን በዋናነት ሊጠቀሱ የሚችሉ ቀደምት አለም አቀፍ ስምምነቶች ናቸው፡፡ከላይ ከተዘረዘሩት ቀደምት አለም አቀፍ ስምምነቶች በተጨማሪ በተለያዩ ግዜያት በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ትኩረትን ያደረጉ አህጉራዊ ስምምነቶች ተደንግገዋል፡፡

ሆኖም እ.ኤ.አ በ1980 ዎቹ መጨረሻ እና በ1990 ዎቹ ገደማ ከላይ የብዝሀ ህይወት ሀብትን ለመንከባከብ የተዘረዘሩት አለም አቀፍ እና አህጉራዊ ስምምነቶች በአለም አቀፍ ደረጃ የብዝሀ ህይወት ሀብትን ለመንከባከብ እንዳላስቻሉ ተስተውሏል፡፡ለዚህም በዋናነት የሚጠቀሰው ምክንያት ስምምነቶቹ በተወሰኑ የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ማተኮራቸው እና ተፈፃሚነታቸውም በአህጉር ደረጃ መወሰናቸው ነበር ፡፡ በዚህም ምክንያት በመጥፋት ላይ የሚገኘውን የብዝሀ ህይወት በተቀናጀ ሁኔታ ለመታደግ እንዲቻል አለም አቀፍ የሆነ እና ሰፋ ያሉ ጉዳዮችን የያዘ አካሄድ እንደሚያስፈልግ ሀገራት ከስምምነት ላይ ሊደርሱ የቻሉ ሲሆን ይህም የብዝሀ ኮንቬንሽን እንዲደነገግ አስችሏል፡፡

5.4.1.2) የብዝሀ ህይወት ኮንቬንሽን

የብዝሀ ህይወት ኮንቬንሽን (The Convention on Biological Diversity) የወጣው እ.ኤ.አ በ1992 ዓ.ም ሲሆን ለፊርማ የቀረበው በሪዮ ዲጀኔሮ ከተማ በተባበሩት መንግስታት የአካባቢ እና የልማት ስብሰባ ወቅት ነበር፡፡ኢትዮጵያም የብዝሀ ህይወት ኮንቬንሽን ፈራሚ ስትሆን ኮንቬንሽኑ በአዋጅ ቁጥር 98/1986 ፀድቋል፡፡ኮንቬንሽኑ ከመፅደቁ በፊት በተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም አስተባባሪነት ለሶስት አመታት ድርድር ሲደረግበት ቆይቶ ነበረ፡፡በድርድሩም ወቅት ታዳጊ ሀገሮች የታቀደው ስምምነት ቴክኖሎጂ፣ የገንዘብ ድጋፍ እና የገበያ እድል እንዲሁም ዘላቂ የኢኮኖሚ ልማታቸውን ለማራመድ ጥሩ እድል እንደሚፈጥርላቸው ሲያስታውቁ ነበር ፡፡ታዳጊ ሀራቱም በወቅቱ የአእምሮአዊ ንብረትን የሚያስጠብቅ አንድ ተቋም እንዲቋቋም ሀሳብ አቅርበው የነበረ ሲሆን ምክንያታቸውም በሀገራቱ የሚገኙትን የጂኔቲክ ሀብቶች የሚጠቀሙ ሀገራት ተገቢውን ክፍያ እንዲፈፅሙ የሚያስችላቸው ሲሆን በተጨማሪም እነዚህ የጀኔቲክ ሀብቶችን ተጠቅሞ የሚገኘውን የባዮቴክኖሎጂ ውጤቶችንም እንዲጠቀሙ የሚያስችል ሀሳብ ነበር፡፡ነገር ግን በኢንዱስትሪ የበለፀጉት ሀገራት በታዳጊ ሀገራት የቀረበውን እቅድ ሙሉ በሙሉ ያልተቀበሉት ሲሆን ምክንያታቸውም የላላ የአእምሮአዊ ንብረት መብት የባዮቴክኖሎጂ እድገትን ያሰወተጓጉላል እንዲሁም አዳዲስ ግኝቶችን ያዳክማል ብለው ሀሳብ አቅርበው ነበር፡፡በመጨረሻም ኮንቬንሽኑ በአብዛኛው በታዳጊ ሀገሮች የቀረበውን እቅድ አካትቶ የያዘ ቢሆንም በርካታ ስምምነት ያልተደረሰባቸው ጉዳዮችም በኮንቬንሽኑ ውስጥ ሳይካተቱ ቀርተዋል፡፡

ኮንቬንሽኑ በአለም አቀፍ ደረጃ ስነ ምህዳርን መሰረት በማድረግ የብዝሀ ህይወትን በዘላቂ ሁኔታ ለመጠቀም በሚያስችል ሁኔታ የተዘጋጀ ስምምነት ነው።ኮንቬንሽኑ መዋቅራዊ ቅርፅ ያለው ሲሆን በአባል ሀገራት ስብሰባ ድጋፍ እና መሪነት በብሄራዊ ደረጃ የሚተገበሩ ሰፊ ግቦችና አጠቃላይ መርሆችን የያዘ ነው።ኮንቬንሽኑ በአንቀፅ አንድ ላይ ሶስት ግቦችን ያስቀመጠ ሲሆን እነዚህም፡

1. የብዝሀ ህይወት ጥበቃ
2. የብዝሀ ህይወትን በዘላቂነት መጠቀም
3. ከጀኔቲክ ሀብቶች የሚገኙ ጥቅሞችን ፍትሀዊ እና እኩል በሆነ መንገድ መጋራት እንዲሁም አስፈላጊ የቴክኖሎጂ ሽግግር እና የገንዘብ ድጋፍ ማግኘት የሚሉ ናቸው።

ከላይ በቁጥር 2 እና 3 ላይ የተጠቀሱት ግቦች የብዝሀ ህይወት ኮንቬንሽን ከመደንገጉ በፊት የነበሩ ስምምነቶች ውስጥ ያልነበሩ ሲሆን የቀድሞዎቹ ስምምነቶች በዋናነት ትኩረት ያደርጉ የነበረው በብዝሀ ህይወት አጠባበቅ ላይ ብቻ ነበር።በኮንቬንሽኑ ድርድር ወቅት ትልቅ ተፅእኖ ያሳደረው እና በጋላም በኮንቬንሽኑ ውስጥ የተካተተው በብዝሀ ህይወት ሀብት የበለፀጉ ሀገሮች ከጀኔቲክ ሀብቶቹ የሚገኙ ጥቅሞችን ለልማት ስራቸው የሚያውሉበትን መንገድ ያመቻቸ ነው።

5.4.1.2.1. የብዝሀ ህይወት ኮንቬንሽንን የተመለከቱ ተቋማዊ አደረጃጀቶች

በኮንቬንሽኑ ውስጥ የተቀመጡ ግቦችን ለመተግበር የሚያስቹሉ የተለያዩ አካላት ተቋቁመው ይገኛሉ። የኮንቬንሽኑ የአባል ሀገራት ስብሰባ የብዝሀ ህይወት ኮንቬንሽንን የተመለከቱ ውሳኔዎችን የሚሰጥ አካል ሲሆን በተጨማሪም ፖሊሲዎችን ማዘጋጀት፣በአባል ሀገራት ኮንቬንሽኑን ለመተግበር የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎችን ድጋፍ እንደሚያደርግ በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 23 ላይ ተጠቅሶ ይገኛል። በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 25 እንደተገለፀው Subsidiary Body on Scientific Technical and Technical Advice የተባለ ቡድን ለአባል ሀገራቱ ሳይንሳዊ እና ቴክኒካዊ ድጋፍ የሚያደርግ ሲሆን በተለይም የብዝሀ ህይወት ሀብትን በዘላቂነት ለመጠቀም እና ለመጠበቅ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን በመለየት ለአባል ሀገራቱ ስብሰባ ያቀርባል።

የብዝሀ ሕይወት ኮንቬንሽን ሴክሬታሪያት የአስተዳደራዊ ድጋፍ የሚያከናውን ሲሆን ዋና ሀላፊነቱም በመደበኛነት የሚካሄደውን የአባል ሀገራቱን ስብሰባ ዝግጅት ያስተባብራል። ከዚህ በተጨማሪም ከሌሎች አግባብነት ካላቸው አለም አቀፍ አካላት ጋር የተለያየ ቅንጅትን ይፈጥራል።በመጀመሪያው የአባል ሀገራት ስብሰባ ወቅት የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም ለኮንቬንሽኑ የሴክሬታሪያት

አገልግሎት እንዲሰጥ የተወሰነ ሲሆን የሴክሬታሪያቱም ዋና መቀመጫ በካናዳ ሞንትሪያል ከተማ ይገኛል፡፡

5.4.1.2.2. የኮንቬንሽኑ ተከባሪነት፣ተጠያቂነት እና የግጭት አፈታት

በኮንቬንሽኑ ውስጥ የተቀመጡ ግዴታዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 26 መሰረት አባል ሀገራት በመደበኛነት ኮንቬንሽኑን ለመተግበር ያካሄዱዋቸውን ስራዎች እና የኮንቬንሽኑን አላማ ከማሳካት አኳያ ያለውን ውጤታማነት ለአባል ሀገራቱ ስብሰባ ሪፖርት ማድረግ እንዳለባቸው ተጠቅሷል፡፡ለዚህም እንዲረዳ የአባል ሀገራቱ ስብሰባ የሪፖርቱን አቀራረብ ይዘት በሚመለከት ለአባል ሀገራቱ የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፡፡የግጭት አፈታትን በሚመለከት በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 27 ላይ የግጭት አፈታት ሥርዐቶች ተጠቅሰው ይገኛሉ፡፡በዚህም መሰረት በአባል ሀገራት መካከል ግጭት ቢፈጠር ግጭቱ መፈታት ያለበት በድርድር ወይም በ mediation ወይም በግልግል ዳኝነት (arbitration) ወይም ግጭታቸውን ለአለም አቀፉ ፍርድ ቤት (International Court of Justice) ማቅረብ እንዳለባቸው ተገልፃል፡፡በብዝሀ ህይወት ላይ የሚደርስ ጉዳት እና ካሳ በሚመለከት ኮንቬንሽኑ ከመፅደቁ በፊት በነበሩ ድርድሮች ትልቅ ክርክር ሲደረግበት የነበረ ጉዳይ ቢሆንም በድርድሩ ወቅት ስምምነት ላይ ሊደረስበት አልቻለም፡፡በመሆኑም በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 14(2) ላይ እንደተጠቀሰው የአባል ሀገራቱ ስብሰባ በቀጣይ የሚካሄዱ ጥናቶችን መሰረት በማድረግ በብዝሀ ህይወት ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች የተጠያቂነት እና የጉዳት ካሳ ጉዳዮችን እንደሚመረምር ተገልፃል፡፡

5.5.1. ደህንነተ ህይወት (Biosafety)

በአጠቃላይ ለማዳ የሆኑትን ጨምሮ፣የዱር እንስሳትና የዕፅዋት ዝርያዎች ህብት ምትክ የማይገኝለት ፀጋ ነው፡፡መመናመናቸውም የመላው አለም ስጋት ነው፡፡ይህም ስጋት ብዝሀ ሕይወት አለም አቀፍ ውል አጠቃላይ ምላሽ ማግኘት ጀመረ፡፡ የብዝሀ ህይወት አለም አቀፍ ውል የማእቀፍነት ባህርይ ያለው ሲሆን ዝርዝር አፈፃፀሙም በሌሎች አለም አቀፍ ውሎች ይብራራል ተብሎ የተዘጋጀ ነው፡፡ በሌሎች አለም አቀፍ ውሎች እንዲብራሩ ከተመደቡት ብዝሀ ህይወት ነክ ጉዳዮች መካከል የደህንነት ህይወት አንደኛው የነበረ ሲሆን ይህም ለድርድር ሊቀርብ ችሏል፡፡

በድርድሩ ሂደት የዘረ መል ምህንድስናን ማጎልበት (genetic engineering) በሁሉም ሲደገፍ፣የደህንነት ህይወትን የሚመለከተው ጭብጥ ግን አወዛጋቢ ነበር፡፡ምክንያቱም አንዳንዶቹ የበለፀጉት አገሮች በዘረመል ምህንድስና በተዘጋጁ ልውጥ ሕያውያን እንደዚሁም በውጤቶቻቸው ላይ የሚካሄደው

ያልተገደበ ንግድ የበላይነታችንን እንደያዝን ለመቀጠል ያስችለናል ብለው በማሰባቸው የተነሳ ነው[21]። ልውጥ ሕያው (modified organism) ማለት ሰው ሰራሽ የሆነ ወይም ከሌላ ህያው የተወሰደ ይሁን ከቅሪት የተወሰደ ወይም እንደ አዲስ የተቀመመ ባይተዋር ዘረ መል ወይም ሌላ ንጥረ ነገር ስለተከተተበት የዘረመሎች ይዘቱ ወይም የባህርዩ ክስተት የተለወጠበት ሕያው ነው[22]።

የብዝሀ ህይወት ባለሀብትና የልውጥ ህያውያኑ ወይም ውጤቶቻቸው ዋና ገበያ የምንሆነው አዳጊ ሀገሮች ደግሞ በዘረመላዊ ወይም በጂኔቲካዊ ሀብታችን ላይ ስለሚደረግ ምዝበራ እንደዚሁም ከልውጥ ህያውያን አዘገጃጀት፣አያያዝ፣ዝውውር እንደዚሁም አጠቃቀም ሊከተል ስለሚችል ጠንቅ ያለን ንቃት ዳብሯል።በደህንነተ ህይወት ፕሮቶኮል ላይ የተካሄደውን ድርድር አስቸጋሪ ያደረገው ይህ እውነታ ነበር።እነዚህን ተግራሪ ፍላጎቶች በሚያራምዱ ነዋሪዎች መካከል በተደረገው ድርድር የካርታጌና ፕሮቶኮል ተዘጋጅቶ ከ እ.ኤ.አ ከግንቦት 15 2000 ዓ.ም ጀምሮ ለፊርማ ቀርቧል።

5.5.1.1. የደህንነተ ህይወት ፕሮቶኮል አስፈላጊነት

የሰው ህይወት እና በጎ ሁኔታ በህያውያን አልባዎች (non-livingthings) ተፈጥሮአዊ ተስተጋብሮት የተመሰረተ ነው። ለህይወት አስፈላጊ ነው እና በቴክኖሎጂ በመታገዝ በተፈጥሮአዊ ተስተጋብሮት ውስጥ የሰው ልጆች ጣልቃ ይገባሉ።በተስተጋብሮቱ ላይ ጣልቃ መግባታችንም ለውጥ ሊያስከትል ይችላል።የሚከተለው ለውጥም ግን የአካባቢ ሚዛንን እስከ ማዛባት ድረስ ሊሆን አይገባውም።አካባቢ ከተናጋ በህያውያን ላይ አደጋ ሊያስከትል ይችላል።

ቴክኖሎጂ ጠቃሚ ቢሆንም እንኳን አብዛኛውን ግዜ ጠንቅን ያስከትላል።እንዲያውም የአንዳንድ ቴክኖሎጂ ጠንቅ ከፍተኛ ነው።ጠንቁ ተለይቶ ከታወቀና ሊወገድ ከቻለ በቴክኖሎጂው መጠቀም ተገቢ ነው።በዚህ ታሳቢነትም በጠንቀኛ ቴክኖሎጂ ለሚጠቀም ሰው በቁጥጥር ሥርዐት የሚገዛ ልዩ የስራ ፍቃድ ሊሰጠው ይችላል።ምንግዜም ግን ተፈጥሮአዊ ስርአትን በሚያናውጥ ተግባር ላይ እንዲሰማራ የሚፈቀድለት ሰው እንዲበለፅግ ሲል በአካባቢና በህይወት ላይ ጉዳት እንዳያስከትል መገደብ አለበት።ከዘመኑ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ዋነኛው የዘረ መል ምህንድስና ነው።ይህ ጥበብ ዘረመሎችን ከአንድ ዝርያ ወደ ሌላ ዝርያ ለማሸጋገር አስችሏል።የዘረ መል ምህንድስና የህያውያንን ባህርይ

[21] Environmental Protection Authority (EPA) and Institute for Susuatainable Development (ISD),Biosafety and Biodiversity:Writings by Dr Tewolde Berhan Gebre Egziabher and others ,ገፅ 9
[22] የደህንነተ ሕይወት አዋጅ ቁጥር 655/2001፣አንቀፅ 2 (1)

ስለሚካካ የህይወትን መሰረት ሊለውጥ ይችላል። ይህም የባህርይ ለውጥ መሻሻልም ወደ መጥፋትም ሊያመራ ይችላል።

የዘረ መል ምህንድስና ብዙ ጠንቆች ታይተውበታል።ለምሳሌ የአኩሪ አተርን ገንቢ ምግብነት ለማሻሻል ሲባል ብራዚል ናት (Brazil nut) ከሚባል ሌላ አኩሪ ሰብል ዘረመል ተላለፈለት። ከልውጡ አኩሪ አተር የሚገኘው ምግብ ግን ገንቢ መሆኑ ቀርቶ ለከፍተኛ የአለርጂ ችግር የሚያጋልጥ ሆኖ ተገኘ።እንደዚህ አይነት እና ሌሎች ችግሮች በዘረ መል ምህንድስና ጥረቶች ላይ ብዙ ግዜ ተከስተዋል።በሰብል ዝርያዎች ላይ የሚደረገው የዘረ መል ምህንድስና በቂ ቁጥጥር ካልተደረገበት በተለይም የብዙ አዝርእት ብርቅዮ ዘረመሎች ባለቤት በሆነችው በኢትዮጵያ ከፍተኛ ጥፋት ሊያመጣ ይችላል።ስለዚህ በኢትዮጵያ በዘረ መል ምህንድስና ቁጥጥር ንቁ መሆን ይኖርባታል።አንዳንድ ግዜ ጥንቃቄ ቢደረግም እንኳን ጉዳት መከተሉ ላይቀር ይችላል።ስለዚህም ለአጠቃቀሙ ደህንነት ከሚያስፈልገው ስርአት በተጨማሪ ለእንደዚህ አይነቱ ወቅት የሚያገለግል የአደጋ መከላከል የእርምት እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ ነው።የዘረ መል ምህንድስና ደህንነት ማረጋገጫ ስርአት እንዲዘረጋ የብዝሀ ህይወት አለም አቀፍ ውል ይደነግጋል[23]።በዚህ ድንጋጌ መሰረት የካርታጌና የደህንነተ ህይወት ፕሮቶኮል ተዘጋጅቷል።

5.5.1.2. የካርታጌና ፕሮቶኮል አባል ለመሆን መሟላት የሚገባቸው ጉዳዮች

የካርታጌና የደህንነተ ህይወት ፕሮቶኮል አባል ለመሆን የሚፈልግ ሀገር በቅድሚያ የብዝሀ ህይወት አለም አቀፍ ውልን ማፅደቅ አለበት።የብዝሀ ህይወት አለም አቀፍ ውልን ላፀደቀ ሀገር ደግሞ የሚቀጥለው እርምጃ ፕሮቶኮሉን መፈረም ነው።ከዚያም ሀገሩ ህግ በሚፈቅደው መሰረት ማፅደቂያ ማሳወቂያ ሰነድ ለተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሀፊ ፅህፈት ቤት መላክ ነው።ኢትዮጵያ የብዝሀ ህይወት አለም አቀፍ ውልን በአዋጅ ቁጥር 98/1986 አፅድቃለች።ፕሮቶኮሉንም እ.አ.አ ግንቦት 24 ቀን 2000 ዓ.ም ፈርማለች።

5.5.1.3. የካርታጌና ፕሮቶኮሉ አላማ

የካርታሄና የደህንነተ ህይወት ፕሮቶኮል የልውጥ ህያውያንን እንደዚሁም የውጤቶቻቸው ድንበር ዘለል ዝውውርን፣ ተዛማጅ የአገር ውስጥ አያያዝንና ሌሎች ድርጊቶችን ይመለከታል። አላማው ልውጥ ህያውያን ደህንነትን በሚያረጋግጥ ሁኔታ እንዲዘጋጁ ፣እንዲያዙ ፣እንዲቀመጡ፣እንዲዘዋወሩና በጥቅም

[23] የብዝሀ ሕይወት ኮንቬንሽን አንቀፅ 19

ላይ እንዲውሉ ማድረግ ነው፡፡ስለዚህም በስው ጤና እንደዚሁም በማህበረሰቦች በጎ ሁኔታ ላይ የሚከተልን ጠንቅ ለመቋቋም፣ብዝሀ ህይወትን ለመንከባከብ እና ብዝሀ ህይወትን በዘላቂነት ለመጠቀም እንዲያስችል ሆኖ የተቀረፀ ነው፡፡

5.5.1.4. ከፕሮቶኮሉ የሚመነጩ ብሄራዊ ግዴታዎች

ከፕሮቶኮሉ ከሚመነጩት የመንግስት ግዴታዎች ዋና ዋናዎቹ፣ከአገራችን ወደ ውጭ ልውጥ ህያው ሲላክ፣መረጃና በደህንነት ላይ የሚኖረውን የልውጥ ህያዋን ተፅእኖ የገመገመ ጥናት መላኩን፣ደህንነትን የሚያረጋግጥ የአያያዝ፣የአስተሻሸግ እና የዝውውር ሥርአት መዘርጋቱንና መተግበሩን፣ልውጥ ህያው እንደዚሁም ውጤቶቹ ተለይተው እንዲታወቁ መገለጫ ምልክት መለጠፉን፣ለሚመለከታቸው አገሮችና አለም አቀፍ ድረጅቶች ተገቢው መረጃ መላኩን፣በሀገር ውስጥ ልውጥ ህያው ሲዘጋጅ በሌሎች ሀገሮች ላይ ድንበር ዘለል ጉዳት እንዳያስከትል የሚያረጋግጥ ቁጥጥር መደረጉን፣ፕሮቶኮሉን በብሄራዊ ደረጃ ለመተግበር የሚያስችል የፖሊሲ፣የስልት፣የሕግ እና የቴክኒክ ሥርዐት መዘርጋቱን፣እንደዚሁም አባል ሀገራት ስብሰባ ላይ የፕሮቶኮሉን አተገባበር የሚመለከት ዘገባ መቅረቡን፣ማረጋገጥ ናቸው፡፡

5.5.1.5. ከፕሮቶኮሉ የሚገኝ ብሔራዊ ጠቀሜታ

ኢትዮጵያ ከፍተኛ የብዝሀ ሕይወት ሀብት አላት፡፡በተለይም የብዙ አይነት ሥርዐት ምህዳሮች በግዛቷ መኖርና የእርሻ ታሪኳ ረጅም መሆን ለኢትዮጵያ የሰብል ዝርያዎች ብዛትና የአጠቃቀም ስብጥር ምንጭ ናቸው፡፡ ይህም በዓለም ውስጥ በሰብል ዝርያዎች ብዛት ተለይተው ከታወቁ አስራ ሁለት አካባቢዎች አንዷ እንድትሆን አድርጓታል፡፡የብዝሀ ህይወት ሀብታችንን ከውጭ ከሚገቡም ሆነ በሀገር ውስጥ ከሚዘጋጁ ልውጥ ሕያዋን እንደዚሁም ከውጤቶቻቸው ሊከተል ከሚችል ጠንቅ መጠበቅ አስፈላጊ ነው፡፡ለጥበቃው ደግሞ የካርታጌና የደህንነተ ህይወት ፕሮቶኮልን መተግበር አለም አቀፍ መሳሪያ ነው፡፡

5.5.1.6. ከቀዳሚ ግንዛቤ የመነጨ የእሽታ (Advanced Informed Agreement) ሥነ ሥርዓትን ስለመተግበር

አንድ ላኪ ሆን ተብሎና ለመጀመሪያ ግዜ ወደ አካባቢ እንዲለቀቅ የተፈለገውን ማንኛውንም ልውጥ ሕያው ወደ ተቀባዩ ሀገር ከመላኩ በፊት፣ልውጥ ህያው የደህንነት መስፈርቶችን ማሟላቱን ወይም አለማሟላቱን የሚገልፅና በወቅቱ የሚታወቀውን ሁሉ ያካተተ የተሟላ መረጃና ጥናት ያዘጋጃል፡፡ይህንንም መረጃና ጥናት በላኪው ሀገር በሚገኘው ለደህንነተ ህይወት ተጠሪ በሚሆነው

መስሪያ ቤት በኩል ለተቀባዩ ሀገር ይልካል፡፡ተቀባዩ ሀገርም በተላከለት መረጃና ጥናት ላይ ተመስርቶ ልውጥ ህያው ወደ ሀገሩ እንዲገባ ሊፈቅድ ወይም ወደ ሀገሩ እንዳይገባ ሊከለክል ይችላል፡፡ውሳኔውንም ለላኪው ሀገር የደህንነተ ሕይወት ተጠሪ መስሪያ ቤት ያሳውቃል፡፡

በልውጥ ሕያው የሚካሄድ የገቢና የወጪ ንግድ የሚመራበት ይህ ሥርአት ከቀዳሚ ግንዛቤ የመነጨ የእሽታ ሥነ ሥርዐት ይባላል፡፡ከቀዳሚ ግንዛቤ የመነጨ የእሽታ ሥርዐት እንዲተገበር ደግሞ የካርታጌና የደህንነተ ህይወት ፕሮቶኮል ያዛል[24]፡፡የሥነ ሥርዐቱ ዋና አላማ አንድ ሀገር ለመጀመሪያ ግዜ ወደ አካባቢ የሚለቀቅ ልውጥ ህያው ወደ አገሩ እንዲገባ ፈቃድን ወይም ክልከላውን ከማሳወቁ በፊት፣ከልውጥ ህያው ሊከተል የሚችለውን ጠንቅ በብቃት እንዲገመግም እና ከቀዳሚ ግንዛቤ የመነጨ የእሽታ ወይም የክልከላ ውሳኔውን እንዲያደርግ ነው፡፡ በመዝራት ወይም ከአፈር በመደባለቅ ወይም በመሰል መንገድ ልውጥ ህያው ሆነ ተብሎም ሆነ ሳይባልም ወደ አካባቢ ሊለቀቅ ይችላል፡፡ ሆነ ተብሎ ወደ አካባቢ የሚለቀቅ ልውጥ ህያው ወደ አገር እንዲገባ ከመፈቀዱ በፊት የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ ላኪው ያቀርባል፡፡አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ተጨማሪ መረጃ ወይም ግምገማ እንዲያቀርብ ይጠየቃል፡፡

በመጨረሻም ወደ አካባቢ የሚለቀቀው ልውጥ ህያው ሊሟላለት የሚገባው ቅድመ ሁኔታ ተዘርዝሮለት ወይም ያለ ቅድመ ሁኔታ ወደ አገር እንዲገባ ይፈቀዳል ወይም እንዳይገባ ይከለከላል፡፡ስለዚህም ከቀዳሚ ግንዛቤ የመነጨ የእሽታ ሥነ ሥርዐት መርህን በመከተል ሆነ ተብሎና ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አካባቢ የሚለቀቅ ልውጥ ህያው ወደ አገራችን እንዲገባ ወይም እንዳይገባ ለመወሰን የሚያስችለንን የተሟላ እውቀት እንድናገኝ ያስችለናል፡፡

5.5.1.7. መረጃ ስለማግኘት

በቀጥታ ለምግብ፣ለመኖ ወይም ለማምረት የሚውሉ ልውጥ ሕያውያን ወይም ውጤቶቻቸው ወደ አገር እንዲገቡ ለመፍቀድ ወይም ለመከልከል የተሟላ መረጃ አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህ እንዲያገለግል የደህንነተ ህይወት መረጃ የማሰራጫ ማእከል ተቋቁሟል[25]፡፡ለሸቀጥ የሚውሉ ልውጥ ሕያዋን ውይም ውጤቶቻቸው በላኪው ሀገር ለገበያ እንዲቀርቡ የተፈቀደ፣ወይም እንዳይቀርቡ የተከለከለ መሆኑንና በሰው ጤና እንደዚሁም በብዝሀ ሕወት ደህንነት ላይም ጉዳት የሚያደርሱ ወይም የማያደርሱ መሆናቸውን የሚገልፁ የተለያዩ መረጃዎችን ከማእከሉ ማግኘት ይቻላል፡፡

[24] የካርታጌና ፕሮቶኮል አንቀፅ 7
[25] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 20

5.5.1.8. የቀዳሚ ጥንቃቄ መርህን ስለ መተግበር

አንድ ጠንቅ የማይከሰት ቢመስልም እንኳ ትንሽም ቢሆን ጥርጣሬ ካለ የተጠረጠረው ጠንቅ እንደማይከሰት እስከሚረጋገጥ ድረስ የጥንቃቄ እርምጃን መውሰዱ ተገቢ ነው፤የሚለው አስተሳሰብ ቀዳሚ ጥንቃቄ ይባላል[26]።ይህ መርህ የካርታጌና ፕሮቶኮል መሰረት ነው።ከልውጥ ህያውያን ወይም ከውጤቶቻቸው ሊከተል በሚችል ጠንቅ ተጠቂ ላለመሆን ብቃት ባለው ስልት መከላከል ያሻል። ይህም እንዲሆን ከልውጥ ህያው ወይም ከውጤቶቹ በብዝሀ ህይወት ደህንነት እንደዚሁም በሰው በጎ ሁኔታ ላይ ሊከተል በሚችል ጠንቅ ላይ ጥናት ማካሄድ ተገቢ ነው።ጥናት ተደርጎም እንኳን ሊከተል በሚችል ጠንቅ ላይ የተሟላ መረጃ ላይገኝ ይችላል።ምክንያቱም ከልውጥ ሕያው እንደዚሁም ከውጤቶቹ የሚከተል ጠንቅ በውል የማይታወቅ፣አጠራጣሪና ክስተቱም ውስብስብ ሊሆን በመቻሉ ነው።እንዲያውም ሊከተል የሚችለው ለውጥ ላይታወቅ፣ወይም ጠንቁ የተከተለ ወይም ያልተከተለ ለመሆኑ ከስምምነት ላይደረስ ይችላል።ወይንም ደግሞ ጠንቅ ስለመከተሉ ወይንም ስላለመከተሉ የሚታወቀው ዘግይቶ ወይም ጉዳቱ ከተንሰራፋ ቦሀላ ሊሆን ይችላል።

አንድን ጠንቅ እንደማይከተል ለማረጋገጥ የማይቻልበት ሁኔታ የቀዳሚ ጥንቃቄ መርሁ የሚጠቁመው እርምጃ መወሰድ እንዳለበት የካርታጌና የደህንነተ ህይወት ፕሮቶኮል ይደነግጋል።የቀዳሚ ጥንቃቄ መርህ የልማትን ዘላቂነት ለማረጋገጥ ስለሚያግዘ በአገራችንም ሆነ በአለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት አግኝቷል።በቅድመ ጥንቃቄ መርህ ለመገዛት እንዲቻል ልውጥ ህያውያን እንዲሁም ውጤቶቻቸው የደህንነት መስፈርቶችን ስለማሟላታቸው በቅድሚያ የማረጋገጥ ሀላፊነትን ጥሏል።ይህም ሀላፊነት ልውጥ ህያዋንን ወይም ውጤቶቻቸውን ከውጭ ለምናስገባ እና አቅማችን ላልጎለበተ አገሮች ጠቃሚ ነው።የቀዳሚ ጥንቃቄ መርህ በካርታጌና የደህንነተ ህይወት ፕሮቶኮል መካተት ፣መረጃ ባይሟላ ጥንቃቄ እንዲወሰድ ስለሚያደርግ በአቅመ ደካማነታቸው እንዳይጎዱ የሚያደርግ አዳጊ ሀገሮች ከድርድሩ ያገኙት ድል ነው።ይህ መርህ መረጃ ከማግኘት መብት ጋር ሲጣመር አገሮች ደካማም ቢሆኑ ፍላጎቱ እስካላቸው ድረስ የተሟላ መረጃ እንዲያገኙና ተገቢ ውሳኔ እንዲያደርጉ የሚያስችል በቂ ሁኔታን ይሰጣል።

[26] ዝኒ ከማሁ አንቀፅ 7

5.5.1.9. የሰውን ጤና ስለመጠበቅ

ልውጥ ህያዋን ወደ አገራችን እንዲገቡ ወይም በአገራችን በኩል እንዲተላለፉ ከመፍቀዳችን በፊት፣በአያያዝ፣በዝውውር ወይም በአጠቃቀም ወቅት በህዝብ ጤና ወይም በብዝሀ ህይወተ ደህንነት ላይ ስለሚያስከትሉት ጠንቅ መረጃ የማግኘትና መረጃውን በመተንተን የተዕእኖ ግምገማ ማካሄድ ያስፈልጋል፡፡ በአያያዝ፣በዝውውር ወይም በአጠቃቀም ወቅት ከልውጥ ህያው ወይም ከውጤቶቹ በሰው ጤና ላይ ሊከሰት የሚችለውን ጠንቅ ለመቋቋም ምን ማድረግ እነደሚገባ የልውጥ ህያው አምራች ከሁሉም በተሻለ ያውቃል፡፡ ያንን የሚያውቀውን ጠንቅ ለመቋቋምም ሆነ ተብሎ የዳበረ አቅም ሊኖረው የሚችለውም እርሱ ነው፡፡ከልውጥ ህያው ሊከተል የሚችለውን ጠንቅ የመከላከል ቀዳሚ ሀላፊነት በአምራች እንደዚሁም መረጃውን ከአምራቹ ለማግኘት በሚችለው በላኪው ላይ የሆነውም ለዚሁ ነው፡፡

በዚህም መሰረት ላኪው ግለሰብ ወይም ድረጅት በዝውውር እና በአጠቃቀም ወቅት ከልውጥ ህያው ወይም ከውጤቶቹ በሰው ጤና ሊከተል የሚችለውን የደህንነት ጠንቅ በሚመለከት በመረጃ የተደገፈ ጥናት ያዘጋጃል፡፡የመረጃውና በመረጃው የተመሰረተው የተዕእኖ ግምገማ ሰነዶች ከልውጥ ህያው እንደዚሁም ከውጤቶቹም በሰው ጤና ላይ ሊከተል የሚችለውን ጠንቅ ለመገንዘብ ፣ጠንቁ እንዳይከተል መወሰድ ያለበት እርምጃ እና ቢከተል ደግሞ የአደጋ መቋቋሚያ ስልትን ለመውሰድ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው፡፡ይህም ከልውጥ ህያው እንደዚሁም ከውጤቶቹም በአያያዝ፣በዝውውር እና በአጠቃቀም ወቅት በሰው ጤና ላይ ሊከሰት የሚችለውን የደህንነት ችግር ገና ወደ አገር ሳይገባ ቀድሞ በማወቅ ተገቢውን ውሳኔ ለመውሰድ ዝግጅት ለማድረግ ያስችላል፡፡

5.5.1.10. የሰብልና የሌሎች ህያውያን ብዝሀ ህይወትን ስለመጠበቅ

አንድ ልውጥ ህያው እንደማንም ሌላ ህያው የመራባትና ከታቀደለት ተቀባይ አካባቢ ውጭ የመስፋፋት ባህርይ አለው፡፡ስለሆነም ከውጭ እንደመጣ እንግዳ አረም አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡እንዲያውም ሌሎችን ህያዋንን ሊጎዳ የሚችል መርዝ፣ በሽታ፣ወዘተ በማምጣት ከአረምም ከተባይም እጅግ የከፋ ሊሆን ይችላል፡፡

ልውጥ አረምን ወይም ልውጥ ተባይን ለማጥፋት በልዩ መከላከያ መጠቀም አስፈላጊ ይሆናል፡፡ስለዚህ የልውጥ ህያውያን መዛመት መከላከያውን ለሚያመርቱና በመከላከያው ለሚነግዱ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ገበያን ያመቻቻል፡፡ለአርሶ አደሩ ደግሞ ቋሚ ወጪ ይሆናል፡፡እንዲያውም እስከአሁን ከተሞከሩት ልውጥ የሰብል ዝርያዎች መካከል ብዙዎች በማሳ ላይ እያሉም በተገቢ እንዲያድጉ

ከተወሰነ ኩባንያ የሚገዛ ልዩ ኬሚካል ያስፈልጋቸዋል፡፡ይህም ገበሬውን አማራጭ የሌለው ቅምጥ የኩባንያው የኬሚካል መሸጫ የደርገዋል፡፡

ልውጥ አረም ከዱር እፅዋት ጋር ተቀላቅሎ ቢያድግ የአካባቢውን ዝርያዎች በማሸነፍ ብዝሀ ህይወትን ሊያጎሳቁል ይችላል፡፡በምግብ ሽሚያም ሆነ በመራባት ችሎታው ከሌሎች ካልተነካኩት ዕፅዋት ሊያይል ይችላል፡፡በአጠቃላይ ልውጥ አረምን ወይም ተባይን በተለመደው የአስተራረስና የከብት ርቢ መቋቋም ሊያቅት ይችላል፡፡በዚህም ምክንያት የአራሹ እንደዚሁ የከብት አርቢው ማህበረሰብ የአኗኗር ሁኔታና ዘይቤ ሊናጋ ይችላል፡፡ስለዚህ የአርሶ አደሩ ሰብል እንደዚሁም ሌላው የብዝሀ ህይወት ሀብት በልውጥ ተባይ እንዳይጠፋ ለማድረግ በልውጥ ህያው እንደዚሁም በውጤቶቹ የገቢ ንግድ ላይ ቁጥጥር መደረግ አለበት፡፡

5.5.1.11. ጉዳትን ስለመካስ

ልውጥ ህያው እንደዚሁም ውጤቶቹ ወዲያውኑ ወይንም ደግሞ ቆይቶ የሚታወቅ ጉዳት ሊያስከትሉ ይችላል፡፡ስለዚህም ከልውጥ ህያዋን እንደዚሁም ከውጤቶቻቸው ከሚከተል ጠንቅ ሊደርስ የሚችለው ጉዳት ኃላፊውን መለየትና የደረሰውንም ጉዳት እንዲያስተካክል ወይም እንዲክስ ማድረግ ይገባል፡፡ከጠንቀኛ ሥራ ለሚከተል ጉዳት ኃላፊ የሚሆነው የስራው ባለቤት እንደሆነ በርካታ ብሄራዊ ህጎች ደንግገዋል፡፡

በልውጥ ህያዋን ወይም በውጤቶቻቸው ድንበር ዘለል ዝውውር ምክንያት የሚከተለውን ጉዳት ለማስተካከል የሚየስችል የኃላፊነት እና የካሳ አፈፃፀም ሥርአት መዘርጋትን በሚመለከት ድርድር እንዲካሄድ ፕሮቶኮሉ ይደነግጋል፡፡የሚካሄደው ድርድር በልውጥ ህያዋን ወይም በውጤቶቻቸው ድንበር ዘለል ዝውውር ምክንያት ለሚደርስ ጉዳት የኃላፊነት አይነትንና መጠንን ስለመወሰን፣እንደዚሁም ጉዳትን የመወሰንና ኃላፊነትን የመወጣት ሥርአትን ስለመዘርጋት ይሆናል፡፡

5.6. በርሀማነት፣የተራራዎች፣የጫካዎች እና የዋልታዎች ስነ-ምህዳር አያያዝ እና ተያያዥ ህጎች

5.6.1. በርሀማነት

በሁሉም በአለማችን ላይ በሚገኙ ሀገራት መሬት ትልቅ ሀብት ሲሆን በምድር ላይ ለሚኖሩ ፍጥረታትም የህልውናቸው መሰረት ነው። በመሬት ላይ የሚደርስ ማንኛውም አይነት ጉዳት ኢኮኖሚያዊ ጉዳት ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ በመሬት ህልውና ላይም ትልቅ ጉዳት ያስከትላል።ለምሳሌ ደረቃማ በሆኑ አካባቢዎች የሚገኝ አፈር በከፍተኛ ሁኔታ ለአፈር መሸርሸር የተጋለጠ ሲሆን ለዚህም በዋናነት እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው በአፈር ውስጥ የሚገኘው እርጥበት እና ብስባሾች አነስተኛ መሆናቸው ነው።በደረቃማ በሆኑ ቦታዎች አፈሮች ከሺህ እስከ ሚሊዮን የሚቆጠር አመታትን ለመፈጠር የሚወስዱ ሲሆን አንድ ሴንቲሜትር ከፍታ ያለው አፈር ከ ሀያ እስከ ሺህ አመታት ግዜን ለመፈጠር ይወስዳል።ሆኖም ረጅም ግዜን ወስዶ የተፈጠረው አፈር በሰከንድ በሚቆጠር ሰአት ውስጥ በውሀ እና በንፋስ ተጠርጎ ይጠፋል።

በረሀማነት በዋናነት የሚከሰተው በተፈጥሮ ለጉዳት የተጋለጡ የመሬት ክፍሎች በተለይም ደረቅ የሆኑ መሬቶችን ከመጠን በላይ በመጠቀም ወይም ተገቢ ባልሆነ የመሬት አያያዝ ምክንያት ነው።የመሬት መሳሳቀል በሁሉም የአለም ክፍል የሚታይ ችግር ሲሆን በአብዛኛው የሚከሰተው ደካማ ከሆነ የመሬት አጠቃቀም ነው።የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም ባካሄደው ጥናት በአለማችን ላይ 51 ሚሊዮን ስኩዌር ኪሎ ሜትር የሚሆነው የመሬት ክፍል ለበረሀማነት የተጋለጠ ሲሆን ይህም የአለማችንን አንድ አምስተኛ ህዝብ የያዘ ነው።በአለማችን ላይ 110 የሚሆኑ ሀገራት ለበረሀማነት የተጋለጡ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 80 ዎቹ በታዳጊ ሀገራት የሚገኙ ሲሆን በአፍሪካ 36 የሚሆኑ ሀገራት በበረሀማነት በእጅጉ እየተጠቁ ይገኛሉ።በአጠቃላይ በአለማችን ላይ 250 ሚሊዮን የሚሆን ህዝብ ከበረሀማነት ጋር በተያያዘ በሚከሰቱ ችግሮች እየተጠቃ ይገኛል።

በረሀማነት የፊዚካለዊ፣ ኬሚካላዊ፣ ስነ - ህይወታዊ፣ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊ ድምር ውህድ ውጤት ነው[27]።ለበረሀማነት መከሰት በዋናነት የሚጠቀሱት ምክንያቶች የደን መመንጠር፣የእርሻ ስራን ለማስፋፋት የሚካሄዱ ምንጣሮዎች፣ ከልክ ያለፈ የግጦሽ አጠቃቀም፣ከመጠን ያለፈ የኬሚካል ማዳበሪያዎች አጠቃቀም፣ተገቢ ቁጥጥር የማይደረግበት የቆሻሻ አወጋገድ እና ደካማ የሆነ የመሬት

[27] United Nations Convention To Comabat Desertification in Countries Experiencing Serious Drought and /or Desertification,particularly in Africa

አጠቃቀም እቅድ ናቸው፡፡እነዚህ በተለያዩ የሰዎች እንቅስቃሴዎች ምክንያት የሚከሰቱ ችግሮች የአፈርን ለምነት የሚያዳክሙ ሲሆን ይህም የእፅዋት ሽፋንን በመቀነስ መሬት በዝናብ እና በንፋስ እንዲሸረሸር እንዲሁም የመሬት መንሸራተት እንዲከሰት ያደርጋል፡፡በሌላ በኩል በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚከሰት ድርቅ እና ጎርፍ የመሬት መሸርሸርን በእጅጉ የሚያፋጥን ሲሆን ይህም የተክሎች በሽታ እና የሰብል ተባይ ወረረሽኝ ያስከትላል፡፡

በአፍሪካ እ.ኤ.አ ከ1950 ዎቹ ጀምሮ ወደ 500 ሚሊዮን ሄክታር የሚሆን መሬት ለበረሀማነት የተጋለጠ ሲሆን ከዚህም ውስጥ 65 በመቶ የሚሆነው የእርሻ መሬት ነው፡፡በላቲን አሜሪካ 300 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በአፈር መሸርሸር፣በደን መመንጠር ምክንያት ተጎሳቅሎ ይገኛል፡፡በአውሮፓ 115 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በውሀ መሸርሸር ምክንያት የተጎዳ ሲሆን በኤሽያ 4.3 ቢሊዮን ሄክታር ከሚሆነው አጠቃላይ የመሬት ክፍል 1.7 ቢሊዮን የሚሆነው የመሬት ክፍል ደረቅ መሬት ነው፡፡

5.6.2. በረሀማነትን የተመለከቱ አለም አቀፍ ህጎች

ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች መነሻ በማድረግ በተለይም በአፍሪካ አህጉር ያለውን ችግር ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አለም አቀፉ ህብረተሰብ በረሀማነትን ለመከላከል የሚያስችሉ እና ድርቅ የሚያስከትለውን ችግር ለመቀነስ የሚያስችሉ ህጎችን ለመደንገግ የሚያስችል መሰረት እንዲጣል አድርገዋል፡፡የመሬት መጎሳቆል እና የበረሃማነት ችግርን ለመካለከል የሚያስችሉ የተለያዩ ህጎች በተለያየ ግዜ የወጡ ቢሆንም (ለምሳሌ የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ መዋቅራዊ ስምምነት) በረሀማነትን እና የመሬት መጎሳቆል ላይ በተለየ ሁኔታ ትኩረት አድርጎ እ.ኤ.አ በሐምሌ 17 ቀን 1994 ዓ.ም የወጣው ከባድ ድርቅ እና/ወይም በረሀማነት በሚያጠቃቸው አገሮች በተለይም በአፍሪካ ውስጥ በረሀማነትን የመከላከል አለም አቀፍ ኮንቬንሽን ሲሆን በስራ ላይ የዋለው እ.ኤ.አ ታህሳስ 26 ቀን 1996 ዓ.ም ነው፡፡ኮንቬንሽኑ ስድስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን በተጨማሪም በአህጉር ደረጃ የሚተገበሩ (በአፍሪካ፣ኤሽያ፣ላቲን አሜሪካ እና ካሪብያን፣ሰሜን ሜዲትራንያ፣ እና መካከለኛው እና ምስራቅ አውሮፓ) ፅዝሎችን (Annex) አሉት፡፡ኮንቬንሽኑ እ.ኤ.አ ከህዳር 2005 ዓ.ም ጀምሮ 191 አባል ሀገራት የያዘ ሲሆን ኢትዮጵያም የኮንቬንሽኑ የፊረመች ሲሆን የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ 12 ቀን 1989 ዓ.ም አፅድቆታል፡፡

የኮንቬንሽኑ አላማ በስምምነቱ በአንቀፅ ሁለት ላይ የተገለፀ ሲሆን አላማውም ከባድ ድርቅ እና/ ወይም በረሀማነት በሚያጠቃቸው አገሮች በተለይም በአፍሪካ ውስጥ በረሀማነትን መከላከል ሲሆን ይህንንም ለማሳካት አለም አቀፍ ትብብር እንደሚያስፈልግ ተገልጿል፡፡ ኮንቬንሽኑ በአባል ሀገራት ላይ ሶስት

አይነት ግዴታዎችን የሚጥል ሲሆን እነዚህም 1) አጠቃላይ እና የተለዩ የአባል ሀገራት ግዴታዎች 2) በከባድ ድርቅ እና/ወይም በረሀማነት የተጠቁ ሀገራት ግዴታዎች እና 3) ኮንቬንሽኑን የፈረሙ ታዳጊ ሀገራት ግዴታዎች ናቸው፡፡በተጨማሪም በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 4(መ) እና (ሰ) መሰረት አባል ሀገራት እርስ በእርሳቸው በአህጉር፣በክፍለ አህጉር እና በአለም አቀፍ ደረጃ ትብብሮችን መፍጠር እንዳለባቸው የተገለፀ ሲሆን ይህም በረሀማነትን እና ድርቅን ለመከላከል የሚያስችሉ በስራ ላይ የሚገኙ ባይላተራል እና መልቲላተራል የገንዘብ ተቋሞችን ድጋፍ ለማግኘት ያስችላቸዋል፡፡

በረሀማነትን ለመከላከል የወጣው ኮንቬንሽን በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት አንዳንድ ሀገራት ቀደም ብለው ችግሩን ለመፍታት የሚያስችላቸውን እርምጃዎች ሲወስዱ ቆይተዋል፡፡ለምሳሌ በአፍሪካ አህጉር የሚገኙ ሀገራት እ.ኤ.አ በ1985 ዓ.ም በተካሄደው የሚንስትሮች የአካባቢ ስብሰባ ወቅት የበረሀማነት ችግርን ለመፍታት የሚያስችል የካይሮ የድርጊት ፕሮግራም አዘጋጅተው ነበር፡፡ይህንንም ከግምት ውስጥ በማስገባት በረሀማነትን ለመከላከል በተደነገገው ኮንቬንሽን በአንቀፅ 4(1) ላይ እንደተጠቀሰው አባል ሀገራት በረሀማነትን እና ድርቅን ለመከላከል ኮንቬንሽኑ ከመደንገጉ በፊት እና ከተደነገገ በኃላ በሁለት ወይም ከሁለት በላይ በሆኑ ሀገሮች የተደረጉ ስምምነቶች በቀጣይ መተግበር እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡በተጨማሪም ኮንቬንሽኑ ሌሎች በረሀማነት ላይ ትኩረት የሚያደርጉ አለም አቀፍ ስምምነቶች እንደሚገኙ እውቅና የሚሰጥ ሲሆን (ምሳሌ የብዝሀ ህይወት ኮንቬንሽን እና የተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ መዋቅራዊ ኮንቬንሽን) አባል ሀገራት እነዚህን ስምምነቶች ለመተግበር ግዴታ የገቡ እንደሆነ ተደጋጋሚ ስራዎችን ለመስራት እንዲቻል ከኮንቬንሽኑ ጋር በተቀናጀ ሁኔታ መተግበር እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡

በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 9 እና10 መሰረት በድርቅ እና/ወይም በበረሀማነት የተጠቁ አባል ሀገራት በረሀማነትን ለመከላከል የሚያስችላቸውን ብሄራዊ የድርጊት ፕሮግራም ማዘጋጀት እንዳለባቸው ተደንግጓል፡፡ ብሄራዊ የድርጊት ፕሮግራሙ የአባል ሀገራቱን ሀገራዊ ሁኔታ ባገናዘበ ሁኔታ መዘጋጀት ያለበት ሲሆን በፕሮግረሙ ውስጥ መካተት ያለባቸው ጉዳዮችም በኮንቬንሽኑ አንቀፅ 10 ላይ ተዘርዝረው ይገኛሉ፡፡በዚህም መሰረት ብሄራዊ የድርጊት መርሀ ግብሩ የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ ይኖርበታል፡

- ለበረሀማነት እና ድርቅ መከሰት ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች፣
- ችግሮቹን ለመከላከል መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች፣
- ድርቅና በረሀማነትን ለመከላከል በመንግስት፣በህብረተሰብ እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብቶችን የሚጠቀሙ አካላት መጫወት ያለባቸው ሚና እና

- በርሀማነትን ለመከላከል የሚያስችል በቅርብ የሚገኝ ሀብት እንዲሁም ችግሩን ለመፍታት የሚያስፈልግ ነገር ግን በቅርብ የማይገኙ ሀብቶችን አካትቶ መያዝ እንዳለበት ተገልጧል።

5.6.3. የተራራዎች ስነ ምህዳር

ዌብሰተር የተባለው የእንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት ተራራ የሚለውን ቃል የመሬት አካል ሆኖ በዙሪያው ከሚገኙት አካላት በመጠን ከፍ ብሎ የሚገኝ ሲሆን መጠኑም ከኮረብታ በላይ የሆነ በማለት ይተረጉመዋል።ተራራዎች በሁሉም የአለማችን ክፍል የሚገኙ ሲሆን የመሬትን 26 በመቶ ይሸፍናሉ።ተራራዎች ስነምህዳራዊ አፈጣጠራቸው ለሰው ልጆች በርካታ ጥቅምን የሚያስገኙ ናቸው። ለምሳሌ አብዛኛዎቹ ተራራዎች የሚፈጠሩት የእሳተ ገሞራ ፍንዳታን ተከትሎ ሲሆን በዚህም ወቅት የቀለጠ አለት ወደ መሬት የላይኛው ሽፋን የሚፈስ ሲሆን ይህም በግዜ ሂደት በጣም ለም ወደሆነ አፈርነት ይቀየራል።በእሳተ ገሞራ አማካኝነት የሚፈጠር አፈር ለብዙ እፅዋቶች እና ዛፎች መፈጠር ትልቅ እድል የሚፈጥር ሲሆን ይህም የተለያዩ የዱር እንስሳት እና እፅዋቶች መገኛ ስፍራ ይሆናል።

ተራራዎች ዋና የውሀ መገኛ ምንጮችም ናቸው። አየር ከተራራዎች በላይ ከፍ ብሎ ከወጣ ቦሀላ የሚቀዘቅዝ ሲሆን ይህም በዝናብ መልክ ተመልሶ ወደ ምድር ይዘንባል በዚህም ምክንያት ተራራማ ቦታዎች ዝቅተኛ ከሆኑ ቦታዎች የተሻለ የዝናብ መጠን የሚኖራቸው ሲሆን አብዛኛዎቹ ወንዞች በተለይም ድንበር ተሻጋሪ የሆኑት መነሻቸው ተራራማ ቦታዎች ናቸው። ለምሳሌ ከሂማልያ ተራራ የሚመነጨው ኢንደስ የተባለው ወንዝ በፓኪስታን ለሚኖሩ 130 ሚሊየን ለሚሆኑ ህዝቦች የሩዝ ምርት ለማምረት ለመስኖ አገልግሎት ይጠቀሙበታል። ወንዙ ህንድ እና ባንግላዲሽንም አቋርጦ የሚያልፍ ሲሆን ይህ ተፋሰስም በአለማችን ላይ ትልቁ የመስኖ ልማት ይካሄድበታል።በመካከለኛው አሜሪካ የሚገኘው የአታካማ በረሀ አካባቢ ኢኮኖሚ አንደስ ከተባለው ተራራ በሚመነጩ ትናንሽ ምንጮች ላይ የተመሰረተ ነው።በአውሮፓ የአልፕስ ተራራ በአውሮፓ ለሚገኙ ራይን፣ሮን፣ዳንዩብ ለተባሉ ዋና ዋና ወንዞች በምንጭነት ያገለግላል።በምስራቅ አፍሪካ ማራ የተባለው ወንዝ በሰሜን ታንዛንያ ብቸኛው የውሀ ምንጭ ሲሆን ሰረንጌቲ በተባለው ፓርክ ለሚኖሩ በሚሊየን ለሚቆጠሩ የዱር አራዊት ዝርያዎች ህልውና መሰረት ሲሆን የሚመነጨውም ከኬንያ የስምጥ ሸለቆ ተራሮች ነው።በመሆኑም በአለማችን ላይ ሀምሳ በመቶ የሚሆነው ህዝብ የምግብ ሰብሎችን ለማምረት፣ኤሌክትሪክ ለማመንጨት እና ለንፁህ መጠጥ ውሀ ፍጆታ የሚገኘው ከተራሮች ነው።

ተራሮች ከአቀማመጣቸው እና ከተፈጥሮ መስህብነታቸው አንፃር ከፍተኛ የቱሪስት መዳረሻ ስፍራ ናቸው።በተጨማሪም ተራሮች የብዙ ማእድኖች መገኛ ሲሆኑ ለምሳሌ በአሜሪካን ሀገር የሚገኘው

የሮኪ ተራራ የብር፣ካድሚየም፣ዚንክ እና ሌሎች ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ማዕድናት መገኛ ነው።በሌላ በኩል ተራሮች አብዛኛው የአለም ህዝብ የሚኖርባቸው ስፍራዎች ሲሆኑ በተለይም ተራራማ በሆኑ ሀገራት እንደ ኪርጊስታን፣ካዛኪስታን፣ታጃኪስታን ከስልሳ ሚሊዮን በላይ የሚሆን ህዝብ ይኖርባቸዋል።

በተራራዎች ስነ ምህዳር የተለያዩ አይነት ጉዳቶች የሚደርሱ ሲሆን ለዚህም በዋናነት እንደምክንያት የሚጠቀሰው ተዳፋት መሆናቸው እና ከባህር ጠለል በከፍተኛ ስፍራ ላይ መገኘታቸው ነው።የተለያዩ የሰዎች እንቅስቃሴዎች የተራራ ስፍራዎች ለስነ ምህዳር የሚያበረክቱትን ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዲዳከም ያደረገ ሲሆን በተለይም የህዝብ ቁጥር መጨመር እና ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተዳምሮ የእርሻ ቦታዎች ወደ ተራራማ ቦታዎች እንዲሸሹ እያደረገ ነው።በዚህም ምክንያት በተራራ አካባቢዎች የሚገኙ ደኖች እየተመነጠሩ ሲሆን ይህም የአፈር መሸርሸርን፣ጎርፍን፣የውሀ ፍሰት መጠን ለውጥ እና ለእርሻ ስራ በሚውሉ ኬሚካሎች የወንዞች መበከል አስከትሏል።በተራራ አካባቢዎችም ከፍተኛ የማእድን ማውጣት ስራ ስለሚካሄድ ይህም ወንዞችን (ድንበር ተሻጋሪ ወንዞችን ጨምሮ) ለከፍተኛ ብክለት ዳርጓቸዋል።በዚህም ምክንያት በታችኛው ተፋሰስ የሚገኙ ሀገራት ከማእድን ማውጫ ስፍራዎች በሚወጡ ኬሚካሎች በሚበከሉ ወንዞች ምክንያት ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰባቸው ሲሆን ይህም ሀገራትን ለግጭት ዳርጓቸዋል።

ሌላኛው የተራሮች ስነ ምህዳር ላይ ከፍተኛ ስጋት እየፈጠረ የሚገኘው የሰዎች እንቅስቃሴ ቱሪዝም ነው።ብዙውን ግዜ በተራራዎች አካባቢ የሚገኙ ደኖች ሆቴሎችን እና ሪዞርቶችን ለመገንባት ሲባል የሚመነጠሩ ሲሆን ይህም በስነ ምህዳር ላይ ብቻ ሳይሆን ተዕእኖ የሚያሳድረው ከሆቴሎቹ የሚወገደው ቆሻሻም በአካባቢው የሚገኙ ወንዞች ላይ ከፍተኛ ብክለትን ይፈጥራል።

በአለም አቀፍ ደረጃ የተራራዎችን ስነ ምህዳር ለመንከባከብ የሚያስችሉ የተለያዩ አለም አቀፍ ስምምነቶች የተደረጉ ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡

የአልፓይን ኮንቬንሽን፡- አልፕስ በምእራብ አውሮፓ የሚገኝ ተራራ ሲሆን ከፍታውም ከ 2000-3000 ሜትር ይደርሳል።ተራራውም የብዙ ሀገሮችን ድንበር የሚያቋርጥ ሲሆን ስዊትዘርላንድ፣ፈረንሳይ፣ጀርመን፣ጣልየያን፣ኦስትሪያ፣ሌስተንስታይን እና ስሎቬንያን ይሸፍናል። እነዚህም ሀገራት የአልፕስን ተራራ ለመንከባከብ እና በዘላቂነት ለማልማት የሚያስችላቸውን የአልፓይን ኮንቬንሽን እ.ኤ.አ ህዳር 7 ቀን 1991 ዓ.ም ያወጡ ሲሆን በስራ ላይ የዋለውም እ.ኤ.አ ሚያዝያ 6 ቀን 1995 ዓ.ም ነበር። በዚህም ምክንያት የአልፕስ ተራራ በአለም ላይ ለመጀመሪያ ግዜ በአለም አቀፍ ህግ የተጠበቀ ተራራ ሊሆን ችሏል።

የካርፓትሀን ኮንቬንሽን፡- የካርፓትሀን የተራራ ሰንሰለቶች በቼክ ሪፑብሊክ፣ ሀንጋሪ፣ሞልዳቪያ፣ፖላንድ፣ሮማንያ፣ስሎቫክያ እና ዩክሬን ይገኛል፡፡የካርፓትሀን የተራራ ሰንሰለቶችን በዘላቂነት ለመንከባከብ እ.ኤ.አ ግንቦት 22 ቀን 2003 ዓ.ም የካርፓትሀን መዋቅራዊ ኮንቬንሽን የወጣ ሲሆን በስራ ላይ የዋለውም ጥር 4 ቀን 2006 ዓ.ም ነው፡፡

5.6.4. የደኖች ስነ ምህዳር

ደኖች ከፍተኛ ስነ ምህዳራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ምንም እንኳን ዛፎች የደኖች አንድ አካል ቢሆኑም ደኖች ከዛፎች ስብስብነት በላይ ትርጉም ያላቸው ሲሆን ደኖች የተለያየ ዝርያ ያላቸው ተክሎች እና እንስሳት እርስ በእራሳቸው እና ከአካባበቢያቸው ጋር ተቀናጅተው የሚኖሩበት ስፍራ ነው፡፡የተለያዩ ሳይንሳዊ ምርምሮች እንዳረጋገጡት ደኖች ውሀ ወደ መሬት ሰርጎ እንዲገባ በማድረግ ለአለማችን የውሀ አቅርቦት ከፍተኛውን አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡በዚህም ምክንያት በሞቃት አካባቢዎች የሚካሄድ የደን ምንጣሮ በወንዞች የውሀ ፍሰት መጠን እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡በተጨማሪም ሰፊ የደን ሽፋን ያላቸው ቦታዎች ለምሳሌ እንደ አማዞን ጥቅጥቅ የደን ስፍራዎች ሰፊ የዝናብ ሽፋን የሚኖራቸው ሲሆን በተቃራኒው የደን ሽፋን ሲቀንስ የዝናቡም መጠን አብሮ ይቀንሳል፡፡

ደኖች የአፈር መሸርሸርን የሚከላከሉ ሲሆን በተለይም ተዳፋት በሆኑ ቦታዎች ላይ ለም አፈርን ለመጠበቅ ትልቅ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ፡፡በተጨማሪም ደኖች በከባቢ አየር ውስጥ የሚገኘውን ካርቦን ዳይኦክሳይድ በአፈር ውስጥ እና በተክሎች አካላት ውስጥ ስቦ በማስቀረት ለአየር ንብረት ሚዛን መጠበቅ ትልቅ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ፡፡በተቃራኒው ደኖች በሚቃጠሉበት ወቅት ከፍተኛ መጠን ያለው ካርቦን ዳይኦክሳይድ ወደ ከባቢ አየር የሚለቀቅ ሲሆን ይህም ከፀሀይ የሚመጣውን ሙቀት አምቆ በማስቀረት የአለም የሙቀት መጠን እንዲጨምር ያደርጋል፡፡

ደኖች ለስነ ምህዳር ሚዛን መጠበቅ ትልቅ ጠቀሜታ ያላቸው ቢሆንም የሰው ልጆች በሚያካሂዱት የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ምክንየት ትልቅ ጉዳት እየደረሰባቸው ይገኛል፡፡የህዝብ ቁጥር መጨመር ለእርሻ፣ለከብት እርባታ፣ለጣውላ እና ለወረቀት ምርት እና ለማገዶ ፍጆታ ሲባል በበርካታ ሀገራት የሚገኙ ደኖች በከፍተኛ ፍጥነት ተጨፍጭፈዋል፡፡የደኖችን ስነ ምህዳር አያያዝ እና አጠባበቅን በሚመለከት በአለም አቀፍ ደረጃ የተደነገገ ስምምነት እስከዛሬ ድረስ የሌለ ሲሆን ነገር ግን ከደኖች ስነ ምህዳር አጠባበቅ ጋር ተያያዥ የሆኑ አለም አቀፍ ስምምነቶች ተደንግገው ይገኛሉ፡፡ለምሳሌ

የራምሳር ኮንቬንሽን፡-የራምሳር ኮንቬንሽን እ.ኤ.አ በ1971 ዓ.ም የወጣ ሲሆን ዋና አላማውም በውሀ አዘል መሬቶች ላይ የሚደርስ ጥፋትን በማስወገድ ህያውያንን የመያዝ አቅማቸውን በማጎልበት ዘላቂ

የሆነ የአገልግሎት አቅርቦታቸውን ማሳደግ ነው።የራምሳር ኮንቬንሽን በኮንቬንሽኑ አንቀፅ አንድ ላይ በተቀመጠው የውሀ አዘል ትርጓሜ ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ የደን ስነምህዳሮችንም አካትቶ ይይዛል።

የአለም የባህላዊ እና የተፈጥሮ ቅርሶች ኮንቬንሽን፡-የአለም የባህላዊ እና የተፈጥሮ ቅርሶች ኮንቬንሽን እ.ኤ.አ በህዳር 1972 የወጣ ሲሆን በስራ ላይ የዋለው እ.ኤ.አ ታህሳስ 17 ቀን 1975 ዓ.ም ነው። ኮንቬንሽኑ እ.ኤ.አ ከ 2005 ዓ.ም ጀምሮ 180 አባል ሀገራት አሉት።ኮንቬንሽኑ አባል ሀገራት በአለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ እሴት ያላቸውን (outstanding universal value) የተፈጥሮ እና የባህል ቅርሶችን እንዲንከባከቡ እና እንዲጠብቁ ያስገድዳል።እስከ ዛሬ ድረስ በአለም ቅርስነት ከ812 በላይ የሚሆኑ ቦታዎች በአለም ቅርስነት የተመዘገቡ ሲሆን 48 የሚሆኑት ቦታዎች 32.3 ሚሊዮን የሚሆን ሄክታር የሚሸፍኑ ደኖች የሚገኝበት ቦታ ነው።

ዝርያቸው በመመናመን ላይ የሚገኙ እንስሳት እና እፅዋት ንግድን ለመቆጣጠር የወጣ ኮንቬንሽን

በአሁኑ ወቅት በአለማችን ላይ አንድ ሶስተኛ የሚሆነው የአለም የዱር እንስሳት ዝርያቸው በመመናመን ላይ የሚገኝ ሲሆን ለዚህም ከእንስት የመኖርያ ስፍራ መጥፋት ቀጥሎ በሁለተኛነት የሚጠቀሰው ምክንያት የዱር አራዊቶች ህገ ወጥ ንግድ ነው።በአለም አቀፍ ደረጃ ዝርያቸው በመመናመን ላይ የሚገኙ የዱር አራዊቶች ንግድ በእጅጉ አትራፊ ሲሆን የትራንስፖርት ዘርፍ መሻሻል እንስሳትን በህይወት እንዲሁም ተክሎችን እና ውጤቶቻቸውን ለማጓጓዝ ረድቷል።እንደዚህ አይነት የንግድ ዝውውሮች በአብዛኛው የብዙ ሀገር ድንበር የሚያቋርጡ በመሆኑ አለም አቀፍ ትብብር ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።በዚህም ምክንያት ዝርያቸው በመመናመን ላይ የሚገኙ እንስሳት እና እፅዋት ንግድን ለመቆጣጠር የሚያስችል አለም አቀፍ ኮንቬንሽን እ.ኤ.አ በ1975 በስራ ላይ ሊውል ችሏል።

5.6.5. የዋልታዎች ስነ ምህዳር

የአርክቲክ እና አንታርክቲክ አካባቢዎች የአለማችን የዋልታ አካባቢዎች በመባል ይታወቃሉ።የአርክቲክ አህጉር በግምት 14056 ሚሊየን ስኩዌር ኪሎሜትር የሚሆን መሬት የሚሸፍን ሲሆን የአርክቲክ ውቅያኖስን፣ሰሜን አላስካን፣ግሪን ላንድ፣የባሬንትስ ባህር፣የቢፎርት ባህር እና የሀድሰን ባህረ ሰላጤን ይጨምራል።የተወሰነው የአርክቲክ ክፍል ስምንት ሀገሮችን የሚያዳርስ ሲሆን እነዚህም ካናዳ፣ኖርዌይ፣ስዊድን፣ፊንላንድ፣ዴንማርክ፣ራሺያ፣አይስላንድ እና አሜሪካ ናቸው።

አንታርክቲክ በአለማችን በደቡብ ዋልታ የሚገኝ የአለማችን አምስተኛ አህጉር ሲሆን በግምት 14 ሚሊየን ስኩዌር ኪሎሜትር የሚሆን መሬት ይሸፍናል።የዋልታ አካባቢዎች በእጅጉ ዝቅተኛ የሆነ

የአየር ሙቀት ያላቸው ሲሆን አብዛኛው ክፍሎቻቸውም በወፍራም በረዶ የተሸፈኑ ናቸው።በአንታርክቲክ ሰፊው የበረዶ ሽፋን ውፍረት 200 ሜትር የሚደርስ ሲሆን በአርክቲክ አካባቢ ደግሞ አስር በመቶ የሚሆነው የአርክቲክ ውቅያኖስ ብቻ ከበረዶ ነፃ ነው።

በዋልታዎች አካባቢ የሚገኘው የአየር ንብረት ሁኔታ ትልቅ ስነ ምህዳራዊ ጠቀሜታ አለው።ለምሳሌ በዋልታዎች አካባቢ በውቅያኖሶች እና በመሬት ላይ የሚገኘው ሰፊ የበረዶ ሽፋን ከፀሀይ በቀጥታ የሚመጣውን ጨረር ወደ ከባቢ አየር አንፀባርቆ በመመለስ መሬት ሚዛናዊ ሙቀት እንዲኖራት አስችሏል።በሌላ በኩል የዋልታ አካባቢዎች የመሬት አቀማመጥ ለአካባቢው ስነ ውበት ትልቅ አስተዋፅኦ ያለው ሲሆን ይህም የቱሪስት መዳረሻ ስፍራ እንዲሆኑ አስችለዋል።የአካባቢው ሰፊ የበረዶ ሽፋን በቀዝቃዛ ስፍራ መኖር ለተላመዱ በርካታ የዱር እንስሳት መኖሪያ ሲሆን የከበሩ ማእድናትም በብዛት በእነዚህ አካባቢዎች ይገኛሉ።

ሁለቱም በአለማችን በዋልታዎች አካባቢ የሚገኙት ስነ ምህዳሮች ለተለያዩ የአካባቢያዊ ጉዳቶች የተጋለጡ ሲሆን በዋናነት የሚጠቀሰው ችግር የአየር ንበረት ለውጥ ነው።በአውሮፓ እና በሌሎች የአለማችን ክፍሎች ከኢንዱስትሪ እንቅስቃሴዎች፣ከደን መመንጠር፣ከግብርና ከሌሎች ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች በሚከናወኑበት ወቅት የሙቀት ሳቢ ጋዞች ወደ ከባቢ አየር እንዲለቀቁ የሚደረግ ሲሆን ይህም የአየር ሙቀት እንዲጨምር ያደርጋሉ።በዚህም ምክንያት የዋልታዎች አካባቢ መቀት ከመቼውም ግዜ ይበልጥ እየጨመረ የመጣ ሲሆን ይህም የበረዶ ሽፋን እንዲቀንስ ያደረገ ሲሆን የበረዶው መቅለጥም ጎርፍ፣የባህር ዳርቻዎች መሸርሸርን አስከትሏል።

ከአንድ ሀገር ወደ ሌላ ሀገር የሚደረግ የነዳጅ እና የኬሚካሎች በመርከብ በውሀ ላይ በሚጓዝበት ወቅት የሚደርስ የኬሚካል እና የነዳጅ መፍሰስ አደጋ በአካባቢዎቹ ላይ ትልቅ ብክለትን እያደረሰ ይገኛል።የአርክቲክ አካባቢ የተለያዩ ወታደራዊ እንቅስቃሴዎች ሴካሄዱበት የቆየ ቦታ ሲሆን በተለይም የኒኩሊየር እና የሌሎች የጦር መሳሪያዎች መፈተሻ እና የተለያዩ አደገኛ ቆሻሻዎች ማራገፊያ ስፍራ ሆኖ ሲያገለግል ቆይቷል።በተለይም በቀዝቃዛው የአለም ጦርነት ወቅት የራሽያ እና የሌሎች ሀገራት የጦር ሀይሎች ራድዮ አክቲቭ የኒኩሊየር ቆሻሻዎችን በተለያዩ ወታደራዊ መቀመጫዎቻቸው ትተው ሄደዋል።በመሆኑም በዋልታዎ የሚገኘውን ስነ ምህዳር ለመንከባከብ የሚስችሉ በሀገራት መካከል የተለያዩ ስምምነቶች የተካሄዱ ሲሆን ዋና ዋናዎቹም የሚከተሉት ናቸው፡

1) እ.ኤ.አ በ2005 ዓ.ም የተካሄደው የአንታርክቲክ ስምምነት
2) እ.ኤ.አ በ1972 ዓ.ም በአንታርክቲክ የሚገኙ የባህር እንስሳትን ለመንከባከብ የወጣ ኮንቬንሽን

3) እ.ኤ.አ በ1980 ዓ.ም በአንታርክቲክ አካባቢ በባህር ውስጥ የሚኖሩ ህይወት ያላቸው ፍጥረቶችን ለመንከባከብ የወጣው ኮንቬንሽን

4) እ.ኤ.አ በ1991 ዓ.ም የአርክቲክ አካባቢን ለመንከባከብ የወጣ ዲክላሬሽን ዋና ዋና የተባሉት ናቸው።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. ከቀዳሚ ግንዛቤ የመነጨ የእሽታ ሥነ ሥርዐት በደህንነቱ ህይወት ፕሮቶኮል ውስጥ ያለውን ጠቀሜታ አብራሩ።

ምዕራፍ ሶስት

ከአካባቢ ጥበቃ ጋር ተያያዥ የሆኑ ጉዳዮች እና የፍትህ አካላት ሚና

ሠልጣኞች በዚህ ምዕራፍ ማብቂያ ላይ

- ከንፁህ ውሀ አጠቃቀም ጋር ተያያዥ የሆኑ አለም አቀፍ ህጎችን ይረዳሉ
- የአካባቢ ተዕእኖ ግምገማን በሚመለከት የተደነገጉ አለም አቀፍ እና ሀገራዊ ህጎችን ያብራራሉ
- የሰብአዊ መብት እና አካባቢ ግንኙነት ይገነዘባሉ
- በአካባቢ ጉዳዮች የኮርፖሬሽኖች ተጠያቂነትን ይገልፃሉ
- የታዳሽ ሀይሎች አጠቃቀምን የስረዳሉ
- በአካባቢ ላይ በሚደርስ ጉዳት ላይ የሚተገበሩ የተጠያቂነት እና የጉዳት ካሳ ህጎችን ይለያሉ

1) የንፁህ ውሀ አቅርቦት

በቂ የንፁህ ውሀ አቅርቦት ለሰዎች ሁለንተናዊ አኗኗር በእጅጉ ከሚያስፈልጉ ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡በመሆኑም በውሀ አቅርቦት ላይ የሚደርስ ማንኛውም አይነት ችግር በሰዎች ኑሮ ላይ፣በጤና እና ኢኮኖሚ ላይ ትልቅ ችግር ያስከትላል፡፡ ባለፉት ምእተ አመታት የአለማችን የህዝብ ቁጥር ቁጥር በሶስት እጥፍ ሲጨምር በተመሳሳይ የንፁህ ፍላጎት በስድስት እጥፍ ሊጨምር ችሏል[28]፡፡በአሁኑ ወቅት ከቢሊዮን በላይ የሚሆን ህዝብ የንፁህ ውሀ መጠጥ አቅርቦት የማያገኝ ሲሆን ከሁለት ቢሊዮን በላይ የሚሆን ህዝብ ደግሞ ለፅዳት አገልግሎት የሚሆን በቂ ውሀ አያገኝም፡፡በአለማችን ላይ ከ 14 እስከ 30 ሺህ የሚሆን በአብዛኛው በወጣትነት የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ እና በእድሜ የገፉ የህብረተሰቡ ክፍሎች ከ ውሀ ጋር ተያያዥ በሆኑ በሽታዎች ህይወታቸውን በየቀኑ ያጣሉ፡፡አሁን ያለው ሁኔታ

[28] Water as a human right ,IUCN Environmental Policy and Law Paper No.51

በዚሁ ከቀጠለ እ.ኤ.አ በ2025 ሁለት ሶስተኛው የሚሆነው የአለም ህዝብ በጣም ከፍተኛ በሆነ የውሀ እጥረት ወይም ጭራሽ የንፁህ ውሀ አቅርቦት የማይኖርበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል[29]።

እ.ኤ.አ የ2003 ዓ.ም በተባበሩት መንግስታት ድርጅት አለም አቀፍ የንፁህ ውሀ አመት ታብሎ የታወጀ ሲሆን ዋና አላማውም በተባበሩት መንግስታት የምዕተ አመቱ የልማት ግቦች ላይ የተጠቀሰውን እ.ኤ.አ በ2015 ዓ.ም የንፁህ ውሀ ውሀ አቅርቦት በበቂ ሁኔታ የማያገኙ ህብረተሰቦችን በግማሽ ለመቀነስ እና ዘላቂነቱ ያልተረጋገጠ የውሀ አጠቃቀምን ለማስቀረት ከታቀደው ግብ ጋር ተያያዥነት ያለው ነው።እ.ኤ.አ በ2002 ዓ.ም በጆሀንስበርግ ከተማ በተካሄደው የዘላቂ ስብሰባ ወቅት ለመሰረታዊ የንፅህና አገልግሎት የሚያስፈልገውን ንፁህ የውሀ አቅርቦት ማግኘት የማይችሉ ሰዎችን ቁጥር በግማሽ ለመቀነስ የታቀደ ሲሆን ስብሰባው የውሀን ሚና በግብርና፣በሀይል አቅርቦት፣በጤና፣በብዝሀ ህይወት እና በድህነት ቅነሳ የሚያበረክተውን አስተዋፅኦ እውቅና ሰጥቶታል።

1.1 ከንፁህ ውሀ አጠቃቀም ጋር ተያያዥ የሆኑ አለም አቀፍ ህጎች

አብዛኛዎቹ ከንፁህ ውሀ አጠቃቀም ጋር ተደንግገው የሚገኙ አለም አቀፍ ህጎች በአብዛኛዎቹ ፅኑ ግዴታን የማያስከትሉ (non-binding) ህጎች እና ዲክላሬሽኖች ናቸው።ሆኖም እነዚህ አለም አቀፍ እና አህጉራዊ ድንጋጌዎች መሰረታዊ የሰብአዊ መብት መርሆችን ማለትም የመኖር መብትን፣የደህንነት መብትን መሰረት ያደረጉ ሲሆን ለእነዚህም መብቶች መከበር ህዝቦች የንፁህ የመጠጥ ውሀ አቅርቦት በጥራት እና በብዛት ማግኘታቸው መረጋገጥ ይኖርበታል።

የስቶክሆልም ዲክላሬሽን ቀደምት ከሆኑ አካባቢያዊ ድንጋጌዎችን ውስጥ የንፁህ ውሀ የማግኘት መብትን እውቅና የሰጠ ድንጋጌ ነው።በዲክላሬሽኑ መሰረት በመሬት ላይ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች ውሀን ጨምሮ የአሁኑን እና የቀጣዩን ትውልድ ከግንዛቤ ውስጥ ባስገባ መንገድ ጥበቃ እንዲደግላቸው ይደነግጋል። በሌላ በኩል እ.ኤ.አ በ 1992 ዓ.ም የውሀ ባለሙያዎች የተሰባበሰቡበት አለም አቀፍ የውሀ እና የአካባቢ ስብሰባ በአየርላንድበደብሊን ከተማ ተካሂዶ የነበረ ሲሆን ከስብሰባውም የውሀ እና የዘላቂ ልማት መርሆችን አፅድቋል።ከፀደቁት መርሆች ውስጥ አንዱ ንፁህ የውሀ ሀብት ውሱን እና ለጥፋት የተጋለጠ የተፈጥሮ ሀብት ሲሆን ህይወት በምድር ላይ እንዲቀጥል፣ለልማት እና አካባቢ አስፈላጊ ነው የሚል ነው[30]።ሌላኛው መርህ ለውሀ ልማት እና አያያዝ አያያዝ አሳታፊ የሆነውን መንገድ የሚብራራ

[29] ዝኒ ከማሁ
[30] The Dublin Statement on Water and Sustainable Develpopment,Principle 1

ሲሆን በዚህም ሴቶች ለውሀ ልማት እና አያያዝ ያላቸውን አስተዋፅኦ እንዲሁም ንፁህ ውሀ እንደ አንድ የኢኮኖሚ ሀብት እንዲቆጠር እውቅና የሰጠ ነው[31]።

እ.ኤ.አ በሪዮ ዲጀኔሮ ከተማ በተካሄደው የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ እና የልማት ስብሰባ ወቅት መንግስታት አጀንዳ 21 የተባለ ዝርዝር የድርጊት መርሀ ግብር የፀደቀ ሲሆን በዚሁ የድርጊት መርሀ ግብር ምዕራፍ 18 ላይ የንፁህ ውሀ ሀብትን ለመንከባከብ በብሄራዊ ደረጃ መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎችን የያዘ ሲሆን በተጨማሪም የአየር ንብረት በውሀ ሀብት ላይ የሚያሳድረውን ተፅእኖ እና መወሰድ ያለባቸውን አስፈላጊ እርምጃዎችን ያብራራል።

እ.ኤ.አ በ መስከረም 2000 ዓ.ም በተካሄደው የምእተ አመቱ ስብሰባ ወቅት ጠቅላላ ጉባኤው የሚለንየም ዲክላሬሽኖችን ያፀደቀ ሲሆን በዚህም ወቅት መንግስታት የንፁህ መጠጥ ውሀን በቅርብ የማያገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን በግማሽ እ.ኤ.አ እስከ 2015 ዓ.ም ለመቀነስ ተስማምተዋል።ከዚህ በተጨማሪም የአለም መሪዎች ዘላቂ ያልሆነ የውሀ አጠቃቀምን ለማቆም የሚያስችሉ የውሀ አያያዝ ስልቶችን በአህጉር፣በብሄራዊ እና በወረዳ ደረጃ መተግበር እንዳለባቸው እና ይህም ፍትሀዊና እና ተደራሽ የሆነ የውሀ አቅርቦት እንዲኖር እንደሚያስችል በምእተ አመቱ የልማት ዲክላሬሽን ምእራፍ 23 ላይ ተብራርቷል።እነዚህ ከላይ የተገለፁት ዲክላሬሽኖች ወደ ምእተ አመቱ የልማት ግቦች በመጨረሻም ሊሸጋገሩ ችለዋል።

2. የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ

የልማት እንቅስቃሴዎች ከብዙ አመታት ጀምሮ በአካባቢ ላይ ትልቅ ተፅእኖ ሲያሳድሩ ቆይተዋል።እንቅስቃሴዎቹ አካባቢያችንን ላይ ጉዳት ከማድረስ ባለፈ በኢኮኖሚ እና በአጠቃላይ በሰዎች ጤና ላይ ትልቅ አደጋ ያስከትላል፡የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995 አንቀፅ 2(1) ላይ እንደተገለፀው የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ ማለት አንድ ፕሮጀክት ወይም መንግስታዊ ሰነድ ተግባራዊ ሲሆን የሚያስከትለውን ገንቢም ሆነ አፍራሽ ውጤት በቅድሚያ ለይቶ የማወቂያ የመመዘኛ ዘዴ ነው። ተፅእኖ ማለት በአካባቢ ወይም በንኡሳን ክፍሎቹ ላይ በሚፈጠር ለውጥ ምክንያት ማንኛውም በሰው ጤና ወይም ደህንነት፣በዕፅዋት፣በእንስሳት፣ በአፈር ፣በአየር፣በውሀ፣በአየር ንብረት፣በተፈጥሮአዊ ወይም በባህላዊ ቅርስ ወይም በአጠቃላዩ ሲታይ በአካባቢያዊ፣በማህበራዊ፣በኢኮኖሚያዊ ወይም በባህላዊ ገፅታዎች ላይ የሚከሰት ተከታይ ለውጥ ነው። የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ የልማት ሀሳብ ንድፍ ሲዘጋጅ ቦታው ሲመረጥ፣ሲገነባ ወይም ሲተገበር እንደዚሁም በመተግበር ላይ ያለ እንቅስቃሴ ሲሻሻል ወይም

[31] ዝኒ ከማሁ Principle 2

ሲቋረጥ የሚያስከትለውን ተፅእኖ በመተንበይና አስቀድሞ በማረም በውል የታሰበበትን ልማት ለማምጣት ያግዛል፡፡በተጨማሪም አንድ ፕሮጀክት በአካባቢ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ተፅእኖ ለመለየት ገና ከመፅደቁ በፊት መገምገም፣የመፅደቂያው ውሳኔ በሚሰጥበት ወቅት አካባቢያዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ባህላዊና ማህበራዊ ታሳቢዎችንና ግቦችን ዘላቂ ልማትን ለማምጣት በሚያመች ሁኔታ እንዲዋሀዱና እንዲቀናጁ ለማድረግ ያስችላል፡፡

የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ ማካሄድ ውሳኔ ሰጪ አካላት አንድ የልማት ፕሮግራም ሊያስከትላቸው የሚችላቸውን ውጤቶች በቂ መረጃ እንዲኖራቸው የሚያስችል ሲሆን አስተዳደራዊ ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲኖር ለማድረግ፣ የልማት እቅዶች ሲታቀዱ እና በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ ህዝብን ለማሳተፍ ይረዳል፡፡በዚህም ምክንያት የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ ሶስት መሰረታዊ ጥቅሞች ይኖሩታል፡፡

- አካባቢያዊ ጉዳዮችን በእቅድ እና በውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ ለማካተት፣
- በአካባቢ ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶችን አስቀድሞ ለመገመት እና ተፅእኖውን ለማሳነስ እና
- የህብረተሰብ ተሳትፎን በውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ማካተት ናቸው፡፡

በአለማችን ለመጀመሪያ ግዜ የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ ህግን እ.ኤ.አ በ1969 ዓ.ም ያዘጋጀች ሀገር አሜሪካ ስትሆን አሜሪካን ተከትለው ከ 100 በላይ የሚሆኑ ሀገራት ከአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ህጎች እና ፖሊሲዎችን አዘጋጅተዋል፡፡በአለም አቀፍ ደረጃ የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ ፅንሰ ሀሳብ በከፍተኛ ደረጃ ተቀባይነትን ያገኘ ሲሆን እ.ኤ.አ በ1987 ዓ.ም የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ አላማዎች እና መርሆዎች እንዲዘጋጁ አድርጓል፡፡በተመሳሳይ እ.ኤ.አ በ1989 ዓ.ም የአለም ባንክ የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ መመሪያዎችን ያዘጋጀ ሲሆን በዚሁም መሰረት ባንኩ የተለያዩ የልማት እንቅስቃሴዎችን በገንዘብ ከመደገፉ በፊት ፕሮጀክቶች የሚያስከትሉትን ሀገራዊ፣ድንበር ዘለል እና አለማቀፋዊ የአካባቢ ተፅእኖዎችን በጥብቅ ሲፈትሽ ቆይቷል፡፡

የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ መርሆዎች በተለያዩ መልቲላተራል የአካባበቢ ስምምነቶች ውስጥ ተካትተው የሚገኙ ሲሆን ለምሳሌ በብዝሀ ህይወት ኮንቬንሽን እና የተባበሩት መንግስታት የባህር ህግ ኮንቬንሽን ውስጥ ይገኛል፡፡በሌላ በኩል በሪዮ ዲክላሬሽን መርህ 17 ላይ ስለ አካባቢ ተፅእኖ ግምገማ የተገለፀ ሲሆን በአካባቢ ላይ ተፅእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ የልማት እንቅስቃሴዎች የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ ማካሄድ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡

የልማት እንቅስቃሴዎች በአካባቢ ላይ ብቻ ተፅእኖ የሚያስከትሉ ሳይሆን በዋናነትም የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተፅእኖን የሚያስከትሉ ሲሆን ይህም በማህበራዊ ተፅእኖ ግምገማ ጥናት ማካሄድም አስፈላጊ ነው ።ለምሳሌ የአንድ ሆቴል ግንባታ በአካባቢ ላይ ብቻ ተፅእኖ የሚያስከትል ሳይሆን አዳዲስ የስራ እድል በመፍጠር ወይም ቀደም ብለው ሲካሄዱ የነበሩ የንግድ እንቅስቃሴዎችን በማፈናቀል ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጽእኖን ሊያስከትል ይችላል።

2.1. የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማን በሚመለከት የተደነገጉ አለም አቀፍ ስምምነቶች

2.1.1. የኤስፖ ኮንቬንሽን

ድንበር ዘለል የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማን በሚመለከት የተደነገገው የኤስፖ ኮንቬንሽን በአውሮፓ የኢኮኖሚክ ኮሚሽን የተዘጋጀ አህጉራዊ ስምምነት ሲሆን በስራ ላይ የዋለው እ.ኤ.አ በ1997 ዓ.ም ነው። ኮንቬንሽኑ እ.ኤ.አ ከ ህዳር 2000 ዓ.ም ጀምሮ 41 አባል ሀገራት አሉት።ምንም እንኳን ስምምነቱ አህጉራዊ ቢሆንም በተባበሩት መንግስታት ድርጅት አባል ለሆኑ ሀገራት በሙሉ ለፊርማ ክፍት ተደርጓል፡የኮንቬንሽኑ ዋና አላማ ድንበር ዘለል የሆነ ብክለትን የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማን መሰረት በማድረግ መቆጣጠር ነው።ኮንቬንሽኑ አባል ሀገራት ድንበር ዘለል የአካባቢ ተፅእኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ የልማት ስራዎችን በሚያካሂዱበት ወቅት እርስ በእርስ ምክክር እና የቅድመ ማስታወቂያ እንዲያካሂዱ ያስገድዳል።

3. የሰብአዊ መብት እና አካባቢ

በአሁኑ ወቅት በአለማችን ላይ በብክለት ምክንያት ከሁለት ሚሊየን በላይ የሚሆን አመታዊ የሞት ቁጥር እና በቢሊየን የሚቆጠር በሽታዎች ይመዘገባሉ።በሁሉም የአለም ክፍል የስነ ምህዳር መዛከም የሚታይ ሲሆን ይህም የንፁህ ውሀ እጥረት፣የአሳ ሀብት መቀነስ፣የመሬት መንሸራተት እና የደን መመናመን እያስከተለ ይገኛል።

ምንም እንኳን ሰብአዊ መብት እና የአካባቢ ጉዳዩች የተሳሰሩ ቢሆኑም አብዛኛዎቹ አለም አቀፍ ተቋማት እና መንግስታት የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን እና የአካባቢ ጉዳቶችን ለያይተው ሲአዩ ነበር።የሰብአዊ መብት ተሟጋቾች የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ላይ ትኩረት እንደሚያደርጉት ሁሉ የአካባቢ መብት ተሟጋቾችም ሰዎች በአካባቢ ላይ የሚያደርሱት ጉዳት ላይ ትኩረት ከማድረግ ይልቅ በተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም ላይ ያተኩራሉ።ሆኖም ከቅርብ አመታት ወዲህ ጤናማ በሆነ አካባቢ

የመኖር መብት እና የሰብአዊ መብቶች የአካባቢ ጥበቃ አላማዎችን ለማስፈፀም መዋል እንደሚችሉ ከፍተኛ እውቅናን አግኝቷል፡

የሰብአዊ መብቶችን በተለያየ መንገድ መመደብ የሚቻል ሲሆን የተለመደው የመብቶች አከፋፈል ትኩረት ከሚያደርጉበት ጉዳይ አንፃር ሲሆን ሲቪል፣ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ መብቶች በመባል ይከፈላሉ፡፡በሌላ በኩል የሰብአዊ መብቶች Substantive እና Procedural ተብለው ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ከሰብአዊ መብቶች ጥበቃ አኳያ ቀጥለው የተዘረዘሩት Substantive መብቶች በአካባቢ ላይ በሚደርሱ ጉዳቶች ጋር በተያያዘ ተፅእኖ ይደርስባቸዋል

- የመኖር መብት (The right to life)
- በንብረት የመጠቀም መብት (The right to property)
- The right to a decent environment (expressed under The African (Banju) Charter on Human and Peoples right
- የሀይማኖት ነፃነት

በሌላ በኩል የስነ ስርዐት መብቶች (Procedural rights) Substantive መብቶች እንዲተገብሩ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ፡፡የስነ ስርዐት መብቶች ሰዎች አካባቢያቸውን በነቃ ሁኔታ እንዲጠብቁ የሚያስችሉ ሲሆኑ እነዚህም፡

- መረጃ የማግኘት መብት
- የመሳተፍ መብት (The right to participation)
- The right to equal protection and to be free from discrimination
- ፍትህ የማግኘት መብት (The right to judicial remedy)

4. በአካባቢ ጉዳዮች የኮርፖሬሽኖች ተጠያቂነት

ኮርፖሬሽኖች ለኢኮኖሚ በእጅጉ አስፈላጊ የሆኑ ምርቶችን እና አገልግሎቶችን እንደሚያበረክቱ የታወቀ ቢሆንም በተቃራኒው በጣም አስፈላጊ የሆኑ የተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅእኖ ያሳድራሉ፡፡ኮርፖሬሽኖች የበካይ ጋዞችን በማመንጨት፣የብዝሀ ህይወትን ዘላቂነቱን በማያረጋግጥ ሁኔታ በመጠቀም፣መርዛማ እና አደገኛ የሆኑ ቆሻሻዎችን ወደ አካባቢ በመልቀቅ በአካባቢ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሱ ይገኛሉ ። እ.ኤ.አ በ1990 ዎቹ የመጀመሪያ አመታት በአለማችን ላይ የሚገኙ ግዙፍ

ኮርፖሬሽኖች ከ 50 በመቶ በላይ ለሚሆን የበካይ ጋዞች መመንጨት ምክንያት ሆነዋል፡፡ኮርፖሬሽኖች የብዝሀ ህይወትን በሰፊው የሚጠቀሙ ሲሆን ይህም ከሰብሎች፣ከመድሀኒቶች እና የተለያዩ የምግብ ምርቶችን ለማምረት የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን ለማጥናት ይጠቀሙባቸዋል፡፡በሌላ በኩል ኮርፖሬሽኖች ታዳሽ የሆኑ እና ታዳሽ ያልሀሆኑ የተፈጥሮ ሀብቶችን በሰፊው የሚጠቀሙ ሲሆን በዋናነትም ነዳጅ በማውጣት፣በማእድን ስራ እና በደኖች ላይ በሰፊው በግብአትነት ይጠቀሙባቸዋል፡፡

እ.ኤ.አ ከ 1972 ከስቶክሆልም ዲክላሬሽን ቀደም ብሎ ኮርፖሬሽኖች አካባቢን በመንከባከብ እና በመጠበቅ ረገድ የሚኖራቸውን ሚና በሚመለከት የተለያዩ ስብሰባዎች ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡በስቶክሆልም ዲክላሬሽን መግቢያ ላይ እንደተገለፀው አካባቢን ለመንከባከብ እና ለመጠበቅ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት እንዲቻል ሁሉም ዜጎች፣የህብረተሰብ ክፍሎች እንዲሁም ኢንተርፕራይዞች እና በተለያየ ደረጃ የሚገኙ ተቋሞች ሀላፊነትን በመውሰድ ሁሉም የጋራ ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው ተጠቅሷል፡፡ በአለም አቀፍ ደረጃ ኮርፖሬሽኖች ከዘላቂ ልማት አኳያ የሚኖርባቸውን ሀላፊነት በሚመለከት የኢንዱስትሪ ሀላፊዎች፣ ከተለያየ ሀገር ከመጡ ዲፕሎማቶች እና ሳይንቲስቶች ለመጀመሪያ ግዜ እ.ኤ.አ በሪዮ ዲጀኔሮ ከተማ በተካሄደው የተባበሩት መንግስታት ስብሰባ ወቅት ውይይት አካሂደዋል ፡፡

አጀንዳ 21 አካባቢን ለመጠበቅ እና ዘላቂ ልማትን ለማራመድ የሚያስችል እና ፅኑ ግዴታን የማያስከትል የድርጊት መርሀ ግብር ነው፡፡ ኮረፖሬሽኖችንም በሚመለከትም አጀንዳ 21 መረዛማ ኬሚካሎች የሚመነጩበትን መጠን የሚያሳይ ዳታ ግልፅ እንዲሆን ይደነግጋል፡፡ይህም ኢንዱስትሪዎች አግባብነት ያላቸው የመንግስት እና አለም አቀፍ ተቋማት እንዲሁም ለማናቸውም ፍላጎቱ ያላቸው ግለሰቦች በስራቸው ሂደት የሚያመነጩዋቸውን ኬሚካሎች የሚያሳይ መረጃ ግልፅ እንዲያደርጉ ይደነግጋል፡፡ ይህም የተለያዩ አደጋዎች እንዳይከሰቱ የተለያዩ ቅድመ ሁኔታዎች እንዲመቻቹ ያስችላል:: በተጨማሪም የአጀንዳ 21 ምእራፍ ሰላሳ የኮርፖሬሽኖችን አካባቢያዊ ሀላፊነት የተመለከተ መዋቅር አስቀምጧል፡፡ ኮርፖሬሽኖች የሚያካሂዷቸውን እንቅስቃሴዎች እና የሚከተሉዋቸው ፖሊሲዎች በሀብት አጠቃቀም እና በአካባቢ እንክብካቤ ላይ ትልቅ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡ይህንንም ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የአጀንዳ 21 ምእራፍ 30 የኢንዱስትሪዎችን ሀላፊነት የተመለከቱ ሁለት መርሀ ግብሮችን አስቀምጧል፡፡የመጀመሪያው ፕሮግራም ንፁህ የአመራረት ሂደት (Cleaner production) ሲሆን ይህም ትኩረት የሚያደርገው ብቃቱ በተረጋገጠ የሀብት አጠቃቀም እና ምርጥ በሆኑ የአካባቢ አያያዝ የስነ ምግባር ደንቦች ላይ ነው፡፡በዚህም ምክንያት ምእራፍ 30 ወሳኝ ከሆኑ

የአጀንዳ ድንጋጌዎች ውስጥ የሚጠቀስ ሲሆን ይህም ኮርፖሬሽኖች የኢኮኖሚ እድገትን ከማሳደግ ጎን ለጎን የዘለቂ ልማትን ለማረጋገጥ ዋና ባለድርሻ መሆናቸውን ያረጋገጠ ነው።

5. የታዳሽ ሀይሎች አጠቃቀም

የኤሌክትሪክ ሀይልን ለማመንጨት የቅሪተ አካል ነዳጆችን ማቃጠል ማለትም ከሰል፣ ነዳጅ ዘይት እና የተፈጥሮ ጋዝ በሚቃጠሉበት የሙቀት አምጪ ጋዞች ወደ ከባቢ አየር የሚለቀቁ ሲሆን ይህም ለአለም ሙቀት መጨመር ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል።የቅሪተ አካል ነዳጆች (fossil fuels) ለአለም ሙቀት መጨመር ከሚያደርጉት አስተዋፅኦ በተጨማሪ ዘላቂ የሀይል ፍላጎትን ለማሟላት ተመራጭ አይደሉም።በተቃራኒው ታዳሽ የሀይል አማራጮች በስፋት እና በዘላቂነት የሀይል አቅርቦትን ለማሟላት የሚያስችሉ ሲሆን ሙሉ በሙሉም ከሙቀት አምጪ ጋዞች የፀዱ ናቸው።ዋና ዋና የተባሉት የታዳሽ ሀይል ምንጮች የሚባሉት ንፋስ፣ከፀሀይ የሚገኝ ብርሀን እና ሙቀት፣የወራጅ ውሀ እና የጂኦተርማል ሀይል ናቸው።

6. በአካባቢ ላይ በሚደርስ ጉዳት ላይ የሚተገበሩ የተጠያቂነት እና የጉዳት ካሳ ህጎች

ባለፉት አስርት አመታት በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ከባድ ጉዳቶች በአለም ላይ በሚገኙ ሀገራት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ማሳደራቸው በአጠቃላይ በአለም ህዝብ ዘንድ የሰዎች እንቅስቃሴ በሰዎች ጤና እና አካባቢ ላይ ከባድ ውጤት እንደሚኖረው ግንዛቤ ተፈጥሮአል።በአለም ላይ በተለያዩ ግዜያት ከፍተኛ አካባቢያዊ ጉዳቶች የተከሰቱ ሲሆን እ.ኤ.አ በ1986 ዓ.ም በቀድሞው ሶቭየት ህብረት በቼርኖቤል የኒኩሊየር ሀይል ማመንጫ ፍንዳታ ምክንያት በአካባቢ ላይ የደረሰው በአደገኛ ጨረር መበከል እና በድንበር በሚዋሰኑ በአውሮፓ እና ኤስያ በሚገኙ ህዝቦች ላይ ያደረሰው የጤና ጉዳት በዋናነት የሚጠቀስ ነው።

በተደጋጋሚ የሚከሰቱ አካባቢያዊ ጉዳቶች መካከል በኢንዱስትሪዎች ላይ በሚደርስ አደጋ ምክንያት የሚከሰት የመሬት መበከል፣ አደገኛ ቆሻሻዎችን በተገቢ ሁኔታ ባለመያዝ እና በተገቢ ሁኔታ ካለማስወገድ፣ እና በእንስሳት እና እጽዋት መኖሪያ በሚደርስ አደጋ የሚከሰት የብዘሀ ህይወት መመናመን ናቸው።አካባቢያዊ ጉዳት ለሚለው ሀረግ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው አንድ ትርጓሜ የሌለው ሲሆን የተለያዩ የህግ ትርጓሜዎች ተሰጥቶት ይገኛል።ነገር ግን እ.ኤ.አ በ1998 ዓ.ም

የተባበሩት መንግስታት የአካባቢ ፕሮግራም በአካባቢ ላይ ለሚደርስ ጉዳት የተጠያቂነት እና ካሳ ትርጓሜን አቅርቦ የነበረ ሲሆን

> "አካባቢያዊ ጉዳት ማለት በአንድ በተወሰነ አካባቢ ወይም በውስጡ በሚገኙ አካላት ላይ ማለትም ጥቅም በሚሰጡ እና ጥቅም በማይሰጡ እሴቶች ፣ ተቀባይነት ያለው የህይወት ደረጃ ጥራት እና ስነ መህዳራዊ ሚዛን ላይ የሚደርስ አሉታዊ ተፅዕኖ እና ለውጥ ነው በማለት ይተረጉመዋል[32]።"

የህግ ተጠያቂነት በአካባቢ ላይ በዋናነት ብክለትን እና ጉዳትን በሚያስከትሉ አካላት ያደረሱትን ጉዳት እንዲጠግኑ እና ጉዳት ለደረሰባቸውም አካላት ተገቢውን ካሳ እንዲከፍሉ የሚያስገድድ ፅንሰ ሀሳብ ነው።በአካባቢ ላይ ለሚደርስ ጉዳት የሚኖር የህግ ተጠያቂነት የበከለ ይክፈል ለሚለው የአካባቢ መርህ እንደ አንድ የመተግበሪያ ስልት ሊወሰድ ይችላል።

የአካባቢ ጥበቃን በተጠናከረ ሁኔታ ለመስራት ይቻል ዘንድ የተጠያቂነት ህጎችን ከዚህ ቀደም ከሚታወቁበት ሰፋ ያለ ትርጓሜ እንዲይዙ ያስፈልጋል።የተጠያቂነት ህጎች በአብዛኛው ሽፋን የሚሰጡት በሰዎች እና በንብረት ላይ ለሚደርስ ጉዳት ሲሆን በአካባቢ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶችን ሽፋን ሲሰጡ አይስተዋልም።ይህም ሊሆን የቻለው የምንኖርበት አካባቢ በሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ጥቅም ላይ የሚውል በመሆኑ አደጋ በሚደርስ ግዜ በግለሰብ ደረጃ ማንም ተጠያቂ ሊሆን ስለማይችል ነው።ከዚህም የተነሳ ሰዎች ለመኖር በሚያደርጉት እንቅስቃሴ በአካባቢ ላይ ለሚያደርሱት ጉዳቶች ተጠያቂ ስለመሆናቸው ግንዛቤ መፍጠር ግዜን የሚወስድ ሂደት ነው።

የተወሰኑ ሀገራት በቅርብ ግዜ በአካባቢ እና በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ በሚደርሱ ጉዳቶች ላይ የተጠያቂነት እና ካሳን የሚመለከት ህግ ቢደነግጉም ብዙ ሀገራት አካባቢያዊ ጉዳቶች ላይ የተለየ የተጠያቂነትና የካሳ ህግ ከማዘጋጀት ይልቅ በፍትሀ ብሄር ህጎች ውስጥ በተጠቀሱ አጠቃላይ የተጠያቂነት እና የካሳ ህጎችን ለአካባቢያዊ ጉዳዮችም በስራ ላይ እንዲውሉ አድርገዋል።

6.1) የሀገራት ሀላፊነት እና የፍትሀ ብሄር የግለሰቦች ተጠያቂነት ልዩነት (State responsibility Vs Civil liability)

በአጠቃላይ የተጠያቂነት እና የካሳ መርሆች ጽንሰ ሀሳብ የሚመነጨው ከውል ውጭ የሚመጣ ሀላፊነትን በሚደነግጉ ህጎች ውስጥ ሲሆን በአንድ ጥፋት ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ግለሰብ ወይም

[32] ዝኒ ከማሁ ገፅ 52

አካል የፍትሀ ብሔር ክስ በመመስረት ጉዳት ያደረሰበትን አካል የካሳ ክፍያ የሚጠይቅበት ሥርዐት ነው፡፡ከዚህ አንጻር የግለሰቦች የጉዳት ተጠያቂነት ሀገራት ከሚኖርባቸው ተጠያቂነት የተለየ ይሆናል፡፡የግለሰቦች የጉዳት ተጠያቂነት ተግባራዊ የሚሆነው በአንድ ሉአላዊ በሆነ ሀገር ውስጥ በሚገኙ ህዝቦች ላይ ሲሆን የሀገራት ሀላፊነት በተቃራኒው ተግባራዊ የሚሆነው ሁለት እና ከሁለት በላይ የሆኑ ሀገራትን ግንኙነት በሚወስነው የህዝብ አለምአቀፍ ህግ (Public Internation Law) መሰረት ነው፡፡በመሆኑም የሀገራት ሀላፊነት የሚኖረው በአካባቢ ላይ ጉዳት የሚያስከትል ድርጊት በተፈጸመበት እና በድረጊቱ ምክንያት ጉዳት በደረሰባቸው ሀገራት መካከል ይሆናል፡፡በሌላ አገላለጽ በሀገራት ሀላፊነት ወቅት የአለም አቀፍ ስምምነቶችን በሚጥስ ሁኔታ ለደረሰ አካባቢያዊ ጉዳት ተጠያቂ እና ካሳ የመክፈል ግዴታ የሚኖርበት ጉዳት ያደረሰው ሀገር እንጂ ግለሰቦች አይሆኑም፡፡

6.2 ሀገራት በአካባቢ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች ያለባቸው ተጠያቂነት

በአካባቢ ላይ የሚደርስ ጉዳት ጉዳቱ እንዲከሰት ምክንያት በሆነው እንቅስቃሴ የሚገኘው ሀገር ላይ፣ በድንበር በሚዋሰኑ ሀገራት ላይ እንዲሁም የአለም ህዝብ በጋራ የሚጠበቅባቸው የተፈጥሮ ሀብቶች (ባህሮች እና ውቅያኖሶች) ላይ ትልቅ ተጽእኖ ያደርጋል፡፡የሀገራት ተጠያቂነት በሁለት የሚከፈል ሲሆን እነዚህም በጥፋት ላይ የተመሰረተ ተጠያቂነት (fault responsibility) እና ጥፋት ሳይኖር የሚኖር ተጠያቂነት (strict responsibility) በመባል ይታወቃሉ፡፡ሀገራት በጥፋት ላይ የተመሰረተ ተጠያቂነት የሚኖርባቸው ተገቢ ጥንቃቄ ባለማድረግ በሚከሰቱ አካባቢያዊ ጉዳቶች ላይ ሲሆን ጥፋት ሳይኖር ሀገራት ተጠያቂ የሚሆኑት አንድ በአለም አቀፍ ህግ ያልተከለከለ እንቅስቃሴ በአካባቢ ላይ ጉዳት ቢያስከትል ለጉዳቱ ምክንያት የሆነው ሀገር ጥፋት ሳይኖር ተጠያቂነት ይኖርበታል፡፡ለዚህም እንደ ጥሩ ምሳሌ የሚጠቀሱት የኒኩሊየር እና የኬሚካል ኢንዱስትሪዎች ናቸው፡፡

በአለም አቀፉ ልማዳዊ ህግ (Customary international law) መሰረት ሀገራት የሌሎች ሀገሮችን መብት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩ እንቅስቃሴዎችን በግዛታቸው ውስጥ ማካሄድ ወይም እንዲካሄዱ መፍቀድ የለባቸውም፡፡በተጨማሪም በስቶክሆልም ዲክላሬሽን መርህ 21 ላይ እንደተጠቀሰው ሀገራት የአካባቢ ፖሊሲዎቻቸውን መሰረት በማድረግ በግዛቶቻቸው የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶችን የመጠቀም ሉአላዊ መብት እና በግዛቶቻቸው የሚደረጉ ማንኛውም አይነት እንቅስቃሴዎች በሌሎች ሀገሮች አካባቢ ላይ ምንም አይነት ጉዳት እንደማያደርስ ማረጋገጥ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ይህ የሀገራት ግዴታ “የሀገራት መልካም ጉርብትና” (good neighbourliness) ለሚለው አጠቃላይ መርህ ዋና መገለጫ ሲሆን ሁለት አጠቃላይ ግዴታዎች በአለም አቀፉ የልማዳዊ ህግ ውስጥ ተለይተው ይታወቃሉ እነዚህም

- ብክለት እና አካባቢያዊ ጉዳቶችን የመከላከል፣የመቀነስ እና የመቆጣጠር ግዴታ እና
- በአካባቢ ላይ የሚደርሱ አደጋዎችን ለመቀነስ የሚያስችሉ የማስታወቅ (notification) የመመካከር እና ድርድር የማድረግ እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ማካሄድንም ይጨምራል፡፡

6.3 በአካባቢ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች የግለሰቦች የፍትሀ ብሔር ተጠያቂነት

በአካባቢ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች በዋናነት ሶስት መሰረታዊ የግለሰቦች የፍትሀ ብሔር ተጠያቂነቶች ይኖራሉ፡፡እነዚህም

በጥፋት ላይ የተመሰረተ ተጠያቂነት፡-ተጠያቂነቱ በጥፋት ላይ የተመሰረተ በሚሆንበት ወቅት ከሳሹ ተከሳሹ አካባቢያዊ ጉዳቱን ያደረሰው በቸልተኝነት ወይም ተገቢውን ጥንቃቄ ባለማድረግ ስለመሆኑ የማስረዳት ሸክም ይኖርበታል፡፡

ጥፋት ሳይኖር የሚኖር ተጠያቂነት፡- ይህ አይነቱ ተጠያቂነት በአካባቢ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች በዋናነት ያለ የተጠያቂነት አይነት ነው፡፡የዚህ አይነቱ ተጠያቂነት ዋና አላማ በተፈጥሮ ጉዳት የማድረስ አቅም ያላቸው ወይም አደገኛ በሆኑ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሰማርተው የሚገኙ አካላት ከስራዎቻቸው ጋር ተያያዥ በሆኑ ምክንያቶች ለሚደርሱ ጉዳቶች ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ ሲሆን የበከለ ይክፈል ለሚለው መርህ ዋና መተግበሪያ መንገድ ነው፡፡ ጥፋት ሳይኖር በሚኖር ሀላፊነት ወቅት ጥፋት ስለመፈጸሙ ከሳሽ እንዲያስረዳ የማይጠበቅበት ሲሆን የዚህ ተጠያቂነት ዋና ጉዳይ ተከሳሹ ጉዳቱን ያደረሰው በማወቅም ይሁን ባለማወቅ መሆኑ ሳይሆን ጉዳቱ የደረሰው በተከሳሹ አድራጎት መሆኑን ማረጋገጡ ላይ ነው፡፡ይህም ማለት ተከሳሽ እንዲያስረዳ የሚጠበቅበት በተከሳሹ አድራጎት እና በደረሰው አካባቢዊ ጉዳት መካከል ያለውን የምክንያት እና ውጤት ግንኙነት ይሆናል፡፡

ሆኖም ጥፋት ሳይኖር በሚኖር ተጠያቂነት ወቅት ተከሳሾች የቀረበባቸውን ክስ የሚከላከሉባቸው የተለያዩ የመከላከያ ስልቶች ይኖራቸዋል፡፡ለምሳሌ አካባቢያዊ ጉዳቱ የደረሰው በተፈጥሮ አደጋ፣በጦርነት ወይም በሶስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት በሚሆንበት ወቅት ተከሳሹ ከህግ ተጠያቂነት ነፃ ይሆናል፡፡

ፍፁም ተጠያቂነት (Absolute Liability) - ይህ አይነቱ ተጠያቂነት ጥፋት ሳይኖር ከሚኖር ተጠያቂነት የተለየ ሲሆን ተከሳሾች በተፈጥሮ አደጋ ከሚደርሱ ጉዳቶች በስተቀር ተጠያቂ የሆኑበትን ክስ መከላከል አይችሉም፡፡በአካባቢ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች የሚኖር ፍፁም ተጠያቂነት በጣም አነስተኛ ሲሆን

ተጠያቂነቱም ከኒኩሊየር ተቋማት ጋር ተያያዥ የሆኑ አካባቢያዊ ጉዳቶች ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡

6.4. በአካባቢ ላይ የሚደርስ ጉዳትን በተመለከተ የሚኖር የወንጀል ተጠያቂነት

በአካባቢ ላይ የሚኖር የወንጀል ተጠያቂነት (environmental crime) ማለት ሆን ተብሎ በአካባቢ ላይ ጉዳት ለማድረስ የሚደረግ ድርጊት ወይም አካባቢን ለመንከባከብ እና ለመጠበቅ መወሰድ የሚገባቸውን ተገቢ እርምጃዎችአለማድረግ (ommission) ሲሆን ይህም የአካቢ መጎሳቆልን በማስከተል በሰዎች እና በተፈጥሮ ሀብቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ አድራጎት ነው[33]፡፡ እነዚህ ወንጀሎች በአብዛኛው በአካባቢ ላይ ቀጥተኛ የሆነ ጉዳትን የሚያስከትሉ ሲሆን ዋነኞቹም ህገ ወጥ የዱር እንስሳት ዝውውር፣ህገ ወጥ የአደገኛ ቆሻሻዎች የንግድ ዝውውር ፣ህገ ወጥ እና ቁጥጥር የማይደረግበት የዓሳ ማጥመድ እና ህገ ወጥ የዛፍ መቁረጥ ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ ህግ በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን በሚመለከት የሚኖር የወንጀል ተጠያቂነት በወንጀል ህጉ እና በተለያየ ግዜ በተደነገጉ የተለያዩ ህጎች ላይ ተዘርዝረው ይገኛሉ፡፡ በወንጀል ህጉ እና አካባቢን በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ በወጡ ሌሎች ልዩ ህጎች ጋር ግጭት እንዳይኖር በወንጀል ህጉ አንቀፅ 3 እና 7 መሰረት የወንጀል ህጉ እንደተጠበቀ ቢሆንም ቅጣት የሚደነግጉ ደንቦችና ልዩ ህጎች የተጠበቁ እንደሆኑ የተገለፀ ሲሆን በእነዚህ ደንቦችና ህጎች ላይ በተለየ አኳኋን ካልተደነገገ በቀር የወንጀል ህጉ መርሆች በልዩ ህጎቹም ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡ለምሳሌ በብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995 አንቀፅ 12(3) ላይ እንደተገለፀው በወንጀለኛ መቅጫ ህግ መሰረት የከበደ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር በአዋጁ የተደነገጉት ቅጣቶች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ ተገልጿል፡፡በብክለት ቁጥጥር አዋጅ አንቀፅ 12 ላይ እንደተጠቀሰው በአዋጁ ወይም አግባብ ያለውን ሌላ ህግ የተላለፈ ነገር ግን ጥፋቱ በወንጀለኛ መቅጫ ህግም ሆነ በዚህ አዋጅ ቅጣት ያልተመደበለት ሆኖ የተገኘ ማንም ሰው ጥፋተኝነቱ ሲረጋገጥ

> ሀ) የተፈጥሮ ሰው ሲሆን፣ከአምስት ሺህ ብር በማያንስና ከአስር ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከአንድ አመት በማይበልጥ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፣
>
> ለ) በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሲሆን ከአስር ሺህ ብር በማያንስና ከሀያ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

[33] Environmental Crime,A threat to our future,Environmental Investigation Agency

በሌላ በኩል በዚሁ የብክለት ቁጥጥር አዋጅ ውስጥ አካባቢን በተገቢው ሁኔታ ለመንከባከብ እና ለመቆጣጠር ይቻል ዘንድ የአካባቢ ተቆጣጣሪዎች ስልጣንና ተግባራት ተዘርዝረዋል፡፡በብክለት ቁጥጥር አዋጅ አንቀፅ 8 መሰረት የአካባቢ እንክብካቤ ተቆጣጣሪዎች የአካባቢ ደረጃዎችና ተዛማች ግዴታዎች በስራ ላይ መዋላቸውን የሚያረጋግጡ ሲሆን ይህንንም ለማሳካት ሳያሳውቁ ወይም የፍርድ ቤት ትእዛዝ ሳይዙ በማንኛውም ተገቢ መስሎ በሚታያቸው ጊዜ ወደ ማንኛውም ቦታ ወይም ቅጥር ግቢ መግባት ይችላሉ፡፡ህጉም የአካባቢ ተቆጣጣሪዎች ስራቸውን በተገቢው ሁኔታ እና ያለምንም እንከን ማከናወን እንዲችሉ የህግ ጥበቃ የተደረገላቸው ሲሆን በብክለት ቁጥጥር አዋጅ አንቀፅ 13 መሰረት

1) የተመደበ ተቆጣጠሪን ሥራውን እንዳያከናውን ያደናቀፈ ወይም ያሰናከለ፣ ተቆጣጣሪው በህግ መሰረት የጠየቀውን ወይም ያዘዘውን ያልፈፀመ፣ በማስመሰል ተቆጣጣሪ ነው ሊባል የሞከረ፣ተቆጣጣሪው ወደ ማንኛውም ቦታ ወይም ቅጥር ግቢ እንዳይገባ ወይም መዛግብት እንዳይመረምር ያደናቀፈ ማንኛውም ወረቀት፣ ማህደር፣ወይም ሌላ ሰነድ እንዳይፈትሽ፣እንዳይገለብጥ፣ ወይም ለይቶ እንዳይቀዳ የከለከለ፣ያሳሳተ ወይም የተሳሳተ መረጃ የሰጠ ጥፋት ፈፅሟል፡፡
2) በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 መሰረት ጥፋት የፈፀመ የተፈጥሮ ሰው ጥፋተኝነቱ ሲረጋገጥ ከሶስት ሺህ ብር በማያንስ እና ከአስር ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፣ጥፋቱን የፈፀመው በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ ደግሞ ጥፋተኝነቱ ሲረጋገጥ ከብር አስር ሺህ በማያንስና ከብር ሀያ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፣የስራ ሀላፊውም ከአንድ አመ በማያንስ እና ከሁለት አመት በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

አደገኛ የሆነ ቆሻሻንና ሌላ ቁስን በተመለከተ የሚፈፀሙ ጥፋቶች የሚያስከትሏቸውን የወንጀል ተጠያቂነት በሚመለከት በወንጀል ህጉ እና በብክለት ቁጥጥር አዋጅ 300/1995 ላይ የተለያዩ የቅጣት ወሰኖች ይገኛሉ፡፡ በወንጀል ህጉ በአንቀፅ 520 ላይ እንደተጠቀሰው

ማንም ሰው፡-

ሀ) አደገኛ ቆሻሻን ወይም አደገኛ ነገርን አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት ያልያዘ እንደሆነ፤ወይም

ለ) አደገኛ ቆሻሻን ወይም አደገኛ ነገርን በሚመለከት መለጠፊፍ ያለበትን ዝርዝር ያልለጠፈ እንደሆነ፤ወይም

ሐ) ያልተፈቀደ የአደገኛ ቆሻሻ ወይም የአደገኛ ነገር ዝውውር ያካሄደ እንደሆነ፤

ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከሶስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

በሌላ በኩል አደገኛ የሆነ ቆሻሻንና ሌላ ቁስን በተመለከተ የሚፈፀሙ ጥፋቶች የሚያስከትሏቸውን የወንጀል ተጠያቂነት በሚመለከት የብክለት አዋጁ በአንቀፅ 15 ላይ የሚከተለውን ደንግጓል

1) አንድ ሰው አደገኛ ቆሻሻን ወይም አደገኛ ነገርን አግባብ ባላቸው ህጎች መሰረት ካልያዘ፣መለጠፍ ያለበትን ዝርዝር አሳስቶ ከለጠፈ ወይም ጭራሹኑ ካልለጠፈ፣ወይም ደግሞ ማንኛውንም አደገኛ ቆሻሻን፣ ወይም ሌላ ነገርን በተመለከተ መረጃ ከነፈገ ወይም ያልተፈቀደ የአደገኛ ቆሻሻ ዝውውርን ለማካሄድ ከሞከረ ወይም ካካሄደ ወይም ደግሞ እንዲካሄድ ለመርዳት ከሞከረ ወይም ከረዳ ጥፋተኛ ነው፡፡
2) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት ጥፋት የፈፀመ የተፈጥሮ ሰው ጥፋተኝነቱን ሲረጋገጥ ከሀያ ሺህ ብር በማያንስና ከሀምሳ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ፣ጥፋቱን የፈፀመው በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካ ከሆነ ደግሞ ከሀምሳ ሺህ ብር በማያንስና ከአንድ መቶ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

በተመሳሳይ ብክለትን በሚመለከት ስለሚፈፀም ጥፋት በብክለት ቁጥጥር አዋጁ እና በወንጀል ህጉ ላይ የተለያዩ ቅጣቶች ተቀምጠው ይገኛሉ፡፡ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 519 ላይ እንደተገለፀው

1) ማንኛውም ሰው አግባብነት ያለውን ሕግ በመተላለፍ በካይ ነገሮችን ወደ አካባቢው የለቀቀ እንደሆነ፤ከአስር ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራት ይቀጣል፡፡
2) ብክለቱ በሰዎች ህይወት ወይም ጤና ወይም በአካባቢ ላይ ከፍ ያለ ጉዳት አድርሶ እንደሆነ፤ቅጣቱ ከአስር አመት የማይበልጥ ፅኑ እስራት ይሆናል፡፡
3) ጥፋተኛው በዚህ ድርጊት ከፍተኛ ቅጣት የሚያስከትል የወንጀል ህግ ድንጋጌ ጥሶ እነደሆነ፤ስለ ወንጀሎቹ መደራረብ የተፃፉት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

በብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995 አንቀፅ 16 መሰረት

አንድ የተፈጥሮ ሰው የዚህን አዋጅ ወይም በሥሩ የሚወጡትን ደንቦች በመተላለፍ በካን ወደ አካባቢ በመልቀቅ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ፣ከአንድ ሺህ ብር በማያንስና ከአምስት ሺህ ብር በማያንስና ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም ከአንድ አመት በማያንስና ከአስር ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል።ጥፋቱን የፈፀመው በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ከሆነ ከአምስት ሺህ ብር በማያንስና ከሀያ አምስት ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፣የሥራ ሀላፊውም ከአምስት አመት በማያንስና ከአስር ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር በማያንስና ከአስር ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማን በተመለከተ በወንጀል ህጉ አንቀፅ 521 መሰረት ማንም ሰው የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ እንዲደረግበት በህግ የታዘዘውን ማናቸውንም ፕሮጀክት ከተገቢው አካል ፈቃድ ሳያገኝ ተግባራዊ ያደረገ እንደሆነ ወይም ይህንኑ በሚመለከት ሀሰተኛ መረጃ ያቀረበ እንደሆነ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ይቀጣል። የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995 አንቀፅ 18 መሰረት

1) የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኑ፣ይህን አዋጅ ወይም ሌላ አግባብ ያለውን ህግ ወይም መመሪያ የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው ጥፋት ፈፅሞአልና ቅጣት ይጣልበታል።
2) ማንኛውም የፕረጀክት ባለቤት የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ እንዲካሄድበት የተደነገገበትን ማንኛውም ፕሮጀክት፣ከባለስልጣኑ ወይም ከሚመለከተው የክልል የአካባቢ መስሪያ ቤት ይሁንታ ሳያገኝ ተግባራዊ ያደረገ እንደሆነ ወይም በአካባቢ ተፅእኖ የጥናት ዘገባው ውስጥ ሀሰተኛ መግለጫ ያቀረበ እንደሆነ ወይም ጥፋት ፈፅሟልና ከሀምሳ ሺህ ብር በማያንስና ከአንድ መቶ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።
3) ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሰረት ፈቃድ ሲሰጠው የተጣለበትን ግዴታ ካልተወጣ፣ወይም ተፈላጊ ዝርዝሮችን በመዝገብ ሳያሰፍር ከቀረ ጥፋት ፈፅሞአልና ከአስር ሺ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።
4) በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ጥፋት ሲፈፅም ድረጅቱ እንዲከፍለው ከተፈረደበት መቀጮ በተጨማሪ የህጉን መከበር ለማረጋገጥ መፈፀም የሚገባውን

ተግባር በትጋት ያልተወጣ በመሆኑ የሥራ መሪው ከአምስት ሽ ብር በማያንስና ከአስር ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

5) ይህን አዋጅ ወይም በሥሩ የሚወጣውን ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያ በመጣስ ጥፋተኝነቱ የተረጋገጠበትን ሰው፣ ከሚወሰንበት ከማንኛውም ቅጣት በተጨማሪ የደሰውን ጉዳት በሙሉ በራሱ ወጪ እንዲያስተካክል ወይም እንዲተካ ፍርድ ቤቱ ማዘዝ ይችላል፡፡

ስለመውረስ እና ወደ ነበረበት ሁኔታ ስለመመለስ በተመለከተም የብክለት ቁጥጥር አዋጁንና በሥሩ የሚወጡትን ደንቦች በመጣስ ጥፋተኝነቱ በተረጋገጠበት ሰው ላይ ከሚወሰንበት ማንኛውም ቅጣት በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ

ሀ) ለጥፋቱ ተግባር የዋለ ማንኛውም ነገር ተወርሶ ለመንግስር ገቢ እንዲሆን ወይም በሌላ መንገድ እንዲወገድ፣

ለ) አካባቢውን የማፅጃ ወይም መሣሪያውን፣ኬሚካሉን ወይም ዕቃውን የማስወገጃ ወጪ ተከሳሹ እንዲከፍል፣እንደዚሁም፣

ሐ) ጉዳት የደረሰበትን አካባቢ ተከሳሹ በራሱ ወጪ ወደ ነበረበት ሁኔታ እንዲመልስ ወይም ደግሞ ይህ የማይቻል ከሆነ ተገቢ ካሳ እንዲከፍል ማዘዝ ይችላል፡፡

የኢትዮጵያን የዱር እንስሳት ሀብት ለመጠበቅ፣ለመንከባከብ፣ለማልማትና በአግባቡ ጥቅም ላይ ለማዋል በተጨማሪም የዱር እንስሳት ሀብትን አጠቃቀም፣እንክብካቤና አጠቃቀም በሚመለከት መንግስት በዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች መሰረት የገባቸውን ግዴታዎች ለመፈፀም እንዲቻል የዱር እንስሳት ልማት፣ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 541/2007 ተደንግጓል፡፡ በአዋጁ መሰረት የግብርናና የገጠር ልማት ሚኒስቴር ወይም የሚመለከተው የክልል አካል ተግባሩን ለማከናወን በሚያደርገው ሂደት ምክንያት ከሚፈፅመው አደን በስተቀር ማንኛውም ሰው የአደን ፈቃድ ሳይዝ የዱር እንስሳትን ማደን የተከለከለ እንደሆነ በአዋጁ አንቀፅ 3 ላይ ተደንግጓል፡፡በሌላ በኩል በአዋጁ አንቀፅ 9(1) ላይ እንደተገለፀው ከታወቀ የሳይንስ ተቋም የተጻፈ የድጋፍ ደብዳቤ በመያዝ የዱር እንስሳት ወይም ውጤት ለመሰብሰብና ለሳይንሳዊ ተግባር ወይም ትምህርት ለማዋል ለሚጠይቅ አመልካች የግብርና እና የገጠር ልማት ሚኒስቴር ፍቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

በተጨማሪም ከግብርና እና የገጠር ልማት ሚኒስቴር ወይም ከሚመለከተው የክልል አካል በተገኘ ፈቃድ መሰረት ካልሆነ በስተቀር በዱር እንስሳትና በዱር እንስሳት ውጤት የመነገድ ተግባር የማካሄድ እና ማንኛውንም የተዘጋጀ ወይም ያልተዘጋጀ የዱር እንስሳት ውጤት በባለቤትነት መያዝ፣መሸጥ፣ማስተላለፍ፣ወደ ሌላ አገር መላክ ወይም ወደ አገር ውስጥ ማስገባት በአዋጁ አንቀፅ 12 (1) መሰረት የተከለከለ ነው፡፡ አዋጁ ህገ ወጥ የዱር እንስሳት አደንን እና ንግድን የሚፈፅሙ የወንጀል ተጠያቂነት ያለባቸው ሲሆን በአዋጁ አንቀፅ 16 መሰረት

በወንጀለኛ ህግ መሰረት የበለጠ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር

ሀ) ማንኛውም ሰው፣

1) ህገ ወጥ የዱር እንስሳት አደን ወይም ንግድ ድርጊት ከፈፀመ፣
2) በዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች ውስጥ ያልተፈቀዱ ተግባሮችን ካከናወነ ወይም በማናቸውም አካኋን በነዚሁ ላይ ጉዳት ካደረሰ፣ወይም
3) የዱር እንስሳትን ወይም የዱር እንስሳት ውጤቶችን ያለፍቃድ ይዞ ከተገኘ፣

ከብር 5000 ሺህ በማያንስና ከብር 30000 ሺህ በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከአንድ ዓመት በማያንስና ከአምስት አመት በማይበልጥ እስራት ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

በከፍተኛ ደረጃ ጎልቶ በሚታየው የኢትዮጵያ የደን ሀብት መመናመን ምክንያት እየተከሰተ ያለውን የአፈር መከላት፣የበረሀማነት መስፋፋት፣የተፈጥሮ ሚዛን መዛባት፣የብዝሀ ህይወት መመናመንና የግብርና ምርት ማሽቆልቆልን ለመግታት ይቻል ዘንድ የደን ልማት፣ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 542/2007 ተደንግጓል፡፡ በአዋጁ አንቀፅ 14 ላይ እንደተገለፀው ማንኛውም ሰው ከግብርና እና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል የፅሁፍ ፈቃድ የተሰጠው ካልሆነ በስተቀር፣በመንግስት ደኖች ውስጥ ዛፍ መቁረጥ፣በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት መስፈር፣የቤት እንስሳትን ለግጦሽ ማሰማራት፣አደን ማካሄድ የእንጨት መሰንጠቂያ መጋዞችና ሌሎች ለደን ጭፍጨፋ የሚረዱ መሳሪያዎችን ይዞ መገኘት፣ቀፎ መስቀል ወይም ማር መቁረጥ፣አይችልም፡፡ በተጨማሪም በመንግስት ደኖች ውስጥ ሰፋፊ እርሻ፣የማዕድን ስራ፣የመንገድ ስራ፣የውሀ ቁፋሮ፣የመስኖና የግድብ ስራ የመሳሰሉ የኢንቨስትመንት ሥራዎች ለማካሄድ ወይም እነዚህኑ በተመለከተ የሥራ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት ከግብርና እና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል ጋር በቅድሚያ በመመካከር ስምምነታቸውን ማግኘት እንደሚያስፈልግ ተገልጿል፡፡

የደን ልማት፣ጥበቃና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 542/2007 በደኖች ላይ ጉዳት የሚያደርሱ የተለያዩ ህገ-ወጥ ድረጊቶችን ለማስቀረት የሚያስችሉ ቅጣቶችን አስቀምጧል፡፡ በአዋጁ አንቀፅ 20 መሰረት ከመንግስት ደኖች ዛፎችን የቆረጠ ወይም የደን ውጤቶችን የወሰደ፣ያዘጋጀ ወይም በማንኛውም መንገድ የተጠቀመ ከ አንድ ዓመት በማያንስና ከ አምስት ዓመት በማይበልጥ እስራት እና በብር አስር ሺህ እንደሚቀጣ ደንግጎ ይገኛል፡፡በሌላ በኩል እሳት መበለኮስ ወይም በማናቸውም ሌላ ሁኔታ በደን ላይ ጉዳት ያደረሰ ከ አስር አመት በማያንስና ከ አስራ አምስት አመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እንደሚቀጣ ተገልጿል

6.5. በአካባቢ ላይ ለሚደረሱ ጉዳቶች የካሳ አከፋፈል

በአብዛኛው በአካባቢ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶችን በገንዘብ ለመተመን በጣም አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ለምሳሌ በብዝሀ ህይወት፣በስነ መሕድር በመሬት አቀማመጥ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶች ኢኮኖሚያዊ እሴት እንደ ሌሎች ጉዳቶች በቀላሉ ለመተመን አይቻልም፡፡ነገር ግን የአካባበቢ ሀብቶችን በገንዘብ መተመን አይቻልም ማለት በአካባቢ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች ተጠያቂነት አይኖርም ማለት አይደለም፡፡ በመሆኑም የአካባቢያዊ ሀብቶችን ኢኮኖሚያዊ እሴት እንዴት በገንዘብ ማስላት ይቻላል የሚለው ሀሳብ በብዙዎች ዘንድ ትልቅ ጥያቄን የሚፈጥር ነው፡፡ጉዳቶቹን ለመተመን የሚያስችሉ መስፈርቶች በተለያዩ የህግ ሥርአቶች የተዘጋጁ ሲሆን ለምሳሌ ያህል አንደኛው መንገድ ጉዳት በደረሰበት የተፈጥሮ ሀብት ይገኙ የነበሩ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን በማስላት ሲሆን በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነትን ያገኘው መፍትሄ ጉዳት የደረሰበትን አካባቢ ቀድሞ ወደ ነበረበት ሁኔታ ለመመለስ የሚያስፈልገውን ወጪ በማስላት ነው፡፡

በአንዳንድ ሁኔታዎች በአካባቢ ላይ ጉዳት ያደረሰውን ግለሰብ ወይም ተቋም በትክክል ለመለየት አስቸጋሪ የሚሆንበት ግዜ አለ፡፡ለምሳሌ ከአንድ በላይ የሆኑ አደገኛ ቆሻሻን የሚያመነጩ ተቋማት ተመሳሳይ የሆነ አደገኛ ቆሻሻን በቆሻሻ ማራገፊያ ስፍራ ቢጥሉ እያንዳንዱ ተቋም ለአካባቢ ብክለት ያደረገውን አስተዋፅኦ በትክክል ለመለየት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡በእነደዚህ አይነት አጋጣሚዎች አንዳንድ የተጠያቂነት ደንቦች ሁሉንም ለአካባቢው መበከል አስተዋጽኦ ያደረጉትን ተቋማትን ተጠያቂ የሚያደርግ ሲሆን ይህም የጋራ እና የግል ተጠያቂነት (Joint and several liabilities) በመባል ይታወቃል፡፡የጋራ እና የግል ተጠያቂነት ለከሳሹ ሰፋ ያለ አማራጭን የሚፈጥር ሲሆን በተለይ በአካባቢ ላይ ለደረሰው ጉዳት የምክንያት እና ውጤት ግንኙነትን ለመመስረት ከአንድ በላይ በካይ ላይ ትኩረት ለማድረግ የሚያስችል ሲሆን ለደረሰው ጉዳት ካሳ የማግኘት እድል የሰፋ ይሆናል፡፡በተጨማሪም በጋራ እና በተናጠል

ተጠያቂነት ደንብ መሰረት በአካባቢ ላይ ለደረሰው ጉዳት ተጠያቂ የሆነው አካል በአካባቢው ላይ ብክለት እንዲደርስ አስተዋጽ ያደረጉ ሌሎች አካላት ላይ ክስ እንዲመሰርት ይፈቀድለታል፡፡

አብዛኛዎቹ የፍትሐ ብሔር ተጠየቂነት ህጎች በተለያዩ የልማት እንቅስቃሴዎች ላይ ተሰማርተው የሚገኙ ተቋማት በአካባቢ ላይ አደጋ ሊያደርሱ ይችላሉ ተብሎ ስለሚገመት ተገቢውን ካሳ ለማግኘት የሚያስችል አስገዳጅ የኢንሹራንስ ዋስትና እንዲገቡ ይደረጋል፡፡የአስገዳጅ ኢንሹራንስ ዋስትና ዋና አላማ ተቋማት ኪሳራ ቢገጥማቸው በአካባቢ ላይ ለሚያደርሱት አደጋ ተገቢውን ካሳ መክፈል እንደሚችሉ ለማረጋገጥ ነው፡፡ነገር ግን የአስገዳጅ የኢንሹራንስ ዋስትና ተቋማት ለሚያከናውኗቸው እንቅስቃሴዎች ተገቢውን ጥንቃቄ እና የቅድመ መከላከል ስራዎችን እንዳያከናውኑ ሊያደርግ ይችላል፡፡ሌላው ችግር የኢንሱራንስ ዋስትና የሚሰጡ ድርጅቶች የኢንሹራንስ ሽፋን የሚሰጡት የአደጋውን ግዝፈት እና ተተንባይነት በማጣራት በተወሰኑ የአካባቢ ጉዳቶች ላይ ነው፡፡እንደዚህ አይነት ችግሮችን ለመፍታት የተለያዩ የተጠያቂነት ሥርዐቶች የካሳ ክፍያ ጣሪያ የሚያስቀምጡ ሲሆን መጠኑም የተለያዩ ዘርፎች በአካባቢ ላይ ሊያደርሱ እንደሚችሉት አካባቢያዊ ጉዳት የተለያየ ይሆናል፡፡

ሌላኛው በአካባቢ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች ተገቢው ካሳ መከፈሉን የማረጋገጫ መንገድ በአንድ የተወሰነ ዘርፍ ላይ ተሰማርተው በሚያንቀሳቅሱ ተቋማት በሚመሰረት የአደጋ ተጎጂዎች የካሳ ፈንድ በማቋቋም ነው፡፡የካሳ ፈንዱ የሚቋቋምበት ዋና አላማ በአካባቢ ላይ በሚደርሱ አደጋዎች ተጎጂ ለሆኑ አካላት ተገቢውን ካሳ መክፈል እና ጉዳት ያደረሰው ተቋም በተለያዩ ምክንያቶች ለተጎጂዎች ካሳ መክፈል ሳይችል ሲቀር ተገቢውን ካሳ መክፈል ነው፡፡ እንደዚህ አይነቱ የጉዳት ካሳ አከፋፈል ዘዴ በዋናነት የሚስተዋለው ከመርከቦች ላይ በሚፈስ ነዳጅ አማካይነት የሚፈጠረውን ብክለት ለመቆጣጠር እ.ኤ.አ በተደነገገው The International Convention on the Establishment of an International Fund for Compensation for Oil Pollution Damage) ውስጥ ነው፡፡በአጠቃላይ በአለም ላይ በአካባቢ ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች የተጠያቂነት እና የካሳ አከፋፈልን በሚመለከት በርካታ የተደነገጉ አለም አቀፍ ስምምነቶች ሲኖሩ ዋና ዋናዎቹ

- እ.ኤ.አ በ 1996 ዓ.ም የፀደቀው International Convention on liability and compensation for damage in connection with the carriage of hazardous and noxious substances by sea
- እ.ኤ.አ በ 2001 ዓ.ም የፀደቀው The International Convention on civil liability for bunker oil pollution damage.
- እ.ኤ.አ በ 1977 ዓ.ም የፀደቀው The Convention on civil liability for oil pollution damage resulting from exploration for and exploitation of seabed mineral resource

- **እ.ኤ.አ በ 1960 ዓ.ም የፀደቀው** Paris convention on third party liability in the field of nuclear energy
- **እ.ኤ.አ በ 1963 ዓ.ም የፀደቀው** International Atomic enregys convention on civil liability for nuclear damage
- **እ.ኤ.አ በ 1971 ዓ.ም የፀደቀው** The convention relating to civil liability in the field of martime carriage of nuclear material
- **እ.ኤ.አ በ 1999 ዓ.ም የፀደቀው** Basel protocol on liability and compensation for damage resulting from transboundary movement of hazardous wastes and their disposal

6.6. በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን በሚመለከት የሚኖር የመክሰስ መብት (Right to standing)

አካባቢን በተገቢው ሁኔታ ለመንከባከብ እና ለመጠበቅ ይቻል ዘንድ የኢፌዴሪ ህገ- መንግስት ሁሉም ሰዎች ንፁህ እና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት እንዳላቸው በህገ-መንግስቱ በአንቀፅ 44(1) ላይ ደንግጓል። ይህ አንቀፅ በህገ- መንግስቱ ውስጥ የተቀመጠበት ዋና አላማ በአካባቢ ላይ ማንኛውም አይነት ጉዳት በሚደርስበት ወቅት ዜጎች እና ለህዝብ ጥቅም የቆሙ ቡድኖች (Public interest groups) ክስ ለማቅረብ እና በአካባቢ ጉዳዮች ላይ የነቃ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ለማስቻል ነው። በኢትዮጵያ የፍትሀብሄር ሥነ ሥርዐት አንቀፅ 33(2) ላይ እንደተገለፀው ለክሱ መነሻ በሆነው ነገር ወይም ክሱ በተመሰረተበት ሀብት ላይ ጥቅም ወይም መብት ያለው መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር ማናቸውም ሰው ክስ ማቅረብ አይፈቀድለትም። ሆኖም በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን በተመለከተ ማንኛውም ሰው የደረሰበትን ጉዳት ማስረዳት ሳይጠበቅበት የጉዳት ካሳ ክፍያን መጠየቅ ይቻላል።

በሌላ በኩል በኢፌዴሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 37 ላይ እንደተጠቀሰው ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት እንዳለው ተገልጿል:: በህገ- መንግስቱ አንቀፅ 37(ለ) መሰረት ማንኛውንም ቡድን ወይም ተመሳሳይ ጥቅም ያላቸውን ሰዎች የሚወክል ግለሰብ ወይም የቡድን አባል ፍርድ ወይም ውሳኔ የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው። ከአንቀፅ 37(ለ) ለመረዳት እንደሚቻለው ፍትህ የማግኘት መብት በግለሰብ እና በቡድን ደረጃ ሊጠየቅ የሚችል ሲሆን በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን በሚመለከት የአካባቢ ተሟጋቾች፣መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ግለሰቦች ክስ ሊያቀርቡ ይችላሉ። በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን በሚመለከት የሚኖር የመክሰስ መብት የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/2002 አንቀፅ 11 ላይ የተጠቀሰ ሲሆን የሚመለከተው መሆኑን ማስረዳት

ሳይጠበቅበት ማንኛውም ሰው በአካባቢ ላይ ጉዳት አድርሷል ወይም ጉዳት ሊያስከትል የሚችል ተግባር እየፈፀመ ነው በሚለው በማንኛውም ሰው ላይ ለባለስልጣኑ (ለአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን) ወይም ለሚመለከተው የክልል መስሪያ ቤት ቅሬታ የማቅረብ መብት አለው፡፡ በተጨማሪም በዚሁ አዋጅ አንቀፅ 11(2) ላይ እንደተገለፀው ባለስልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መስሪያ ቤት በሰላሳ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ወይም ቅሬታ አቅራቢው በውሳኔው ካልተስማማ፣ውሳኔው ከተሰጠበት ወይም የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ ካለፈበት ቀን አንስቶ በስልሳ ቀናት በውስጥ በፍርድቤት ክስ መመስረት ይችላል፡፡

የመወያያ ጥያቄዎች

1.የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ ሕግ ዋና አላማ አብራሩ፡፡

2. በአካባቢ ላይ በሚደርስ ጉዳት ላይ የሚኖር የፍትሀ ብሔር እና የወንጀል ተጠያቂነትን አብራሩ፡፡

በኢትዮጲያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

ለአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን

አዲስ አበባ

<u>በአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995 አንቀጽ 11 ንዑስ ቁጥር 1 መሰረት የቀረበ አቤቱታ</u>

ቅሬታ አቅራቢ: አክሽን የባለሙያዎች ማህበር ለህዝብ /አፕአፕ/

አክሽን የባለሙያዎች ማህበር ለሕዝብ/አፕአፕ/ እ.ኤ.አ በ1993 ዓ.ም የተቋቋመ ገለልተኛና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ሲሆን የተቋቋመበት ዋነኛ አላማም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉና የተገለሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ማለትም ድሆች፣ ሴቶች፣ ሕፃናትና የሌሎችንም ዞኖች መብቶች ሰብአዊ መብትና ሕግን መሣሪያ/መሰረት በማድረግ ማስጠበቅ ነው።

ድርጅቱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ ከአከናወናቸው ተግባራት ከቀሰመው ልምድ በመነሳት ከያዝነው የአውሮፓውያን 2005 ዓ.መ ጀምሮ ተግባራዊ የሚደረግ የሶስት ዓመት ስትራቴጂክ ፕላን ቀርጸል። አዲሱ ስትራቴጂክ ፕላን በዋነኝነት ያተኮረው በኢኮኖሚ፣በማህበራዊና በባህላዊ መብቶች በተለይም የሕብረተሰባችን ዋነኛ ችግር በሆኑት ትምህርት የማግኘት፣ መጠለያ የማግኘት፣ ምግብ የማግኘትና የጤና አገልግሎት የማግኘት መብቶች ላይ ነው።

አነአነ ለሚቀጥሉት ሶስት አመታት አላማውን እውን ለማድረግ ሶስት ዋና ዋና ፕሮግሞች ቀርፆ እየተቀሳቀሰ ሲሆን፣ እነዚህም የትምህርትና ቅስቀሳ (educational mobilization) ምርምርና ህትመት (reaserch and publication) እና የፖሊሲ ሕግ ማውጣትና ፍርድ ቤት ክርክር (policy work, legislative advocacy and litigation) ፕሮግራሞች ናቸው። እነዚህም ፕሮግራሞች የአፕአፕን አላማ ለማሳካት እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉ ከመሆናቸውም ባሻገር እያንዳንዱ ፕሮግራም የድሆች፣ የሴቶች እና የሕፃናትና ችግሮ ላይ ትኩረት ያደርጋል።

ሶስተኛው የፖሊሲ፣ ሕግ ማውጣትና የሕዝብን ጥቅም በሚመለከቱ ጉዳዮች የፍርድ ቤት ክርክር ማካሄድ ፕሮግራም ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ መብቶችን ተፈፃሚ እንዲሆኑ የሚያስችል አመቺ ፖሊስ፣ ሕግና ደንቦች እንዲወጡ ከማድረጉም በተጨማሪ መብቶቹ ተግባራዊ በማይሆኑበት ወይም በሚጣሰቡት ጊዜ መብቶቹ የተጣሰባቸው ዜጎች በፍርድ ቤት መፍትሔ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። ይኽ ለዚህ መስሪያ ቤት የቀረበው አቤቱታው በዚህ ፕሮግታም ስር የሚሰሩ ስራዎች አካል

ሲሆን በዜጎች የጤና መብት ላይ እየደረሰ ላለው ጥሰት አስተዳደራዊ መፍትሄ ለማስገኘት የቀረበ ነው።

እንደሚታወቀው አገራችን ኢትዮጵያ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ መብቶች አለም አቀፍ ቃል ኪዳን ስምምነትን ከፈረሙ አገራት መካከል አንዷ ነች። በዚህ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ስምምነት ላይ እያንዳንዱ ግለሰብ ክብር ያለው ሕይወት እንዲኖር አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ መብቶ የተካተቱ ሲሆን ከእነዚህ መብቶች ውስጥም በስምምነቱ አንቀጽ 12 ላይ የሰፈረው የጤና መብት አንዱና ዋነኛው ነው። ይህ አንቀጽ ሊገኝ የሚችል ከፍተኛ የጤንነት ደረጃ ለማግኘት አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ መገልገያዎች፣ ቁሳቁስ አገልግሎትና ሁኔታዎች የማግኘት መብት የሰው ልጆች መሰረታዊ መብት እንደሆነ አረጋግጦአል። መብቱ ለእያንዳንዱ ዜጋ የሚያጎናጽፋቸው የለተያዩ መብቶች ያሉ ሲሆን እነሱም የእናቶችም እንዲሁም የስነ ተዋልዶ ጤና መብት፣ ጤንነቱ የተጠበቀ የተፈጥሮ እንዲሁም የስራ ቦታ የመኖር መብት፣ የበሽ መከላከያ ምርመራ እንዲሁም መቆጣጠሪያ የመግኘት መብት እና የጤና መገልገያዎች ቁሳቁስ እና አገልግሎቶችን የማግኘት መብት ናቸው።

እነዚህ ከላይ የተገለጹት መብቶች እውን ሆነው ሁሉም ዜጋ የመብቶቹ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማድረግ ግዴታ በዋነኝነት የመንግስት ሲሆን መንግስት ፖሊሲችንና የተለያዩ ህጎችን በማውጣትና ሌሎች አስፈላጊ ዕርምጃዎችን በመውሰድ መብቶቹ ለሁሉም ዜጎች እውን መሆናቸውን የሚረጋግጥ ግዴታ አለበት።

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የጤና መብት ከሚያካትታቸው መብቶች መካከል አንዱ ጤንነቱ በተጠበቀ የተፈጥሮ እንዲሁም የስራ አካባቢ የመኖር መብት ነው። ይህም መብት ልክ እንደሌሎቹ ሰብዓዊ መብቶች በመንግስት ላይ ሶስት ግዴታዎችን የሚጥል ሲሆን መንግስት መብቱን በተመለከተ ያለበትን የማክበር፣ የማስከበር እና የማሟላት ግዴታ ቀጥሎ ለማሳየት እንሞክራለን።

የመንግስት የማህበር ግዴታ፡- በዚህ ግዴታ ስር መንገስት ሊወስዳቸው የሚገቡ እርምጃዎች

- የኑክሊየር ባዮሎጂካ ወይም ኬሚካል የጦር መሳሪያዎች መጠቀም ወይም መሞከር ለጤና ጎጂ የሆኑ ንጥረ ነገሮችን የሚያመነጭ ከሆነ ድርጊቱን ከማድረግ መቆተብ፣
- ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ከባ አየርን ፣ ውሃንና አፈርን ለምሳሌ በመንግስት ይዞታ ስር ባሉ ፋብሪካዎች ተረፈ ምርት ከመበከል መቆተብ አለበት። ከባቢ አየር ጎጂ በሆኑ የማዕድናት ወይም የዘይት ምርትና ፍለጋ፣ በደን ልማት፣ በአሳ ማጥመድ ስራና በእርሻ እንዲመረዝ ወይም እንዲጠፋ መፍቀድ የለበትም።

የማስከበር ግዴታ፡- በዚህ ግዴታ ስር መንግስት ሊወስዳቸው የሚገቡ እርምጃዎች

- በግል ኮርፖሬሽች በማዕድናት አውጪዎች ወይም አምራች ፋብሪከዎች ውሃ፣ አየር እ አፈር እንዳይበከል ለመከላከል ህጎችን ማውጣትና ማስፈጸም፣
- የአልኮል ምርትን ሽጭን እንዲሁም ሲጋራ እፆችና ሌሎ ጎጂ ንጥረ ነገሮችን መጠቀምን ማዳከም፣
- ግለሰቦች፣ ቡድኖች ድርጅቶችና ኮርፖሬሽች የሌሎችን የጤና መብት እንዳይጥሉ ለመከላከል የሚያጀናውኗቸውን ተግባራት መቆጣጠር፣
- ሽማቾችና ሰራተኞች ለጤናቸው አስጊ ከሆኑ ተግባራት እንዲጠበቁ ማድረግ፣
- ሶስተኛ ወገኖች ጤናን የሚመለከቱ መረጃዎች የማግኘት መብ ላይ ገደብ አለመጣላቸውን ማረጋገጥ ለምሳሌ አሰሪዎች መድሃኒትና ምግብ አምራቾች፡፡ በዚህ ውስጥ በተቻለ መጠን በስራ ቦታ በተፈጥሮ ለጤና ጠንቅ የሆኑ ምክያቶች ሊኖሩ ስለሚችሉ አደጋውን ለመቀነስ የመቆቀጣጠሪያ መንገድ ማበጀት ናቸው፡፡

የማሟላት ግዴታ፡- በዚህ ስር በመንግስት ሊወሰዱ የሚገቡ እርምጃዎች

- ለጤንነት አስፈላጊ ለሆኑ ነገሮች ለምሳሌ ጤናማ የሆነ አልሚ ምግብና ንፁህ የመጠጥ ውሃ፣ መሰረታዊ ንጽህና፣ በቂ የመኖሪያ ቤት እና የኑሮ ሁኔታ ሁሉም ሰው እኩል የማግኘት መብት እንዲኖረው ማረጋገጥ፣
- የአካባቢ አየር እና የስራ ቦታ የጤና ጠንቆች እንዲሁም ሌሎች ማናቸውም ተላላፊ በሽታ በሚመለከት በቀረበ መረጃ የተደገፉ አደጋዎችን ለመከላከል እርምጃዎችን መውሰድ፣ ለዚህም ኣላማ ዓላማቸውን የአየር፣ የውሃ እና የአፈር ብክለትን ለመቀነስ ወይም ለማጥፋት ያደረገ ብሔራዊ ፖሊሲ መቅረጽ እና በተግባር ማዋል፡፡
- የስራ ቦታ አደጋዎችንና በሽታዎችን ለመቀነስ ወጥነት ያው ብሔራዊ ፒሊሲ መቅረጽ በተግባር መዋልና፣ በየጊጊው እንደገና ክለሳ የማድረግ፣
- የስራ ቦታ ጥንቃቄ እንዲሁም የጤና አገልግሎትን በተመለከተ ወጥ የሆነ ብሔራዊ ፖሊሲ የማቅረብ ናቸው፡፡

መንግስት ይህ መብት ለዜጎች እውን እንዲሆን በህገ መንግስት ለመብቱ እውቅና ከመስጠት ጀምሮ የተፈጥሮ አካባቢ ጤንነትን ለመጠበቅ የተለያዩ ዕርምጃዎችን ወስዷል፡፡ በዚህ ረገድ ይህንን የመንግስት መስሪያ ቤት ለማቋቋም የወጣው አዋጅና የዚሁ መስሪያ ቤት እንደገና በተሸለ አደረጃጀት

መደራጀት ፣ የአካባ የፅእኖ ግምገማ አዋጅ የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ እና የህዝብ ጤና አጠባበቅ አዋጅ በዋነኛነት ይጠቀሳሉ፡፡

ወንዝ ማለት ለሰው ልጆች በህይወት መኖር አስፈላጊ የሆነው ውሃ የሚገኝበት ቦታ ነው፡፡ ውሃ ደግሞ አካባቢ በሚለው ትርጉም ውስጥ የሚካተት ነው፡፡ የገርህ የተፈጥሮ አካባቢ ጥራት መለወጥ ወይም የሚሰጠው ጥቅም እንዲቀንስ መደረግ በሰውል ልጆች የጤና መብት ላይ አሉታዊ ተፅኖኖ እንደሚያሳድር ግልጽ ነው፡፡

በአካባበቢ ብክለት በቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995 አንቀጽ 3 ላይ ማንም ሰው ተገቢውን የአካቢ ደረጃ በመተላፍ አካባቢውን ሊበክል ወይም በሌላ ሰው በኩል እንዲበከል ለማድረግ እንደማይችል የተደረገ ሲሆን ህግን በመተላለፍ ማንኛውንም በካይ (Pollutant) ወደ አካባቢ በሚቅ ሰው ላይ የባለስልጣ መስሪያ ቤቱ አስተዳደራዊ ወይም ህጋዊ ዕርምጃ መውሰድ እንደሚችልም ይኸው የሕግ አንቀጽ ይደነግጋል፡፡ በጤና ወይም በአካባቢ ላይ አደጋ እንዳያስከትል ከሚያስሰጋ የስራ እንቅስቃሴ ሊመጣ የሚችል ጉዳትን ለመከላከል የበለስልጣን ስሪሪያ ቤቱ ድርጅትን የመዘጋት፣ የማዛወር እንዲሁም ሌላ ማንኛውንም አስፋጊ ዕርምጃ የመውሰድ ስልጣን በዚሁ የሕግ አንቀጽ ተሰጥቶታል፡፡

አክሽ የባለሙያዎች ማህበር ለህዝብ በአገራችን በሚገኙ ሁለት ወንዞች ማለትም የአቃቂ ወንዝ እና የሞጆ ወንዝ ላይ ብክለት እያረሰ እንደሆነ ሊገነዘብ ችሏል፡፡ ለነዚህ ወንዞች መበከል ወነኛው ምክንያት እንደሆነ ለመረዳት የታቸለው እንደቅደምተከተላቸው በአዲ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሚገኙ የተለያዩ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ ፋብሪከዎች ወደ ወንዙ የሚለቀቁ ፈሳሽ እና ጠጣር የሆኑ በካይ የፋብሪካ ተረፈ ምርቶችና ከከተማው ነዋሪ ወደ ወንዙ የሚለቀቀው ጠጣርና ፈሳሽ ቆሻሻ እና በኦሚያ ክልላዊ መንግስት ምስራቅ ሸዋ ዞን ሞጆ ከተማ ከሚገነው የሞጆ ቆዳ ፋብሪካ ወደ ወንዙ የሚቀቀቀው ፈሰሳሽ ተጣር በካይ የፋብሪካ ተረፈ ምርት ነው፡፡ የነዙግ ወንዞች መበከልም በአካባቢው የሚኖረተውን ህዝብ ጤናማ በሆነ የተፈጥሮ አካባቢ የመኖር መብት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደረ ይገኛል፡፡ ህብረተሰቡ በብክለቱ ምክንያት ከወንዞቹ ማግኘት ይችል የነበረውን ጥቅም ማግኘት ካለመቻሉም በላይ ለህይወቱ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለማግኘት ወንዞቹን ጥቅመ ላይ ለማዋል በሚሞክር ጊዜ የተለያየ የጤና ወታወክ ደርሶበት ህይወቱን አስከማጣት ደርሶአል፡፡ ይህ ነው የማይባል የጤና መታወክና ሞት በተለይ በህፃናት ላይ እየደረሰ ይገኛል፡፡ በአካባቢው የሚገኙ እንስሳትና እጽዋት ላይ እየደረሰ ያለው ጉዳትም በህብረተሰቡ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ሁኔታ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያስከተለ ይገኛል፡፡

ወንዞቹን ጥቅም ላይ ለማዋል አዳጋች ከመሆኑም በተጨማሪ ወንዞቹ ውስጥ የሚለቀቀው ጠጣር ወይም ፈሳሽ በላይ የሚያመነጨው ክርፋት በነዋሪ ህብረተሰብ ጤንነት ላይ የበኩሉን አሉታዊ ትጽእኖ እያሳደረ ይገኛል፡፡ በዚሁ ከወንዞቹ በሚመነጨው ክርፋት ምክንያት ነዋሪው ህብተስብ ለተለያዩ የጤና ችግሮች ተጋልጧል፡፡

ከፍ ብሎ ለመግጽ እንደተሞከረው ድርጅታችን የዜጎች የጤና መብት እውን እንዲሆን የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ ስራው የሚያከናውነው በመብት ማዕቀፍ ስር (right based approch) ሲሆን የመንግስት አካላትና ባለስልጣኖች ማድረግ የነበረባቸውንና ያላደረጉትነ በመጠቀም የተለያዩ ዕርምጃዎችን በመውሰድ መብቱን እውን የማድረግ ግዴታቸውን እንዲወጡ ጥረት ያደርጋል፡፡ ከላይ የተገለፀው አዋጅ ቁትር አንቀጽ 11 ይህንን ስራውን እንዲያከናውን ያግዘዋል፡ በአካባቢ ላይ ጉደት ቁጥር አንቀጽ 11ይህንን ስራውን እንዲያከናውን ያግዘዋል፡፡ በአካባቢ ላይ ጉዳት እያደርሱ ያሉ መንግስታዊ እ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ላይ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ተገቢውን እርምጃ በመውሰድ አካባቢው ከብክለት እንዲጠበቅ እንዲያደርግ አቤቱታውን ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ እንዲያቀርብ ያስቻለውም ይህ የሕግ አንቀጽ ነው፡፡

በመሆኑም ከላይ በተገለፁት ሁለት ወንዞች ላይ እየደረሰ ያው ብክለት አካባቢውን ከብክለት ለመጠበቅ የወጡ ህጎችን በመጣስ በተፈጸሙ ድርጊቶች በመሆኑና ይኸው ብክለትም በህብረተሰቡ የጤና መብት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እያደረሰ ስለሚገን ለብክለቱ ሃላፊ በሆነው በማንኛውም ሰው ላይ የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ተገቢና አስፈላጊውን እርምጃ በአፋጣኝ ወስዶ በአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995 በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ውሳውን ለድርጅታችን እንዲያሳወቀን በማለት ድርጅቱ ያመለክታል፡፡

KENYA

Abdikadir Sheika Hassan & others v Kenya Wildlife Service
Civil Case No. 2059 Of 1996, High Court Of Kenya At Nairobi

Introduction

In this case, the Plaintiff on his own behalf and on behalf of the community sought anorder from the High Court of Kenya restraining the defendant, a Kenya GovernmentAgency operating under an Act of Parliament, from removing or dislocating a rare and endangered species named the"Hirola" from its natural habitat.

Legal Framework

Customary Common Law.
Wildlife Conservation Act.

Held

The Court observed that according to the customary law of the people, those entitled to the use of the land are also entitled to the fruits thereof including the fauna and flora.While this could be changed by law, according to the Wildlife Conservation Act, the defendant is required to conserve wild animals in their natural state. The Court held that the Respondent would be acting outside its powers if it were to remove any animals/flora from their natural habitat.

KENYA

Prof. Wangari Maathai Pius John Njogu John Makanga v City Council Of Nairobi, Commissioner Of Lands and Market Plaza Limited
High Court Of Kenya At Nairobi, Civil Case N0 72 Of 1994

Introduction

The plaintiffs sued the defendants and seeking, *inter alia*, an injunction to restrain thethird defendant from selling or carrying out any construction work upon a particular parcel of land, due to its alleged illegal acquisition. The third defendant challenged the standing of the plaintiffs to bring the action.

Legal Framework

Local Government Act 1972

Held

The Court held the plaintiffs had no locus standi to seek injunctive relief as they did not have the sufficient interest to bring the action. The Court established that section 222 of the Local Government Act 1972, only allowed the Attorney General to sue on behalf of the public for the purpose of preventing public wrongs. A private individual could not do so on behalf of the public, though he might be able to do so if he would sustain particular injury a result of a public wrong. However, the courts had no jurisdiction to entertain such claims by private individuals who had not suffered and were not likely to suffer damage.

MAURITIUS

Ste Wiehe Montocchio & Cie v Minister Of The Environment and Quality Of Life
Mauritius Environment Appeal Tribunal (Case No. 2/95)

Introduction

Ste Wiehe Montocchio & Cie (the appellant) appealed against the refusal of the Minister of Environment & Quality of Life to grant a licence to operate a poultry project at the St. Felix Industrial Estate at Chamouny. The Minister refused to grant the EIA licence noting: (1) its incompatibility in a residential area, and (2) the potential risk of nuisance to nearby neighbours by noise, odour and fly proliferation.

Legal Framework

Environmental Impact Assessment Act.

Held

The Environment Appeal Tribunal revoked the Minister of Environment & Quality ofLife's decision refusing to grant an EIA licence. The Tribunal noted that the case restedon factual matters. It visited the proposed project site and found that both the site andbuildings were suitable for the project, because there was adequate distance between theproject and a neighbouring house. Further, the site was well-fenced and two buildingson the site were spacious and well-aerated. Finally, the appellant promised to maintainthe project as well as abide by the conditions imposed by the Ministry of Health.

The Tribunal ordered that an EIA licence be granted to appellant on the condition thatthe two buildings at the poultry project were made flyproof, that waste be properlyremoved and disposed of, that the buildings and premises are cleaned and disinfectedafter each production cycle to the satisfaction of the Ministry of Health, and that nonuisance by virtue of noise, odour and fly proliferation is caused to the nearby residents.

The Tribunal also noted that the Ministry of Health is responsible for monitoringcompliance with conditions set forth in an EIA licence, but that the Ministry ofEnvironment & Quality of Life's EIA Committee is charged with making the decisionabout whether or not to grant an EIA licence.

SOUTH AFRICA

Van Huyssteen & others v Minister of Environmental Affairs & Tourism & others, 1996 (1) SA 283 (c) South Africa.

Introduction

The Respondents proposed the construction of a steel mill on a portion of a farm at Saldania, near the West Coast National Park and the Langerian Lagoon and had appliedto the Provincial Administration of the Western Cape for the rezoning of the land underthe Land Use Planning Ordinance 15 of 1985 (c). The Lagoon's wetlands were protectedby the Convention on Wetlands of International Importance to which South Africa wasa contracting party. Erf 2121 Langebaan was situated opposite the Lagoon and wasowned by the Witterdrift Trust, the trustees of which were the first three applicants. The fourth applicant was joined in his personal capacity as a trust beneficiary. The trustees intended to build a holiday home or a permanent home on the trust property. Expert opinion was divided on whether the proposed mill would be environmentally undesirable. The applicants sought a temporary injunction and an order that the respondent to make available copies of all documents relevant to the proposed mill andto appoint a board of investigation to evaluate the environmental effects.

Legal Framework

S.23 of the Constitution of South Africa
S 151(1) of the Environmental Conservation Act 1989

Held

The applicants had no right to compel the first respondent to appoint a board of enquiry under S.151(1) of the Environmental Conservation Act 1989; but the applicants, under S.23 of the Constitution were entitled to require the documents sought for the purposeof protecting their rights to the trust property which was potentially threatened by the proposed mill. An injunction was accordingly granted.

TANZANIA

Festo Balegele & 749 others v Dar es Salaam City Council, Civil Appeal No. 90 of 1991

Introduction

The applicants sought orders of: (i) certiorari - to quash the decision of the respondentto allow the dumping of the city waste at Kunduchi Mtongari; (ii) prohibition - barringthe future use of the refuse dump site; and (iii) mandamus - to direct the respondent toestablish an appropriate refuse dumping site. It was not disputed that KunduchiMtongani lay within the jurisdiction of the city council and that, although that the sitewas zoned as a residential area and the applicants resided there, the respondent had beendumping the city refuse and waste at the site. The burning of the waste had generatedsmoke and offensive smells and had attracted flies. The respondent contended that thedisposal of refuse in the area was temporary and sought an order to continue dumping as without this facility it could not perform its statutory duty of collecting refuse for disposal.

Held

The court upheld the locus standi of the applicants and granted them orders sought. The court ruled that it was a denial of a basic right deliberately to expose anybody's life todanger and it was eminently monstrous to enlist the assistance of the court in this infringement.

UGANDA

Greenwatch and Advocates Coalition For Development & Environment v Golf Course Holdings Ltd. MISC. APPUCATJON No390/2001(Arising From H.C.C.S. N0.834/2000) High Court of Uganda at Nakawa

Introduction

The plaintiffs (NGOs, whose main objectives are policy research and advocacy forprotection of the environment and environmental rights in Uganda) claimed that theconstruction of a hotel on a land owned by the defendants threatened the environmentand contravened environmental law. Thus, they requested a temporary injunctionrestraining the defendants from further development of the land until the final saying onthe issue.

Legal framework

0.37 p. 1.7 and 9 of the Civil Procedure rules

Held

The second plaintiff was dismissed from the application since she never signed theplaint. On the merits issues the Court held that, in order to grant a temporary injunction, theremust be a pending legal action, which there was. There should also be a serious issue tobe tried in that suit such that the applicant would be entitled to the relief sought, whichthe applicants should refer to in their affidavit. Finally, the occurrence of an irreparable damage to the applicant should be threatened. However, this last condition was not met by the applicants. The land referred to in the plaint belonged to the respondents. As the applicants did not have a proprietary interests in the suit property, notwithstanding the potential use, the application failed.

ዋቢ መጽሐፍቲ

- Dinah Shelton and Alexandre Kiss, Judicial Hand book on Environmental Programme, United Nations Environment Programme, 2005
- Selected Texts of Legal Instruments In International Environmental Law, United Nations Environment Programme,2005
- Cpmpendium of Summaries of Judicial Decisions in Environmental Related Cases, United Nations Environment Programme, 2007
- Multilateral Environmental agreement,Negotiators Hand Book,University of Joensuu, United Nations Environment Programme,2007
- Sharon Beder, Environmental principles and policies : An Interdisciplinary Introduction ,2006
- Sourcebook on Economic Instruments For Environmental Policy, Sofia Initiative on Economic Instruments,1999
- Environmental Protection Authority (EPA) and Institute for Susuatainable Development (ISD),Biosafety and Biodiversity:Writings by Dr Tewolde Berhan Gebre Egziabher and others,1996 to 2009,Addis Ababa
- Water as a human right ,IUCN Environmental Policy and Law Paper No.51
- Debbie Banks,Charlotte Davies, Justin Gosling, Julian Newman,Mary Rice, Jago Wadley and Fionnuala Walravens. Environmental Crime, A threat to our future,Environmental Investigation Agency,2008
- **የኢፌዴሪ የአካባቢ ፖ/ሊሲ,** 1989
- **የአካባቢ ጥበቃ አካላት፡ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር** 295/1995
- **ባአካባቢ ብክለት፡ ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር** 300/1995

- **የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር** 299/1995
- **የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ ቁጥር** 513/1999
- **የደሕንነተ ህይወት አዋጅ ቁጥር** 655/1992
- **የኢንዱስትሪ ብክለት መከላከያ የሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር** 159/2000